«ሁለተኛው ሲሙ ነው። በብጥብጡ መሀል፤ ወደ ጎንደርን አልመሰለ፤ ትግሬ እንዳትለው የትውልድ ሸንት የለውም። ከመሀል ሁዋ ሲያታጥና ነገር ሲያመለስ ጎንደሬ ተመስጄ ሁሉ እንደሀ አለው። ትግሬወች ደበታቸውን ያህል የወረ አቀባበይ አድርገውት ከረመ፤ የጎንደርና የትግሬ በሬሉ በጉዋ ሲለይ የሚጠለም ሆነ የሚለቶም ወረ ጠፋ፤ "የእባብን ልጅ በእንጭው" በማለት ገጥሀን ለይ አሉት። ዘመድም ከደው። ያየኸው ነው፤ ደፍን ጎንደርንና ጭሁሩ በሙሉ ዘረ ነው። ግና ወገኑ እኩ እንትፍ ብሉት አስጠጊ ሲያጣ ወጀጆ ማድረግ ጀምሯል። ግበዶ በግልጥ ታይቷል። እኔስ አይቸውም አላውቅ፤ እንዳንዴ የሚወሰደው ነገር አለ አሉ። ታዲያ ነገርን ያላከከው፤ ከዘመድ ጋር አጣላኝና መገፋ አራራቶኝ ያለው ዘዋለን ነው።

«ሶስተኛው የአከለ ታሪክ ነው። የአከለው የተብራራ አይደለም፤ ግና ሰሬ ነው። ሰው አጥርቶ አላወራውም፤ እሱም ቢሆን እንዲጠራ አልተጨነቀበትም። የሚባለው ግን፤ ተግሬ ባለሁና ከምበር ጎንደር ስመሰለስ ቸቸላ ከበረ ማንቂያ ላይ እየተቀመጠ አንተ ሟከለ ሰረ፣ ተሸከሚና የቡዳ ልጅ እያለ ሰደበኛል፤ ሁለተኛው ዘዋለ... መቸስ በክርስቲያንነት በጣም አይደል የሚጠረጠረው? የታወቀ የፈላሻ ዘር እስካሁን አልታወቀለትም። ቸቸላ ደፕር ነበር አሉ። ያለ አባት ልጅ ሰርቶ ወደውጭ አገር ሊሸጥ ሲሞክር ተይዘ አርባ መገረፉን ታውቃለህ... » ሲል፤ አይኔ ፍጥጥ አለእንጂ መልስ አልሰጠሁትም። ይህን ተመልክቶ፤ «ካልሆነም ሰምተህ ይሆናል። የዚያን ቂም እዚህ ሊበቀለው ይመስለኛል፤ ይህ ጭምጭምታ በሁሉም ተነግሯል። ይህን አለመስማትህ ይገርማል። አከለ ታዲያ ያባቱን አርባ ጅራፍ በዘዋለ ሞት ሊወጣው ጎምጅቷል። ባንደኛነት የተያየው ሰው ነው።

«የቀረው አጂቢ በሴት በኩል የተጣላውና ከዚያ የተፈጠረ ጣጣ የያዘው ሰው ነው። የዘዋለን ጊደኛ ታውቃታለህ። ቻኘው በጣም ጉድ ተሰርቷል። ከኢትዮጵያ እንደመጣች፤ የሆነ አገር የሀበሻ ሴት ውድነት ታውቀዋለህ፤ ቻኘው በሴት ፍለጋ ቢገዛ ይቀርብታል። እሷም የተንደገደገች ናትና ከሸግውን አውቃበታለች። ሴት ጊደኛዋን ሁሉ እያስከተለች በነጋ ጠባ መግቢያና መውጫ ቻኘ ይሆናል- የቀለም ቴሌቪዥኖን ከገዛ ሰንብቷልና፤ እሱም ሲጠራ በዚያቹ እያመካኘ፣ እሷም ከነአጂቢዋ ሰትዝመትበት በዚያቹው እቃ እየተመሁኘ መቃረቡ አልፈት ይሆናል። ሴትነት ያውቃል። ግብሰል ከቻኘው የቀረ ነው። ቴሌቪዥን ባይገዛም ባልትናው ከጠራ ሜዳ ሰይ የለመደን እፍንጫ ይወዘውዛል። ወጡ ልዩ ነው፤ እንጀራ ከማንክስከሽ አቤት፣ ወየሁ! ብሉ ይመጠላታል። በሱ ግድም አገር ጥሉሀ ገብተሀ ኑረሀል ከንዴ?»

«እረ ምን ጥሉኝ፤ በል ግፋ!» እልኩት፤ የእውነት ከሆነ፤ አሁን አቃረኝ እንጂ፤ እስራኤል ውስጥ እንደቻኘው ቤት አልበላሁም። ይህን ውዝፍ ጨዋታችንን ስንጨርስ እዚያ ቤት እንዳይወስደኝ ፈራሁ፤ የግድያ ገመዱ መፍትያ እንዲሆን ከብዙ አቅጣጫ መገምገም የቻልኩት ነበርና።

«ታዲያ ቻኘ ሆየ ይህች ጉብል ወደቤቱ እገር ማብዟ ቢትወደኝ ነው ይልና ማታለያውን፤ ማታረቢያ ብትለውም ይሆናል፤ የለይ የታች ሹራቡን፣ ራንግለሬንም ገዝቶ በመጨረሻ ያገር ሸማግሌውን እዘጋጅቶ፤... እሷም ሰው ላከ ባትለው የቀረች አይመስልም፤ ወደዘመዷ ይልከና ይችን ልጅ ለቤቴ ያሰኛል። ዘመድ አዝማዷ የሚያውቅበትን ጉድ እንጂ እንዴት ቢደፍረን ነው ይሀ...!» ይላሉ። ሳገር የተከሰተ የእድሜው መገፋትእንጂ ሌላው የኩርፍያ ምክንያታቸው አልታወቀም። ከእድሜው መገፋትን አንተም ገምተው፤ ግና የወንድ እርጊ የለውም፤ በሰባና በስማንያም... እድሜ ስጥቶት ከዋረ ያስወልዷል፤ ወንድ ደም አይቶርጥ! ቻኘም እምቢታውን እንደሰማ ለጊዜው እሷን እየተሸሸ ገም ይላል። እንዲህ በፍቅር በነደደበት ሰሞን ዘዋለ ዘው ብሉ ጥልቅ ይላል። ቻኘ ሆየ በዚህ ጊዜ የዘመዷን እምቢታ ሁሉ ወደዘዋለ ያላክከዋል። ይመስለኛል፤ አንተም ሆንክ እኔ በቻኘ በታ ብንሆን እናፍራለን። የቻኘ ቂም የበቀለው እንዲህ ነው። በዚህም መሰረት ይህችን የመሀከል ሴት ለቻኘ ሊያገቡ የከጀሉ ሁሉ አጅበውታል - ከዘዋለ ጋር ያፈራትታት ይሆናል በማለት። ከክርስቲያን ጋር እየተኛች ዘር እንዳታበላሽ ፈርተዋል። ብዙ ዘመዷ እንዳትጠጋ አስደንግጧታል። ስትሰነብት ግን በጣም

ተሳመደችው፤ ዘዋለን ከሙራቷ ደልቶ መለጠቂ ባስ። የታገ አጃቢዎችም ጥቃት ዊ በዚህ መንገድ ነው። እንግዲህ እርምጃ ወሰጅ ሁሉ ይህን ይመስላል።»

«በመጀመሪያ የነገርከኝ ዘዋለ የህዝብ ጠላት በመሆኑ ህዝባዊ እርምጃ እንደወሰደበት ነበር። አሁን ሳብላላው ግን የገለሰበች እርምጃ ይመስላል። የመላው ቤተእስራኤል አድማ እንዲመስል እንዴት ተደራጀ?»

«በዚህ በኩል የፖለቲካ ስራ እየተሰራ ነው። ይዉንታቸዋልና ያገባቸዋል ለተባሉ የቤተእስራኤል አዉራዎች ተጠቅሟል። አንዳንድ የተፈራ ሰው እንዲደሰግ ሁኗል»

«ፖለቲካው ምንድን ነው?»

«ኮሚኒስት ነው፤ ኢህአፖ ውስጥ ዋና መሪ ነበር፤ ኢህአፖም የቤተእስራኤል ጠላት ድርጅት ነበረች። ከያሲር አረፋት ጋር ግብሩን እስራኤሎችም ጠንቅቀው ያውቁታል። የምታውቀው ነገር ነው፤ ኢትዮጵያን የሚያምስ ነገር ምንግዜም እርሽ የሚፕስውና የሚበትነው አረብ አገር ነው፤ ከታሪክ ያየከው ነው፤ ግንኙነቱም የህበሻ ንቅናቄ የሚጀምረው ባረብ በኩል ነው። አረብ አገር ሲሉህ ደግሞ እስራኤሎች ምን እንደሚሰግቸው ታውቃለህ። ስለሆነም፤ ዘዋለ የእስራኤልን ቁጣ በቤተእስራኤል ላይ ተወጥቷል። ቤተእስራኤላውያንን እንበለ-ፍርድ ገድሏል። ሴላው፤ በኢትዮጵያ ባለን ሲያድኑን፤ ሲቀጠቅጡን፤ ሲደበድቡንና ሲያጥርዱን የነበረው የፊውዳል አግሬ ብሎም ክርስቲያን ቅንጮ ዘር ነው። ከዚህ በመነሳት እዚህም ሲበጠብጡን፤ ሲሰልሉን ነውና የመጣው የጠላችንና የከፍፍለችን ዋና መሪ እሱ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ምስክር መረጃ እየተዘጋጀ ነው። ከድብቅ ከሚኒስቶች (እስራኤላውያን) ጋር በመሆን የደቡብ አፍሪካን ጉዳይ እንስቶ በሰልፍ አገሪቱን አባጥቷል፤ ማናቃትም አድርጓል። ኢትዮጵያ ውስጥ የታሰረ ሰዎችችን ለማስፈታት ያቤቱታ ምክር ባደረግንበት ጊዜ እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ወንጀል የሚሰራውን ሌባና ሰው በዳይ ሁሉ በዕየናዊነት ስም ለማስፈታት እልሞከርም፤ ለመንግስት ማባበሉም ልክ አይደለም ብሎሏል፤ ይህ የሚያስየው በኢትዮጵያ በኩል ጥብቅና መቆሙን ነው።

«ያደፈውና ያላደፈውን ሰው (ይሁዳዊ ያልሆነና የሆነ) ለመለየት ወጥታ ሲነሳ ተቃሳቅሰው የመጡ ባሮችን እንደገረዙ ማሳሰቢያ በተነሳበት ጊዜ ሀይማኖት የግል እምነት ነው፤ ስለሆነም የጥርነት ጥያቄ ከተነሳ ሁሉም ፈላሻ ባሪያ ነው፤ ሌሎችን ባሪያ ብሎ ራሱን ነፃ የሚወጣ ህዝብ አይደለም፤

ከመጀመሪያውኑ ፈላሽ መልዋ ያለ ሀበሽ ነው፤ ሀበሽ ደግሞ ሁሉም ባሪያ ነው፤ ፈላሽ ሀበሽ ከሆነ ሌሎችን ይሁዳውያን አይደሉችሁም ብሎ ከስ በዚያ ላይ ለመጠቆም መብት የለውም፤ ባሮች እንደጠመቁ ከተከሰሱ፤ የገዟቸውና በጉልበት የገረዷቸው መሰቀል አለባቸው።» ብሎ ተችቷል። ሌላም ብዙ የተነሳና የማሳስታወሰው ነገር ሞልቷል፤ ነገር ሲብራራ በጊዜው ይጠራል።

«በእርግጥ፤ እንዳንድ ዘዋለን የሚደግፉ በተቃውሞ ይነሱ ይሆናል፤.. ከእርምጃ ወሰጆቹ ጋር ጠብ ያላቸው። መቸም ሰው ያለበ ጉም፤ ያለጠብም አይኖርም፤ ሁሉም አይወደውም። በመሆኑም መንግስት ከእርምጃ ወሰጆቹ አደርሳለሁ ብሎ ምርመራ ከጀመረ ለተቃውሞ ስለማይሰልፍ እስወጥቶ በደልን መንገር። በዚህ ብዙህ እርምጃው (ግድያው) ህዝባዊነቱን ለማስመስከርና መጠቂያ ጉዳናውን ለመዝጋት ተከጂሏል»

«ዘዋለ በክርስቲያንነቱ ሲገደል መዘዝ አያመጣም? የቅማሬ ፈላሽና ጉንደሬ ፈላሽ ታሪቀ በቅል፤ ዘዋለ ፈላሽ ባለመሆን ሲወነጀል፤ የጉንደር ሰው ኢትዮጵያ ለቀረው ፈላሽ ደም መጋቢና ማለቂያ ምክንያት አይፈጥርም?.. ይህ እንዴት ታየ?»

«ይህም ተብላልቷል። መንግስቱ ሀይለማርያም ህዝቡን ተበረቅሁ እያለ ነው ቀን በቀን የሚሞኸው... ቢሆንስ አንድ ክርስቲያን ተገደለ ብሎ ህዝቡን የሚዉርስ ነው እንዴ? በመንግስት በኩል እንደዚህ ከየኸው፤ ክርስቲያኑ ህዝብ ከተቆጣ ደግሞ ሲሆን የሚችለው በግብጥና እስራኤሉ ጦርነት ጊዜ አረብ ይውጣ እንደተባለው፤ ቤተእስራኤል ይውጣ ይሆናል፤ ይህም ተወዳዳሪ የሌለው የቀረ ሰዎችን ማውጫ መንገድ ይሆናል፤ ሰስት ወፍ ባንድ ደንጊያ ተመታ!.. ሁዋ የማያውቅ ጀብድ! የሰውየው መገደል፤ እዚህ ያለው አንድነት መፈጠር፤ የተለያየውን ቤተሰብ ሁሉ ሲያገናኘው የተዝረከረከው ሁሉ ስምረት ይገባል። የመጣ ቢመጣ በበደለን ሰው ምክንያት መቅረየስ ከፍተ መንጋ ልዉርስ የሚል ፍጥረት አይገኝም፤ ሂትለር ተመልሶ ከልቶመ በቀር» አለ።

ነፍስ ገዳዮች በሙሶሎኒና በሂትለር ለምን እንደማይታዩ ንገረኝ ብለው በወደድኩ ነበር፤ ግና፤ ይህ ዘመዴ የግድያው አውራ እንደሆነ በደንብ ግልፅ ነውና ጥያቄየን አይመልስልኝም። የመጨረሻው እስተያየቱም በሉ የተፈጠረእንጂ ከድማው ሳይ የተጠነበት መሆኑን ተጠራጠርኩ። እንዲያ ግለቤ ቅንሽ መዝናናት ቢሰጠኝም የጥርጠረ ማጥሪያ ጥያቄየን ገና አላበራሁም፤

«ፍርድ ቤት ማስረጃ ይጠይቃል፤ ለዚህ የተጤነ ነገር አለ? ብርሌ።»

«ከላይ የጠቀስኩልህን መሰረት እንዲለ ይዘህ... እንዲያውም

ፍርድ ቤት እስኪደርስ ግን ይጠብቃል! ከመንደር ሰራው እንደተፈፀመ ጋዜጠኛው፣ የሬዲዮኑ፣ የቴሌቪዥኑ ዜና አቀባይ ሳይቀርብ ይህ ነገር ይታፈንልን ብሎ ለፖሊስ ማሳወቅ እንጂ። ፖሊስም ይህን ምስጢር ወደ ውጭ አያወጣም። ፈላሻ በፈላሻ ቢሆን የዜጋ ወንጀል ነውና ስዕሉት እርቅ አይቶ ደም፣ ይጣራ አይጣራ የሚባል ነገር የለም። የዘዋለው ግን ለሀገሪቱ የውጭ ፖለቲካ መበላሸትን ስለሚያስከትል መደበቁን እነሱ (እስራኤሎች) የበለጠ ይጨነቁበታል፣ ዋናው ነገር አስቀድሞ መጠቆሙ ነው። ክርስቲያን በይሁዲዊ ተገደለ ብለው የሚያወጡ አብደዋል? ለመጠበቂያው ግን፣ ስለሰላይነቱ፣ ከኢትዮጵያ ማስተወቂያ ሚንስትር የመጣ ማህተም በድንቹ በመቅረፅ ዳብዳቤ ተፅፎ፣ ግንኙነቱን ለማስመሰከር ሁሉን ነገር አስመሳዩ ቀራጭ ሰአሊ ሁሉ በደንብ ተደራጅቷል። ፅሁፉ እፍደሁኔታው የሚረቀቅ ነው ብለዋል»

«እደራሁን፣ እንዴት ቢቀባጥፍ ነው! መተህ ነበር አትለኝም! ይህ ሁሉ ተግባር እንደህ ሲደራጅ ነጋሪ ዘመድ ማጣቱ የሚገርም አይመስልህም?»

«በያለበት መፈላሰም ለፈላሻ አዲስ ነገር አይለደም። የኢትዮጵያን ሰነ-መንግስት ያረቀቀው፣ የነደፈውና የተራቀቀበት ግን ሆዋ ነው! በፖለቲካ በኩል የሄድክ እንደሆነ ደግሞ አይነታ ሰው ፈላሻ ነው። እዚህም ብዙ ሊቅ የሚወጣ ይሆናል፣ ይህ ሁሉ እቅድ እስካሁን ያልተነገረህ ተፈርተህ ነው።»

«ዘዋለ ፃፈ፣ አሊያም ተፃፈለት የሚባለው ነጥብ ምን ሊሆን ይችላል?» አልኩ፣ የድጋፍ ሀሳብ ለመስጠት ብየ የወጠንኩት ሳለ፣ መልስ ግን ልናገረው ያልኩት ተምታተብኝ ወደ ጥያቄ የወዘፍኩት ነበር። ብርሌ መልስ ሲሰጥ እርቅ አልቶየም። ግና የተናገረውን ከመድገም በቀር ሌላ የሰጠኝ አዲስ ፍንጭ አልነበረም። ለሰጠኝ ትንተናና፣ ትችትና ዜና ድጋፍ ለመስጠት፣ «እውነትክን ነው። ሀሳብ አይጠፋም። ደግሞም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማዘዣ መፃፍ የለመደ ሰውም አይጠፋ ይሆናልና ይህን የሚያውቅ ተፈልጎ ይሰራል፣ ግና አስቀድሞ ማዘጋጀትን የመሰለ ነገር የለም። – አሁን እኔ እንዳደርግ የሚፈለገው ነገር ምንድን ነው?»

«ያንተው በኩል ርምጃ ቀላል ነው፣ ከእርምጃ አትግባ። እላየሀ፣ አልሰማሀ፣ ሁሉም በየዘመዱ እየተሸከፈና ለሰሞኑ የሆነ ነገር ፈጥረሀ ከዘዋለ መራቅ ብቻ ነው። ጉዳዩ ከተበራ በኋላም... ወየልሀ! አየሁ አላየሁም ነው ብለህ፣ ነገር የመጨረሻ ፈረንጅ እስኪደዝ ይሆን በሚመስከት አካባቢ እንዳትደርስ። የፈላሻ እንድነት የሰርጉ ወጭት እስኪፈቀፈቅና ቀንጫም ማህደረን

እስኪያበስ ነው። አንድ ነገር የመረቀዘ እንደሆነ፣ እርሱበራሱ ነው የሚፈጀው መብላት ሲጀምር ተብላ ብለህ አንተ ግን እንዳትበላ ዘር ነው»

«እርምጃው የሚወሰደበት ቀን ተቆርጧል?»

«ሰሞኑን። እንዳንተ ያሉትንና ይቀርቡታል የሚባሉ፣ በደንብ እንዲርቁ ያልተደረጉትን እርቆ... እስዚያ ዘለው ይደረጉሉና፣ እንድነት እንፈጥራለን ስንል እርስ በራሳችን ገበያ ለገበያ እንዳንፈላለግ፣ ደም እንዳይበቅል. በማለት፣ ሁሉ ተሸከፈ ሲበልና ብቻውን ሲቀር ቅንጡን ይሉታል»

ከመጀመሪያው ያሳሰበተኝ፣ ካንዳንድ በደም የተሳከረ ነፍስ ገዳይ የሚወጣ ቃል መደረብ ሲጀምር ሰበከኝ። ዘዋለ በእውን ሙቶ ይታየኝ ጀመር። የቁርጡን ቀን አለማወቂ አንድ የገዘሁትም ቁርጠት ሆነኝና እዚያው እንደተቀመጥኩ የገደሉትም መሰለኝ። ውስጥ እካላቴ መንዘፍዘፍ ሲገባ መሳቀቅ የፈለኩት ይህን ዘመዱን ነው።

ጥቅምት መግቢያ ነው። አየሩ በጣም መበላሸት ጀምሯል። ለኸታሙን የበጋ ሰው፣ አዳብ በገዛና በብራንዲ ሙቀት የተነደ ለከራም፣ ከላይ ሜን ተንፍስ እንጃበሀ! ብሎ የረገጠው ጠብ ያስመሰለዋል፣ እስራኤላውያን በቅብት ሲቿቿሙት፣ ብሉም እመድ ስለሚያስመስል፣ ፉታ ቢያጡ የቶዳ ንጣታቸው አያስጠቻውም። ከጥቁር ላይ ነጭ ግን ይፈጠል። ኢትዮጵያውያንን በቅብት ወጭ ያስቀቀ ነፋስ ነው። እንደህ የተወናበደና የተበበለበ እርጥብ ወበ የመሰለ ፊቱን ይዘ የቀረበኝን ዘመዱ መሳቀቂያ መፍትሄ አእምሮየ ገና እያሳወለ መድፈያ መላ ግን አጣሁ። ቢቀለኝ ብየ ሽንት ቤት ገብቸ በሬን የሂሊት ከንችረ ዘጋሁት። የመቀመጫውን መድፈኛ ጥየ ሱሪ ሳልፈታ እንዲያው ቁጭ አልኩበት።

«ወይ የሰው ልጅ አመል መብዛት! ከዚህ ቲያትር በኋላ የሚመጣው ታሪክ ምን ሊሆን ይችላል? ዘዋለ ሞቶ የሚፈራ ይሆን? ምን አስፈራው፣ ከገደሉት በንብተዋል! ግን አልሞተም የሚለኝ ቢገኝ፣ እንዴት ዳነ? ምን... እንዴት ብሎ?» አልኩ። ይህን ደርድሮ በመልስ ላይ ግን እንዲያው ሀሊናየ ጭንገ ለበሰ። «በጄ! አሁን እዚህ ምን እያደረኩ ነው? ይህ ሰው፣ እኔን በሆነ በታ ይዞኸው ዘወር በል ተብሉ ይሆን? እንደህ ከሆነ፣ የዋልኩበትን አረም በላው! ብየ ያልከፈልኩበትን (ሳይወርደኝ) የሽንት ቤት፣ እናጠጭ ውሀ ለቀቅሁበት። ፍርሀቱ ሆዋእንጂ ብርሌ ቀርቶ ከጠገቤ የሚገኘው ግድ-ቤተኛእንኳ የሚሰማው ነገር አልነበረም። ፊቴን ደግጊ-ደጋግጊ መስተዋት ላይ ተመለከትኩት፣ ሳነሳው የቻልኩት ገፅታ ግን ምንም አልነበረም። ታጠብኩት፣

ክባድ የወሀ ክለልታ ማየት በቀር እይኔ ሳይጠራ እንደቧዘዘ ቀረ።

«ወይ ጉድ! ፒለጦስ እንዴት ቢደንድን ነው? አልም ያለ አረመኔ፤ ወከኝና ሰካም የነበረ ሰው ነው። ከራቱ ላይ የሚፈስ ደም ተንብዮ 'ከደሙ ንጡህ ነኝ' ብሎ ከጠራ ጎዳ ላይ እጁን ታጠበ። የራሱን የዋለ የሳበቅና ቁሽሽ እድፍ ከላእንጂ ወደየሰዉም ሆነ ወደገዲዮቹ የተባለፈ አንድም ቀምነገርና ምስሌነት አልነበረውም። በገሀድ አላየሁም፤ አልሰማሁም የሚል ደረቅ ቅጥፈትና ወሸት የተጀመረው ያኔ መሆን አለበት። የዛሬው ጊዜ ጥበቅና፤ ፍልስፍና ሁሉ የመነጨው ከሱ፤ ታጠብኩ ብሎ ከወረደው እድፍ የመጣ ነው... እንዲያ መሆን አለበት! የህግ ት/ቤት ክህደትን በመሉ የሰራሽው አንተ ነህ... እኔም ታዲያ ያንተ ሀዋርያ ልሆን ማለት? ዘወር በል! ያንተ እርስት ወራሽ የምሆነው ጉዳይም የለኝ! የመጃጃልም እንደነፈሊጶስ በሰው ገመድ አልገባም፤ ይህ ደግሞ መልኳ ያለ የህይወት መረታት ነው። ሁላችሁም ዘወር በሉ፤ የማደርገውን አውቃለሁ! አየሰልም ይሆን ድራማ አውቆ እንዲሆን ከፈጠረው የበለጠ ተጠያቂ ነው፤... በቃ! አለቀ ነገር!...» አልኩ፤ ብዙ እንሰላሰየ። የተከነቻቸረ መሀረቤን አወጣሁና እንዲያው ወረዳውን ሞዠቅሞዠቅ፤ ፊቴን ቀላቀል አናጠጥኩት። ባልጠርገው ይሻል ነበር። ደብሱን የአቾሉኒውን ገለባ እንደሸሀ የሚዋጋው የሳለስት የፊት ፀጉሬ ላይ አታምኩት። ሳንሳው ብሞክርም አልሆነም። ያዳረቅሁትን ፊት እንደገና አጠብኩ። ይኸኔ የሹራቢ ወሰጡገላ አማራጭ የሌለው ረዳት ነበርና በሱ አደረቅሁት። ልወጣ ያጣኝና እንደገና መሰሰኝ፤ አወስነውን አጣሁ! አቅሌ አልፈገልኝ አለ።

«ብርሌ ክፉ ሰው ነው? እንዴት ብሎ! ለምን ጠላሁት? በጣም ደግ ሰው ነው፤ 'ካ ጉረሰኩ እጁን ተነከሰኩ' የሚባለ ወከ እንደኔ ያለ ሰው ሲገጥም ነው። ምን ሆነኝና ነው ሳየው ያሰበኝ? ደጉን ሰውስ... ገና ከቤቴ አላስደረገውም! እንደህ ከደረግሁ ነፃነቴን አጣቃለሁ። ይሆን የሆደን ሸብር አንድ መስኪያ ምናምን ሀው አድርጌ ብወልጥበት ይሆን። 'ራስ ሲያም ጠላ' ይሏልና መልከም መድሀኒት! ሰው ሁሉ እዳ የሚገበው እንደህ ሲፈራ መጠጣት ይጀምርና ለምደበት እየቀረ ይሆን?...» ብየ የመጨረሻውን የሽንቅቢት መበተክተክ ወርሾ ወደብርሌ ስመለስ፤ «ከንዲ፤ የተረቡ ነገር ደረሰ... ምነው ራቴ?» አለ።

«መሚኛ ወጠሀል ልትለኝ ፈልገህ ነው፤... አይደል ብርሌ?»

«ሲመሽ ታዲያ ምን ይባላል!»

«እራቴ ሆዶ! ባንተ ቤት መሽቷል፤ ገና ዩኒቨርሲቲ

ቢተመፃሀፍት ስንቅ የተገለተ ነገር ይጠብቀኛል፤ አንድ የቤትስራ አልሰራሁም። በል! እግር-መንገድህን ገፋኝና የቤቴን ቁልፍ ወስደህ፤ ዲቡውን በምናምኑ ተባብተህ፤ ያገኘሽውን ሁሉ ጠርመስ አስሰህ፤ አማረኛ ዘፈኑንም ቅወደለሁና ያሽህን ስታደርግ ቶይተህ ሲደክምህ ተኛ።... ወይስ ሌላ ሰው ዘንድ መሄድ ታደቶሀል... መቸም አሁን ወደቤትህ አትክጀልም፤ መሽቷል»

«እስከሁን ስራ ያስፈታሁህ ይበቃል፤ ቢተመፃሀፍት አድርሼህ ወደነታኘው አክባቢ እሄዳለሁ፤ ለወዋታው!... የሚቀጥለውን የእንቅስቃሴ እድገት በዚያው ለማጠራቀም ይበጀናል። የተገኘ አዲስ ነገር ካለ ሳንተ ማስማቱም ይጠቅማል።» አለ። የሁለታችንም ቀልም በመረ፤ የፈለግሁት እንዲያ ነበረ፤ የፈቅከለት መንገድ አስመቸው፤ እርሱም ወደአምባያው እኔም እዲያ! ሁለታችንም ደል በደል ሆን።

ከመኪናው ላይ ከተሳፈርኩ በሂላ፤ ይህ ወደቢተመፃሀፍት ወሰደኝ ያልኩት ነገር የማይጠጣም ሁኖ አገኘሁት። ያለጡንክበቅና የተዘበራበረ ሁኔታ። ከቤቴ በጣም እርቆ የሚሰደኝና አውቶቡስ ጣብያ የሚያስገባ ነገር! ስለሆነም፤ «በግ ብርሌ፤ እዚህ ሆነየ የሚዋር ገደኛየ አለ። መሀ ፊን ተወሰኛል። ከሱም ጋር ትንሽ ሂሳብ ቢጤ፤ ስለፈተናው እወራለሁ። አንተም በጊዜ ተሸከፍ፤ እንዳትዘር፤ በጣም መሽቷል» ብየው ስወርድ፤ «ቶሎ ማለህ!ክ-ን-ዲ! መያ በልብ ነው፤... መጨረሻው ሰላም ይሁን!» አለኝ። እጁን አውለብልቦለት፤ መኪናውን ሲያስፈተልከው፤ መሳበሪያ መንገዱን ይገር ከሰወቸ ልደርስ ራጫውን በቅኒኒ ተያያዝኩት።

ከመጠለያ ሰፈሬ ስቃረብ በሰውነቴ ቅኩል የማውቀው፤ አሁን ግን ሳየው የማልፈልገው ዲሌው በሰውነቱን የገዘው ደንደሳም ሀበሻ፤ «እንዴት አመሸህ እቴቡ!» አለኝ። ያገኘውን ሁሉ በሆነ የታየው ነገር ቀጥሉ ከልጠራው ስለም በሀኪናው ወስጥ ስፍዋ አያውቅም። በጣም ይወዳል ተቀጣሳ መፈለግ። እቴቡውን በሳወቅለትም፤ "እቴቡ" ብሎ ሲጠራኝ ፈገግታ የሚወራቸው ብዙ ናቸው። "እቴቡ" ብሎ ሲጠራኝ አቤት እንጂ ዝም ብየው አላውቅም። እሱ የሰጠኝ ልዩ ስሜ ብየ ለምጄዋለሁ። ሲጠራ ብሰፋው የሰውን የቅልቅል ሰም ስለሚፈጥር ጠቅልየ "እቴቡ መሆንን" መረጥኩት። ሆነና፤ የሰላምታ ምልልሱን ቀጠልን። ለሰጠኝ «እንዴት አመሸሁ እን እቴቡ!» መልስ ይሆነው ዘንድ፤ «ደህና ወለሀል አጅሪ?... ከብቱ፤ እሀያው፤ መላው ነገር ሁሉ እማን ዉሏል?» አልኩ። የዘልማድ የገጠር ቤት ተረባችን ነው፤ እዚህ ሆቅ አይሆን እንጂ ሁላችንም ገጠሬወች ነን። እንደመጣልኝ

በተጫጫኩበት ንግግር፤ "ወሽ በቀደደው ጆብ ይገባል" እንደሉ ድክመቴን ተጠቀመበት። ከዚህ ጭፍን ንግግሬ ቅኔ ዘረፈበት።

«እሀያውን ፍራ ይለዋል፤ ክረምት ሊገባ ደመናው ዞሮ የል! ጣሸና ጆብ ይቀደዳል፤ ታዲያ ለእሀያ አይመችም። ገና ለገና እየፈ ይነግረዋልና በቀን እ-ው-ው እይ! ማለት ጀምሯል።» አለ። ያ "እጅሬ" ያልኩት ቃል ቆንጥጦታል። ለጊዜው ያለኝ እማራጭ ነገር ማቀዝቀዝ ነበርና፤ «ከመሸ ወዴት ትሄዳለህ? ፍጥረት ወደ ቤቱ በሚሸከፍበት ጊዜ፤ እኔ ወደቤት፤ አንተ ወደ ውጭ፤ በደህና?» አልኩት።

«በኛ በኩልእንኳ አልመሸም፤ ደግሞም የጠይብ ስራ ሌሊት ነው... ይሆንም ተወው፤ ወዛበ (ጉንደር ውስጥ ትንሽ ክልል) መሰለህ እንዴ ያለነው? እዚህ አገር ቀኑም ሌቱም እኩል ጠሀይ ነው። ሌት ከቀን መብራት!» አለ። "ጠይብ" የሚለውን ቃል ፈሳሽ ያልሆነ ቢናገረው ኑሮ ክፉ ይሰልበት ነበረ። ግና ከሁለታችን ሌላ ሰው አልነበረምና፤ በቃሉ ዝና ሰራበት። «እውነትክን፤ "እንደት ኩራዝ የሚበራት ትንኩሽት አገር" አሉ እያ ተበጀ!... ጨዋታህ ይመስላል!»

«እድሜ ለስጠው፤ እንድ መትረዝ የሚሸፍነው ቤት ያገኘ ሰው እግዜርን የሚያመር አይሆንም። እድሜ ግን ዋና ነገር ነው፤ በጊዜ የማይሆን ነገር የለም። ለተመሳሰለ፤ ኩራዝ የሀብታም ድግስኛ ህዝብ እራት አብልቶ ይሸኛል። በል! "ቸር ተመኝ፤ ቸር እንድታገኝ" ነውና እንገናኛለን፤ ደህና ክረም!» ብሉኝ ተለያየን።

ጊዜያዊ ደስታ ቢወረኝም፤ ቆመት እንሽ ፈረጠማም ክንዱን ከኩፍተኛ እመሉ ጋር አቅብሮ የሰለጠውን ሀይል እንዲስገዝሁት ቶየቶ ብሉ የተጠነኝ ጉዳይ ነው። በሰው መቀለድ እራት፤ በሱ ላይ ግን፤ ከእምሮው በተመዘገበ የታሪክ መፍቻ ያልተጣጣመ፤ የማያውተውም ሊሆን ይችላል፤ እሱን በበጎ የሚከብ ቃል ቢሆንም፤ "ይህ ያልተረዳኝ ቃል ስድብ ነው" ብሉ የቂም ገመድ ሲፈትል አዳሪ ሰው ነው። በሀቅ የሚያመሰግነው ቃል ሆኖ ከጠብ በኋላ የተጣለ የእመዘዘኝ ራሱን መቶ (ግለ-ሂስ) የማለባጭ ስድብ ነው ብሉ የሚያምን ጠማማ ሰው ነው። ስለሆነም፤ ከሱ ጋር ትንሽ የማይጣጣም ነገር ሲፈጠር፤ ዝም ማለትን የመሰለ ነገር የለም።

እሱን እንዲያ ትቸ ደረጃውን ተቃንቸ ወጣሁ። ከዘዋለ በቀር መጀመሪያ ከእከሊ ቤት ልገባ ብየ ማግረጥ ሀሊናየ አልነጠቀውም። ተራውን ቆፈቆፍኩ፤ ታፈረ የለም፤ ዘለቀም እንደዚያው፤ ቀጥሉ ዘዋለ ነው፤ ዘለልኩት። ተከፋ በቆረጠ ሀይሌ የሰለሞንን ቤት ደጋግሜ ስመታው አባይ አብሮቶ ነውና

የሚዋረው፤ «ምን ያበደና እጁ የደመ ሰው ነው ይሆን ያሀል የሚቀጠቅጠው፤ ጆሮችን በኩስን ተዘግቶ አይሰመም እሉት?» ብሉ እየተሳለቀ ከፈተለኝ። የማእዘን ላይ ብሉም ሽጉሬያማ ክፍል ስለሆነ፤ ዘዋለ ቀጭ የሆነ ወረቀት እያነበበ፤ ሌሎቹ በካርታ ጨዋታ ተበወዝዋል። ማእዘኑን መቶቸ ሳልፍ ሁሉም በየጂቸው እንዳንተረፈፉ ተመለከቱኝ። በሬን ስዘጋው፤ ዘለቀ ከሌሎቹ የበለጠ ይዛናኛልና፤ «ብቻህን ነው የምትንተረፈፈው የኛ ነፍሳሉ?» ብሉኝ መልስ ሳልሰጠው ወሀ ፍለጋ ስሄድ ተዝናንተው ወደካርታ ጨዋታቸው ተመለሱ።

ከመሀከላቸው እንግዳ ሰው ተደርበ ማየቴ ፍጥቶ የዋለበትን ያእምሮ ሸክም ሳላራግፍ ሌላ ማእበል ተተከለት። ልተርክ ከመጣሁበት ጉዳይ ትንሽ ከፍየ ብናገር የማገባሬ ሳበት አይንጣለልም ነበር። ተሉ የሚያናግረኝ ሁኔታ ጠፋ። የምግቴን ጠጥቸ እእምሮየ በተቃርኖ እንደተገየደ፤ ሁኔታውን ልገመግም በወጣ-ብገባ! ብየ ለካርታ ጨዋታው ተራ ያዝኩ። እስከዚያው ግን፤ ሳናገረው መፍራቴና ምቾት ማጣቴ እንዳለ ሆኖ፤ እንዲያው በማግሽ ሀረየ ዘዋለን እየቀባለድኩ ጉች አልኩ።

እየቶየሁ ስሄድ ባእድ ቃላት ጆሮየ ይሰማ ጀመር። የማወቀውን ካርታ የነፍስ ወከፍ ስም፤ ከሞላ ጉደል በሌላ ተቀይሮ ስም ቀይረውታል። ይኸ፤ ቀደም ሲል በር ላይ ተሰክክሬው ያስፍኩት ሰው ትልቅ ተፅእኖ ያደረገባቸውም መሰለኝ፤ የቡን የማይጥም ምልኪት ሲጠቀምበት ላይ እሱን ሆኑብኝ። እንዱ የሆነ ካርታ ሲጥል ከቅፅል ስሙ ሌላ፤ ማጀቢያ ሀረጉችም አብረው ከጠይውም ሆነ ከንሽው ተወረወረ። ከመገረሜና ለማወቅ ከመጓጓቴ ሌላ እእምሮየ ከስራው ስልና ከስማው ታሪክ ጋር በፍፁም አልጣጣምልኝ አለ።

«ጉበዝ፤ እዚህ ቤት በእነዚህ የፈውዳልና የካፒታሊስት የካርታ ስሞች ላይ በሻሊበት አብዮት ተካሄደ እንዴ? የካርታውን የማእረግና የደረጃ ስም ሁሉ ገፈፋችሁትሳ፤ ሌላ ያለመድነው ስም አለበሳችሁት? ሽርመጣን፤ ወስድን፤ ንጉሱንና ንግስቲቷን ሁሉ ምን በላቸው?» ስል፤ ታፈረ ካርታ ካርታውን እየተመለከተ፤

«እየኸው! እንዱ ተራ ካርታ ሲመጣ?... ሰው ሁሉ የካርታ ሹም-ሽር ሲደረግ አይመጣም ነበር እያ? ቀርፋፋ የትግሬ ዘንቢል ነህ! በሰአት ብትገኝ ሹም-ሽር ታይ ነበር። ወደፊት፤ በጊዜ ቤትህን ከገባህና በሰአቱ ከተገኘህ እንዱን ጥለን መተኪያ ትሆናለህ፤ ለዛሬው ግን ተቀጥተሀል። በል፤... መቸም፤ እየቶየ ይገባሀል።» ሲል ተሸክሜው የዋልኩት ሀላፊነት ትንሽ ቀለለኝ። «ይህ ጉበዝ ሁሉ፤ እንደኔ በጉን ደርሶ ወሬ ያሸከመው ዘማች

አገኝቷል።» አልኩና ሌላው መፈተኛ የዘዋለን የመንፈስ ፅንታ ማረጋገጥ ነበር ሳወራው ለፈለፍኩ። ከዘወትር የተለየ ቅኝት አጠሁብት፤ ዘዋለ በጨዋታ ስሌቱ አልተሰወጠም። ይህ አቅጣጫ አላሲዘኝ አለ።

«ይኸ ነገር? ዘዋለ ሳይረዳው... ይህ የካርታ ፖለቲካ? ሞቱን ከሰማ ደግሞ እንዴት ለውጥ አይታይበትም? እኔን ከሀገር የበለጠ ፍርሀት ያርበደበደኝ ለምንድን ነው?... የለም፤ ዘ ዋ ለ ሞቱን አላወቀም። ምን ደንጋይ ቢሆኑ ነው እይን-ባይን የሚያሽፏብት ?... ወይ ዘሬ! እኔ ሳጉቴ ልጆ እሜን ብየ እንደመጣሁት፤ እነሱም ይህን እጣኑ-ነፍስ ከዱት?!» አልኩ ለራሲው ጨዋታቸውን እንደሚመለከት ሰው ከፊታቸው ላይ በሀሳብ እንደተዋጣኩ።

ከካርታወቹ ቅፅል ስያሜ ስሉቶ፤ ዘዋለን የሚገድሉ አድመኞች የሚኒከ ሲሆን፤ የቀረት ስያሜወች ግን ፍፁም ሊጣጣመልኝና ልረዳቸው አለቻልኩም። በመሆኑም፤ በዘወትር አጠራር "ሸርመጣ" የሚባለው "እከ ክ"፣"ክሜ" (ሰባት)ን "ሉባሮ"፣ " ወለ ድ"ን " የተልባ ማሽያው ታብቅ"፣ "ፉንዋ"(አንድ) - "ዘቢደር" ብለዋቸዋል። የጨዋታው አስተጋቢና አቀናባሪም (ዜና) ታፈረ ነው። መቼም እንደህ ያለ ነገር ማስተጋባት ይወዳል።

«አባ ገብረሀናን ከመአት ዱላና ዝርፊያ ያወጣኸው የተልባ "ማሽያው" ጊዮርጊስ ዋሳ ሁነኝ! የያዘኝ ካለም (በሚጨርስበት ካርታ) እእምሮውን መዘናጋት ከተቀበቅና እንዲዋል ይሁን... በሞታችሁ፤ ከጨረሰኩእኮ ዘመን አልፎኛል!... ሉባሮዋንግ እንግዲያ በጆርባዋ እለያታለሁ፤ ሌላው ያደፈና ወዙ-ያነሳው ካርታ ሁሉእንጂ የጠጠበጠኝ። ሉባሮን ግን የያዘ ይዟታል። "ሲ-አይ-ኤ" በመገልበጫው ቢገለብጣት ምነው!... ተመልከት! ያ ጉበዝ "ሲያክ" ያዙሉት። እራቴ!... አንተ፤ አይችሀለሁ፤ የሞተ ነገር። ይህችን አፋጆ እከክ ጣሳት። እኔ እንደሁ አልፈልጋትም።... ነግሬህ የል! የምፈልገው የተልባ "ማሽያውን" (ነቢዩ) ነው።... ተበላህ ጉንደሬ!» ብሉ ከደረደረ በሂሳ ተቃንቶ ተመለከተኝ። ተስፋ የመቁረጥና የመሰልቸት፤ አሊያም መምሸቱን በማሰብ ሀሳፊነት ተስምቶት፤ የያዘውን ካርታ ከጠረጴዛው ላይ ወረወረውና፤ «ጉበዝ፤ በገበጣና በደባ ጨዋታ ስንት ያልተሰቀመ የዱራኛ ቀርም አስጨርሸ ከተገረፍኩት፤ የዛሬው ተቆጣጣሪ አባት የሌለበት የካርታ ጨዋታ ከሚጥለኝ አደጋ አይበልጥም። ይኸኛው የለ የለት የብሰለት ብልግና ነው። አገር የያዙውን ሁሉ ወረቀት ሁሉ ጣል! እለዚያ እዚሁ እንደተቀመጥክ እጅህ ይያዛል። የታሰበው እጅ መያዝ ነውና።

«ንሰማ! ሰለሞን፤ ለ"አቂባው"... መርዶ ባንተ ሲሆን ያምራልና በጣም አጠር አድርገህ ለኩሰውና ወደይት እንጀምር።» ሲለው፤ ሰለሞንም አላቅማማም፤ የንግርር ዘርፍ ማወጣት አይሆንለትም፤ አረፍተ-ነገር መቆማመጥ በጣም ይወዳል፤ በለመደ ስሌቱ ይነግረኝ ጀመር።

«እንደኛና! አዝማች ቅገሬ! ዘማች ጉንደር! ስሌት በሆታ!

«ሁለተኛ ታክቲክን በሚመለከት፤ የዘዋለን ሀይሌ እስከተቻለ ድረስ አራትና አምስት ሰው ለአንድ የኛ ወገን እጆች። እጆቻንን ገጥም አድርጉ መያዝ፤ ተደዘ ሲያልቅ ዘዋለን መገደል! ለመያዝ ሲያቅት (ተባባሪወችን) እክል እንዳይጉደል እያደረጉና ብልት እየመረጡ ወቅቶ ማደከም።

«ሶስት- እኛን በሚመለከት፤ "ካውንተር አክሸን"- (ማክሸፊያ) በፍጥነት መንደፍ፤ እስካሁን እዚህ የተቀመጥነው አንተ እስክትመለስና ዘዋለ እስኪተኛ።... ጋሽ ከንዱ ገባያቅ? ማብሪሪያ፤ ዋያቴና ዜና መዘርጋት ያንቱ ፈንታ ነው፤ በመልስ ረገድ ቤቱ ይተባበራል። ጨረስኩ!» አለኝ፤ በጣም በተገረዳደፈና አብሮት ሳልዋረ ሰው በማይረዳ የቅንተና ስሌቱ። እንደተመራሁትም የተማታብኝን ነጥብ እስመርኩዝ በጥያቄ ጀመርኩ።

«ዘዋለ ሲተኛ ለምን ዝም አላችሁት፤ ወይስ ገና የሰማው ነገር የለም?»

«የቢቅሉትን ነጥብ አግኝተሸዋል፤ እስካሁን ብቻውን የተገለተውና ከካርታው ጨዋታም ያላሳዘነው የተንኮል ነው። ብቻውን መቶመጥ ሲሰለቸው እንዲተኛ ብለን ነው፤ ያልነገርነው ደግሞ መጀመሪያ እሱን-አልባ እናብሳሳው ብለን ነው። ካገኘነው የወሬ ታሪግ ብትዋር ኑሮእኮ ወዲያው ለዘዋለ ቅንነገረው ነበር- ሳይበሳለ! እንኳን አልነበርክ!» ብሉ ተሳለቀብኝ። ጉጉቴ ምን ያህል ጥልቀት ያለው ዜና እንዳገኙ ማወቅ ነበርና ዝርዝሬን እጡብቅ ጀመር። «ታዲያ! የሚቀጥለው እርምጃ ምንድን ነው? ጉበዝ!» አለ፤ ጠያቂው ታፈረ ሆኖ፤ ሰለሞን በዚያው መሳሽ እንዲሆን።

«ዘዋለ ከመመለሱ በፊትና ከቤቱ ሳይወጣ እንመለሳለን የሚል ማስታወሻ ለደባሉ ትቶ፤ ሲያጣን ግራ እንዲይገባው፤ ወደዘዋራ ቦታ በመሄድ ነገርን አብሏልቶ ቶሉ መመለስ ነው። እለዚያ ዘዋለ በድንገት ይመጣና፤ ቀደም ያወራውን ሳንሸከፍ፤ ዘማቶብን እንዳንቀለጨለጭ።»

ለመሄድ ተስማማመ፤ ቀደም ጨርሰውት የቶዩት ውል ስለሆን ሳስቀይረው አልቻልም። በፍታ ተንቀራቅበው ቶመና አባይ

እየመራ ከመሸሁበት ቡና ቤት ይዞ ወኝ ገቡ። ሆን ብሎ ከቤት ከሚፈላው ቡና ይልቅ ውድነት የፈሰሰበት መጠጥ ይበልጥ ይጥመናል። አንዱ አበሻ ያየው ጊዳ ለሌላውም ጊዳ ሆኖ የማይታያቸው ብዙ ገጥሞኛል። ከዚህች "ዘዋራ" ቡናቤት እንደገባን ሊተኛ የሄደው ብርሌ ቻፕውን ይዞ ተጎልተውብታል። መጀመሪያ ብርሌን አላየሁትም፤ ቻፕውን ሳየው ስውነቴን ንዝረት ወረረኝ። ብርሌም እርቅ ሳይቶይ ከሸንትቤት ወጥቶ ተደረበን። የቀደመ ወደል ወሸቴ ሁለት ሰአት ባልሞላ ጊዜ ዘገብኝ። ተጨባብጠው ተሳሳሙ። እኔም ብሆን ዝም አላልኩም፤ ቻፕን ጨብጬ፤ ከብርሌ ጋር እንዳልተያየሁና አብረን እንዳላመሸን ሁሉ ያውም እዚያው መቀመጫ ላይ፤ ተሳስመን የረጅም ጊዜ ሰላምታ ተለዋወጥን። የብርሌን ስሜት ባላውቅም ለኔ ግን መሳሳሙ ድንጋጤየን ቀነሰልኝ።

ብርሌ ለቻፕው ያመሸንበትን ሁሉ ለመለፍለፍ በቅቶ ይሆን? ይህ ከሆነ፤ ነገር በጣም ተበላሸ። ያውም ቻፕው በተፈጥሮው በጣም ጠርጣራ ነው። የኛ እዚያ፤ በዚያ ሰአት መገኘት በምን ይተረጉማል? ቻፕው፤ ከጠርጣራነቱ የተነሳ የጠረጠረውን ነገር ልክ እንደሆነና ተጨባጭ ነገር አድርጎ የሚያወራ ሰው ነው። ብዩ አሰብኩ። እውነቴንም ነው፤ ብዙወች ከዚህ ባህሪው የተነሳ ያሙታል። በጨዋታ ላይ ሁሉ በሌለበት በተረብ ስሙ ባይነሳ ቀርቶ አያውቅም፤ «ብሉ እለ እሉ» በመባል ያው ቅንሹ ገብረ-ሀናን ሊሆን ምንም አይቀረው። «ቻፕው፤ ራሱን በሚመለከትም ሆነ የሚወደውን ነገር በማሞካሸት የመጠለት ወሸታም ነው። የጠላውን ነገር በማይገኝም ቀለምና አገጅቶ ይቀባዋል። የእውነት መጨበጫ ጅራት የለውም። ከጨዋታው ሁሉ እርበ-ፍሬ አይወጣውም፤ ለሰው የሚቀዳውን ቢራ ያህል ነው። ቢራ ሲቀዳ፤ ማንደልደያው እንደተጎመደበት ጠላ ማቅረቢያ የጠርሙሱን አፍ ከመከፈያው ብርጭቆ አውቶ ያርቀውና ባረፋው ብቻ ይሞለዋል። በመሆኑም አንዱን መለስተኛ ጠርሙስ ቢራ በክቡር ዘበኛው እምቡት ያወጣዋል።» ይሉታል። በተለይ፤ እያ ተብጀም በሚቀመጡበት የጨዋታ በታ፤ አባባሉ የተጠነቀቀ-ተጠንቅቶ ቢሞላላቸውም፤ መላ ፈልገው፤ ምን አይነት ነገር ነው፤ የቻፕ ቢራ አቀዳድ እዚህ ቤትም ተገኘ፤ የቢራ እጃችሁ አጠጣ እንዴ? ብለው ሳያሾቁ አይወጡም። መጠጣ ቢራ ብቻ ከሆነ ለማለት እንጂ ሌላው ጉልበታም መጠጥ እንደቢራ አረፋ ስለማይወጣው ቻፕን አያሳማም።

ቻፕ በጣም አተረተረልን፤ ያልጠበቀ መስተንግዶ ዘራልን። በአቀዳድ ቢያሙትም ከሰው ጋር አብሮ በመብላት እንክን

አይወጣለትም፤ ትልቅ ፀጋው ነው። እኔ ሳውቀው፤ አረፋ ማብዛቱ የቀልድና ዝና የመስራት ስስ ይመስለኛል። ወደአረፍት የምንወጣበት ጊዜ ነበረና ደህ የተማሪ ኪሳችንን ሳያስፈታን ቀረ። እኔ ግን ገና ሀሳብ ማእበል ውስጥ ነው ያለሁት። መጋበዙ በጀ፤ ግና በዚህ ያልጠራና በያቅጣጫው ተመሰበ የተመለከትኩት ሁኔታ እንዳለ፤ የቢራ ሞቅታ የተፈጠረ እንደሆነና አንዱ ያላግባብ ነገር አስጀምሮ፤ ስጨነቅበት የዋልኩት ንድፍ ሁሉ ተጋልጦ ዘዋለን በስሁተት እንዳላስገደለው ፈራሁ። ብዙ ከተጎለቅን በኋላ፤ የዳር-ዙሪያና የቿመጠብትን ርእስ የማይነካ ጨዋታ ሲሰለቻቸው ቻፕው ተነስቶ፤ «ሂሳቡ በሙሉ ተከፍሏል። ደኅ እንግዳየ (ብርሌ) እራት አልበላም። ከምምጣታችሁ በፊት «ረጅም ጊዜ» ተቀምጠናል። ለተማሪ ሌሊቱም ሁሉ ቀን ነው። መቀመጥ በሌሊት ይጠብቃችኋል።» አለንና ጊዜያችንን ከልተው ወጡ። መጠጥ ቤቱ ከግማሽ ሰአት በኋላ ይዘጋል። የጉለትንነውን እንሚልጠን፤ ያልተከፈተውንና እንደናስከትል የተተወልንን ቢራ ሁሉ ሸንጣ ውስጥ ዶለን ቤታችን ተመለስን። ዘዋለ ተኝቷል። ቡናውን ጥደን በታፈረ ጀማሪነትና ማእከልነት ተከታዩ የሁኔታ ቅንቀና ተጀመረ። ከሁላችንም አድሜ የዋጠ እሱ ነውና ታፈረ እንደርዳሪ ሆነ።

«ጌበዝ፤ ይህን የፒጃንት" አድማና የነገር አያያዝ "ባይክሎጂ" ምን አይነት ሊሆን እንደሚችል ባዶገበት ሁሉ የምታውቀው ነው። ከመሀከላችሁ የከብትም ሆነ ቀፎ ለብ ዘር የለም?... ደቅርታ፤ ማለቴ፤... መስረቅን ያመቀ። የሌብ መላ ዙሪያ ነው፤ ረቅ ስታሰበው ዋናው ከመንደር ይገኛል። መግቢያ መውጫውን አውቆ ተጠብቆ ገብቶ ማውጣት ለቀረበ ሰው ይቀላል። ቅኝ ስርቆት የሚሰርቁ ሰወች በዚያ አባይተው በዚህ የሚገልቡት ናቸው። እያንዳንዳችህ፤ እንደህ ያለ ጀብዱ እንዳይፈፀምብህ ሆቲታህን ስር አሲዝ፤ ከወዲያ-ወዲህ ምታ፤ በገጥ ማሰስ ትኩረት ይደረግበት።

«ያመሸህበት የቢራ ሰው ሁሉ ጤነኛ አይደለም። ጤና ማጣት ...ዝም ብሎ ይታየኛል። እንዲያውስ! ምን ዳር-ለዳር ያስኬደኛል! ከመሀከላችን የሚፍረከረክ፤ ደም-መጋበት የሚፈራ ከሰ ይኸኔ ተናግሮ ገጥ ይያዝ። የፖለቲካ እርምጃ ነውና የሚወሰዱት ብዙ ትእይንት ይፈጥራል። የኛ ጥረት ያሰቡት የፖለቲካ እርምጃ ወደማለሰብ ጉዳይ ተለውጦ የእስር ቤት እራት እንዳሆን፤ የቀበጭ መቀጠጫ ማድረግ ነው። በቅር አትቀርልንም። ብቻየን ቢሆን ከዘዋለ ጋር አብሬ እወድቃለሁ። ይቻት እንዳጉጥር ጥይት በባማው ቀጥ!» ሲል አባይ የታፈረን መንደርሪያ ተከተለው።

«ሌላ ምን አማራጭ አለና ነው?... ስለቱን ከዱግ አዘጋጅቶ፤ ሲመጣበ ጥሆን እየያዘክ መጥረብ ነው። ሌላ አማራጭ አለ? የታፈረ ጥያቄ ከሁሉም በፊት ይቅደም። አቷም ይወስድ! ዝርዝር ልናስበ ከጊላ ይከተላ። ተፈው፤ እኔን ከንተ ደርበኝ፤ አልሸሽም። የቀረሁ ሁሉ በግልጥ ተናዝዝ፤ መቸም ኑዛዜ ነውና። እንደህ ወደእንገረብ፤ እንዲያ ወደመገጭ፤ ከዚያ ወደጠዲ የሚሀልበት በታ የለም፤ ምርጫ አንዲት ብቻ ናት፤ ሆሞቷን መቷጠር!»

የዋለብኝ ፍርሀት የመከፋፈል ሁኔታ ነበርና እነዚህን ሁለት ተቾወቾ ስለግ እንጆቴ መደንደን ጀመረ። ሁሉም አንድ ሆነና ቡና ጥንቅርት ቀሰቀሱ። ቡና መንደርደሪያውን የሚጀምረው ፈርቾው የዋልኩት እንግዳ ሰው ሆነ። ቀደቾ ስረዳው የዘለቀ ዘመድ ነው። ዜናውን እንተረተረው። አዲስ ወሬ ሊስጠኝ ይቅርና በያዙት ወሬ አፕሬገጥ አልደረሰም። ስለሆነም "ጆሊ" ዜናዩን ሳበረከትና ከኔ ሳይ የዋለውን ድንጋጤ በነሱም ላይ ለዘራብቸው ሲያስመኘው፤ ታፈረ እኔን ተመልክቶ፤ «አቲበ፤ እንተስ የስማኸው ወሬ የለም?... ነገረስ አውሬ ነህ፤ ዘመድ ማቷጠርና መቃረብ አታውቅም። እንዲያው ወንን ለማድረስ እንጂ ማን እንዲልንገረሀ ነው? ዳብተር ዘመዱ!» ብሎ ያሬጠጠ ሽመጥ ሰራብኝ። ይሀ ዘለፋውና መሳለቁ ግን ከራት አደሉት ከሉት፤ እንዲያው ዝም ብሉ ሀደልና መዝናናት ሰጠኝ። ከእድሜ የሚገፋኝ ስለሆነ እንጂ በባዶው «ጋን እና! አንተ በዘመድ ቀራቢነትሀ ምኑን ወሬ አምጥተኸው ነው?» ብለው በወደደኩ ነበር። ግና አጥብቶ መዘናት ሳሁን አይሆንም ብዩ ተውኩት። እንደመታሽትና እንደመጆንን ታጠኝ፤ ቀጥዩ የወሬ ስልቾየን ፈታሁ። ለጊዜው የነጋሪየን ስም፤ አቅጣጫ ብሎም ፍንጭ መደበቴ ሁሉንም ምቾት አሳጣቸው። ተናገርም ግመናቸውን እንጂ! ከብርሊ ጋር የዋልንበትን ወዋታ ወርሽ አቀንቅኝ ወረስኩ።

«እያንዳንደሀ አሁን ተቾገሬሀል። ቢራ ከጋበዘሀ ጉበኝ ጋር የነበረው ጉብሌ ነው ይሆን ሁሉ ያሸከመኝ።» ስል የሁሉም አይን ፈጠጠ። የደከመውን እኪል ሁሉ ነፍስ ዘራሁበት። የዘለቀ ፊቅ ከሁሉም ያለፈ ተሰከረ። ቀጠቀ-ብድግ አለኝና ወደእምድጃው እየዳደ፤ «የሚያስጠጣ ነገር መጣ፤ እስካሁን አልፈራሁም፤ አሁን ወረረኝ። ነፍሳሌ፤ ዛሬ ታዲያ አስገደለሽኝ ነበራ!»

«እየተሰተዋለ! እኔ ነኝ እንዴ፤ ዝዋራ በታ ብዩ መርቾ የወሰድኩሀ? አበሽን አበሽ የሚገለው ከሆነ፤ ዘዋራ በምትለው መጠጥቤት አጥምዶ ነው። እንዴ የሚገኘው ሌላ ሀበሻ ከሚዞድበት ነው።» አልኩ፤

«ጆረ... ባንተስ ጥፋት የለም። እንዲያው ያጋጣሚው ነገር ገርሞኝና የምናገረውን መቀኘት አቅቶኝ እንጂ! ጉበኝ ከነፍስገዳይ ጋር ቢራ ስተፍፍ አመሸሁ። እሱ ግን በጣም ሲበዛ ወገኛ ነው! እንጆራ ይወጣለት፤ "ነፍስ ስትወጣ፤ የመሸኛዋን ትተምባለች" የሚባለውን ወግ አደርሰ፤ ጠበል ቢጤ ሲያተምስን አመሸ። ፈሳሽ፤ በጣም ተራቷል።» ብሉ እንዲያው ብቻውን፤ ከቡና መጠጁው ምድጃ፣ ከማተዘተዢው፤ ከመሀፍ መደርደሪያው ሳይቀር እየተሟሟጠ ይደዘውን አጠ።

ምንምእንኳ ለድብድብ ሲጠቀምበት አይቾ ባላውቅም ታፈረ በደህና የተገነባ ሰውነትና አካለቀመና አለው። ከሰውነቱ መመሳት ጋር ቀመቱ በዚያ ግድም ከሚኖረው ሀበሻ ልዩ ያደርገዋል። እንደእያ ተበጆ ባይበልጥም፤ ረጠጥ ብሉ ስለሚራመድ አንዳንድ የከጆላቸው ተብለው የሚታመና ከሱ ጉን ተወሽቀው ለመታየት ያልበቁ ቅብጥብጥ ልጆገረዶቾ ገና ለገና እንፈራዋለን ይሉታል። የጆንበቾ ቤት፣ አሊያም ጆርመዋቾ በቁመታቸው ይቻቻሉት ይሆናል፤ የሀበሻ ቤት ግን የዘመኑ ሳይገስ የተገዘገለገቾ ቤት ከልፈለፈለለት የእግዚሮን ፍጡር ይገነጣጥለታል። በጣም የሚያስፈራ ነገር ይሉታል። ግና ሁሉም እሱን ለመወሸም ሞክረው ያልቀናቸው ናቸው እንዲህ የሚያወት። ከጉርድ ሸሚዙ ተበቦ የወጣ የፍንጆ ከንዱን ሀዋሳት በእንክሮ ቀጠረ። አብጦና ጌልቶ በተከሰተው ጥቁር ደም ተሸከሚ ቢንቢ ሳይ ለበ ጣቱን እያመሳለሰ ዝምታ ዋጠው። ከዋጠ አመለካከቱ የተነሳ ብሉወቻቸን የሱን ወሳኔ አውቀንም ሆነ ሳይታወቀን የመተበል እምልክ ይሜነናል። ዝምታው እኛን ምቾት ሲያሳጣን፤ ዘለቀ ጆበናውን ጥዶ ተመለሰና፤

«ታፈረ!... ምን ይዋጥሀ? ለሀይል መሪነት የመሾሚያሀ ጊዜ ደረሰ። ነገሬማ የቅኛውን መሳሪያ አስይዘሀ በዚሀ ግቢ፤ በዚያ ውጣ ልትለው ይሆን? የኢ-ሁ-እ-ፓ ተመክሮ አፈር በልቶ ቀረ። የለመድከትና ባንድ እጅሀ እንጠልጥለሀት ትሮጥ የነበረቸው "ብሬይን" (መትረየስ) እዚሀ ብትኖር ኑሮ እንደለብዋን ዱፈጣ ተዋጊ ከሰማይ ጠብታ ሆንየ ወጥተሀና አስተክለሀ፤ "መደሽው ጥፊ ነው፤ ደቻት ግን ሊቀርብ ነው?" ብለሀ "አጥር ምጥን ያለች አኝሬሽን" (ግብር) እከሂደሀ... ጆረወዲያልኝ! ምን ያደርጋል! ሰው ትጥቅ ፈቶ ከእንዲሀ ያለ ጊዜ ይደርሳል?... ቅዝቃጤ ንእሰ ከበርቴ ተሰብስቦበት የነበረ ድርጅት አልከሰከሰሀና የጥቃት እራት አደርገሀ ቀረ! "ሰው በላው ጉንዳረ፤ ተበላሀ ዛሬ" ያለ ጉበዝ እንዲሀ ያለው ጆል መፍረክረክ የጠመው ነው።» ሲል ታፈረ ሰጥ ብሎ አዳምጦት በሹም ተነፈሰ።

«መጅ እፍ! በጣም አልቧረቅህም? ወዴትና ወዴት ትፈጫለህ? ከፍህ እየተገረደፈ የሚወጣውን እሾር ልብ አላልከውም። ከዘዋለ ሞት ላይ ተገኮር ልትበላ ቿምጠሀል መሰል!.. እርፍ! ተገኮር የሚያወጣም ሆነ የሚወጣለት ሰው አይኖርም።» አለው።

ከሚዳ የተነሳ ገዉት ነበር። የዘለቀ የተረብና የዘና ጨዋታ ነበር። የታፈረው የሚያበደነብር ግለኝ ሆነ። ዘለቀ ታፈረን ዝም አላለውም። «ሰው አንዳንድ ቀን ልዘና ሲል አታዘናኝ፤ ባንተ ቤት እርምና ዘበት ነው። ዝም ብለህ ስፕራይትኽ ክክክላ እንደሆንክ እድሜህ አለቀ። እንጀት የሚበላ ነገር ከሆዱ ጣልክበት።» አለ የዘዋለ ብቸኝነት ስለተሰማው።

ታፈረ፤ በእውነትም ነገር መምረግ ያውቃል። የታየውን ለትም ዘወር ለለሚል፤ ከሱ ጋር አፍ የሚከፈቱ ሰዎች ተጠንቅቀው ነው። የጉድን አሽሟጣጮች «እግዜር ከደብተራው ቀጣ ያድን» ይሉታል። ይሆን ሀሜት እሱም በደንብ ያውቀዋል። የሚለውጠው ያቀራረብ ስልት ግን የለም። እንዲታወቅ የሚፈልገው እንደዚያ በመሆን ስለሆነ ነው መሰል። ዘለቀ፤ ከፈላው ቡና ጋር ለስታ ቅቤውንና ግርግራታውን ጨምሮ ዳቡውን ይዞ ከተፍ አለ። የተሸነገልንበት ቢራ ሆዳችን ገፎት ስለነበረ፤ ሁላችንም አልከፋንም። ታፈረ የሆድ ነገር የሚያሟጠት ሰው በተለየ ይወዳል፤ «አሁን፣ የተቀየምኩህን በሙሉ እንባሁልህ፤ የተናገርኩትን እንዳልተናገርኩ፤ ይህ አልዋዋልህ ካለ ዳግም፤ እያ ተናገረያለሁና እንዳልሰማህ ቁጠረው።... ዘልቂ፤ በጣም ባልትና ለምደሀል! ... የተገኘውን ባገረ ያቀረበ ልክ ስራ የሰራ ሰው ነውና ልክ ሰርተሀል!» ብሉ የሁላችንም አቅል አዘናው።

ቤቱ የጥናት ጠረጴዛ መጣያ ብቻ ባይሆን ማብሰያም በመሆኑ፤ በስሚስሚ የተለቀመው «እረብ እመጣሹ» የወጥ ቅመም ሁሉ ኢትዮጵያዊውን ባልትና የሚጉትትልን ይመስል የእቃ መደርደሪያችንን የሞላው ቅመም-ነክ ነገር ብቻ ነው። ከምጠናው ስሁተት እልፍ እያንዳንዱ ከድስት የሚገባበት ጊዜ ያልተጠና በመሆኑ ያለቅጥ ሲደወር፤ ጅል ስብቀት እየሰበቀ የቢያ ከተማ የኬሚካል እንዱስትሪ የሚተፋውን ክርፋት ሲሆን ምንም አይቀረው። ባልትናቸውን በናውቅም ሀንዳውያን ሪዛቸውን እንበለ -ቅመም አይቀቅሉም፤ የመናውያን ኢትዮጵያውያንን ሊመስሉ ምንም አይቀራቸውም። እንዲያውም ቅመም በማስጉልበት ከእኛ ይበልጣሉ። ሞሮኮወች የረመጥ ላይ ስጋ ነፍባቸው ነው፤ ቅመሙ ከመቀው ባቁ ላይ ሲወድቅ፤ የሽንኩርት ገለባ ያመሰችና ያቀፊነዉቹ ሴቱ ኬታ በክበቡ ያስፈልጋል። ቅጥ ያጣል። አረቦች፤ ከህንዶች ጋር ይመሳሰላሉ... ምናልባትም፤ በደህና አብስለው

የሚበሉ ናቸው ብለን እናግቸዋለን። የከባቢው እኩሌታ ይሆን ይደይዝና፤ የመሰሉ ግፅጃ ኬሚካል ሲጨመር ቤቱን ከግፅዳት ይልቅ ባንድ ላይ ተዳብሉ ያፍንጫ ዝለት ይፈጥራል። ከቤት ከገቡ በኋላ ምንም አይደለም። በድንገት በር በርግዶ የሚገባ ሰው ግን አፍንጫውን የተሰበረ ያሁሉን ነው የሚቶፐረው። ሲጋራው የሚፈጥረውን ሁላችንም አጫሾች ስለሆን ለይቶ ቶቸው ነው። ከረምት ኪልሆነ በር ማንገርበቡን ማንም ይመርጣል። ብቻ፤ የቀረብልንን ተስናጠቅንና መገቱ ቀጠለ። ስለሞን የመጀመሪያውን እስተያየት መሰል ጥያቄ ወረወረ፤ «ይህን ሁኔታ በምክጠር ለፖሊስ ማስታወቅ አይቻልም?» ሲል ታፈረ ተቀበለው፤

«ምን መረጃ ይዘህ ነው ለፖሊስ የምታመለክተው? ያለመረጃ የቀረበ እንዳም ፍርህት ወይም ተንኮል መስሉ ይታያል። በተንኮል መንገድ ከተረጉመት እንከሰራለን። ከዚህ እልፍ፤ የማገናዘብ አቅም ካለህ ከፖሊስ ፊት መገደል በጣም ያምርለቸዋል። የፖለቲካ እርምጃ ተብሉ መስየሙ ከተራ ወንጀል ለመውጣት አይደለም። ታዲያ አመቻችተህ ትሰጠው? ጉብዝ፣ ካልሆነ ስህተት እንዳንገባ እየተጠነቀቅን። አንዱ ያቀረበውን ሌላው ሊቀበለው ስለሚችል መሪ አታቹ ነገር በደንብ ይበልጥ። ሌላውን ተወው፤ የቤርሽበን ፖሊስ ጣቢያ ያስመረረ የኢትዮጵያውያን መተራደድና በየጊዜው መጠራት ነው። አሁን በጣም ሰልችተው፤ ንጉስ ሸዋል ጉዳና የሚል ጥሪ ቢጠረ፤ «ተወው ይህ ጅንገል (የሚከ ሰው) ሁሉ እርስ በራሱ ይቀራደድ፤ አንድ በወደቀ ቁጥር ለእስራኤል አንድ እዳ አብሮ ወደቀ» ይሉልሀል፤ ከዚህ ቀደም ተብሏል። በተማሪነቅሀም የምትለውጠው አይኖርም።» ብሉ ገለፀው። ይህን ጉዳና ሲዘጋው፤ ሰሎሞን በመከተል፤ «የእፍ በቅርህን እጅን በማንሳት ተቀብያለሁ። ግና እኔን እንቅፈህ ዝምታህ ለምን ነው? ይህ አይሆንም ሲባል፤ ሌላ ይሆናል ማለት ጀግንነት ነው።»

«ሊቀመንበርነቴን ረሳኸው እንዴ? የኔ ዋና ተግባር ስራውን መስመር ማስያዝ ነው። አገር የሚናገረውን መጠቅለል ነው!... ተረታህ፤ አይደል? ምን ታደረግ! ቅሽረኝ? ምን እድርጊ?»

ይህ እንዲህ ሲታለድ ዘለቀ መሀል ገባ፤ «መመታት የነሱም የኛም ነው። በበኩላቸው መርጠን መቅተን እንድናለንን ብለው ሲተልሙ- እኛ ተከላክለን እንድናለን እንበል። አለመመታትንጅ ነው። መመታት ብዙ ክስረት አለበት፤ አንደኛ የሞራል (ቅስም) ውድቀት፤ ሁለተኛ ክስረት! ክስረት ሲባል ደግሞ በጣም ተርቅራቸሁ እዩት ያማል፣ ወጭው ምጣት ነው፤ ከመርህግብር ያስተጓጉላል። ሲከፋ ጉደሉም ይሆኗል። መመታትም ይኑር፤ ግና ሁሉ አይውደቅ። ከእኩል ጉድለት ሞቱን እመርጣለሁ፤ ጣጣ

የለበትም። ስለሆነም ዘዋለ ይጠራና በደንብ «ብሬፍ» ይደረግ (የወረው ጭማቂ ይነገረው ለማለት) ከዚህ በኋላ፤ ሁሉም ጉዳዮችን ከነቃ፤ ዶሴውን ተሎ እንዲያደርጉት መገሬያ ዘዴ ይደራጅ...። እለዚያ ስንጨነቅ መዋራችን የራስ ምታት ነው። ገፋፍተን፤ የታወቀ ነገር ነውና ሲመጣ «ክርነር» (ማእዘን) ላይ ሆነህ ማምባር ማምባሬን አፍልስህ ዘወር ነው። ቅስማቸው ከተሰበረ በኋላ አገር ይረጋል። ሌላ ድርጅት ሊያደርጉ ቢሞክሩም ቶይተው ይሆናልና እኛም የምንፈልገው ጊዜ ማግኘትን ብቻ ነው። እንደዚህ ያለው የመገፋፋት እቅድ ከፖሊስ ያደርሳል፤ ባትለምን ፖሊስ ይገባል። መሀል ፕርጊያ ላይ መንጋው ነጭ በሁለት ደንጊያ ተወራዋሪ ጥቁር መሀል ሲታመስ ፈረንጅ ዝም ብሎ አይመለከቱም። ሰለሞን የዘለሰውን፤ ታፈረ ዳግም ውድቅ ያደረገውን ሀሳብ በዚህ ማጠጦም ይቻላል። ገና አገር ሊናገር አይደል? መገሬያው ምን ይሁን? የሚለውን መፍቴ በጥልቀት ቤቱ ይመለከተው።... መቀስቀስ ዝም ብሎ መቀስቀስ ነው። ሊሉቻችሁን ለማናገሪያ የማበታ ወረወርኩ። በቃኝ።»

«በል! ገፋ፣ አገር። የዘለቀን ሀሳብ የሚያሳድግ ከሌለ የሚነቅፍ፤ እሊያም የተለየ ያለው ይናገር!» ሲል ታፈረ በሊቀ-መንበርነቱ፤ አባይ ጥያቄ የመሰለ፤ ግና የነጠረ አስተያየት መስጠት ቀጠለ፤ «ከዚህ ሁሉ መአትና ግርግር አድማው በዘዋለ ላይ ከሆነ ለምን አይሸሽም? ትምህርት ቤት ቢያቃጥል አንድ እሙት ነው። «ከመሞት መሰንበት» አይሻልም? አገር በሙሉ ባንድ ሰው ታመሰ!» ሲል የታፈረ አይን ተጉረዘረዘ፤ «ቢሆን ኑሮ መልካም ነበር፤ የዋልንበትን መማገል አፈር በላው። የፈለጉት ከኛ እንዲነጠል መሰሉን! ይኸግ በጣም አግረላቸው። ከሚዳ በተነሳ ፍርሀት፣ ትምህርት ሲከብደው ፈረጠጠ ብለው ይክሱትና «ሰክንት» (ይሁዳዊ መረዳጃ ተቋም) ከእዳ ወጣሁ ብሎ ቁጭ ነው የሚልበት። የእስከሁኑን እዳ ለመክፈል ሽቃላይ ሁኖ ይቀራል። አሁን የሚሰጡትን አገልግሉት በዚያ ወቅት ቢጠይቅ አያቀምሱትም። በራስህ ሰርተህ ተማር ይሉታል።... ያውም ነገ ጧት መኮንኑ ለወታደርነት አገልግሉት ይዞት ሲሮጥ ከተፍ ይላል። አባይ! ይልቅ ስለደንጊያ አወራወር፤ ስንጢ እያያዝና አመካከት ብታጠን አይሻልም? ገና ለገና አገር ያልተረዳልንን የረጫ ስምሪት ከምትተነትን!»

«እርምጃው የሚወሰደው የት ላይ ነው?»

«የትም!»

«እንዲያ ከሆነ፤ አንዱ የሚያልፍ መስሉ ከራ ሊሸጉጥበት አይደል? በሌላው በታ እብረነው ብንሆን ት/ቤት ስንት ጊዜ

ልንጠብቀው እንችላለን?» ሲል ታፈረን የትእግስት ከዳት ይብሰው ጀመር።

«ካንድና ከሁለት በላይ መሆን አለባቸው፤ መጠርጠሬን ያውቃሉ። የነፍስ ወከፍ እርምጃም በጠራራ ፀሀይ አይደፍሩም። ከዚህ ሌላ ዘዋለ "ካራቴ"ና "ጁዶ" ይችላል የሚል ፍርሀት አለባቸው። ሰሞኑን የበለጠ እናስወራለን፤ እንዲፈሩ። ሌላውን ተወው፤ ባለፈው ሰምንት ዘዋለና ቃኘው ከኔ ቤት ተገናኙ፤ ቀኝ ሲፈትነው የንጉቲያ ቀልድ አስነሳ፤ ደጋግሞ ሞክሮት ሄደ። ይህን ያገናዘብኩት አሁን ነው፤ ሰበበው አይን ያጣ ስለ ነበር። ከዚህ በተረፈ ግን "ከመን ሲንሰሙን (ተመክሯዊ ግንዘቤ) ተጠቀምበት፤ ከት/ቤት ላይ ሰንጢ ይመዝል የምትለው ሰውም ተሸክሞት የሚዞር ነፍስ አለው፤ ይፈራል። ከጠራ ሜዳ ላይ ሰው ሲወጋ፤ ፈረንጁ ሆዩ ሽብር ፈጠረ ገባ ብሎ እጅ-በእጅ ይቀራመተዋል። ት/ቤት ላይ ከተማቱ እቅዳቸው የገቢያ ትቢ ሆኖ እርምጃቸውም ህዝባዊነቱን ያጣል። የሚመቱን ከመንደር ላይ ብቻ ነው። ይልቅ፤ ዉለማንና መታጠፊያን ማስወገድ፤ ብቻ መጊዝን ሁኔታው አቅጣጫ አስኪይዝ ፍፁመን ተው። ከፈትህ አንድ ህበሸ ስታይ ፊቱህንና ሂላህን ገላምጦ ማየት ካሁን ጀምሮ እንደፍርሀት እንዲይቶጠር፤ የህበሻዋ ኩራት ያለችበት ለጊዜው ይተዋት፤ አታዋጣም። ከጆል ባለንጋራ ጋር የተጋጠምን መሆኑን አትርሱ።»

ትንተናው እየቀጠለ በር ተመታ! ታፈረ መቀመጫውን ለቀቅ፤ ወንበሬን ከጠረጴዛው ራቅ አደረገና፤ «ዘለቀ ቁም! እሱን በርና የከንድ ግወራጫ ሆዋ ልቀቅልኝ! ጉበዝ የምትይዘውን ያዝ!» ብሎ እኔን ገፋ ሲያደርግ በሬ ዳግም ተንኳኳ፤ «ማ-ን -ነ-ህ!» ሲል ድምፁን በጣም አጃጃለው። መቺው ድምፅ ዘዋለ ሆነ። በሬን ለመክፈት ጋጋታውና የሱን ፊት ለማየት ኳኳቴው በዛ። ዘዋለ ሲገባ ሁሉም እንባቆ ጠየቀው። በዚያ የሌሊት ሰአት አመጣጡ ያልተለመደና ያልጠበቅነው ሆኖ፤ እሱ ይገረምብን ጀመር፤

«በሞታችሁ ምን ቢወርድባችሁ ነው እስካሁን የተጉለታችሁት? በጣም ሰቅጠጡ አመሻችሁ እንዴ?» አለ። የሰራነው ስህተት ቢኖር የተውንለትን የማስታወሻ ወረቀት ከመጠጥ ቤት በተመለሰንበት ሰአት አለማንበታችን ነበር። ታፈረ ለዘዋለ ጥያቄ መልስ፤ «አለም! እኛስ በጣም ደህና ነን፤ በጊዜ እንደዋዘ የጀመርነው ክርታ ወደቁማር ተለውጦ እንዳንድ ሰው ኪሱ በብር ደክሟል። ይልቅ ጆብ ያስበረገገው መንገድ ይመስል አንተን ከዚህ የጣለህ ጉዳይ ይገርማል።»

«ሸንት ቤት ስገባ፤ መብራታችሁ እንደተገተረ ታየኝ፤ በመሆኑም የጤናቸው ነዉ? መጣሁ። ስቀርብ ታገመግማላችሁ፤

በዚያው ተሰብሰቡ። ያስነሳኝ ግን መልስ የማያስተኛ ቅዠት ነው።»

«ምኑን ታዝኸው?... በሰሞኑ፤ ከሏቧ የተጣደች ልጃገረድ አመለጠችህ? ገደል ስትገባ አየሃት? ቀሚ አበረረህ?» ብሎ ታፈረ አፋዘበት።

«ኧረ አትቀልድ! ልጃገረድ የሚያስብ አእምሮ በዚህ ወቅት የለኝም! ሁሉም ህልም ቅዠት አይደለም። ወደእውነት የሚለወጥ ሞልቷል። ልብ ካለህ ነው!...» ብሎ ህልሙን እንዳናጣጥልበት የፈራ መሰለ።

«በል የታዘኸውን፤ እውነትም ደብልልህና ህልምህን ተናገር!»

«ሌላ ሌላ የዳር አጃቡን ተወውና ትግረ በሙሉ ሁ-ብሎ ሲከተከተኝ በእንቅልፍ ልቤ ሙሂ ነው ከርሊስ (የከፍል ተደበ ፎ) «ምን ሆንክ ብሎ» ቀስቅሶ ከሞት ያዳነኝ። እንዲህ ገጥሞኝ እያወቅም፤ ህልሜ ይኸው ነው።» ሲል ሁላችንም መገረምና የለጠ ውጥረት ታየብን። የታፈረው የባሰ አይኑ ፈጠጠ፤ እንደመገረምም ቃጣውና ዙሪያ ባይኑ በሌሉን፤ ከዘዋለ ላይ ሊደርስ ሲል አይኑን በዚያው መሬት ላይ አሰረገው። «እናታችን ላይ በምን የማይሆን ነገር ተጫንከን? እውነትም «ቅዠት!» ትግረወችን በጣም ትፈራለህ መሰል? ቀን ያንገራጠጠህ ኑሮ ይሆን ?... ዘዋለ፤ በል! ደህና ልብስም አልለበስክ፤ እንደኛ መቶመር ከፈለክ ወደክፍልህ ሂድና ደህና ልብስ ለብሰህ ና! እኔ ቡና ስጠጣልህ እቆያለሁ፤ ቡናውን ስትቀምስ ቅዠቱም ብኖን ይሆናል፤ ራስ ምታቱም ቢሆን ያልፍልሃል። በል! አንተን እኮ ነው! ትግረወች ባይቀራመቱህ ነፍስ ጡትስርህን ብሎ እንዲይገልህ! ሰው የገደለው ይሻላል፤» ብሎ ከዚህም ከዚያ ነክኮ አጣደፈውና ዘዋለም፤ በእውነት የተጨነቀለት መስሎት የተባለ ልብስ ለብሶ ሲመጣ ሞሰስ ብሎ ሲወጣ ሲል የወለል ላይ ምንጣፉ ጠለፈውና መሬት ላይ እጊጉል ተሸበለለ፤

«ዘራፍ! የበሪያይቱ ሽል!... ተዘንቡ!» ብሎና ሳይታገዝ ተወናጭር ሲነሳ ታፈረ ፈገግታ መጀመሪያ ሰጠው፤ «በዚህም እንዳትከሰስ፤ ... አንተ ልጅ ወሳጅ-ነክነት ባይዋርብህ ይቀራል? ይህች ብረት ኪ ባለች ቀጥርና እንቅፋት ሲመታህ የማትለ ውጣት መረገረጊያ ቅርጉም መዳረሻዋ ጠፋኝ። ከንድ ወናና ሽግግሉ የተዳህት ባትሆን ትቀራለች!»

«እንዴታ! እናቴ የወጣላት ኩርችች ፀጉር፤ በግባሽ የወተወለወለ ሙጉጉ የመሰለች ጥቁር፤ እግሯን መጀሊ ከእንቅፋት እክሱም - ሸዋ እሰኝቶ አንቀራፎት ስድ የተረገጠች፤ ጥፍሯ - በወገ አድጉ ከመኪርከም ይልቅ ተንጨርፎ እየተቀረፈ ሊወድቅ የቀረበ፤ ልብሷ ግባሽ ከኩብቶ ጠብ አንቡቶ ከባበቷ ጋር ተዳብሎ

የከረፋ፤ እፍንጫዋ ስከራም የረገጠው ጣብ ይመስል ተዘብቶ የተደፈጠጠ፤ ከንፈሯ የተዝረከረከና እሽካፊ የምትጤይት የመሰለ... ቅልጥ ያለች... ይቻት ጥቁር አፍሪካዊት ብል ምን ትፈጥራለህ... ትክ ብለህ ተመልከተኝ፤ ደጋግመህ ብትመለከተኝ ብዙ አይነት ነገር እሆናለሁ። እንተንም ከሀያ ስከንድ የበለጠ በቀን ትክ ብዬ ከየሁሁ ዝንጀሮ ትመስለሀ... በላሊ እፍ!»

ፈጠን-ፈጠን ስንተያይ ታፈረ ተረገመ ተንፍሶ ከበደበድ ያሉ ከንፈሮቹን ከማከማቸው፤ የቃል ትንፋሽ ግን ሳይወጣው ቀረ። ዘዋለም ሲለበስ ሲወጣ አሁን መሬቱን አላመነውም። እንደወጣም ታፈረ፤ «ማን ነህ? በቀምህ ሰንበቶ ታቀምህ! በራዱን ጣድና ተሉ ተመለስ!» ብሎ ድምፁን እንደገና ዝቅ አደረገው፤ «ይህ ሰው እኮ በተከፈተ አፉ ደህና አድርጉ ደብድቦኝ ነው የሄደው፤ በጣም አገኘኝ... ግን፤ አየኸው! ጥና ጠረው ለፍፎ አስነስቶት!... እዚህ የህልም ፈቻ ዘር አለ?...ነገሩስ ግልጥ ነገር ነው። ምን ቀርቶታል! ወርሶ ነው ያወቀው ።... ጉብዝ... ይሁን ልጅ፤ ግዳላችሁም... መቅተውታል! እንነገረውና ይረፈው! የእርምጃ ወሰጆችን ስም ግን አንድ ብላችሁ እንዳትነግሩት፤ ቻል ብትሉትም የደም ጥሬ ከፉ ነውና ስውነቱ እየተሽማቀቀ፤ ባጠገቡ ሲያልፉ መንታቱን ያስበላብናል። ይህ ከሆነ ደግሞ የሚያድነውን መላ አንሰራም። ኩነቱ፤ እኛ ከተበላን፤ ሁለተኛ እቅዳቸውን ማግኘት አይቻልም። እንኳን ገዳይህ ይኸ ነው ብለህ ነግረኸው፤ ከምንም በታ አይቸው የማላውቀው ሰውና በድንገት ባጠገቤ ሲገጥመኝ የሚያስደነግጠኝ ሰው አለ። ይህ ሰው፤ እንደም አጥሬ የ እሊያም በጣም የምወደው ሰው ነው ብዬ በመጨረሻ ግን መሬት ነው የምፈልገው፤ ያጥፋኝ፤ ያልገኝ ስለማይረዳኝ። የሆነ ሀይል ግን ይገፋኛል፤ ስለሆነም፤ ዘዋለን ከሀሊሙ ጋር ሰታዩት እነዚህ ሰወች ባጠገቡ ሲቀርቡ ይቅርና ስማቸውም ሲጠራ መደንገጡ አይቀርም። ያን ድንጋጤ ግን መግለፅ አይሆንለትም፤ አቅም ያንሰዋል። ከዚህ በመለስ በፍርሀት እቃ ሊያነሲም ጉንበስ ብሎ ጥባው ሲመታው ያንዱን ራስ ቀዳምኩ በማለት ቀንጭሎልህ ያርፍና የእስርቤት ቀለብ አድርገኸው እንዳይቀር። በመረባቸው፤ እንደጀመረት፤ የጦቢያ ክርስቲያን እስራኤል ላይ ፈላሽ ገደለ ተብሎ ነገር አለቀ፤ ድል በድል ሆኑ ማለት ነው።»

የዘዋለ በዚያ ስአት መንቃት ሁኔታውን አፋጠነው። ጋቢውን ተጎላምና ተመልሶ ሲገባ፤ ታፈረ በጨዋታ አመቻቸና አደረጃጀቱ ከመሀከላችን የጉላ ነውና፤ «ሰማህ ዘዋለ! ቶንጆ ቅዠት ነው... ያታዝህ! ነገርየው የ«ቴሌፓቲ» (እኛ ወቃቢ የምንለው አይነት ነገር) ይመስላል። ፍጥረት የሚያወራው

ስለምክሩ ነገር ነው። እኛም ቢሆን እናወራ የነበረው ስለትግሬዎች ነበርና ግድግዳውን ሰርስሮ «ቴሌፓቲው» ከንቱ አድርሶት ነው።... የጠንቋይ ዝርያ አለብህ መሰለ። እኛ ከዚህ የምናወራው ስለጎተና ስለትግሬዎችና ሌሎችም ነው። ከጠጣው ዘምቶ፤ ከእኛው ጋር ተጋጭቶ፤ ማባረሪያው ያንተ ጆሮ ሆኖ ነው። ቢሆንም፤ «ቴሌፓቲህ ሰርቷል።» ሲል ዘዋለን ገር አለውና፤ «ምንድን ነው የምታወራው? በደረቅ ሌሊት ስለትግሬዎች? የምትሰራው «ማግኔቲክስ» አጠሁ እንዴ? «ቴሌፓቲያዊ» ሀይል እስኪፈጠር ስለትግሬ የሚያስወራ ነገር ምን አገኘህና ነው?»

«ያመሸነው ከመጠጥ፤ የምንጫወተው ካርታ ነው። ከዚህ የማይነሳ ሀሜት ምን ሊሆን ይችላል? ትግሬዎችም አቤይ የመነጋገሪያ ርእስ መሆናቸው አቅርሷ? ገና ከእንቅልፍህ አልነቃህም መሰለ?» ብሎ ተፈራ ነገር መዘዝ ሲጀምር፤ ዘዋለ ፀጥ አለ። ግራ ገባው፤ ይኸኔ ታፈረ ዘዋለን ትክ ብሎ ተመለከተ... «ጥሬ ቴሌፓቲ መቀበልህ ብየሃለሁ እኮ ዘዌ! ወደፊት፤ ስለኔ ያለምክ ቀን መለድ ብለህ ንገረኝ፤ ፍቱን አለሚ ሰው ነህ። የእውነት ከሆነ ግን፤ ቀድመን ያገናኘው እኛ አይደለንም፤ ያገርህ ሰው ሲያወጋ እሊያም ሲበላ ጥርሱ ስቶ «ምላሱን ቆረጠኩት» ሲል ሰምተህ እንደሁ፤ እንዴያ ያለው በራሱ ጥርስ ቀርጫ፤ ሰው ሲያማህ ነው ይባላል፤ በመሆኑም «ቴሌፓቲህ» የእነሱንም ሀሜት ጉትቶት ነው። ለሀያል በቅርብ ከጆሮ ውናል። በግራ በቀኝ ስለድብድብ ነው የሚወራው። የፈለሽ ለዚህ አዲስ አገርና ሁኔታ የመነጋገሪያ ጊዜ ነውና ብዙ የምንነባበር ሳይሆን አይቀርም። «ልንወርሳችሁ ነው» ብለው አወርተዋል። ግና፤ «ህልም ተፈርቶ ባይተኙ እያደረጉም እንደሉ ...» ሲል ዘለቀ፤ የታፈረን ያልተደፈ ተረትና ምሳሌ ነጠቀው፤ «አቤት፤ አቤት... ከምኑ ሁለት ውስጥ ልትደል ይሆን? ለሌ ማቆሚያህን እንደፈለግህ፤ ይህን ያረጀ ተረትና ምሳሌህን ግን ውድቅ አድርጊሃለሁ፤ ምንው ፊትለፊት አእምሮውን ልታጥበረብረው ባትምክር!... ህልም ያስፈረጠጠው ጉበዝ ከፊትህ ጋቢ ተጉንፎ ተቀምጦ፤ አንተ ሌሊቱን ቀን አድርገህ ተቀምጠህ... እሩቴ! ታፈ፤ እጅ ሰጥ አሁን አገኘሁሃለሁ፤ ቅምባሉህን አንሳ!» ብሎ ተዘበዘበት። ታፈረ በጣም ፈጣን በሁተት እውጭ ብሎም የራሱን ጉድፍ ለይ በመሆኑ እንደያው በባቅ ተንፈቀፈቀ። ቀደም የጀመረውን ታሪክ ሊወርስ መስመሩን ከለላ ጣልቃ ገቢ «ኧ..ኧ..ኧ» እያለ ሊጠብቅ ሞከረ፤ ባቄ ግን አየለበት። ዘልቶ የድል አድራጊነት ተሀድሶ እንሰራራለት፤ «ሰማ ታፈ፤ እትልፋ፤ ከዛሬ ጀምሮ ዘለቀ፤ እንዲህ ብሎ አለ እያልክ ተናገር! በሌላ ነገር ልትገልኝ አትተናተኔ፤ ቀድሜሃለሁ። ተረትና ምሳሌ ብሎም ጥቅስ

የሌለበት አረፍተ-ነገር አጠራሁ ብቻ ዝብዘባህን ቀጥል። እንዲሁኑ ከጥቃት ይጥልሁል።» ሲል፤ ታፈረ አፈረ፤ ሲናገር የነበረው ከራሱ ተረና የተሰባለለ ምልሱን ከዘለቀ ጋር ቀጠለ፤ «በጭጭታ! መሀል ዘለህ ገብተህ፤ ብሎም የምደረስበትን ሳትረዳ ዝም ብለህ ቀርጭፈህ ዝና በራሠበት፤ አሁን «እንዲህ ሊል ነው የነበረ» ብለ እውነት አይመስለም፤ የመከላከያ ነገር ነው ብለህ በተጨማሪ ከምትወነጅለኝና ሁሉንም ባህሪ የን ከምትበላው በዚሁ «ተጠቃሁ» ማለትና ዝም ይሻለኛለኛል። ግና መስዋእት መሆኔን አትርሳ፤ ይሁንልህ፤ አትቀትሀል... ይንጨባጨብልህ!» አለ፤ ሲባ ጣቶችን እያማገረና የፈገ እየጠበጠበ! የዘለቀን ተረብ በዚህ ጎታውና ወደዘዋለ ተመለሰ፤

«ሞት የሁሉም የጋድ ነው። ከመጣ አይቀርም። ከኛ ዘንድ ግን ልዩ የሆነበት በቀርጥ ቀን «መጠሁብችሁ» ማለቱ ብቻ ነው። የመምጣትን አዋጅ በኛ በኩል ልምምድ እያደረገ ነው። «የአገሬ ባለገር፤ «እጟጟቴን አበምረው» ይላል፤ ፊት ለፊት ቀጥ ያልረባበ ሞት ለሳኛው ሲሞት ሲያየው። የትርጉም ነገር እየሆነ ነው እንጂ ራሱን ተፈለጥ፤ እገር ከእጅህ ዱቴት ሆኖ ሙት፤ ሁሉም አንድ ሞት ነው። ቢሆንም እንዳበት አዳራ፤ እኛም «ያገሬና ጠፈፍ ያለ» ሞት የሚለውን ገጥ ልንሞክረው አስበናል። ለዚህ ደግሞ ሀሞት ዋና ነገር እንዲሆን ትንቢተናል... ቶንጠር፤ ጠከፍ እንደማለት። «ዘ ዌ፤ ያለ ነገር ተጉልተን አላደርገም። አንተ በሰላም ነው የዋልከው፤ ያመሸኸው፤... የጠበጠው ነገር ቢኖር፤ ትንሽ ትኩሳት ነው። ግና፤ ትኩሳቱ ነገ ልንነግርህ የቀጠርነውን መርዶ ወደዚሬ ለውጦታል። ብቻ በተራህ እንዳትጉልተን፤ ... ያለምከውን፤ ሀልም- እልም ብለህና ባፈፈ አይንህን ከለህ ተመልሰህ ተኛ። እኛም ትንሽ ወንፍረን እንነሳ። አደራችሁን፤ ከቅ/ ቤት አድግችሁ እንዳትቀሩ! ዘዋለ ይበቃህን ያህል ተኝተሀል፤ ቀሰቻሽ ሁን። ደህና አደሩ ብሎን ለመከታከሚያ ቀልድ ወመረበት፤ «እየተደራረብክ ተኛ! ወደ የክፍሉ እሄድ ስትል አገርን ትተስትስና በእንቅልፍልቡ የተነሳ እንዳይጠርብሽ።» ሲል ስተንለት፤ እየተደመጥን ሁሉም በያለበት ወደቀ።

የዘዋለ አቤይ ጭንቀት የዚህ ቀን «ሳይኮሚትሪ» (ያእምሮ ገሪትና ትንች) ሆኖ፤ መደበኛ እንቅልፍም በመተኛቱ ቡና አፍልቶና ጉትጉቶ አስነሳን። የኛ በደንብ አለመተኛት እንደለ ሆኖ፤ የለሞን አፈጣጠር ተጨማሪ ራስ ምታት ነው። ተኛም አልተኛ በጣም ደተኛ ፍጥረት ነው። ከመጉተቱ ብዛት በአትን አይቶ አይኑን ሲጠልጦና በርጋታ ተደላድሎ ሲዝናና ማየት ባንድ ዳቲያ የአት ጉዳና የሚከንፍ ያስመስለዋል። የተለመደ ነገር ነውና

ሁሉም ይጨንቅበታል። የዳኘ ቢድህ ክፉ ንግግር ግን አይወጣውም። ስለሆነም ሁሉም ሸከሬው ነው። ሰለሞን እስኪደራጅ የሰላብንን ያህል ጊዜ ከልቶብን የፈተናውን አዳራሽ ተጠጋን።

ከጠዋቱ ዘጠኝ ሰአት ከስድስት ደቂቃ ስንገባ ከዳራሹ የሚወጣው ሟሟቴ ሳይሆን የሚወጣው ጩኸት ልዩ ነው። ከሰው የሚወጣው ሟሟቴ ሳይሆን ከንድ የስፖርት ጋዜጠኛ ብሉም ያንድ ሬዲዮ ጣቢያ ልፍላፎ ሆኖ፤ በንፍስ-ወከፍ ተደዘና ያለቅጥ ተከፍቶ ከሚሰማው የስፖርት ዘገባ ነበር። ይህ የሆነው የስራ አል ብሄራዊ ቡድን ሳውሮፖ ዋሉ ማለፍ ጃርመን ላይ የሚሟወትበት ሰአት ስለነበር ነው። አብዶች ለቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡበት አዳራሽ መሰለ። ሽንጣሙን ወለል ተሟምተን ስናያምስ፤ ከፈታኞቹ አንዷ ከፌ የማገዶቸውን ሬዥም ብርድ-ወይ (የቅምባህ ጥቅልል አይነት) የጠንፈር ቀለሟን እንዲያሳስበት ተቸገሩ አሳቻ፣ በእፍኝ ያስቀረቸው ጠበ ሲትጉለጉል እይኗን እያጠናበሰው፤ «ሄይ! እናንተን ነው … ኑ ወደህ!» ስትል ቀረብናት፤ «ምንድን ናችሁ? … አብሬት፣ እንግሊት፣ ስፖኒያ፣ …?» ስትል አባይ በመልስ፤ «ኢንግሊሽ!» ብሉ በተረገጠ የዜማ ቅኝቱ፤ ምድብ በታችንን ያዝን። ባለሬዲዮው ሁሉ በቅጋል ከቶመ በ ሂላ ያእምሮ ማስሸው የፈተና ወረቀት እየታደለ መሬየ ወደድምፅ ማገጠሪያው ቀረበች፤

«ትኩረት! እያንዳንዱ ጥያቄው መታጻሉን ያረጋግጥ፤ ባባእድ ቋንቋ የምትፈተኑ ሁሉ (በየራሱ ቋንቋ የሚፈተነው ጥቂት ነው) አልነበረም) ማብሪሪያ ለስጧችሁ የሚችሉ ሰወችን መቅረብ ይቻላል። ፈተናው የመከረጅ ባህሪ የለውም፤ እንዲትታሰሉ፤ ይኸው ነው፤ ጀምሩ» ከማብራሪያ በቀር፤ ቃልእንኳ አትቅዱ። ያወጋ ጀመር። ብዙ ስትወርስ፤ ሰሎሞን እንገቱን ደፍቶ ብቻውን ያወጋ ጀመር። «ይኸ እንግሊዝ ሀበሻ ሁሉ በርግተ ወዋታው ለኛ የተበጀ ነበር። «ይኸ እንግሊዝ ሀበሻ ሁሉ በርግተ ወዋታው ለኛ የተበጀ ነበር። በጩነቀ አያችሁልኝ? ጉድ ፈላበት፤ እነጉለምን እዚያ ግዶ በጩነቀ አያችሁልኝ? የከፋት ጉዳቱ እንደህ ባለ ጊዜ ነው። ወርዶበቸው! ምኒትን ከምን ሊያደርጓቸ ይሆን! እዚያ ግዶ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን የመርግሪ ከሚሸን አቀማመጥ አይነት ተሰይመዋል። ይኸ ነው!» አለ። አገር ዝም በል! ደህና በቅር ይሉህል ይኸ ነው!» አለ። በባላንጠነት የሚመለከቱንን የኛ ሰወች ሲዘልፍ፤ ዘዋለ ዘለፋውን ተቸው። «አንተ ሞግዳፍ! "ሳይኮሜትሪ"ና "ሉጅክ" አጃጃይ ፈተና ነው፤ አቅዛበት፤ የናቅሁቸው ሰወች አልፈው አንተ የወደቅህ እንደሆን ሰቄ አይወጣልኝም!»

«አልፈለሁ ብየ አልመፃደቅም፤ ነገር ግን የነሱን ስእለንት ደግሞ አትክደኝም፤ ከስድስተኛ ክፍል የመጣው ሁሉ ከኮሌጅ

ተማሪ ጋር "ሳይኮሜትሪ!" የኔ አወዳደቅ የቅል፤ የነሱ ሌላ። የሚገርመው የነሞች መጃጃል ነው፤ እኛ ሰናወቅ "ሳይኮሜትሪ" በድሜና በውቀት የሚመሳሰሉ ሰወችን የሚያማቅር ነበር፤ እዚህ ግን ሁሉንም የሚደበልቅ ነው።»

«ልብ ክልክ ው፤ የሚፈተነው ሰው ሁሉ ብዙ የሚያመሳስለው ነገር አለ፤ ዝም ብለህ አትፈቅፍቅ!» ብሉ ዘዋለ የሰለሞንን ቅቻት ዘጋው። ሰሎሞን የከፈተው ወሬ በድሉኛል፤ ፈተናውን ተሉ ከመጀመር ይልቅ ትኩረቴን ወደሌላ ነገር አዘረው። አብዛኛውን ጊዜ ያጠፋሁት የነዚህን ዳብዳቢወች የእይን እንክርታቶ መፈተሽ ሆነ። ሌላው ያይኔ ማረፊያ ዘዋለ ነው። አቀማመጡ አስፀያፊ ከመሆኑ በላይ፤ ወገቡን ነው እንደመቀመጫ የሚጠቀምበት፤ ይህን ጊዜ ይበሉኑ ሟጭቶ፣ የተቀመጠበት ወንበር ፈፍቶ የበላው መሰሉ ታየኝና ነዳደኝና፤ «ወ ን ድ ሚ! ምን ጊያ የሰበረው ይመስል በወገቡ ይቀመጣል!… ቀና አይልም? "እንኳን ዘንበብሽ፤ እንደያውም ጭቃ ነሽ!" ይላል የነሀሴ ሀበሽ። ሰውነት እንዳለው ሁሉ በወገብ መቀመጡ! ወጋም! ቀና በልና ሰው ምሰል!» ስል መልስ መስጠቱን ትቶ አዳራሹ ዳር እስከ ዳር እስኪዳረስ ተንከተከተ፤ ከሳቁ በመጣ ሰው ሁሉ የመገረም እይን ታየበት። ተሉ መልስ የሰጠበት ጉዳይ አልሆነምና መምህሯ በክራ እርምጃ ተጠጋቸው፤

«ያሳቀህን ነገር ማወቅ ይቻላል ጊደ!… ሳቅህን ሰክው፤ ሌላውን እስከማትረብሽበት ደረጃ! ከመፈተኛ ክፍልእክ ነው የተቀመጥከው!»

«ይቅርታ! ደግሜ አልስቅም! ጨርሻለሁ።» ሲል ሲትየዋ በመገረም ተመልክታው፤ የሳቀበትን ማወቅ የፈለገችም መሰለ፤ ግና ፈገግታ ብቻ መግበው ዘረች። የሳቀበትን ማወቅ የሷም ሆነ የሌላው ሆኖ፤ እሱ ግን ቢቷራጭ መልስ ዘጋበት። መምህሯ ግባው ስትርቅ ሁሉም አንገቱን ወደስራው ደፋ። እኛ ግን በጥተ ድምፅ የሳቁን መነሻ ለማወቅ እናዋጣው ቀጠልን።

«ሰማ እንጂ ዘዋ፤ እንደህ ያለ የወጣለት ሳቅ ሰምቸልህ አላቅም።»

«አንተ ምን አይተህ! እንዴት ፈልገው ቢያገኙት ነው አደራችሁን! ለዚህ ሰስተኛ አለም የመጣ የ"ፒዘንቅ" ጥርቅም … ሳቅ የበላ "ፒዙ" የደረሰው ድርሰት! እንብበህ በዚያው ቀጥለህ አሳድገው የሚለውን ምንባብ ገና አላያችሁትም? ልጆች፤ ስምትሳችሁ ይህንን ብቻ እንብቡ። ጠፈፍ ያለ ገበሬ … "ጅንጉል" (የሚከ ሰው) የደረሰው ድርሰት» ብሉ ተሳልቶ ሌላ ቃል አልጨመረም። እውነቱን ነው፤ የምንባቡ ትእዛዝ፤ «ይህን አጭር ምእራፍ እንብበህ ከሙቶ አምሳ ቃላት ባልበለጠና ባላነሰ

አሰደገው» የሚል ሲሆን ያስቀመጥም ይኸው ነበር። የኔም የመጀመሪያ ትኩረት ያገኘ ማንበብ ሆነ።

ምንባብ

ዝናም ወይስ ቸነፈር?

«በልጅነቴ፤ የምድጃ ዙሪያም ሆነ የተዘነበ የታል ታሪክ እስጠኒ ሸማግሌ ከተረከው ትንሽ የትዝታ እርሾ ቢኖረኝም፤ የህፃንነት መደነቅና ገሬ ስሜት ተደባልቆበት ስለሚሆን አሁን እሬን እስምልቶ እያናገረኝም። የያኔው ሲሆን የሚችለው ከትንሿ ልቤ የወጣ የፍርሀትና ያድናቆት ውኸንብር ነው።

ከእድሜ መዋጥና ብስለቴ ጀምሮ ግን እይኔን የገጠመ እጋጣሚ እንዲህ የተበባሰ ያየር ሁኔታ ባይ የመጀመሪያየ ነው። የመጀመሪያው ሆነና ጠርቶ የሚናገረው ያደም ዘር አልነበረም። የከባቢውን ሙቀት ዘር ዝናም አወራረድ ሀያል ሆኖ አፈወሰው። ብርዱ የውስጥ አከላቴንም ሙቀት መልጦ አድርጎ በላው። ብርዱ ይደነዝዘኝና ይከተክተኝ ጀመር። ነስቶ እንዳጥንት ሰብራት ወደፊትም ከተጋደመው የግንድ ባት ከስክሽ ረመጡን ግራና ቀኝ፤ ወደላይ እንዲያመልጥና እንዳይከዳ ሆነ ጉንና ጉን አስፋሁት። እግዳሚያየን እግረን እራጥጬ፤ ክንዴን በላዩ ላይ አግግሬ፤ ከወደደረቴ ስቤ አጠገግሁበት።

ሰውነቴ እንደገና ሙቀት ማንሳት ጀመረ። ይህ የዝናም መአት ያጠረረው ውጭ የዋለ ሰው «አገሮች እንዴት ዋላችሁ!» ይላል ብየ ከሁን-አሁን ተመኘሁ፤ ይሆን ምጣት ግስ የማይመጣውን። ታዲያ ወይአንድ ነገር ቢሆን! እየቶየ ሲሄድ የረመጡ ሙቀት ባይታወቀኝ ሆደን-ክልቢ ሲያገለው ምላሴም ደረቀ። የከባቢው ቅዝቃዜ ከስቱ እየተራዳ እኔንም እተነነኝ። "ይጥር ይሆን?" አልኩና የተጋደመ ግንብና የሰለለ እስር-ወሀ ቢጠ ይዋር መጋጠሚያየ ሁሉ ተነሳሁ። ከሙቀቱና ከቅዝቃዜው ግጭት የተነሳ ጅማቴ ሁሉ ከብርዱ ጊዜ ይልቅ እንደተቀለበ ሙክት ተንቃቃ። እሁን የበለጠ ታበሯል።

"ወይ ጉድ! ጊዜ ጉልበት ይበላል?... አረጀሁ መሰለኝ" ብየ ከመዝጊያ በሬ ከገንቡ ፍትሽ በፊት የውጭውን አለም ልያኝ ከጎነበ ተጠግቼ በቀደዳ አንጠለጠልኩ። የቤቱ ፊትለፊት ጋራ ከመዝጊያው ጋር ገጥሟል። አለ የተባለ ወለወል፤ ከንደኛው ለላኛው ይሸል እንደሁ ብየ ወሲጋን ከበ ዘርኪት። ከሌጋውና ከመደቡ ሁሉ ወጣሁ፤ ጉጆዋ ቶኖ የላትም እንጂ ያም አይቀረኝ

ነበር። ግና እንዲ የተመረገ ነገር ነውና የተሸለ የምለው ጠፋ፤ ርቆ የሚታይ ነገር አልነበረም፤ ጉሙ ሁሉንም ፍጥረት አንድ ሰማይ አድርጎታል።

በዚያች፤ ጋራውን ከቤቱ ለየሁ! ባለች ጠባብ የሁዋ መስመር ላይም ነፋሱ ጉሙን እያበዘተ የሚንቻፈቻፈው ከሬያ ከያወቱ ጋር አይኔን ቅጥ አሳጣት። በርግጥ የተቸገረው አይኔ ነው። በጠራ ሰማይ ጊዜ የማውቀውን ጋራ የሸፈነ የማያዞፍ ዛፍ ደን ባወራው ነፋስ ሲንገላታና እርቡበራሱ ሲተራመስ ከማሳየው ፍጥረት ላይ የሚወጣ ድምፅ ብዙ ጥርጣሬ ውስጥ ከተተኝ።

«እሀ? ከጋራው ፈንቅሉ ሊወጣ የተዉነቀ ባተ-ገሞራ?... ወይ ጉድ!... ከዚህ ድዳን መሀል ባት?... አይሆንም። እንዲያ ቢሆን ቢቷም እኔም አብረን በተንቀጠቀጥን ነበር።» አልኩ። ከጭንቀት ላይ፤ ደመነፍሴን፤ እንክላ ቢጤ እንሰቸ እስር-ወሀውን በተጋገዘ እጄ እንዳያዝኩት ወደዚያ የባት አውድማ ተመለስኩ። መጀመሪያ ሁለቱንም እግሮቼን ከምድጃው የወሰን መከተሪያ ከንፈር አሳልፌና ተጫምቼ ቆምኩና ያለ ድጋፍ ወ ረ ድ ረ ድ ብየ ልቀመጥ ስል በውነቱ አልገዘኝ አለ። መቀመጫየ ከወለሉ ጋር ገጭ ሲል ያለ ቅጥ የምላሁት እንክላ ተንቀጥቅጦ ከዚያ የተፈነጠቀው በረዶ-ነክ እስር-ወሀ ከጉልበቴ ላይ ፈሰሰ። ቅዝቃዜው በጣም አበሳጨኝ። እንደተክሳተርኩ ገርጨጭ፤ ገርጨጭ ባደርገው የጉሮሮየ ጨኸት ባሰ። «ሙቀት ስታንስ እጠጣሁ እንደሆን እንጂ አሁንስ በጀም አሳልክ፤ ሁሉም ነገር ተባላ ሆነብኝሳ?... ወይ ቀን!» ብየና አደላድየ ከመዱ ላይ ጉለትኩት።

ከዚህ የተቃረነ ሁኔታ የተፈጠረው ደከም ወደመድቀስቀስ ተስወጦ ከተለሸለሸኩት እንቅልፍ ስነቃ፤ ሀዋሳቴ ደህና የደም መለወስ ቢገዙም አይኔን ከፍቸ አደብ ለመግዛት ስንቀሳቀስ ከዋለብኝ ባት የተነሳ ጥፍረ ለምቾ ንጥቀት የተዘጋጀ የከቢ እንጨቱን ያህል ይጠበሳል፤ የጥፍሮቸ መዋያ መሪና ዙሪያ ከፈፍ ስጋ ቀልቶ አብጧል። እንዲያው ወደግራ ገሰስ እንዲልኩ ኑሯል የቀረሁት፤ ከምድጃው ከንፈር።

ሀይል የገዛሁ መሰሉኝ ስነሳ እንገዳገደ መሀል ረመጡ ላይ ሊደፋኝ ሲል ታግየ ቀረሁና «ወይ ጠባይ!» ብየ ወደጨለጨሏ አመራሁ። ይህ አባባሌ በወቅቱ ከእምሮየ ሊፈስ የነበረውን እሮሮም ይሁን ሌላ ሀሊናየን የጠመነ የሀሳብ ጥንስስ የሚገጥም ሀረግ አልነበረም፤ እንዲያው ከእሁቴ የወረስኩት መረገረጊያ ነገር፤ የልማድ!... በእርግጥ፤ እሷ የምትጠቀምበት ቀምነገሯን እንተርስ ነው፤ ስትኪሽም። እኔም ብሆን "ነፍስ ካለ መንቀሳቀስ አይገደም ይሏል፤ ሰው ግዛዝ ነው፤"ግየ ነበረና....?

እንደሆንኩት ሁኖ እዚያች መከረኛ ወለወል ተጠግቶ ባንድ አይኔ ስያኝ፤ ከሚሰነጠቀው የመብረቅ ጩኸት ድምፅ ሌላ በልጭታው መረብ ከመረብ እንደምትጉንጉን ሸረሪት እሳይቶ፤ በመልኩ እንደምትመገምገው፤ የሚሰራው ብልጭ-ድርግም አይኔን አንበረበረው፤ ያው የሳዘር ሳብሬቶሪ"1 ሁኖት አረፈ።

ጉም ቢጠራም፤ ከላይ የተሰራው ጥቁር ደመና እየተቀረፈ የሚወድቅ ሳጣ ገደል ሁኗል። "ጅብ ስትወልድ በዝናም ጠሀይ ይወጣል" እንደሚሉት፤ የሰረቀው የጅቡ ወልጃው ፀሀይ ፈንጥቆ ዝናቡ በነጩ ይወርደዋል።

«ወይ የኪነት ብዛት!... ዛሬ ፍጥረት በሀይል ተቆጥቷል። ምህረት ወረደ! ምን አይነት ጭንቀት ነው? ከይኔና ከጆሮየ የሆን ችግር ተፈጠረ? የሌለ ሽብር ፈታኝ?... ይህች ጠባብ ወለወልክ ...እኸኸ?

«ቀጠሮ፤ እንዴት ነው? መልስ አትሰጥም? ተነስ፤ ጅብ ወለደች!» አልኩ፤ የሱ ደብሱና ከወለሉ ላይ የጋን ማስተጫ ግቶት መስሉ ተሸብልሉ የተኛ የቤታችን ወሻ። በመንቀሳቀስ የመልስ ምት ሊሰጠኝ በቀር የእንስሳ ነገር ቃል አልወጣውም።

ዙሪያየን በሁለቱም አይኖቼ ልፈትሽ፤ በሬን ልከፍት መወርወሪያውን ሳነሳ፤ በነፋሱ ሀይል ተበረገደና ጋቢየን ነቅሉ ከግድግዳው ለፍጦ፤ ርቃን-ሰጋየን ወለል ላይ ሸበለለኝ። «ይች ናት ጨዋታ _ ኧ-ፉ-ሹ-ሽ _ ኡ-እ-ይ! ጠፈፍ ያለች ትግል! _ የውጭው ግዛት እልበቃው አለና ነው? ዙሪያ ከበቡ ጠበበው? ከሳጠው የሉል ስፋት ይሆን ያሀል መስገብገብ? በዚህች ጠባብ ጎጆየ ተቀንቅበ ትዕ!» ያለኝን ቷንቁሩና ግስንግስ ሲያተራምሰውና ሲፈጀ ሲገለባበጠት የቃታ እንኳ ምንም ነገር ሳላነሳ፤ የግሬን መሚጊያ ብልጭታው እያደናበረው፤ ማገርንጡ እስኪጠመጠር ታግየ ልዘጋው ስሞክርና እምቢ ሲለኝ፤ «ያልጠረጠረ፤ ተመነጠረ!... በል እንደልብህ፤ ክፍቹ የሰጠሁህን! የቀረህ ቤቷንም አትል መንሳት አይደል! _ያውልህ!»

እኔም አብሬ እዚያ ወለል ላይ እንዳጥናናም ከብት እምባ ሉሉ፤ እንዲያው እምባ ሉሉ! የት ብሉ ይሄዷል! የት?...»

የሁኔታ በአል ሊያመዝም እየተንደረደረ ነውና ደህን ሀሳብ ከቶን የሰነበተ ፈተና በመጨረሻችን ደስታችን ከየፊታችን ይነበባል።

እለቱ ጥቅምት ስድስት ሆኖ ግብያች የጦር ሀይላቸውን መመስረት የሚያከብሩበት ቀን ሲሆን፤ የነሱ በእል ግርፍ ደግሞ መከከለኛውን ምክሬት አብሮ የሚገርፍ ነውና፤ የሰራ-እልን

የፖለቲካ ሰወች መርሀ-ግብር ያዘበ ብሉም ተጨማሪ መታተር የሰጣቸው ቀን ነበር። ግብያች፤ የዚህን እለት ከብሬቸውን ግን ሌላ ገርገር ቢፈጠርበትም ለመጨወም ሆን ከዚያ እየተጠለ ለሚሄደው ጥቅምት ስድስት ቀን ሌላ ተደራቢና እድግቲ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑን ከቀኑ እናት ቀደም ብሉ የነበረው የከባቢ መንፈስ የሚገልፀው ነበር።

ለምን ያሁሉ የመካከለኛው ምክሬት ሰው ወጣሪ ነገር እንደሆነ ለመገምገና ለመፍረድ ቢያስቸግርም የፕሬዚደንት አንዋር ሳዳት ጠዋት መቀሰል፤ ከሰራ-እል የፖለቲካ ሰወች ጭንቀት አልፎ ፖለቲካ የማይገዳቸውንም አስፈራራ። አንድ ሀቅ ቢኖር የተራው ህዝብ ሽብር የተፈጠረው የፖለቲካ ሰወች በህዝብ መገናኛ ላይ ከሰራት የመሳ-ምት ቅድመ-ሀተታ ነበር።

የቀትር በፊቱ ሀተታ የነፍስ መውጣት ጉዳዩን በድፍረት ተረግጦ አላነሳውም። ፀሀይ መመለስ ሲጀምር ግን ሬድዮኑ የነፍሳቸውን ጣር በየደቂቃው ተጨንቀበት። በተለያየ መልክ ይቀርብ የነበረው የሳዳት ባህሪ አንድ አይነት ብቻ ተደረገ- የሰላም ሰው! በ"ካምፕ ዴቪድ የሰላም ድርድር" የምናሄም ቤጊን ጠረጴዛ ተካፋይ ነበረ። የሰላም ሰውነታቸው ይነሳ የነበረው ከዚህ ጥራዝ በሚወጡ ሀረጎች እየተቀኘ ነበር። «የቀትር በፊቱ ጉራማይሌ ሀተታ ወደቀትርበ ሂሳው የተሸበለለ ትችት መድረሱ የማዘኑን ተከታይ የፖለቲካ መድረክ መሪ ከለማወቅ የመጣ ትዝብት ነው። መጭው ሰው የሳዳትን ሰላማዊ ጉዳና ይከተል ዘንድ ደብጅ ጥቆማወችን የማድረግ ዘዴ ነው» ማለት እደብ ከገዙ ሰወች (እልጄልፎ ይወረወር የነበረ ትችት ነው። እስቸጋሪው ነገር ግብፃውያን የሚፈልጉት የመሪ መመዘኛ ጠርቶ አለመገምገሙ ስለሆነ፤ ለሁሉም የምሽቱን የቴሌቢዥን ዜና ደመራ እ-ሀ! ብለን ጠበቅነው፤ በምሽቱ ሰስት ሰአት ወደመዝናኛ ክፍሉ ተጓጉደ ጉደን።

እዳራሹ ያለቅጥ በመመላቱ፤ ርእሰ-ዜናውን ከሰማን በኋላ የክፍሉ ሙቀት ናረ። የሰው ትንፋሽ እያመሰ በመሄዱ ተራምጄ ዘለቀን ተጠጋሁት። «ሰፈልገህ መጣህ! የሳዳትን ሞት ስትመለከት፤ ያንተም ሞት እየተጉነጉነ ይመስላል። የምንጠረጥራቸው ሰወች ምችት አጥተዋል። እኛን እሳዩንም፤ በዚህ እምስት ደቂቃ ውስጥ መውጣት መግባት፤ አይናቸው መቅለብለብ አብዝቷል። ዘዋለ የተቀመጠው ከሰው መሀል ነው፤ እንዴት ባይን ጠቅሶ ማውጣት ይቻላል?» አለኝ።

«ምን አስፈራህ እዚህ መሀል ጠብ የሚጀምሯ ይሆናል እንዴ?»

«የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል' ነውና ከሳናቸው ያስጠቃናል። ዜና ሲባል እግሬን ዘርግቶ ቀጭ ነው የሚለው፤ ዜና ወዳጅ እንደዘዋለ የለም። የሚያስጠቃን በታ ይኼ ዘኑርጊሬናውና የግርግር መሀል ነውና እንሽከሬው»

እንዴ ፍርሀት በደብናልና አንድ ሰአት ሙሉ ጠብቀነው፤ ዜናውን ወርሶ ሰው መቅለል ሲጀምር ዘዋለም ደክሞት ስለዋለ ነው መሰል ከርቀት እንደቆመ፤ ሲተኛ መጌዴን፤ አንገቱን ጠንን፤ እጁን ከጆሮ ግንዱ እንደማንተራስ አድርጉ እሳይቶን ወጣ። የምንጠብቃቸው ሰዎች እንደተቀመጡ ሰለቀሬ ተከቅለነው መውጣት አልታየንም።

የክረምት አብሯ ደመና ዋዜማውን የማብየት አየሯን ከላይ ተረግጦ ይዞት የብቢው ሙቀት ነጠላ እያስጥለም። የዘዋለን መተኛት ለማረጋገጥ ከተሰየን አንድ ሰአት በኋላ ከክፍሉ ስንገባ አርጀንቲናዊው የክፍል ተዳባ ፕቅልል ኢሮገሬም ከፊቱ ደርድሮ በሽክክና በታ አብታቂ ፊደላት ለዘመዱ ሁሉ ደብዳቤ ይፅፋል። በዘዋለ በኩል ደህና የተግባባሁት ሰው ነበረና ያስለፉ ነገር ገርሞኝ፤ «ይህን ሁሉ ኢሮገሬም ለመጨረስ ነው የተቀመጠው ሰርጀ?» ስለው ዘዋለን በንግግሬ ሳለመቀስቀስ ፈርቶ አንጋጦ ተመለከተው። መልስ እይቶኝ ድምጌን እንድመገን ሌባ ጣቱን ከከንፈሬ መትቶ ምልክት ሰጠኝ። ለጠየኩት መልስ ይሆን ዘንድ መብቢያውን መዞ ሌላ ቅልቅ ፕቅልል አሳይቶኝ ዘጋው።

«ይህንንም የምጨርስ ነኝ። ለመጨው በስቅ ወር ሌላ ደብዳቤ አልፅፍም። ሁልጊዜ ከምስቀቅ በረፍቱ እንዴ መወረዱ ይሸለኛል። ከትምህርት ጋር ደብዳቤ መፃፍ አልወደም። እናንተ አትፅፉም ... የናንተ ሰውእክ ጠቅላሉ አስራአል ገብቷል መሰል፤ አርጀቲናውያን ግን የናንተን ያህል ወደስራአል ስላልመጡ ሰው የሚያተክረኝ ሬቅ ሁዋ ነው። የምጠጣው ደብዳቤ በመፃፍ ነው። እናንተ እድለኞች ናቸሁ። ዘዋለ ግን የመጣ ሰው እንደሌለው አውቃለሁ፤ ግን ሲፅፍ አላየውም፤ የሱ እንዴያ መሆን ደብዳቤ ያለመውደድ ይመስላል። ተደም ያልኩት ልክ ነው ወይስ የዘዋለ በሽታ አለብህ?»

«ሁለቱም አይደለም፤ እንዳንተ በንድ ቀን አልፅፍም፤ እንደም እንደደረሰኝ ስለምፅፍ፤ መልስ ሳልሰጠበት ጥቂት ቀናት ከቆየ ደግሞ እፍርና ሳልፅፈው ይቀራል» ብየው ፈገግታ ብ[illegible] ተለዋወጥን። በዚያው ቀጥሎ፤ «ዘዋለን የምትፈልግ ትመስለህ[illegible] የምረዳህ ነገር ይኖራል? ዛሬ ዘዋለ እንደሁሌው አይደለም። ገ[illegible]

መታጠቢያ ቤት እንደወጣ የጠየቀኝ አስፕሪን ነበር። ራሱን አሞታል። በእንቅልፍ ያልፍለት ይሆናልና ባትቀስቅሰው ይመረጣል።»

እንበሶ-ነጠላ፤ በፊ እንደተደፋ መተኛቱን ተመለከቸ፤

«ምንም የምፈልገው ጉዳይ የለም። «ደህና እደር» ልለው ነበር የመጣሁት፤ መልካም በእንቅልፍ ይለፍለት። ደህና እደር ሰርጆ!» ብየ የራሴን የእንቅልፍ ጊዜ ሳደራጅ፤ ሌሎችንም እንዳልቀሰቅስ ተንጠሽ ገላ መታጠቢያ ገባሁ።

ብዙ ደቂቃ አይቢልም። የሆነ ነገር ተንጏጏ፤ ግን አልቀጠለም። ሳዳምጥ ውሀውን ዘጋሁት፤ ምንም ድምፅ አልነበረም። የስነበተብኝ ሀሳብ ነውና እየተጠራጠርኩ ገም ከማለት በሚል ቢያንስ ገላ መታጠቢያ ቤት እንደገባሁ ነገር መናቤ አስፈራኝ። የተዝረበረበብኝን ውሀ ብዙም ሳላደርቀው፤ ፎጣየን እየጉተትኩት ወጣሁ፤ «ጌበዝ ይኼ ግርግር ምንድን ነው!» ብየ ጮኩ። ዘለቀ ተደናብሮ ተነስቶ የሚሆነውን ሲያጣ፤ «በሰው አብ በል! የውጭውን ጫጫቴ አልሰማችሁም? ገላ መታጠቢያ ቤት ነበርኩ፤ ምናልባት ሰምታችሁ እንደሆን ብየ ስነጋገር ነው የተነሳሽው»

«ጫኸቱ ምን አይነት ነው?»

«ምን አይነት እንደነበር ባውቅማ መች እጠይቅ ነበር? ... አንተ የሆነ የሰው ንግግርም ይሰማል። ተሎ ተነሱና ዘዋለን እንየው። ሁሉንም አስነሳቸው። የኛ በር በጣም መወገሬን እርግጠኛ ነኝ ... በጣም ነበር የተወገረው።»

«እዚህ እንደተኛ ተናገረ ነበር፤ አገር ጠመመብኝ እንጂ። የኛ በር ከተመታ ነገር አልቋል በለኛ፤ ግን ሳንደራጅ በር እንዳትከፍት፤ በር የማስኩፈቻ መላቸው ሊሆን ይችላል።»

ተላብሸን ከጨረሰን በኋላ፤ «መልካም! ዘለቁ ተዘጋጅተሀል አይደል? በር ልከፍት ነው!» ብየ ሰራመድ ወደል ጠርሙስ እንሳና ጠሬን መንገርበቢያ ገፕ ይዞ ቆመ። እኔ የምከፍተውን ሳንታ እየብብኩ ማእዘን ውስጥ ገባሁ። ፀጥታ ሆነ። ከማእዘኑ ወጥቸ ወደበር ልጣም ሲያጣኝ ከመቃብሬ ላይ ተንሰራፍቶ የወደቀ ሰው እጅ የመግቢያ ከፈፉን አልፎ ከርቀት የተሰደደ የለማኝ እጅ መሰለ። ከውስጥ ሰሬ በቀር የለበሰው ነገር አልነበረም፤ ያም ደም ለብሷል።

በሬን የደበደበው ከራሱ የወረደው ደም ገና አፍላ ይፈልቅ በጀመረበት ስለነበር ብጠራው መልስ አልሰጠም፤ ተከታዩ እርምጃየ ምን እንደሆነ ሳላስተብታው፤ ከምንጠረጥራቸው ሰዎች መሀል ሁለቱ የፊት ለፊታችን መውጫ ደረጃ ከታች ወደላይ

ሲያያዙት አይኔ ያዘቻቸው። «ዘለቀ፤ ዘዋለን ገድለው፤ አሁን የኛ ተራ ደረሰ፤ መጠልህ፤ ተጠንቀቅ» ስል በዉሸት፤ ዘለቀ የያዘ ውን ጠርመስ ለስድ ሲያማትር ወደፊት ከመምጣት ይልቅ፤ መመለስ አይሉት ሌላ ነገር፤ አይናቸው ፈጠጠና የጠርመሱን አወራወር የመመልከት አይነት ነገር፤ የመሪው ፊት ተዉንቶ እንደመሸበር ሲታጠው፤

«የምንሄደው እኮ ወደፊት እንጅ ወደ ሂላ አይደለም፤ የገደላቸሁት ሰው ቤት ወዴት ነው? ... ሄድ» የሚል ህይልና ትንፋሽ የዘበት ቃል ሰጠማ የዘለቀን እጅ ወበጥ አድርጊ ገታሁት፤ ጠርመሱን ተሉ ብለህ አስቀምጥ!»

«ፖሊስ እየነዳቸው ነው፤ ጠርመሱን ተሉ ብለህ አስቀምጥ!» ስለው በቅፅበት አልጋው ላይ ወረወረው። የዘዋለ አጊጊት ሰለው በቅፅበት አልጋው ላይ ወረወረው። የዘዋለ አጊጊት በዉንቀንም፤ የገዳዮች ጭንቀት ግን የቀመትን ወታደሮች ግስን ልንመታቸው እንደምንችል የመሰጋት ነበር።

እንቢ-ባንቢ ይዘነው በንወርድ ከመጠን በላይና በሁይል ያስታወክው ጀመር። ይህን የተመረከዘው አንዱ ወታደር፤ «ትሁክት ጥፊ ነው። ሰውየው የሚድን ነው! አልሞተም!» ብሎ እየተንገዳገድን ከወስከ (ታሪዘ) ተሸከሚው መኪና ደልነው። የፖሊሶችን በዚያ አጭር ጊዜ መድረስ የፈጠረው፤ ሁለት ሰዎች ሲቱር ከከከላ የሚይዙ ጠርመዞች በወሀ ሞልተው በር ያከፈቱት፤ ብሎም ገፍትረው ያስወጡትና በመደናገጥ የሮጠው አርጀንቲናዊው ሰርጆ ነበር።

ከዘዋለ ጋር ለመጨረሻ የተያየሁት ከዚያ የዉድቅት ጊዜ ነበር። እረፍቱን በሙሉ ህኪም ቤት እባልፎ ባሰሎ አምስተኛው ቀን ጠዋት፤ ናላው ላይ ጠርመስ የሰበረበት ሰዎች ክስሽ በማጣት ዘዋለም ከህኪም ቤት የተፈታው በነዚያን በዘጠኝ ሰአት ሲለቀቁ፤ ደቂቃወች፤ ማለት (እነሱ የፍች ወሳኔ በተሰጠበት ፋታ) እንደነበር ከጫዋታ-ጫዋታ የነገረኝ ከ ወር በ ሂላ ለእንግድነት የመጣው ታፈረ በዚያ የተለያየንበት ዝነኛ ባምንት የገጠመውን ትኔ እንብበልኝ በቀጠልነውም ወሬ ነበር።

«ሰማ እንጂ ታፈ!»

«እሺ!»

«ማገምህ በጣም ትኔ ነው፤ ግን አልሰትኩትም፤ በጣም ገብቶኛል፤ የዘዋለ መጨረሻ ምን ሆነ?»

«ምን ይሆናል! ያው እንደተጀመረ በቁማር ያለቀ ነገር።»

«የቀረውን ቁማር አውራኝ።»

«ወደህኪም ቤት ሲሄድ ነበርክና አይተሀል። የጠበቀት መሞቱን ነበርና ‹ኮማ› (የመሳት ሁኔታ) ውስጥ ገና እንዳለና እንዳልሞተ ይሰማሉ፤ ከዚህ ፍርሀት ያድርባቸዋል። የጠበጣቸው

ነገር በስቱን ቀን ሰው ሊገባ በማይችልበት በታ መቶ የቱ ስለነበር የተቻላቸውን ዘቻም ሆነ ገመድ ሲገምዱ ሰነበቱ። ሲመልሰትና ከ‹ኮማ›ው እንደወጣ ግን በንድነት ሆ! ብሎ ገብቶ መጨረስ የሚል እሳግ ወስነውና ደምድመው ተቀመጡ። ...»

«ለምን?»

«ለምንማ፤ ከሞት ከተረፈ ብዙ ጉድ ስለሚበረብርባቸውና እሱም ጠበታ ከቶመ ነገሬ ሁሉ ወደመጋለጥ ያመራል ከሚል ፍርሀት ነዋ። ከሞተ ግን የሚናገር ስለማይኖር በሆታ ሰላይ ተገደለ ብሎ ፋይልን ማዘጋት ይቀላል የሚል አመለካከት ነበር።»

«መልካም ቀጥል።»

«በመጀመሪያው ምሽት ያን ያህል አልተጠነቀቁም ነበር። እጅ ከፍንጅ ተያዙ። ሰርጆ ያስሞላው ቃል፤ የተማሪው ማደሪያ ቤት አስተዳዳሪ ያቀረበውን ዘገባ፤ ፖሊስ ከኛ የተቀበለው ዜናም እንዳለ አልተመለከተም ነበር። በመጀመሪያው ቀን ባይሞት ደሙ ሲያልቅ በሁለተኛው ቀን ይሞታል የሚልም ሀሳብ ኑሯቸው ይሆናል። ያድግውን ሁኔታ በስታችንም በደንብ እንከታተል ነበርና፤ ከኔና ከዘለቀ ስም በቀር ዘዋለን ልጎብኝ ያለ እንዳይገባ ለህኪም ቤቱ አስተዳደር አመለከትን። እንደጠረጠርነውም ባራተኛው ቀን ሊገቡና ሊስልሉት ሞክረው ባይሳካላቸው ይቀራል። እንዲያ ሲሆን በህኪም ቤቱ አስተዳደር ላይ፤

«ልይነት ተደረገበን፤ ወገናችን ታሞ ተኝቶ እባስገብኝን አሉ፤ ነጮች ቢሆኑ ግን አይከለክሏቸውም ነበር፤ ሀበሻ በሽተኛውን እንዳይጎበኝ ሆነ ብለው ያጠውራሉ። ይህን የመግቢያ መሳ አከሸፍነው፤ ሊጨርሱት እንደሆነ እዋብቀን ስንጠቀምና ለዘዋለም ሌላ ሰው እንዳይገባ በመሳከተኛ ስናስጠንቅቀው ብዙ ነገር ይበላሽባቸዋል። እንዴት? ብትል፤ ከስደብዳቢወቹ አንዱ እዛኝ መስሎ ሊገባ ሲሄድና ሲጠይቅ-መልክም፤ መታወቂያ ወረቀትህን አምጣና ግባ ይሉታል። መታወቂያውን አውልቶ ይሰጣል። ነርስ ሆየ እያንከበከበች ከዘዋለ ዘንድ ትወስድና ይህን ሰው ታውቀዋለህ? ስትለው፤ ‹በጣም! አንዱ ተንከለኛ ይሆናል፤ ከመቸውም እናገረው እላውቅም፤ እታስገቢው፤ መታወቂያውን ለፖሊስ እንዲጣራ አስተሳልፊው ሲለት ነርስም ባዶዋን ተመልሳ ብትሄድ ያ ሰው የሚገድላት ይመስለታል። ሰላይም ነገር ሲዘገይበት ይጠረጥርና ቤቱን ይጊዛል። እሷም ሲጨንቃት ፖሊስ ስትጠራ፤ ዘዋለ ሁኔታውን አቶቶ መታወቂያ ከነርስ ወደፖሊስ ይሸጋገራል። ይህ ትርኢት ግን ከፖሊስ ጠቢያ የሚል ማህደረ ይመዝገብ አይመዝገብ አይታወቅም።

«ፖሊስ ይህን ባለመታወቂያ በመንደር ይፈልገዋል። ትንሽ ሊደበቅ ይሞክራል፤ ግና የቅርቡ ሰው ጠለጠ እንደሚያስጠረጥረው ስለተረዳ ውጣ፤ ውጣ! ተብሎ ይወጣና ሲጠየቅ ቃሉን እንደጠበቀና አዝዋ ሊጎበኘው ብቻ እንደሄደ ይናገራል። ወታደርም የጠረጠረውን በሆዱ ይዞ፤ አሁን ምንም ጉብኝ እንዳይገባ ተከልክሏል፤ ሁለተኛ ብትሄድ ሌላ መዘዝ ይከተልሃል፤ መታወቂያህን ደግሞ እንደሰረቀ ሰው ጥለህ አትሂድ፤ መታወቂያህን በጣታው መጣል ብቻ ከብዙ ፍዳና መዘዝ ያድርሀል ብሎት ይሄዳል። አገርም ከዚህ ልብ ይገዛና ያ በዚህ ይዘጋል።

«ገዳዮቹ በሁለተኛው ቀን ፍርድ ቤት ቀርበው ሁለተኛው ቀጠሯቸው ባስራ አራተኛው ቀን እንዲሆን ተደርጓልና የሚቀጥለው መሳ ታዲያ ምን ይሆናል ይመስልሀል?»

«ከዚያማ ምን ይቀራል?» አልኩ።

«ዋናው ጉድ ገና ወደ ኋላ ነው። ይህ ሁሉ ደደብ መሳቸው አለበራ ቤል ጠበቅ ያለ ዘዴ ይፈትላሉ። ያንዱ ገዳይ ዘመድ ባለስልጣን ባሰቺኪይ ይጠራና መሳ ተደርድሮ፤ ያሸም አለታ ሆስፒታል እንዲገባ የሚገባው ስለሌለ መሳው ከማጠን የመጠ ነው። መጋቢቱ ብዙ ሽንጉ ያስራል። ዘዋለን የጀርባ ሀይል ምናልባት መንግስት በጉን እንዴት እንደተደራጀ ማጠራት፤ የሚደግፈው ነገር እንዳለም ጉድ እንዲያበዛ ነገር ለመንደፍ፤ ከሆስፒታሉ በሚሄድበት ወቅት፤ ዘዋለ ቃለ መጠይቅ ስለሰጠ ራሱ ደም እስኪተክና እስኪዛወር ድረስ ስለጠቀቀ ዘገባ ለማበላሸት፤ ሲሆን፤ ዘገባውን ይበርዝና እንዳንድ የመከራከሪያ መሳ ይገባል፤ ብለው ይለብሙና፤ ሹምም ይህን መክሮ ከቸች ይላል። ይህን የሹም ተንኮል ቀድመን እዝግተንበታል፤ እንዲዘጋንው ሆነ ... መቸበ በየስፍራው ክትትላችን ነፍስእልፍ ነበር። እንዲህ ያለ አይኑን ያፈጠጠና ጠንከራ ጥቃት አባቴም በሰው አድርጌ አወርቶኝ እያውቅም። ይኸ ደፋር ሹም ከሀኪም ቤት የሚሄድበትን ሰአት ገምተን እዚያ ገቢ ውስጥ መቀሁብሯን አንተን ወቶ የምንለቅ ሆነ! ታጅበ እንደቀትር እባብ በቀትር እየተንበለበለና

«ጠበቅንነው፤ እንደቀትር እባብ በቀትር እየተንበለበለና እሱ መልክም ግቢውን ሲቃረብ፤ አጀቡ ወደ ኋላ አፈገፍጎ ከግቢ ጥልቅ ይላል። ኪሊንጀር አይነት በርሳውን እንጠልጥሎ ከግቢ ጥልቅ ይላል። ልናስደንግጠው ምን እግር ጣለህ፤ የታመመው ሰው አለ እንዴ? ስለዘዋለ ስንለው፤ ያዘኝ ቅቢ እንጊቾ እንደሉ ባልጠዳን ሁኔታ ነበር፤ ግን እንስቶ አተፈተፈብን። እኛም የመጣነው ልንጠይቀው ነበር፤ መብል መግባት አይቻልም» አሉን፤ ገና ሀመሙ እንደጠናበት ነው መብል ስንል፤ ቢጠናበትም ባለየው አልሄድም፤ ምድር እንዴት ትታዘበን

ብሎ ዘው ብሎ ጥልቅ ያለለ መሰለህ! ተደናገጥን። የገባው ግን ወደዘዋለ ሳይሆን ወደቢሮው ሆነ። ቢሮ ሲገባ ዶክተር ሆየ ፖሊስ ይጠራና ሰው ስትፈልጉ ነበርና የሀበሻው ዋና እለታ እዚህ አለላቹሁ፤ እኛም የቶሱን ታሪክ እንመዘግባለን ይልና ሹም የጠበቀውንና የፈለገውን ጉዳይ ያደራጅለታል።

«ያናደደን ነገር ቢኖር ፈትለፈታችን፤ ለማንሰማው የቢሮ ጨዋታ ይዘውት ሲገቡ ማየታችን ነበር። ብናር የሚለወጥ ሁኔታ አልነበረም። ከዘዋለ ሳይደርስ፤ ጠበቃ የሚፈልግ እንደሆነ የሚተጥርለት መሆኑን ይጠቅስል፤ ነገር ሲያዋጡቸው። እወ ይፈልጋል ሲሉት መልክም ብሎ ይወጣል። የሀኪምን መዝገብም፤ ከግድያ መከራ (ሪፖርት) ወደእለት ብጥብጥ (ክታታ) አስለወጥና ሀኪምም በቅናቅንነት ፈርሞበት ቤቱን ጅው ይላል።»

«አሁን ዘዋለ ያለበ ት_!»

«እሱንማ ምን ገደደው! ነገርን ነገር ይስበዋል ብሉ የሚያምንና ከደባም በጉ ይወለዳል ብሉ የሚያመልክ ሰው ነውና ድብደባውን ወደታል። ንዴት የከሳን እኛንእንጃ እሱን አይደለም፤ ዘዋለ እስታማሚ ነርሱን ይወዘውዛል።... ይገርማል፤ ዘዋለ እህያ ነው፤ ከዴሳ የተረፈው እየየ የምትለለት ነርስ ነው!»

ቴልአቢብ

በሩቅ ብሉም ስሙ-ጥርነቱ የተደበቀና የተለየ ነገር ያለበት ያስመስለዋል። ለትንሽ-ትልቁ ጉዳይ ቀጠሮ የምንሰራው ቴልአቢብ ነው።

የጉዳይ ቀጠሬየ በትርብ ያወቅሁት ጉብሊ ሁና፤ አገሬ-መንገዱን ደግሞ የት/ቤት የደብተርክረጅ እዚያ ይረክባል ብለውኛል። ከ ዉሮፖም ሆነ ከሀገሬቱ የወርቃ-ወርቅ ማምረቻ አጥር -እዘሳይ የለበ ነጋዴው ሸቀጥ የሚያማክልበት ከተማ ነው። ወራጅና የመንግስት አገልግሎት ንብረት ባይቀር ይሸጠብታል፤ በጣም ረጅም ጊዜ ፈጅቶ ከሰበሰብኳት ወረቴ የፈራተበ ገምሽ በኪሴ ቿጥሬያለሁ አጋጣሚ ለኔ ያለው ጥብቆ መባይ ነገር ቢጥልልኝ በማለት። እንበሲ፤ ጠዋቱን ከቀጠሬየ ጋር እሳልፌ፤ የቀትር በታቹን በዚያው ውስጥ-ለ ውስጥ ስሽሉክሉክ ቆይቶ ምሽቱን ከየናታንና ሮበርት ጋር በዲዚንጎፍ ስንዘንጥ ልናመሽ በ ኛ የመዝገቤ ተራ እስምረብታለሁ። የናታን- ሆንዲ፤ ሮበርት- ፈረንሳዊ ሆኖ አብረውኝ የሚወጡና የሚገቡ ጓደኞቼ ናቸው።

ዲዚንጎፍ ዝነኛ ነው በጉደኛው ቴልአቢብ ውስጥ ብዙ ሌላ ጉዳናወችን የበዘበዘ ሽንጣምና ወርዳም ነው። የምእራብ ዘመን-አነሳሽ ቅራቅምብ የመዋኒያ እምብርት ነው። ቢያንስ በዚያ ጉዳና ላይ ለዘንጥ የሚሄድ ሰው ሁሉ እንዲያ መባሉን ይስማማል። ፈረንሳዮች በወርቃ-ወርቁና በሽቶ ማብዛት፤ በመንሸራሸር ደግሞ ሌሎች ምእራባውያን በቁጥር ይመታሉ። ፈረንሳዮች ምንጊዜም ከዚያ የመንገድ መርከብ ጠፍተው አያውቁም። ታዲያ በስራ ኢሉችም ሆነ በጉብኝዎች ከርታ ላይ በመሪነት ጉልቶ የሚሰመርበት ነጥብ ነው።

የጉዳናው ስየማ ከንድ የእርሻ ሰው ታሪክ ጋር የተያያዘ ሲሆን ልጃገረድም ሆነች ምራት የዋጠች ሴት ዛሬ እስኪ-እንዲህ በዲዚንጎፍ ስትል፤ ከስእል ያየችውን መሽቀርቀርና ትክለ-ሀካል ለመግለፅ ከንዶቿን ከርፈፍና ደገን፣ ጡቶቿን ዘርዘር፣ ዳሌዋ የሂሊት ዘንበል፣ ወገቢንም ሰበር አድርጋ ስትትወዘወዝ ኩታዋን አጥብ የምታናጥጥና የምታዳርቅ ሀበሽ ነው የምትመስለው። ከንገት እስከ ዳሌዋ መዲፏን አስታክካ በማውረድ ስትመስል ው፤ እይኗ ከሚሰራው የመቅለብለብ ታሪክ ጋር ሲደመር ያልንተንሰለከከችው (እንደ ዲዚንጎፍ) ልጃገረድ ሁሉ፤ የሚጉላ ወራቷን ልታዳርስ፣ ንስሀ የከረመችና በእህል የተቀጣች የሀበሻዋን ቅንት ልጃገረድ መስላ ታርፋለች ለዚያች ፋታ ብቻእንጂ

የተንሰለከከች ብትሆን የግድ እንዲያ ማድረግ ባልታያትም ነበር።

ከንዲህ ያለ ዝና የተነሳ ገርደፍዳፋውና ገዲለሹ ሰው እልፏልፎ ላይን ትእይንት መለወጫ ጣል-ጣል ሲልበት በቀር አብዛኛው ደህና ለብሶ የሚወጣበት ጉዳና ነው። ስምንኛ፣ የከረመና እንደገና የሚነሳው የጥንት የወርቅ ቅድ ሁሉ ጉዳናውን ይሞለዋል። የትክል ገዲለሽነት ከልሆነ ማንኛውም የተለበሰ ነገር ሁሉ ራሱን የቻለ ኪነት ሁኖ የሚታይበት በታ እንዲያ አላየሁም። ለማኞች የሚለብሱት ሁሉ እዚያ መንገድ እስከልወጡ ድረስ ችግር የፈጠረው ስእል ባይሆን የዚያ አለባበስ ኪነተኞች ነው የሚመስሉት። አንድ ለማኝ ልብሱን ለሸጥ ቢዘረጋ ጠያቂም አይጠፋም። ያከል ወዝዋዜውና የያንዳንዱ ልዩ ባህሪ አይንን እስቸጋሮ ይገዝዋል። ሁሉም፤ መዘናከት "ሊህዝዳንኬፍ በዲዚንጎፍ" ብሎ ነውና የሚወጣው የምሽቱን ጊዜያችን ድልደላ የመጣው ከንዲህ ያለ ወሬ በመሸቀል ነበረ።

ታዲያ፤ ያን ያህል ባይጋነንም፤ የተባፈርኩት ሰማዩ ያሀያ ሆድ መሆን ሲጀምር ነበር። ዋናው ያውቶቡስ ክባንያ «ኢጌድ» በመባል የሚታወቀው ነው። ወጣት አንበሳና ጉሹ-ጉንዳር ያንበሳ ስምሪት ቢሉትም ይሆናል- ኢጊድ እስራኤል ውስጥ ባገልግሎት ሲያረጅ ታድስ የሚሸጠው ለኢትዮጵያውን እሊያም ባንዳንድ መሰል አፍሪካውያን ነው ተብሉ ይታማል፤ ትክለ-ሀከሉን ባንሰሳሰለው ሆትም ይመስላል። እስራኤሉች በፈንታቸው፤ ምቾታም ያውቶቡስ ስሪት በመሆኑ ብዙወች ህይወት ይሉታል። አባባሉ ሽሙጥ የተንተራሰም ነው፤ ጃርመን ውስጥ ሂትለር በፈጃቸው ይሁዳውያን ስም፤ ለደም ማካካሻ ያሁነኛው መንግስት የሚከፍለው ንስሀ ነው ብለው የወቅያዋስ ጠርዝ አሳሳፊወች እንዳንዴ ያመታል። እናም፤ የቅዕል ሰሙ ያንን ለመሚወት የተደረገ ተረብ ነው።

አገር ግን ይድረስ አይድረስ አላውቅም። አባቱ ግን የታወቀ የፈላሻ መሪ ናቸው ብለውኛል። በመሆኑም ለሙሴ ተልእኮ አስተባባሪነት የተመረጠውና ያስተባበረው እርሱ ነው። ይህም የሆነው የፈላሻውን/ቤተ-እስራኤል/ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ፤ የኢትዮጵያ ስደተኞች በርገው እንዳይገቡ ለመለየት ነበር። ሲያስተባብር፤ መግለጫ ሲሰጥ ሁሉ በተደጋጋሚ ቀርቤ አይቸዋለሁ። አሁን አልያዝኩ እንጂ ፎቶግራፉም አለኝ። አንድ ያማታኝ ነገር ቢኖር እኔ የማውቀውን ስሙን ሲጠሩት አለመስማቴ ነው። ስሙ ተቀይሯልም ብለው የነገሩኝ ፈላሻወችም ገጥሞኛል። ነገሩኝ ስላቸው ግን አብረነው አላደግንም፤ ከመጣ ብዙ ጊዜው ነው፤ የምናውቀው አባቱን ነው። አባቱ ?? ??? ይባላሉ። የቤተሰብ ስሙን ባገኘም የሆነ ስህተት እንዳለ ለመረዳት በቃሁ።... ስለማን እንደማወራ ገብቶሻል?» በዚያው እኔን ዞሮ አይቶኝ ተመለሰ። ህሊናየ በድንጋጤ ተወረረ። ብቻ የሷ መኖር አላጋለጠኝም። «ለንደን ነው የሚኖር ካሉህ፤ እኔ የማውቃቸው እዚህ ያሉትን ነው፤ ምናልባት ጥናቴን ጨርሸ ስመለስ አድራሻውን ካገኘሁው እተዋወቀዋለሁ። ከንዴ የሚለውን ሰው ታውቀዋለህ?» አለች ዞራ ተመልክታኝና ጆሮዋ መልስ እየጠበቀ።

«ኸ-ኧኧ! የለም አላውቀውም!» አልኩ፤ አንገቴን ጭምር በማንቃንቅ ቃለ ዜማየን አራዳቸ።

«የፖስፖርት ስሙን ከሰጠሁ አይበቃህም? በምትፅፈው ፅሁፍ ደብሳልን ከጠቀስክ ምን ያመጣብሀል?»

«ስሚ! ዲፕሎማሲን፤ ድብቅ የመንግስት ስራን የሚጠኑ ሰዎች ስማቸው መቶ ነው። በመሆኑም በዚህ ተልእኮ (የቤተ-እስራኤል ገፈፋ) የተሰማራ ሌሎች ቁልፍ ሰወችም ስም አውናብደኛል። የዚህን ተልእኮ ቅንብርቅና ስልት የመራው በሱዳን አንድ አሜሪካዊ ባለስልጣን ነው። ከሱ ጋርንኪ ብዙ አውርቻለሁ። የግል ታሪኩን ጠይቄው የተማረበትን ዩኒቨርሲቲ ስም ከሰጠኝ በኋላ ለስራ ጓደኞቼ ከግል ማህደሬ ማስታወሻ እንዲያወጡልኝ ደውየላቸው ሊያጣሩ ሂደው የሚገርም መልስ ሰጡኝ። በሰጠኸን ስም፣ ከጠቀስከው ዩኒቨርሲቲ፣ ከወረቀት ላይም ሆነ ከኮምፒዩተር ላይ የተገኘ ነገር አይደለም። አሉኝ። እርግጠኛ ነኝ አሜሪካዊ ነው። ጺሙን ሳጭቶም ሆነ ሳይላጭ ጠቅላላ ዘይቤውንና ቅላፄውን ስመለከት የጠራ የምስራቅ ጠርዝ (ኢስት ኮስት) የድምፅ ቅኝት ነው ያለው።...» ንግግሬን አቋርጣ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁ ትንሽ ሸክር አለ፤

«አንዳንድ ነገርህ ይማታብኛል፤ የምትፅፈው በጉ ነገር ከሆነ እሱን ምን ጨነቀውና ነው፤ ደልቀን ስሙን ለማስታወቅ፤

ያልከፈለበት ገንዘብ ዝና ሲያተርፍለት... ሰወች ስማቸውን በተለያየ የህዝብ መገናኛ ሊያወጡ ስንት ነው የሚናገሬት...»

«የህሊ-ውድና የንግድ ባህሪ ያለው ስራ የያዘ ግለሰብና የመንግስት ባለስልጣን የተለያየ ነገር ነው። በእንዲህ ያለ ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰወች ታውቀው ከሚደነቅላቸውና ተበልተው የሚቀጥለውን ሸር ከሚያጡ፤ ሳይታወቅ ሰርተው የሚያገኙት የህሊና ተህድስ ይበልጣቸዋል። ህዝቡን ከሚመራው መንግስት የበለጠ የራስ መተማመን አላቸው፤ መንግስት ራሱ የነሱ አሽከርና ጥገኛ ነው። ከሁሉም በላይ መሆናቸውን የቀረበ ያውቅላቸዋልና የተራው ስለነሱ ማወቅ አይገዳቸውም። እንዲያውም ተራው ህዝብ ሲያውቅ ብዙ ውጥናቸው እንደሚበላሽ ይታያቸዋል። ስለሆነም፤ በጨበጣ ሲጋለጡ በቀር በፈቃደኝነት ወደአደባባይ የሚወጡ ሰወች አይደሉም።»

«እንዲያ የሚረዳህ ከሆነ ለምን ማወቅ አስፈለገህ?»

«ፀሀፊወች ለህብረተ-ሰብ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ቢኖር፤ እንደዚህ ያሉ የጋን መብራቶችን ተመክሮ አደባባይ አውጥቶ የህዝብ ንቃትንም ማሳደግ ነው። ልዩ ሰወች ናቸውና እነሱን የሚተኩ ሰወችን መፍጠር የሚቻለው እነሱ ያደረጉትንና የሆኑትን አውጥቶ በማስነበብ ነው። አይመስልሽም?»

«እነዚህ ሰወች ተመክሯቸውን የሚያስተላልፉበት ማእከል የለም እንዴ እንዲህ የተጨነክው?»

«የተቋም አቀራረብ፤ እንደኔ ካለው ያንን መያ የማያውቅ ፀሀፊ አቀራረብ የተለየ ነው። እራሳቸው ይፅፋሉ ብትይ ደግሞ ስለራሳቸው የሚፅፉትና ሌሎች ስለነርሱ የሚፅፉት በጣም የተራራቀ ነው። አንድም ስለራሳቸው አግነው፤ አሊያም ራስነታቸውን ወደጉን አግልለው፤ ስለ ቅንፀል ድርጊት ብቻ ነው የሚያወሩት፤ ያም ስንት ዘመን ሸብቶ ከተቀመጠ በኋላ ነው።»

ቀደም ሲል መዝናናት እየሰጠኝ የተመዘገበ፤ እኔን ግን የረሳ ወሬያቸው ላንድ እፍታ መጥጥ ብሉ ተረሳኝ። አሁን የገበበት ምልልስ እንደቀጠለ እኔ ብቻየን መግቶ ገባሁ።

«ይህ ሰው ምንድን ነው? ጋዜጠኛ? ብሉም አሜሪካዊ?... አሜሪካዊ ከሆነ፣ በመጨረሻው የገፈፋ ምሽት (የሙሴ ተልእኮ) ለምን ታስሮ ተፈታ? በአገሬ ቢሆን ዋሮ ይምስል ነበር። ሱዳን ላይ ግን እንዲህ ለምን ሊሆን ቻለ?... መልኩም! የሲ-አ-ይ-ኤ» አባል ስላልሆነና ጋዜጠኛ ብቻ በመሆኑ ይለፈልፋል ብለውም ይሰረዱ፤ ይህን የሚልክልብበትን ጥያቄ መልስ እዚያው በዚያ ማግኘት ይችል አልነበረም? ይህ ከጋዜጠኛ የመጣ የበለሳ ጥያቄው አልገባኝም!

«የሌላ ሰላይ ድርጅት ሰላ የላከው? ወይስ... ግን ግን? ይህ ውዝግብ የፈጠረ ሰሞነኛ የጭንቀት ግርግር እስራኤል ውስጥ ከባህረ ህዝቡም ሆነ ከፈላሻዎች አካባቢ የተበላና ያልተበላ ነገር እንዳለ ለማሰስ የተላከ ሊሆን ይችላል? ግን ደህና ያሰለጠኑት ሰው አይመስልም፤ በጣም ቀርፋፋ ቢጤ ነው። ይህች ገራገር ልጃገረድ ምን ያህል የኢትዮጵያ ይሁዶችን የጭንቀት ጉዳይ ጠልቃ ታውቃለች?... ሆን ብላእንኳ ምስጢር የምትበጠው አይመስለኝም። በዚህ ሁኔታ እያየሁት ባስተርጓሚነት ኢትዮጵያውያን ሰፈር አብረው ብገባ ምስጢር አገኘሁ-አሰገኘ፤ ከመዘዝ አልደንግም። ማግኘትእንኳ፤ እኔ ባልተባበረው ቀርቶ ብተባበረውና ባዝናናቸውም ሀበሾች በተለምዶ አይተውት ለማያውቁት ሰው ይቅርና አብረዋቸው ለዋሉ፤ የግል ማህደረ-ታሪካቸውን ከፍተው ያንዱን ለንዱ የሚያቀምሱ አይደሉም። የደረሰ ጉዳት ደርሰበት ጣልያዎችን እምነት እመት ያጃጀለ ህዝብ ነው። ፈላሻም ከዚያ የተለየ አይደለም፤ እንዲያውም ጨዋታ መቅበር በፈላሽ ይጠናል። በተለይ አብዛኛው ቤተ-እስራኤል ገጠር-ቀመስ በመሆኑ እጅ ከፍንጅ ካልታያዘ በቀር ከራቱ ላይ በገደለ ሰው ላይ ነበርክና መስከር ቢሉት፤ አይ! ተሳስታችሁና በእምነቱ ተጭበርብራችሁ እንጂ እዚያ አልነበርኩም ብሉ እሊ ማለትን ይመርጣል፤ በግራ በቀኝ ከመጉተትና ከስጋትም የመዳን መላና ተመክሮም ነው። ታዲያ ይህ ጋዜጠኛ እንደ ዘለላ የማያውቁ ጥያቄ ሲጠይቅ ሁሉም እኔን በሚሊዮን ገንዘብ ተገዝቶ ልሸቀጥበት እንደሄድኩ ቆጥሮ እዚያው ላይ ልረብረበው ይል ይሆን?። ወይ ቅብጠት!» አልኩ በዚያ ጊዜ ላይ የመጀመሪያ የብቻየ ወግ።

ከንጠለጠለው እድፋምና ዙሪያ ከፋፋ እያለተ ብል ከጉዳው ባዶ የወረቀት ከረጢው ጀምሮ እስከለባበሱ፤ እድሜው በሰላሳ ህይወት ያለቀ ማባይ (ኬንያዊ ዘባን) የሚመስለው ወጣት ጋዜጠኛ ነገር ከራስ ምታት ወደህይወት መግት አስገባኝ። የሚጠይቀው ጥያቄ የአደባባይ ምስጢር ቢሆንም ከራሳቸው ያልወጣ (እስራ-ኢሎች) ትችት ላይ በጣም አልቃሾች ናቸው... እንግዲያ ከራሳቸው በራሳቸው ቀልድና ቧልት ፌዝር በመዝናናት ወደር አልነበራቸውም። ከኢትዮጵያውያን ወገና ብሎም አሁን እዚህ በጅምላ ከደረበት፤ ከውጭንትዋ የመጣ ሽብርና አድርባይነት መሀከል እኔ መበሳቴ ታየኝ። ሰዋዊው ሀይሌ ከሰውና ወገኝነቴን መስከታዊ ሀይል በላው። ዝም ብየ የምታወጣ ሀይል አወጣኝ ማለት ብቻ ሆነ።

ጎርፍ ከበላው አፍሪካዊ ጎዳና ላይ ደህና አድርጎ በማሽርሽር የሰለጠነ መሆኑን ማረጋገጥ አስቸጋሪ አልነበረም። ከኢየሩሳሌም ናዝሬት ጎዳና መሀል፤ ጆርዳንን ከሚያክትረውና ፊት ለፊት እየታከከ፤ የተራራዎቹን ሰንሰለት እያሰመታን ከሚሄደው አጥር የጎዳና አካሉ በቀር ለጥ ያለ የአስፓልት ንጣፍ ነው። ከርታሚውን ለማርጋት ከተበተነውና አደስ ጥግን የአሸዋ ልባስ ሲገባ ሌላ ስልት ቢያስይዘውም፤ ከሰላው አስፓልት ላይ ግን ከከንፈር ደርቻ ያረብ አህያዎችና ፍየሎች ያስፈንጠረትን አንዳንድ ጠጠር ቢንከው የመንጂያ ፊታዱን በአደባባይ የሚተግ መስሎ ታየው። መሪውን ከርቶ ሲይዘው ግግሸ ደረቱን በጉራ ማንታው በኩል ደጋፍ የሰጠውን ምቹ ወንበር ተጠቅሞ ለዳንሰኛዋ አይን ዳረገው። በቀጭን የብረት ምሰሶ ከእናቱ የወጣውን ያንገት በላይ መደገፊያ ዳሰ ለዳንሰኛዋ የሚያደርገውን አኪሸሚ ተውኔት ለማጀብና አንገቱን በስልት አስመችቶ ለማንቀሳቀስ ረዳው። አንዳንዳንድ ወጣት የፈረንጅ ልጃገረዶች... ሰሞኑንስ ኢትዮጵያውትም እንደፋሽን ተጠብበው ቀድተውታል (ትንሽም የጠበጣቸው የሚርገፈገፍ ፀጉር ሲያጥጣቸው በቀር) የንግግር ዘይቤ መለመዴ አሲያም የተመለከቻቸውን አይን-ትእይንት ወደትእይንት ለማሸገር፤ የመከረም ጥቁር ዝምብ ያስቃየው ፈረስ ይርገፈገፈውን አይነት ራሱን እየጠቃቀሰ ሲመልሰው በቀር ዳውላውን በደንብ ተጠቅመበት። "ኪላንዳንድ አመል አይሰራም ሰው" እንደሉ፤ ዳንሰኛዋ ደግሞ፤ ባንገት ከመርገፍገፍ ይልቅ ሌላ የመርገፍገፊያ መላ ነበራት፤ የተሻረ ቃል ለመንከት ከሚጨነቀውና ዳሰስ ከሚተወው የሰው አይነት በመሆኗ ቃል አመራረና አነባበቧ «ኧ ...ኧ...ኧ...ኧ» ከልተጨአረበት በፍፁም አይሆንላትም። ቃል በወረወረች ቁጥር እንዲያ የምትለው ዜማ ነገር አላት፤ እሱም እቧን ትክ ብሎ እየተመለከተ እከቧን የሚቆጥርበት ፋታ እንዲያ «ኧ ኧ ኧ ኧ!» ስትል ነው።

እከባቴ ሰጠኝ።

ከጋዜጠኛው ጋር የተነሳንበትን ጉዞ እንዲያ ከልተን ከመንደር ስንደርስ፤ ዙሪያ መስኮቱ ከተከፈተ፤ ጥርት ባለ በርቶ የሰው ራስ በተራ ከሚታይበት ያጋጠመኝ ቤተእስራኤላዊ ቤት መርቸ ገባን። የፈጀብኝን ዙሪያ የማስረጃ ጊዜ ከልቸና የጋዜጠኛውን አመጣጥ ነገሬ፤ የትርጉም ስራውን ልጀምር የቤን

ጥያቄ ለማሰማት ሰማቅር ቤተእስራኤላዊው ተጠያቂ አቋረጠኝ።
«አሜሪካ፣ የየትኛው ጋዜጣ ጠሀፊ ነው?» ያልጠበኩት ጥያቄ ነበር፣ ጋዜጠኛው ግን ለመልስ አላገደደውም ነበርና የጋዜጣውን ስም ሲነግረው፣ (የኔ አስተርጓሚነት በመሀል ሳይደርስ)

«የና ሰው... ይሁዳዊ ነው?» ሲል የጋዜጠኛውን ፊት ብሾታ ወረረው፣ «ስለይሁዳዎች የሚናገርና የሚጽፍ ጋዜጠኛ፣ የግድ ይሁዳዊ መሆን የለበትም፣ ከሌሎች ያንተ ሰዎች የገጠመኝ ተደጋጋሚ ጥያቄ ነው፣ እንዳንዴም ጥሩ ይሁዳዊ ነኝ ያልሆንበት ቦታ አለ። የናንተን ጉዳይ በሚመለከት ምንህም ለፍ የሚበጃችሁን ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ በመሪት ያሜሪካ ጥቁ፡ነክ ንቅናቄ በማምቢር ተደምቅነት ተሳትፌያለሁ። ከንደሁያለ ዴሞክራሲያዊ ፍቅር የመጣ ይመስለኛል፣ በየሄዳችሁበት ሁሉ እየተከተልኩ የሆናችሁትን ሁሉ ያሜሪካ ህዝብ የነገርኩት። ሱዳን ላይ በትግሎም ነበርኩ። ከንተ ጋር ባይገጥመን እንጂ ብዙ የሚያውቀኝ ሰው አለ።» ብሎ ሊያበረታው ሲሞክር፣ ደንበኛዋ ተመራማሪ የማርያም ይሁን የሌላ ጥልቀት የተንተራሰ ነገር ይዛ ድንገት ጣልቃ ገባች። «አንተ ያነሳኸው ነጥብ፣ ያሜሪካ ይሁዳዎች ሁነው የኢትዮጵያ ይሁዳዎችን የሚደግፉ አብዛኛው የሚጠቅሱት አባባል ነው። የማርቲን ሉተርን የትግል ተመክሮ በኢትዮጵያ ይሁዳዎችና በስራኤላውያን መሀከል የምታነሳው መሆን ያለበት አይመስለኝም፣ በባህሪ ይለያያሉና።»

«በኢትዮጵያ መድሉ አልተደረገባቸውም? ከዚህ ከደረሱስ በእኩልነት ታይተዋል? እየተገረዙ መሰሉኝ የሚገቡ፣ ይህ የመጣው ከቀለም ጥያቄ አይደለም ማለትሽ ነው?»

«እንደኔ፣ ያሜሪካን ጥቁሮች፣ ብሎም አሁን ደቡብ አፍሪካ ላይ ያለውን የዘር ልዩነት ከኢትዮጵያ ይሁዶች የቀደምት ተመክሮና ዘረም ከገጠማቸው ግጭት ጋር የምናጋጥመው መሆን የለበትም። ምክንያቱም የቤተ-እስራኤል ተመክሮ የቀለም ሳይሆን ሀይማኖትነክ ነው። አንተ ያነሳኸው ግን የቀለም ነው።»

ብዙ ማተት የፈለገ አልመሰለም። ነገር ግን እሷ እንደተናገረች ዝም አላለም። «ዘረኝነትን የማየው ባንድ አይን ነው- ልዩነት በማድረግ። ጠረ-ሰማዊነትንና… አንዱ ሌላውን መገረዙን በምን ትለይዋለሽ? የቀለም ልዩነት የሀይማኖትን አንድነት ሲለየው ማየት እቻተሽ! ብቻ ዘማየት ብለን መተንተን ያለብን ይመስለኛል! ስለሆነም፣ ቃለ-መጠይቄን ልጨርስ እዚህ ላይ ተወያይተን የምንግባባ አልመሰለኝም።» ብሎ ዘጋቢትና ቀደም የተጠዘረውንና እሷ ያቋረጠችኝን ትርጉም አቀረብኩ።

«ይሁዳዊ አይደለሁም፣ ግን ጥቁር-ነክ ነገር እወዳለሁና የምፅፈው እናንተን ብቻ የሚጠቅመውን ነው፣ የማይበጃችሁን ብትለምኑኝም አልጽፍም ነው ያለው።»

«በስብከት በኩልማ ጅል ነገር እፅፋለሁ ይልሀል እንዴ? የጥቁር-ነክ ማለቱ እንዴት አይነት ጨዋታ ነው?»

«ሀበሻ ማለቱ ነው።» አልኩት። ሀበሻ የሚለው ቃል በጣም ለምደብኝና ትርጉም አልወጣልኝ ብሎ ነውእንጂ ሰውየው ያለኝ አልነበረም። «ዘወር በል በለው! እኛ ይሁዶች እንጂ አበሾች አይደለንም። በደም የሚያገናኘን ነገር የለም በለው። ነገር የዘዘው ከሀበሻ ጋር እያያዙን ነው። ሀበሻ ሌላ፣ ፈላሻ የቅል ነው። ኪስ የመሰለ ሁሉ ዳብ ነው እንደማለት አይሆንም? ምን ይሆን ስለኛ ታሪክ ጠልቆ ያላወቀ እንበስላ ፊት አመጣህብን!» ብሎ ሆዱን አሸበረው።

እንግሊዛዊቷና ሀበሻው አንድ ሆኑ፣ በጣም አስደነገጡኝ። ጋዜጠኛው ፋታ እንደሰጠኝ ጠይቄ ከዚህ ልዩ ሰው ጋር መግት ጀመርኩ፣

«ጥቁረታችን ሀበሻ ካልሆነ ምን ትለው? አፍሪካዊ?» ብየ እንዲያው መዳፉን ዘወርኩት፣ በጣም ጨንቶኝ፣

«አፍሪካ ማለት አበሻ ማለት አይደል! ዝም ብለህ ቤተእስራኤል ነን በለው።»

«ስማ ወገን ይሆን አሁን የምነግረው ነገር አይሆንም፣ እሱ ሲሄድ በወይይት እንጨርሰዋለን።»

«የሚጥፍ ሰው ስለሆነ፣ ዝም ብለህ የማትነግረው፣ ለኛ የሚጠቅም፣ ሌላው ሰው ልዩነታችን እንዲያውቀው የሚያደርግ ነጥብ ነው። ያልታረመና እዘንብሉ ያገኘሁትን የታሪክ እያያዝ ማቃናቴ ነውር የለበትም።» አለ።

«ስማ ወገን፣ በመጀመሪያ ከሌላው ቤተእስራኤል ይቅርና ከራሰው የቅርብ ዘመዶች ጋር ጠብ የሚያበቅልብህ ይመስለኛል፣ ሀበሻነትን የሚክድ ፈላሽ አልሰማሁም፣ ሀይማኖቴ ይሁዳዊ ነው የሚል እንጂ። በሌሎች እንጠርም- ከሞሮኮ፣ ከየመን፣ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመንም ሆነ ከሌላ በታ የሚመጣ ሁሉ የኛ አገር መጤ ይሁዳዊ ነኝ እያለ ነው የሚናገረው። በሌላ ሀይማኖት ረገድም፣ የግብጥ እስላም፣ የሞሮኮ እስላም፣ የኢራን እስላም፣ የሱሪያ እስላም እየተባለ ነው የሚጠራው፣ ይህ የማይበቃህ ከሆነ፣ አረብ የሚለውን ቃል እስላም ብየ ባስገበሁትና በሌላው ሁሉ እየተካህ እየው። ወደእስራኤል መምጣት የምርጫእንጂ የደም ፍላጎ ከሆነ ብዙ ጠብ የሚያስነሳብህ ይሆናል። ምክንያቱም፣ አንድ ሌላ ቤተእስራኤላዊ ያልሆነ ሀበሻንና ራሰውን ብታስተያየው የመለያያ

ጉዳናው በጣም ይከብዳል። ሁላችንም የሀበሻ ገፅታ ነው ያለን። ያልከውን ነገረው ከልክ ደግሞ የሚመስል ታሪክ እምጠና ተፈረደው።»

«በጣም አጥብቀህ ተሟገትከኝ፤ ለጊዜው እንዳልክ ይሁን፤ ግን ይህ ጋዜጠኛ የኛ ካልሆነ ነገር የበለውን እንዲያበላሽ። የክርስቲያንን ነገር… በጠቢያ የምታውቀው… ከዚያ የተሰራው በደል ይበቃል፤ የነሱ መሳከተኛ እንዲይሆንና ነገር ብልሽትሽት እንዲደል።» ሲል ባለቤቱ ቀማቸው፤

«አገር የሚያውቀውን ነገረው። የሚያጠራጥር ነገር ሲኖር የማድ መናገር የለብህም። ከቤታችን ድረስ መጥቶ ስለፈለገ ልጠፍ የሚል ሲመጣ ፈራሁ ብለህ ትመልሰው እንዴ? የሰሞኑ አትገርሙን ባዶ ሰባማዊ ሰልፈኛም፤ ጋዜጠኛ አልመጣለትና ሮሮውን እ/ዶፍለት ብሎ ለቴሌግራም የፈጀው ገንዘብ በሰው ቁመት ይለክል።» ለባሏ እንዲህ፤ ብላ፤ ማማሽ አፍራ ተመልክታኝ፤ «ወንድሜ የሚበጅ የሚበጀውን ተርጉምለት፤ የማይበጅ ነገር ወች ይጠፋሀል!» አለች። እሱም እንዲህ ሰምቷት ሊናገር ተተከ፤

«የፈቃድ ወረቀት አለህ ወይ? በለው!» ሲል፤ ደግን አፈላው፤ የሷን ትችት ከምንም ሳይቆጥረው፤ ቀግደኛና በጣም ተጠራጣሪ እንደበቱ አናደደኝ። ለጋዜጠኛው ይህ ሰው ጠማግና በጣም ጠርጣራ ነውና ከቤቱ እንውጣ ብየ ልነግረው ከጀልኩ። ወገቡን የወመደደኝ ነገር ቢኖር፤ ሌላ አደስ ሰው ቤት ገብቶ እንደገና ማጧሸቱ ከዚህ ያለነሰ ሲሆን እንደሚችል ነበር። ስለሆነም እንደነደደኝ ያለውን ተረጉምኩለት።

«ገና ካሜሪካ ሳልነሳ (የመጣው ግን ከኬንያ ነው) የጠየኩትና የተቀበልኩት ፈቃድ ነው። በሁሉም ኢትዮጵያዊ መንደር የምዞርና ሁሉም የሚለውን የምሰማ ነኝ።» አለው።

መልጭ ያለ ወሸት ነበር። ይኸኔ፤ የኢትዮጵያውያን ሰፈር ለማንም የውጭም ሆነ የውስጥ ጋዜጠኛም ሆነ ጎብኚ የተከለከለበት ጊዜ ነበር። ተጠያቂው ሰው የቀረው ነገር ቢኖር ወረቀቱን አውጣ ማለትና መፈጠር ነበር፤ ግና ይህ አልታየውም። ሁለቱ በየተራ ምልልሳቸውን ሲጥሉ እኔ አቀባባይ ሆንኩ።

«ስምህ ማን ይባላል?»

«እከላቴ ሰጠኝ።»

«ስራህ ምን ነበረ?»

«ያንደኛ ደረጃ ሂሳብ መምህር!»

«እስከስንት ቤተሰብህ ነው የመጣኸው?»

«በቤት ውስጥ ያለና በባልና ሚስት ስር የተመዘገበ ለማለት አይደል?»

«እያ!»

«እግዜርግ! ስንት ሆን ማለት ነው እንቺ?» አለ፤ ሚስቱን ዞር ብሎ ተመለከታት፤ እንደገና ወደኔ ተመለሰ፤ ሚስቱ የመለሰችለት ነገር አልነበረም፤ ዝም ብላ አይኗትና ማያቲውን አቅርቦ፤

«ቢስ አይቀጠርብኝና አይደብኝ እንጂ፤ አስራ ሁለት ራቢን ነው የገባሁ፤ ይከበር ይመስገን።»

«ለብዙ ዘመን፤ ተሰዳችሁ ዋራችሁ፤ ከሌሎችም ይሁዳውያውያን ጋር ምንም ግንኙነት ሳታደርጉ ብሎም በሌሎች ተፅእኖ የተነሳ ስትዘነጉ፤ ይሆን ወደስራኤል መመለስን እንዴት ከግብር ለማዋል በቃችሁ?»

«በሌላው አገር የሚኖረው እንዴት አልረሳም? ሀይላችንና ብሎም የመቋሚያ በትራችን እሪት ነው። ስለሆነም፤ በእሪት ውስጥ የተጣፈ ትእዛዝን ሁሉ ማድረግ ግዴታችን ነው። ተማለንበትና ተማልለንለት የምንኖረው ለእሪቱ ነው። ጊዜው ሲደርስ የተጣፈው ትንቢት በራሱ ቀስቅሶ አስነሳን። ታሪክም ቢሆን የሚረሳ ነገር አይደለም።»

«መልከም! ወደስራኤል የመምጣቱ ተግባር አጀማመር ትዝ ይልሀል?»

«ባጼ ሀይለስላሴ ዘመነመንግስት ነው የተጀመረ።»

«አብራራልኝ፤ ያጼ ሀይለስላሴ ዘመነመንግስት ብዙ አመት የሸፈነ ሲሆን ከለተ ደግሞ ገና አስር አምስት አመት አልሞላውም።»

«ቀደም፤ … ባባቶቻችን የተሞከረውን ወደ ሂላ ትቸ፤ ከየሩሳሌም ጋር ግንኙት ከተመጀመረ ከሰላሳ አመት በላይ ይሆናል። የመስማማትና የነጭ ይሁዲወች እንዲሉ የመረዳት ግን እስከ እምባ አመት ድረስ ያመጣል።

«ባጼ ሀይለስላሴ ስራው ገልፆ ነበር፤ የስራኤል መንግስት እንደተቋቋመች ቤተእስራኤልን ሰጡን ብላ ጠየቀች። ንጉሱ በሰደት እዚህ አገር ነበረና ሁሉንም ነገር ጠልቀው አውቀዋል። እንደደቡብ አፍሪቃ አይነት ልዩነት ታደርጊብቸዋለችሁ፤ ልዩነት እናደርግም ብላችሁ ቃል ከገባችሁ ደግሞ ወሰዷቸው በማለታቸው እስራኤሎችም ይሆን በማሰብ ማደራጀቱን ቀጠሉ። ከገጠር ቀጥታ ማውጣቱን ግን በጣም ፈሩት። መያ ሳይዝ ቢመጣ እዳ ብቻ ይሆናል በማለቱ።»

«መደራጀት ስትል፤ እንዴት ያለ መደራጀት?»

«እስተማሪወችን እምጥተው አሰለጠኑ፤ የሰለጠነው ተመልሰን፤ በትምህርት ቤት፤ በጤና ብሎም በእናጢነትና በብረት

ስራ የማስተማር አገልግሎት ተሰማራን።»

«አንተም ከሰለጠኑት አንዱ ነህ?»

«እኛ ማለቴ፤ ራሴንም የጨመረ መሰሉኝ?» አለ። የትርጉም ችግርና የቋንቋም አለመጣጣም ነበርና፤ ፈገግታ የወረረኝ እኔን ብቻ ነበረ። ባጭሩ ግን «አወ እሱም አብሮ ሰልጥኗል።» አልኩት።

«ምን ተማራችሁ?»

«በብዛት ስለመፅሀፈ ኦሪትና ስለፅዮን መሠረት ሁኖ የሂሳብ ነክና ሳይንስ ነገርም አብሮ ተደምሯል። የሸክላ ስራ አደረጃጀትና አናጢነትም በከፊል የተማረ ነበረ።»

«የእስራኤል መንግስት በመውጣት በኩል የረዳችሁ ምንድን ነው?»

«ሰው መርጦ ማስተማረን፣ ትምህርት ቤት መክፈትን፣ የህክምና ጣቢያ መስራቱንና ይህን የመሰለውን ሁሉ ከርዳታ አልቆጠረውም? ይኸ ሰውስ.. አንድ ሲናገሬ፤ ለሌላው ምላሽ መስራት አይሆንለትም፤ ሁሉን ዝም ብሎ መየት ወንድሜ!»

«የምልህ በመውጣት በኩል?»

«እስራኤሎች ያሰቡት፣ መጀመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ የብራይስጥ ቋንቋም ሆነ መሰረታዊ እውቀት፣ ቤተ-እስራኤል እንዲያገኙና በኋላ እዚህ ችግር እንዳይገጥመው የተለመተ ሲሆን፤.. በመጨረሻ ግን የሚሆን ሁኖ አልተገኘም። በመሀል የደርግ መምጣት ስራውን በጠበጠው፤ ሁሉም ነገር ተዘጋ። ጎጆ ሙሉ እየለቀቁ ገንፍሉ መውጣት የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። የእስራኤሎች መላ ሊሰራ አልቻለምና ፈላሻውም ትእግስት ማድረጉን እንደመበለጥ አድርጉ ተመለከተው። ሱዳን ከገባን በኋላ ግን፤ እዚህ ቀድሞ የገባው በጩኸት በመራዳት መንገዱ እንዲከፈት ሁኖ ይኸው እዚህ ለመድረስ በቅተናል።»

«ስለ እሸባለከችሁ ንገረኝ!»

«ኢ-ሁ-ም-ም-ም! መሸለክም፤ እንዲያው ሹልክ! ማለት ነዋ.. ሰው ሳያይ፤ ሳይሰማ.. ሌላ ምን እንድለው ፈልጉ ነው በሞቴ?... አየኸው! ቀስ በቀስ ነገር ሊያዋጣ ሲመቻች! ግና እዚያ የረገፈ ሰው ሞልቷል። መላውን መላ እንደዘረዘርለት ፈልጉ ነው?» ሲል እኔን በጣም ቸገረኝ።

«በጨለማ፤ ባንታይ፤ እየተሰረቅን ነው የምንወጣው ይልሀል!» አልኩ ለጋዜጠኛው በትርጉም።

«ተሰርቀው መውጣታቸውማ አልጠፋኝም፤ የፈለኩት፤ እንዴ-ት ከንዱ እንዴት እንደሚሰማማ፤ ገንዘብና ንብረታችሁን እንዴት እንደምታስቡፉ ነው! ብሎም እንደምታሸሹና ወደእስራኤል እንደምታስቡ እንዴት እንደነበረ ንገረኝ የመንገዱ ችግርና የጉዞ ስልታችሁ እንዴት

ለማለት ነው።»

«ይህማ ብዙ የሚያናግር ነው። ገና፤ ከወዲያ የጀመርክ እንደሆን ብዙ የሚነባ ታሪክ አለ። በመጀመሪያ ሰው ከሰው አይተማመንም፤ በደርግ በኩል የሚወገን ሞልቷል። ዘመድም ቢሆን ለቁርጥ አሳልፈው የሚሰጡና ፀረ-ፅዮናዊነት አቋም የወሰዱ ብዙ ናቸው። በተለይ፤ ከብየት (ኢትዮጵያ) በዚህ አቋም የቆመና እስራኤልን የሚቃወም ብዙ ናቸው። ወደዚህ የጥቁር ይሁዲ የለም ብለውም ይከራከራሉ። ስለሆነም፤ ወደዚህ ለመምጣት የፈለገና የመንገድ አናጋሪ የሚሽ ሁሉ ሌላውን ሲፈትን ጊዜ በጣም ከባድ ነው። ከፋም-በጄ፤ በዚህ ነገር የሚጠያየቀው የተቀራረበ ዘመድና ጠዋትና ማታ የማይለያይ ጓደኝነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። አንዱ ለፋታ ዘወር ከለ፤ ሰው ሲኖር፤ ስምምነት ሲደረስና ለመምጣት ሲወሰን፤ ተመልሶ ሲመጣ ይሆነውን ማወቅ ያስቸግራል። እንዳልኩት አይነት የመጀመሪያው መላ ከቤተ-እስራኤል የከባቢ ወንደረኛ ሰው የገዛ ነገር የሚደበቅበትን መላ የማዘጋጀት ነው። የመሸሻ ነገር የሚገዛው ከጉደይው ሳይሆን ከፈላሻው ነው፤ ይኸ ማለት ሁሉም ጉረቤት ፈላሻ ነው። ዝግጅት ከተበላ ከመንገድ ያስፍላል። ይሀ በጥንቃቄ ከታየ፤ ያየና የሰማ አለመኖሩ ከተመረመረ በኋላ በተከታይ የሚነሳው ነገር የንብረት አደረጃጀት ነው።... ቀደም የወጡ ብዙ ችግር አልደረሰባቸውም። ከንዱ ከፍለ-ሀገር ወደሌላው፤ ወደአውራጃም በማስመሰል ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረት ሲሸጡ አልተነቃባቸውም ነበር። ሰው በብዛት መውጣት ከጀመረ ወዲህ ግን ንብረት ሲሸጡ ጥንቃቄውና ሰቀቀኑ በጣም ብርታት አለው። በመጨረሻው ቀን ፍርሀቱ በጣም ያስቸግራል። መቸም፤ ይህ የማወራህ ከሙሴ ተልእኮ በፊት የወጣውን ሰው ሁኔታ ነው። እቃን በተገኘው ከሸጡ በኋላ አሁን የሚመጣው ነገር እሸባለክና የመንገድ መሪ ጉዳይ ነው። የመንገዱ እርዝመት፣ ማለት ከሱዳን መሬት እስኪገቡ ድረስ እስከ አስራ አምስትና አስራ ስድስት ቀን ይደርሳል። ደካማና ህፃናት የያዘ ደግሞ ከሀያ ቀን የበለጠም ይወስድበታል።

«ጭንቅ ነገር፣ ታማኝ መሪ የማግኘቱ ጉዳይ ነው። መንገዱ በረሀ በመሆኑ፤ ጉዞ ሲታሰብ የበረሀውን አመል ያወቀ ሰው መገኘት አለበት። በበረሀውን አዋቂ ሰው ካልተያዘ ማናቸውም እረኛ ያስፈራራል። መሪውን ሰው በሚናገረው የገንዘብ ዋጋ ልክ ለመከፈል ከተዋዋሉ በኋላ መንገድ ይገባል። እስከበረሀው ከንፈር ድረስ ጉዞ በሌሊት ብቻ ነው። ከበረሀው

ሲገቡ የወሀ ምንጩ በተወሰነ፤ በቁርጥ፣በቁርጥ ለእት ብቻ የሚገኝ በመሆኑ፤ በስእት ለመድረስ ያልበቃ በወሀ ጥማት ይሞታል።

«በተፈጥሮ በኩል እንደዚህ ሲሆን፤ ከመሪዎች ጋር የሚደረገው የሽወሊያ ጨዋታ ራሱን የቻለ ሌላ ፈተና ነው። ዝዘውን ስለሚያውቁ፤ የቶለኛው መሪ የፈለገውን በደቂቃ እንደትልቅ፣ ሰሞነኛና ቀረጥ ያልተጠለበት ንግድ ቶጥሮት፤ በልበት ከመቀማት ይልቅ በመሳ መገፈፍ የተጠቀመበትና ከጃቸው ሰልት ነው። መሪ ተብየው ከመንደር ከሰገባን በኋላ፤ ያገር ሰው (ጠባቢ ተወካጅ) አይቶናልና የመቻቻያ ገንዘብ ተጠይቋል፤ ካልሆነ፣ ጡረምባ ንፍተው በህዝብ ያስብቧችሁና የናንተን እጅ ለመንግስት ሰለጡ፤ እኛ ባስጠጊነት ተብርብረን መጨረሻ የእስርቤት ራት እንሆናለን። ገፋ ሲል ሞትም ይኖር ይሆናል። ይኸ ቢያጠን ጠዋት ከማታ ከምንተያየውና በክፉ በበጎው ከማንለየው ህዝብ ጋር ራት ታዚዙረናላችሁ።» ይላል። ይህ የመጀመሪያ የማስገበሪያ መንገድ ሲሆን፤ የዘረ ጨዋታ ቢዝር ገንዘቡ የሚገባው ባንድ ሰው ነው። ቢከፈለው የምክጨር ተጋሪው ነው። የመጀመሪያውን ቀን መሳ በሁለተኛው ቀን አይደግሙትም። በወል የተሰጣቸው አይበቃቸውም፤ ከመሀል የከረሀው ማረፊያ ላይ መንገድ ረዘመ፤ ይህን ያህል የሚያደክም አልመሰለንም ነበር፤ የሆነው ይሁን ብለን እንድንገፋችሁ ተጨማሪ ገንዘብ ከፈሉ። ማለት የተደጋገመ መሰቸው ነው፤ ያለው ለሌለው ጨምሮ እየከፈለ ሱዳንና ኢትዮጵያ መለያያ ላይ (ደንበር) የመጨረሻው ገፈፋ ይሆናል። በግልጥ ሲመራ የነበረው ሰው ይጠፋና ከግንባር ያልታየና፤ እኛን ጎን እየተወ ሲከተል የዋለ፤ የመሪው የቅርብ ሰው ጉደብ የጉልበት ቅሚያ ይሆንና ሱዳን የምንገባው መለመላ አካላችን ብቻ ነው።

«ቀደም ያወራሁት ንብረታቸውን ለመሸጥ የቻሉት ወገን ሲሆን፤ ለዚህ ያልበቃና በድንገት የተነሳ፤ ንብረት መሸጥ መያዝን ያስከትላል ካለ ጠረት ከብቱ ባይቀር እንደተዘጋ፤ ገሥ ብሎ ነው የሚመጣው። አንድም የቀረ ዘመድ ይሸክፈዋል፤ አሊያም ከድርቅ አከባቢ የመጡና የኛን እግር መንቀል የሚጠብቁ ሰዎች ያነሱታል። መቸም ሽከሬ አይታጣም። የቀበሌ ሹሙም ቀደም ካወቀ «ከዳተኛ ንብረት» ተብሎ በቀበሌ ይወረሳል።

«የገንዘብ መያዝ ዋና ጥቅሙ እስራኤል ሲደርሱ ለመቋቋሚያ ለመብቃት ሳይሆን ከመንገድ ለሚደርሰው የወንበዴ እንግልት ስለሚያድን ብቻ ነው። የማለፊያ ግብር ካልተከፈለ ሱዳን ከመድረስ ይልቅ ሰማይ ይቀርባል፤ የሚቻል አይሆንም።»

«ያለገንዘብ ሱዳን ስትገቡ ምን በላችሁ?»

«ገና ከደንበር እስከመሀል አገር በመድረስ የነበረውን ችግር መች ደፋሁና ነው ተሸገር ይህንን የሚጠይቅ?»

«ስለሱዳን ችግር ብዙዎችን እንጋግሬያለሁ፤ እኔም ዙረ ያየሁት ችግርና የተፍከበት ታሪክ ነው።»

«ይህስ የሱዳን የህይወት ጥያቄና ሀተታ አይደለም?»

«የጠየኩህ ያላገኘሁትንና ለፅሁፌ የምፈልገውን ነጥብ ነው። ሁሉንም ነገር ባንድ ቀን ፅሁፍ እንጨርሰን ማለት አይደለም። ከዚሬ የሚገለውን ሌላ ጊዜ እናየዋለን።»

«ይኸ ጉዳይ ነገር አልገባኝም፤ እፅፋለሁ የሚለው መፅሀፍ፤ ደግሞ የመተረክ ነገር ከሆነ፤ ሁሉንም ነገር ማስፈር ይኖራል፤ አሁን ደግሞ ተመልሶ፤ ወደንድ ቀን ፅሁፍ ለወጠው ይህ ሰው ምስጢር የሚቀዳ እንዳይሆን?»

«ከሰጠኸው ወሬ የተሰጠም፤ የተቋጠም ምስጢር የለም። ልንጨርስ እንምሰናል፤ ብንጨርስና ቢሄድ ምን ይመስልሀል?»

«ነገር የሚያቋጥ ሰው ከሆነ ምን ሲባል አፍ ይከፈትለታል፤ መቸም አንተን አምኜ ነውና የምለፈልፈው የመጣው ይምጣ! የልጆች አባት ነኝና እግዜር ለኛ የሚበጅ ያድርገው! በቀይ መስቀል በኩል ክግሬክ የመጀመሪያ እርዳታ ይሰጣል። መዝገቢዎች ቢገኙ ደግሞ (እስራኤሎች) ማደራጃውና መገኛው መንገድ ጊዜ ይወስዳል እንጂ፤ ቋሚና ከንጀት የሚወደት እርዳታ የሚሰጠን የእስራኤል መንግስት ነው። ይህ የሚሆነው ከገዳሪፍ ጀምሮ ነው። አሁን ቅርብ ጊዜ ግን ከዚያም እያለፉ ገዳሪፍ ገና ሳልተጠጋው ሁሉ የራትና ምሳ አድሰዋል።»

«በቂ ገንዘብ ይከፍሏችሁ ነበር?»

«ከቀይ መስቀል ጋር ሲወዳደር ሰማይና መሬት ማለት ነው፤ በጤናማ ኑሮ አይን ሲታይ ግን እንዳይሞትም እንዳይደጋም አይነት ነው።»

«እንዴት ታገኙዋችሁ? (እስራኤሎችን)»

«ሲመጡ እናገኛቸዋለን! የፀጥታ ሁኔታው ሲበጠበጥ ደግሞ ሰው በመላክና በመላ ግንኙነት ይሆናል።» ብሎ የጋዜጠኛው ምንም አለመመዝገብ ገርሞት፤

«ጋዜጠኛ ማለት የነገሩትን ለትም የሚመዘገብ ነበር፤ የምለፈልፈውን ሁሉ ከምንም አልቆጠረውም። ሰነኛ ጠልቶ በማወቁ? በቃሉ እየያዘው? ወይስ የሚያደበውን ምስጢር ነክ ነገር አለማግኘቱ? የቡና ወሬ አዳማጭ መሰሉ ተጉዝሮ ተቀመጠ!»

«አደከምኩህ ወይ በለው» አለ ጋዜጠኛው፤ እንዲያው ወታቢው የነገረው ይመስል፤ «የሚበጅ፤ የሚበጅ፤ ይሆን

ወዥንብር (የቤተ-እስራኤልን በእስራኤል መታመስ) የሚያስተርክ ጥያቄ ጠይቅ በለው!» አለ።

«መልካም! በመሴ ተልእኮ ጊዜ ሊያስተባብር የተላከውን ፈላሻ ማንነት አውቀኸዋል? በጣም ነው የረዳችሁ፤ አይደል?»

«አዎ፣ የረዳውን ረድቷል፤ ጠቆር ያለውን ባሪያ፤ ቀላ ያለውን ደግሞ ፈላሻ ብሉ በመከፋፈል ሰንት ጥቁር ዘመዱ ሱዳን ተርቶብኝ ሰንብቶ በመጨረሻ ነው አሜሪካ ለዘመድ እይን ያበቃኝ። የመሴ ተልእኮ ከበቃ በኋላ ባሜሪካዎች ከተነሳው ዘጠኝ መቶ ሰው አብዛኛው ባሪያ ተብሉ የተጣለ ነበር። ይህን ያየ እግዚሀር ግን እንዲያ ሁኖ እንዲቀር አልተወውም በፈታዱ አምጥቶ እዚህ ነቀው። ንግርት አይቀር!»

«ይህን በደል ሰራ የምትለው ሰው የፈላሻ ስሙ ማን ይባላል?
»

«ማን ሲሉት ሰማህ? በለው!»

»ጆምስ።»

«እንደሁ ከሉት፤ እኔን ምን አስጠየቀው? እኛም እንዲያ ሲሉ ነው የሰማነው።»

«ጆምስ፤ የኢትዮጵያውያን ስም አይደለም ብየ ነው።»

«በውጭ የተደቀሰ፣ አሊያም ስሙን የቀረ.. የዚህ አገር ስምም ይሆን ይሆናል። ከኢትዮጵያ ይጠራበት የነበረውን ስም አላውቀውም። ወልደቀ እኛ ከነበርንበት ከበብ ደርሷል።»

«አባቱ ማን ይባላሉ? የታወቁና ስሙ-ጥር ቤተ-እስራኤላዊ ናቸው ይባላል።

«ዝናቸውን ከሰማህ፤ ስማቸው እንዴት ጠፋህ?.. ይህ ነገር፤.. እየተበላሸ መጣ፤ ሆዴን ፍርሀት፣ ፍርሀት አለው!» ሲል፤ ጋዜጠኛው የሰጠኝን ፊት መለወጥ ተመልክቶ፤ «ያበሳጨው ነገር አለ ?»

«የጠየከውን ሰው ስም ጥክሮ ለማስታወስ አምቢ ብሉት ነው።»

«መልካም! ይህን ከሚያውቅ አጣራዋለሁ፤ ለታሪክ ምዝገባው እንዲያመች፤.. የምፅፈው መፅሃፍ ጥምር ስለሆነ፤ ዋና አስተባባሪ የነበረውን አሜሪካዊ ታውቀዋለህ?»

«ወይ መፅሃፍ ጥምር ነው የምፅፈው ማለት! ወልብዱ ነው። ማና፤ እኛ እስራኤላዊ እንጂ አሜሪካዊ አላወቅንም በለው።»

«እንዲያ ከሆነ ስሙ ማን ይባላል?»

«ስሙ ያልተያዘኝ እስራኤላዊ።»

«ከዚህ አገር የተማርክ ሰው ከነበርክ፤ እንዴት የእስራኤላውያን ስም አይያዝህም።»

«በጊዜው የሚፈጠረው ስም ልዩ ነው፤ የሰው ስም የማበዛበት እንደእስራኤል አላየሁም።»

የጋዜጠኛውና የሰጠኝ ግንኙነት በጣም ሸከረ። ሁላችንም ምቾት አጣን። ባለቤቱ፤ ከሁሉም በላይ ምቾት ያጣች መሆንዋን መረዳት የቻልነው ሁኔታ ነበር። ከሰጠኝ ጋር ከመፋጠጥ፤ ፋታ የሰጠኝም የጋዜጠኛው መፀዳጃ-ቤት መግባት ነበረና፤ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ፤ ከሰውየው ትድረት ጋር ግጭት እንዳይፈጠር እሱን ሰላ ገባሁ።

የሱዳን አፈር

ቤትየዋ በቀደመው የትምህርት አሰጣጥ ስልት እስከ ስድስተኛ ክፍል ገፍታ የወሰደ ደንብና ወግ አስገድዶ ያስረገጣትና ለትዳር የዳረጋት መሆኗን ከዙሪያ ሁኔታዋና ከየቀኑ አቤቱታዋ መረዳት ይቻላል። የትምህርት አሰጣጡና ስነ-ደንቡ የእንግሊዞች ትናት ስለነበረ፤ የነገር ግንዛቤዋ ከዛሬው የኮሌጅ ተማሪ አያንስም።

ቢሆንም ቅ/ቤት የረገጠና ብሉም የገፉ፤ «ይህ ነው» የሚባል ወረቀት የለውምና ከትዳር ተፅእዋ ጋር ተዳብሉ የቤት ቤት ሆናለች። ይህን ሁኔታዋን በጣም ታጣውረዋለች።

«የኔ እድል በሰባራ ወፕእንጨት የተመታና የተማሰለ ነው። ደህና ከመውጣት ይልቅ ጉርንቶ የቀረ ወፕ ቢሉት ይሆናል። ትምህርት መማር ከፈለጋችሁ የተማረ ወላጅ ይስጣችሁ። የእድሌም አሰነካከል ሁለት ሰባራነት አሰበት፤ ባንድ በኩል መጀመሪና አለመጨረሴ ነው። ከሴት ጓደኞቼእንኳ ስሟን የማነሳት ተወዳዳሪ የለችም። ሁሉም እንደኔ ተሰንክለው የቀረ ናቸው። በትምህርትና ባስተሰበብ የማይልቁን የነበሩ ወንዶች ዛሬ ያሉበትን ሆዱ ያውቀዋል። ይህን የሰራኝ አሮጌታ ሀበሻዊ የፊውዳል ስርአት ነው። እንደጀመርኩ ያስጨረሰኝ ቢኖር የሰው እጅ የምመለከትና የምለምንም አልነበረም!

«ሁለተኛው በደል በጣም የላቀው አይነት ነው። በሰመጥርነት ለዘላን ልጅ እንዲያው ግድም ተጣልኩ። ዘላን ቢሏችሁ ደግሞ የእውቀት ዘላንነት አይደለም፤ የነገር ግርድንትና ትርኪምርኪነት የበዛበት አተላ ማለቴ ነው። የማህፃናችን የራሱ ተፈጥሯዊ መዝጊያና መክፈቻ (አውቶማቲክ) ቢኖረው ኑሮ አደብ ከገዛ ቀን ያደርስና የማይሰማማ ቢሆን ወግድ ይባል ነበር። ግና ምን ያደርጋል!

የወጣች ቀሰቢ ሆኜ ቀረሁ። የተፈጥሮ ተዋረድ (ቤት መሆን) ልምድና ከዚያ የሚወጣው የልጅ ፍቅር፣ እያየ ከማይሸሹት በርካት አስጠመነኝ። ሳእምሮ የሚሰማማ በሆነም ምንም አልነበረም፣ ቤት ከመሆኔ የመጣ፣ በእውቅ ለሴጣ ጭንቅላቴ ተዳርኩ። ፊቴ ደረመን ለበሰ፣ ያለተፈጥሮየ ጠቅረ ቀረሁ። እድሜን እያቆመችም፣ ሲመሽ ሲነጋ አረጀሁ። ልጃገረድን የሚክሳክል ስንደንብ ገና አልተደረሰም። እስራኤል የምትጠቅመን ምናልባት በዚህ ይሆን ይሆናል፣ ግን እርግጠኛ አይደለሁም። ... »

አሁን ካለችበት ሁኔታ እየተንደረደረች ቀደም ያነቀፋትን አገኩን እስታወሰ መንገብገብና ባለፋት እድል ሁሉ ቀጭት በጣም የተፈረባት ሴትየ ሁና፣ ከዚህም የሚሰርቀው እቡቀታቸና ቸና ምሬቷ ደግሞ መስፈሪያ የለውም። ግና፣ ይህንን ጉን የሚያሳብባት ነገር ቢኖር በገጠማት የሕይወት ፈተና በብዙ ክስተቶች ላይ የነጠረ አመለካከት የወጣት መሆኑ ብቻ ነው። ያም፣ አሁን በሷ ደረጃ ያሉ ሁሉ የምክር እምብርት አድርገዋት ከነሱ በበለጠ እእምሮ የዋጠች ተደርጋ መታየቷ ብቻ ነው። ጥቅልል ኑሮዋን ግን ሲሳኛው አለም እስኪጠራ (ሞት) የተደራደር ሕይወት ብላ የምታጠውር ሰው ናት።

ባለቤት በመሆኑ እሱ ከፊትለፊቷ ተቀምጦ እሷን ተቸ ማድረግ ፈተና ሆነብኝ። እሱ ባለበት ግባ ለመናገር እስራኤል ውስጥ ከገባች ለምዷ ካልሆኑ ምናልባት ትናገር ይሆናል። በሌላ በኩል ከነበረው ወጋችን የተነሳ እስራኤል ውስጥ ሴቶችን መዝናናት፣ ወንዶችን ደግሞ ፍርሀትና ጥርጣሬ የሰፈረባቸው ከውርደሳን ማረፊያው ጀምሮ ነው። ይህም ለዚህ ጊዜ አልተመቸኝም። ይህን ሁሉ እንዳለ ይዥ ሰውየውን በተቻለ መጠን ብዙ ነገር ሳይቆነጥጠው፣ ሴትየዋን ደግሞ ምቾት ሰጥቶ ለማናገር፣ «ስማ ወገን! ለሷም ትንሽ ተራ እንስጣት፣ እኔ እስካሁን ድረስ ዘንግቼ ነው፣ ያተኮርነው ከንተ ላይ ብቻ ነበር። ጋዜጠኛው ውሀውን ድርሱ ሲመለስ በምናደርገው ውይይት ባለቤትህን እናስቀድማት፣ ካንተ ጋር መኪከር እብዛታች ሂልና አሁን እሷን እንጠቀምባት፣ ዋናው አላማ ስለቤተ-እስራኤል እትኩሮ እንዲፅፍ ለማድረግ ነው። ደግሞም ጋዜጠኛ የሚፅፈው የተነገረውን ብቻም አይደለም፣ የገመገመውንና በከባቢው የታየውንና ተረድቸዋለሁ ያለውንና ያልተረዳውን ሁሉ ወምሮ ነው። ታዲያ ትንሽ ዘዋራ ፖለቲካ መጫወት ያስፈልጋል። ሴቶቻቸው አይናገሩም ካለ አያውቁም አሊያም በጣም ጭቁና ይበዘባቸዋል ወደማለት ያመራልና ይህንን እንለመጠበት» እልኩ።

«እኔ ተናገርኩና ያበሽ ሴት ጭቁና ሁሉ ተፋቀ ማለትህ ነው?

» ብላ፣ ሰውየው ገና ሳይፈቅድላት ከተናገረችው እረፍተነገር ጉድፍ እውጥታ ሁሉንም አማረኛ ተናጋሪ አሳቀቸው። እሱ ጥያቄየን እንደመለሰ፣ ቀምነገር ሳዘለው፣ የመሳና የፍቅር አቀራረብ ለተመሳበት ቅቾቷ መልስ አልሰጠሁም። ሳቁን ፈጅቶ፣

«እረ እንዲያውም፣... ከልክስ፣ የጉድ ነበልባል ናት፣ በጣም፣ በቅንነትና በብርታት ይዟት ነው የምኖረው። (እሱም አሳቀን) የሱዳንን ነገር ስታበጀው አይነት አይገኝላትም፣ መክተብ ይሆንላታል። እንቻንእክ ነው፣ በይ የታየሽን...»

የግር መግቢያ ብቻ ሰጥቶና ወገድ በተወው እረፍተነገር ግብታ ሌላ ሆነች። እሱ በተመሳደፈበትና ነገር ማያያዝ ባጠጠው ቀጥር እያለፈች እንደሁ አትሰወም አያ! ያለችውን ያዙል፣ አሁን ራሷ እናባቢ ሆነች።

ሰመቸውም መልስ የማሳገኝለትና ያኔ ሳይረዳኝ የቀረ ቢኖር ጋዜጠኛው ከከረጢቱ ሰፊ ወረቀት ያወጣው ሴትየዋ መናገር በጀመረችበት ጊዜ ነበር። ሲናገር በቀለውና ባልተመዘገበለት ባሷ ላይ ትናት እንደሚያበደር ታየኝ። እእምሮየ ተጓገተ፣ አሁን ለምን ወረቀት ታወጣለህ? ልለው ፈራሁ። ከሱ በኩል የማልፈልገው መዘዝና ገመና ወጋለጥ ቸገረኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰጠኝ ሴትየዋን ከመናገር እንዳያስቆማት፣ እስቅሟትም ጭቅጭቅ ቢያበቅሉ ትዳሬን እንደበጠበጥኩበት የሚቆጥረውና እንደሚወነጅለኝ ታየኝ። ግና ምርጫ የለኝም፣ የወጣው ይውጣ አይነት መድረኩን ዝም ብየ ተውኩላት፣ እሷም ጀመረች፣

«በሴት በኩል ሆኜ ሳስበው፣ ጥፋት የሱዳኖች ይሁን የሸደት በራሱ... ብቻ ይኸን መለከትና መዘዝ አትም ያገሰኛል። በወንዶች በኩል ሱዳን የሚመሰገንበት ነገር እንዳለም አላውቅም። አመሰግኝ እስካሁን አልሰማሁም። በኔ በኩል ግን፣ ከኔ በሂላ፣ የምትወለደኝ ሄዋን የሆነች ዘሬን የሱዳን መንገድ አይገጠማት። በኢትዮጵያ ታሪክ ቢገመገም ዘረ የማምጃቤት ቅርስ ነው፣ ከመሳፍንቱ በራት አንዳድ ነውር ያለውት እንደነበር ይነገራል፣ የልጃገረድ ግብር አግቡልኝ እሚል ነበረ። ጋሽ-ጃግሬ የሚሆነው ብዙ በደል መስራት ግልፅ ነው። ስለሆነም፣ ከቴህ (በሱዳንና በጉንደር ደንበር ላይ የምትገኝ ትንሽ ከተማ)... ጀመተማ በኩል የገባው ሰው የሆነውን አላወቅም፣ አልነበርኩም። ወርደት ሀ-ብሉ የሚጀምረው ርጥበ እንወቅ ከደረቅ መሬያው ደንበር ሲደርሱ ነው። ኢትዮጵያ የሚቀረው፣ ሱዳን የሚጀምረው እዚያ ሳይ ነው። ከንፈራቸው የሚንቀጠቀጠውና ቀድመው የሚተያዩት ሴትን ነው። በተለየ፣ ለወጋወገዊ ስርአትና ደንብ ያደረ በሽብር ይፈታል። ይህንብኝ

ብሉ መደራደር የሻለ ይድናል፡ የቤት ግብር የለጠ። ያበትና የናት ወግ የፈታው ከሆነ እዚያው ላይ በመለቀቅ በደልን በደን ማየት ነው። ትርፉ ህመም ከልሆነ በቀር ተጓጉቶ አይደገም። ብረት የተሸከመው፤ ያልተሸከመውን ሲያገኝ በመል የተቀጠ ከልሆነ የፈለገውን ነውና የሚፈፀም፤ እኛንም የገጠመን ያ እጣ ነው።

‹የነገር መጀመሪያቸው ቤትና ወንድን መለየት ነው፤ ስለሆነም ከበሬን በግዴታ ያልተገፈፈች ሴት አገኛለሁ ማለት እንዲያው የመፅናናት ነው። ዝም ብሎ የቤቶች ገመና ሁዋ በሴቶች መሀከል የሚቀር የጨለማ ታሪክ፤ እህ... ሳወራው አይመቸኝም። እስከሁን ያልኩትም የደፍረት ነው፤ ይሰብጣል። ሰደተኛ አልቀበልም ማለትና ከደንበር መቆርቆር የወግ፣ ገፕ የያዘና የማያስተማማ ይሆናል፤ ግና በኢትዮጵያ ስደተኞች ሰም እንዲተሩበት ድርጅት በቁጥራችን ቀረጥ ከተባበሩት መንግስታት እየወረደላቸው፤ የደበደቡትን ደብደበው አፈር በማፈስ፤ "ይኸን አፈር አሸትተው፤ ቅመስውም፤ ሱዳንን እንጂ ኢትዮጵያን እይሸትም ብሉም አይጥምም ማለታቸው ወደእብደት ይመራል፤..› ብላ ስትጨርስ በውየው አደናቀፋት፤

‹ይሆንንእንኪ ጨዋታ ብለሽ አትጨምሪ፤ እበሻው ሲጠግባቸው የሚያናሱት ገበያ ነው። ይህን አትንገረው፤ ብዙ ተጋበኛ የጌይ ሰደተኛ ሞልቷል።› ሲል ሰጠኝ፤ ግሰቱ ምንም መልስ መስጠት አልፈለገችም፤ ዘለለችው፤ እስተያየቱን ያስማጉደፍ ይመስል እንጂ ለትችቱ መልስ መስጠት ያጠራት አልመሰለኝም። አሊያም አደብ የገዛች ተንታኝ ነች የሚል እምልከም አድርብኝ ይሆናል። ብቻ፤ ይህን ዘሳ ቀጠለች፤ ‹ያለፈውን አሳልፈን መሀል አገር ገብተን ደግሞ በየቀኑ የተደየነው - ደህና ቀን ይወሳል ብለን የተነሳንበት፤ ደህና ሊሊትም ያደራል ብለን የተጋደምንበት ጊዜ አጭር ነው። አሁን እርሱ እራሱ (ጋዜጠኛው) ተዋበ፣ ገዳሪፍ፣ እምራከብ፣ በሌሎውም ሁሉ ነበርኩ ብሏል። መጀመሪያ ነገር፤ የኛ ሰው ሲገባ የሚከተመው በጎድ ነው። ትግሬ በጎድ፤ ጉንደር በጎድ። ገዳሪፍ ሰንደርስና ከእስራኤሎች ጋር ግንኙት ሲጀመር ግን ተጣታ የብቻ መሸሸጊያም ተበጅቶ ነበር። ያው የትግሬው ከደላና የጐንደር ፈላሻ በጎድ ገጠሙ በመሄድና በገንዘብ ከፍፍል ጠብ ሲሆን በቀር።›

‹ለምን ነው ትግሬ ቤተእስራኤሎችን ከደላ፤ ጉንደሬዎችን ቤተእስራኤሎች ፈላሻ ያልሽው፤ ከደላ ማለት የሁሉም ሰድብ አይደለም እንዴ? የቃላት ግጭት ይሆን?› ይህ የኔ ጥያቄ ነበረ፤ የጋዜጠኛው አልነበረም።

‹የቃላት ግጭትም አይደል፤ ፈላሻ መባል በጐንደሮች ያደላል፤ ከደላ መባል ደግሞ በትግሬ በኩል ይጠናል፤ አሁን ትርብ ጊዜ ነው ሁለቱ ቃላት ከልል መለዋወጥ የጀመረት፤ ግለት ትግሬዎችም ተደርበው ፈላሻ መባል የጀመረት፤ በትግሬ ከፍሊ. ሀገር ከደላ ማለት የጅ መያ ያላቸውን ሰዎች በሙሉ የሚነካ ሰድብም ሆነ የሙያ መለያ ነው። በጐንደር ከደላ ግለት ቡዳ ግለትም ይሆናል። ቡዳ በግለትና ፈላሻ በግለት ግን በጣም ትልቅ ልዩነት አለው፤ ፈላሻ ማለት የይሁዳ ዘር ነው። እይሁድ የሚለውን የክርስትያን ሰድብ ይመስከታል። በክርስቶስ ላይ ያመፁ ብሎም ከሀዲ ግለት ነው። የሚገበው ከሆነ (ጋዜጠኛውን) በጐንደር ገፕ ሲሆን ፈላሻ፤ የይሁዳ ዘር፣ ከደላ የእጅ መያ ያለውን ይጠቅልላል። ቡዶች ምንጊዜም ከይሉች ናቸው፤ ሁሉም ከደላ ግን ቡዳ አይደለም›

ለጋዜጠኛው ልተረጉመው፤ ያልተጠየቀ ጥያቄ ነበርና፤ ጠላቶቹን ጊዜና የተናገረችውን በመመዘን ምን እንዳለች እንዲይጠይቀኝ በመለ ተወጣሁት። ትንሽ ዝብዝክ ከወራን (መወራከብም የጨመረ.. ልሸፍን የምክርከበት መላ ነጥር ስላልሰራልኝ) ያልጨረሰችው ነገር እንዳለ ሊያስረዳት እድል ሰጣት፤

‹መንደር-መንደር ነበረን፤ የኛው ሰው ከፖለቲካ ነጣ ነበር፤ ጉዳያችን የማለፍ ብቻ ነበር። ሌላው ግን የየራሱ የሆነ የፖለቲካ ውክልነት ስለነበረው በተባከረ ቁጥር ሲተራረድ፣ ሲመታደረ መገበያ ያመቸውና "በደረቅ አበሳ እርጥብ ነደድ እንዲሉ፤ ለኛ የተረፈን ዝርፊያ፤ በትርና ሌላም በደል የወግ አልነበረም። ገና ለገና የመኪና ድምፅ ሲሰማ፤ መቸም ሰራቸው ከኛ የተለየ... ሰባም በጣም ያገቡ ናቸው፤ ባይግቱም ከንዳቸውን ሲያዩት ባህር ያስገባል። ይህ አንድ ሀሳብ ነበር፤ ባይመጣም እንዲመጡ ነበር የሚነጋውና የሚመሸው።

‹ሌላው በከግሬ የሚፈጠር ብጥብጥ ነበር፤ አልክል ለምኔ ያለ እስላም አገር ስለሆነ፤ በነጋ በጠባ ፍተሻ እየተባለ የሚደረገው ዘመቻ ብዙ ሰው ጉድ ሰርቷል፤ ብዙም ሸብቧል› ብላና የቧን በኩል እንደሀ ደመደመች።

ጋዜጠኛው የትኛው እድራሻውን የያዘ እንደሆነ ያልተረዳኝ ብጣሽ ወረቀት ለሰጠኝ ሰጥቶትና የሚፈሩውን ትጂ-ታሪክ ሊልክለት ቃል ተለዋውጠው ቤቱን ተራምደነው ወጣን።

ተብጀና ዘፈን

የኃዜጠኛው የምርምር ጉዳይ በውዝፍ እንዳለ፤ አሁን የዳንሰኛዋ ፈንታ ተጠዶ። እሱን ሸኝተን እዚያ ነገረኛ ሰፈር ተመልሰን ገባን። እንደኔ ቀደም የተሰመደቻትና ሰምሪቷን ያወቀች ሀበሻ ከሰፈሬ ውስጥ የዛር ውዝዋዜ ሊያስነሳ የሚችል ድግስ የተጠነሰሰበት ቤት እንዳለ ሹክ አለቻት። ይህ ትርኢት የተከጀለበት ክፍል መግቢያ መውጫዋ የሆኑ ሴትዮ ቤት ስለነበረ «እንዴት ዋሳችሁ!» ስትል ወጥተው ተቀበሏት። እስክስታ እንደምታጠና ሁሉም ያውቃል። መቅርፀትርኢቷን እስክትራትምበው እዘጋጅታና (ይኼኑ የዛር ጉሪ ልትቀርብ!) ተደራጅታ ገባች። የጉረቤት ጥቂት ከበሌወችም እግር-በግር ተከለው ተቀሳቀሱን።

እውነትም የዛር ዳንስ ድግስ ይመስል። በመሰረቱ፤ ድግሱን ያሰጣሉት እቢታቸው ከናታቸው ቅይስት ጋር የተጉግጉመበቸው ልጆች ናቸው። ዛሬ በበታቸው ላይ ያሰደረውን አንዳንድ የመብሽክሽክና ጤና ማጣት ተፅእዋ ለመለግለድ የተጤኑ ነው። በእንዲህ ያለሁኔታም ትይስት ተለምዋ ነው የሚወርድ። ይህን ሊያደርጉ ከበሮ ሲደበድቡ ቅኝቱን የሰሙ ባለዘሮችም ቤቱን ሞሉት። ጥቂት እንደተቀመጥን፤ ከባብሉቹ በለትይስት ሚስቶቻቸውን እየጉተቱ ማስወጣት ጀመረ። በመንገድ ላይ የነበረም እንዳይገቡ መታገዳቸውን ሰማን። የመቅርፀትርኢቱ ቀደሞ መታየትና "በራዲዮ መግበትን ሰለፊ ነበር ይህን ያሰወሰናቸው። ስለሆነም የዳንሰኛዋን ዝግጅት በደ አስቀረት። እቃዋን አጥፋ፤ ዛር እንዴት እንደሚያደርግ ማየቷን ግን አልክለከሏትም። በሬት ያሰየችው ጉዳይ ነበርና ይህን ቀን ጉሪ አየች። «አንዳንዱ ያበሸ ለጋዘር ያለትዋ ሰሚያመሳግድ በተሊብኛን ማስገበቷን ትተውን» ባሉት ከበሉች እንደታጃብን የዛር ምልጃውና መለግመኑን ክልተን ሁኔታው ወደሌላ ያልታሰበ እቅጣጫ ተመራ።

እያ ተብጀና መሰል ሽማግሌወችም የተቀገኙበት አጋጣሚ ስለነበር የሀበሾችን ዘፈን ፍጥረትና ስራ (ዳንሰኛዋ ባልመተረቸው ጉዳና) በሚመለከት በስክፊትነው ውይይት ተብጀ ጀግሪ አቀንቃኝ ሆኑ። በንዳንድ ሁኔታ ልንቀኛቸው ሞክረን አልተሰከም፤ ፊር እየለቀቁ ሲያስቸግረ ከታያቸው ሀተታ መሀል ትራሚ እይጠፋም በግል እንዲያው ልቅ ዝርፊያቸውን እንበለልጊም ተውነው።

«የዘፈን መምጫው? መሰረታዊ ግንዛቤን ስትወስድ ልጅነት ነው። በልጅነት ይሉኛልን እታሰበውም። ሁሉም ነገር ነጠ ሁዋ

ይታይሀል። በሌላ ገፕ እድሜ መገፋት ነወር ማበጀት ነው። ስለነፃነት የምትግረው፤ ለእርጅናህ ጊዜ የነፃነት ብጠሽ እርሽ የምትጥለው በልጅነት ነው። እድሜ መገፋት ነፃነትን ማሰርና ልጅነትን ውግዘት ነው። ይህን ከልብህ ጠልና የመቢያን ዘፈን መነሽ እብረን እንመርምር።

«ሀፃኑ በገኘው ይዘፍናል። ጉበጉቡ፤ ሀፍረትና ነወር መሰረት የጀመረው ደግሞ የሚሸሽግበት ዘዋሬ በታ ይመርጣል። እድሜ እየጠለቅህ ስትሄድ ያስምክንያት የሚሆን ነገር የለም። መዝፈን ሲያምርህ ምክንያት መፍጠር የግድ ነው፤ በልጅነት ግን ሲታይህ ማድረግ ብቻ ነው።

«ሰው ሁለትጊዜ ይወሰዳል፤ እትብቱ የወደቀ እለትና እርጅና ሲስት የሚሉት ከእውቀት የጠለቀ ሰው የዘረፈው ንግግር ነው። ልዩነቱ ግን በልጅነት ያነበኸው የህይወት ውዳሴ (ተመክሮ) በእውቀትህ ዘመን ይጠቅማል። የቱ ሰወች የታዛቢወች መስተዋቶች ናቸው። ዳግሚያ ልጅነቱን የሚያየው የቤተው ባይሆን የሚያጋመተው ሰው ነው፤ በሰተው ላይ ልጅነትን ማየት - ታዛቢው ከሰተው! የቱተውግ እንገዲያ ያለበትን አያውቀውም።

«ሀፃን ልጅ፤ አይኑ ይበላቀጥ፤ እገሬ ደምቢያና ፎገራ ይምታ ግድ የለውም። ቀደም ነገሬህ የል፤ እድሜ የዋጠው ነወር ሰሪ፤ ሀፃን እንደፈለገው ደንክሬ ነው። ከጉዳይ የሚጥፈው ነገር የለም። የሰውነት ገሬቱ የሚበጠው ከዚህ ጊዜ ጥሬቱ ነው። ገሬት ማለት ማድረግ አይደል! ፈረንጆች በዚህ በኩል ውብ ተሰብመዋል፤ ሁሉን ነገር ግልፕ ማድረጋቸው አንዳንድ ጥቅም እንዳለው ይታየኛል።» ሲሉ፤ «ምን ማለትዎ ነው ተቢ? ያሁኑ ዉዋታዎ አጠጣሉ እንዴት?» ብየ ጠልቃ ገባሁ።

«ግልፕ ነገር ነው ያልኩት፤ ይህ በኛ በኩል ነወር የሆነው፤ የተቆጣመጠ አለባበስ፤ ገላ አስቶጣሪው ልብስ፤ ሰድ እትጋመጣቸው፤ ያለወግ ዝሊያቸውና የመተጣጠፍ ነገር ማለቴ ነው። አሁን በኛም ቢሆን፤ ትግሉ፤ ንጥቂያው፤ ወንጭፍ ምሪዘው፤ የወገብ ማስሊያ በትር ሹልኪያው፤ እመርታ ውድድሬ፤ በራስ መቶመና ሌላውም ሁሉ ፈረስ ግልቢያው፤ እንቁር (ገና) ጨዋታው፤ ይህ ሁሉ ፈተና አለበት። ገና፤ ብቱው ለወንድ ብቻ የተፈጠረ ነው፤ ወንድ እንጃ ሴት ስታደርገው እላየሁም፤ ክጠራሁት ነገር ሴት ከገባች፤ እይኗን በጨው እብሽ ሀፍረቷን የከሳች ናት። በፈረንጆች ግን የሆነለት ከተገኘ ሴትና ወንድ አይልም። እንዲያውም የቤቷን መመናጠዝ ወንዱ ሲያትተው አይቻለሁ። እንደጠቢያ ሴት ጥንክርናግ የዚህን አገር ድፍረት ብታገኝ ስንት በተሰራ ነበር፤ ግና ያልሆነ ነው።» አሉ። ይኸ

ዉሃታቸው ለጀመረት ሁተታ የተበጀ እንደሆነ ቢረዳኝም ግኝንጣቸውን የሚያስቡዝ ጥያቄ ማቅረብ በወደድኩ ነበር፤ ግና ግጠብደፈ ያስተፋፍረናልና ይሆን ዘለልኩት።

«መልካም፤ ብቢ ወደዘፈን ታሪክም ይመለሱ»

«በመሀል ወጣ ነገር እያስገባቹሁ!

«እንግዲህ ዘፈን ማለት ፍጥረት አይደለ! የምንሰማው የዚህ አገር መዚቃ ሁሉ የተፈጠረው ከሚንጋጋው የመኪናና ፋፍሪካ ውኸት ነው እራስ አግሬ በሞተር የሚሰራ። ምን አለፋሁ፤ ዘፈንን የምትሰራው ከከባቢህ ፍጥረት ጮኸት ነው። መቢያ ባለው ፍጥረት ልክ።..

«አሁን ብቻህን ቆጭ በል! ዝም ብለህ አዳምጥ፤ አሁንም አዳምጥ፤ ከግደ ተቀምጦ የሚያደህ ታዛቢ በፀጥታ የተጥፐከ ይምከለው፤ አንተ ግን የተጥፐከው ግሊሆን ያሬደች፤ የዘፈን ጠቢብን ብትለውም ይሆናል! እና እነሱ የደረደሯትን ያህል የለጠ፤ ኧረ እንዲያውም እናብጀው ቢሉ የማይሆን የኪነት መደበል ጆሮህን ያጅበዋል። እኔ ታዲያ፤ የዚህ፤ የሰው እጅ ያልተጨነቀበት ውዘማ በልቶ አክ ሄድ አይገበኝም። መልሸ፤ ጆሮ የሚሰራው ይሆን? እላለሁ። መሰመር የሚይዘውና የዜማ የሚሆነው ጆሮህን እረ እሰኘተህ ለፍጥረት እንቅስቃሴ ስትዳርገው ነው። ጠእምም የሚመጣው ዝም ብለህ ስታዳምጠው ነው።

«ለምሳሌ፤ ከብርድ ላይ በረ እየቅረቀርክ ተቀምጠህ ይሁን፤ እንበል፤ ከንገትህ ግደም የሆነ እደፍ ነገር ያሽክክሁ፤ በጋቢህ ውስጥ የተጐነፈውን እጅህን ወዳንገትህ ስትልክና ኸዋኸዊ ...ክው፤ ከላይ ነፋሱ ከሚሰራው ኪነት ጋር ሲታከል ተሰምቶ ...ይታወቅ የማሲንቆ ምት ትሰማለህ፤ ጋቢህና እጅህ ሲታከክ ሌላ ይሆናል። ከጆሮ ግንደህ ግደም ምን ሳትነክክ የሚፈጠር... መምጫውን የማታውቀው፤ ዝም ብሉ እህ! እ! ሁ! ህ! ሁህ! ውህ! ... ድዳት! ብራት እያለ፤ ሌላም አይነት ዜማ እየሆነ ...ቀጥል። ዝም ብለህ ከቀጠልክ በተቀመጥክበት እንጉላጀቶህ የምትነቃው ተፈንግለህ ነው።

«ዜማ የሌለበት ቦታ አታገኝም፤ በመንጠሬ፣ በጉልጉሌው፣ በው..ው፣ በቁጥቋጦው፤ በዋልክበት ነገር ውለህ ማታ ፍጥረት ተሸክፈ በምትልበት ሰአት የዋለብህን ጭቃ አለቀህ፤ ወይም ላጋኸ (ግሳት) የበቃህ ትሆናለህ፤ እድፍህን አወርዳልህ፤ የምትበላውንና የምትጠጣውን ከውነህ፤ እግዜረን የሰማዩ ጌታ፣ የምድሬ ባለቤት፤ ይኸው፤ የቀን እብድህ የሌት ግንድህ መጣሁልህ! ብለህ ስትጋደምና አለም በሙሉ ወደረፍት የወረደች ሲመስልህ የሚመጣውን ዜማ ሆን ብለህ አዳምጠው ልዩ ነው። የቀን

እንቅልፈን ሱስ የቀናው እንዲያ ያለውን ዜማ ለመቅመስ ስጋደም ነው። ከታራው ሲበጠብጠኝ ንዴቴ ገደብ የለውም። ስጋደም እንዱ ተያዘኝ፤ ሌላው ተተከ፤ ቀጠነ፤ ወፈረ፤ ያመለጠኝ ተመልሶ ቢመጣ ምን አለበት? ሲልና ሌላ የዳንኪራ ዜማ ሰመጡ እንዲያም ሲል ዘለላው ድምፅ ከደረሰበት ልደርስ ስከተል እቶ ስመመንና እንቅልፍ ጤና ይሰጥልኝ ይሉኛል። ያለም እርፈት ይለህል ያኔ ነው ስትተኛ!

«ሌላ የዘፈን መምጫ ጉዳና የሚመስለኝ፤ ከወንዝ ዳር ስትቆም ልብህ ውስጥ የሚሳለው ኪነት ነው። አገር በተዘበራ ውኸት ያልታመሰበት ሲሆን፤ እየተበጠረ የሚነፍሰው ዜማ ልዩ ነው። ዙሪያ ከበቡን የሚገዛው ስመምተኛው የወንዝ ዝዛና የፏፏቴው ዜማ ነው። ከዚያ የሚመጣውን የዜማ ቅንብርት፣ ሽህ አይነት ከበሮ፣ መቶ ክህምባ ማሲንቆ፣ መእት ክራር፣ በንደኛው ጆሮህ ገብቶ በሌላው ዘልቆ አገር የሚፈታ የሚመስልህ የእምቢልታ መንጋ፣ ሌላም ሌላ ብትደረድር፤ በዘጠና ብትቶኘው ከላይ የሚዘለውን ውሀ ፈጠራ ይቅርና ከባህሬ ወለል የሚንተረውን ዜማ ከሰር እጅ ያንዱን እጅ እርቦ ያህል አትሰራም። ልሰራ ብትል ደግሞ አይሆንም፤ ምነው ማለት ይበላሽ እንደሁ እንጂ እንዲያ በዝቶ ጣእመ ዜማ አይወጣውም። ከውፍረት - ውፍረት፣ ከቅጥነት - ቅጥነት አበራይቶ ለጆሮህ አቀባበሉን ሲያሰምረው፤ ከላይ ሲወርድ፤ ሿ እለ ብለህ ከታች ዱፍ ሲል፤ ከንጥረቱ የተመለሰውና በየር ላይ ካረገው... ከፈተኛው ሂሳ ከለው ጋር ሲገናኝ የሚመጣው ነገር፤ ከቋቱ ወጥቶ እንዳገና ከጉምቱ ተጋጭቶ ወዲያው የሚሰመው ውሀ የሚሰራው ጥበብና ኪነት ውበት በፈቃዱ ብለህ ዝም ነው፤ አፁብድንቅ!.. ገና፤ አድማው ከውሀው ዳር እንደቆመ አይደል ይሆን የምንግርህ?»

«እም! ገና ከዚያው፣ ከውሀው ዳር ነን... አባይ ከፏፏቴው፤»

«እንዲያ፤ ውብ ይዘሀል፤ ይህችን ነጭ ውብ እያደረክ ጨዋታየን አቅማት! ከይንታ ጨዋታ አልገባንም። ይኸ የዳርዳርታ መሆኑን ንገራት!»

«ይግፊ፤ ውብ፣ በጣም ውብኛ ይዘዋል!»

«እግዜር በበጐ ይበልህ!

«እም! እንግዲህ!

«ከግራ ከቀኝ፣ ከፊት ከሂላ፣ እንደህ ወደኩፍቶ ሰማይ ደግሞ ሰአት - ሰአት አለው እንጂ፤ እድል ሲሰጥህ ትሉ፣ ወፉ፣ አግግሱ የሚያንቀሳቅሰው የቅጠልና የተክል ዘር ውዝዋዜ ሁሉ፤ የውሀውን ዜማ በቃል አወራረድ ሲያጅበው፤ የውስጥ አካላትህ

ይነዝራል። ያኔ፤ እንደፉጨት፣ እንደማንጉርጉር፣ ተረርቶም መሰል ነገር ማለት ያሰኝሀል። ወዲያው ጠርቶ ባይወጣልህም በቅጠቅጡ ያልከሰከሰሀል። ሆኖም ከሆንክ በኋ። እንደወጣ ይወጣ ትሞህለህ፤ ቅኝትና ስልት የያዘ ዜማ ማንቆርቆር የሚወጣው ቆይተህ ስታሟሙተው ነው። ከበከብ ሆነህ ከወንዝ ዳር ስትቆም የሚወጣህን አታውቀውም፤ በስልት ባቅዘፍንም በልክ የዘፈንክ ነው የሚመስልህ፤ ሲታሰበው ታልህ ይገራና ብጤ ዜማ የምትደርሰው ያኔ ነው። ቅንልህ በፈታዱ ከሚወጣው ዜማ ጋር የገረረ ጉሮሮህን ልታጣጥመው ነውና ባይሆንልህም መቸም የመሰለ ነገር ይወጣል። ይህ ከፍጥረት ያጊደን መሰሉ የሚታየን ዘፈን ሁሉ ነው። የዝንጀሮ ጩኸት ቅኝት አትለው የለሳ ይሆናል፤ የሌላ እንደሁ ያለ እንዳደበል የሚመስልህ ነገር ታጠለታለህ። መቸም አንድ ድምፅ ይመጣል! እንዳልከሁ የወንዙ በዜማ ወበቅ ሲቀሰቅስህ፤ ፉጨትም ሆነ ሌላ የጉሮሮ ጉርጉር ይጀምርሀል ብየሀለሁ። እንሰሳው፤ አውሬውም ሁሉ ዘፈን ያስተምራል። ጮኸት ጉሮሮን ማለት አይደል? ታዲያ ከማይው የሆነ አውሬ አው አው አው! ያለ ጊዜ አንተም በዚያው አይነት የመልስ ምት ትሰጠዋለህ። ዳንኪራ መፈጠሪያውም ይህ ሁሉ ኪነት በንድ ላይ ተሰብስቦ ሲገፋህ ነው። ምን አለብህ፤ ሰው እንደሁ እንዳያማህ ብቻህን። እንደልብ እናከሽ፤ እናከሽ! ያልከው ጊዜ የራስህ ድምፅ በጠረ መራጃ እየሆነ ስምረት ይለሁል ያ ነው፤ ዝንጀሮው አው፣ አው! ብሎ አንተ በመልስ አው! አው! ስትል።

ያወረውን ዜማ መልመድ በየትም ያለ ነገር ነው። ቆቅን ወዳጠመድክበት መታነቂያ ሰጆና በራሱ ዜማ ታታርበዋለህ፤ ከንፈርህን ገጥመህ ጽር ጽር ጽር... ስትል፤ ቆቅ ሆየ መሰሉ ፍጥረት ዘመረ ብሎ ይንደረደርና ወደመጥመድ ሲቀርብ ከጆርባው ያለ ባለአሽከላው ጊደኛህ ሌላ ዜማ - የሰው፤ ኧ-ኸ፣ ኧ-ኸ-ኧ-ኸ ብሎ ያሰማው ጊዜ ዘሎ ከማነቂያው ይደረገማል። በሁለቱም ገጥ ዜማ ነው፤ ይሆን አትርሳ! የራስህ ዜማ መጥፊያህም ይሆናል። ቆቅን ሁነህ እየው። አንድ ብለህ ቁጠር፤ እንግዲያ እንደቆቅ ያለ ጠርጣራ ፍጥረት አለ የሁም። ግና መጠቂያው የራሱ ዜማ ነው።

«በቆቅ ብቻ የሚደረግ ጨወታ አገባብ አይደለም፤ አሁንም በንተ በኩል አድርገን እንየው። ፍጥረት በመዚያው ሲጀነጅንህ፤ ከዳንኪራው ላበት ገዝተህ ሲመጣልህ፤ ከብት መንጃ በቅርህ የወደቀበትን የምትፈልገው ያኔ ነው። ከብቱም የማጃጃያ ዜማውን አብርህ ከመዋር የመጣ ያውቅበሃል፤ መጠመድህን ከሁኔታህ መገምገም ይችላል። ከውዝዋዜህ ጆመራ ላይ በግመሹ፣ በግመንዝቱና ከዚያም በሚወጣው ቅንፋሽ አጆብ ከዝላይና ከዜማ

ጋር ያገባሀል። ከቆምክበት ፍጥረት ጋር መጣጣምህን ታዝቦ፤ መሳቅህን ሲረዳ፤ በዝግታ እየጋጠ፤ እየተራመደ፤ እዘገረ እየተመለከተህ፣ ከመታጠሪያ ይደርስብሀል፤ ያኔ እግሬ አድርሸኝ ብሎ በቅርብ የታወቀ አዝመራ አይጠፋም፤ ተንክልኩሉ ይገባል። እምቡት ጋን ጠላ ሹመህ፤ በምሳ ጥንድ በሬ የሰራሁትን እኮም ፍጆልኝ ብለህ እንዳሳከርከው ባለደብ መቅን ተሰልፎ ሲያምም፤ ዘፈንህ ወደለቅሶና ሀዘን ይለወጣል። አሁን ዙሪያ ሜዳው ገደል ይሆንብሀል። በዙሪያህ የሚፈጠረው ዜማ ሁሉ መሀዘን ዜማ፤ ወዲያው በፋታ ተተኝቶ ያርፋል።

«ከብት የጋጠው አዝመራ የሌላ ሰው ሲሆን፤ ከዚያ የሚመጣው አፈሳግ መሳጆህን ስለሚያስጩንተው ጎዳትን መወዱ መሳ አለው፤ አንተን መውቃት። የሚከፍለውን እዳ ጎዱት ከንተ ጫንታ ላይ ይመጣዋል። በንዱ ከልወቃህ ነገም እንደምትደገም ያውቃል፤ ታዲያ ዱሳ አይቀርም። ለገናው ይህ ይታይሀል። ያኔ ፍጥረት አንተን አይሁን! የማታው የጠቅር እዳ ሲታይ እኩል ቀኑን የዘፈንከውን ያሀል፤ እኩሉን ወየታ ትማርበታለህ። የአይነታው በቅር ለቅስ ሌላ አይነት ነውና ያንን ለ ኋላ ተወው። በፍፁም ከወየታ ጋር በባህሪ አይገናኝም። ወየ ያለበቅር የምታደርገው •ዜማ ነው። የዚህን ልምድ ለሞቅ ተን ታደርገዋለህ። የዘፈን መፈጠሪያው ሌላ መንገድ አይታየኝም። እገር የሚታይህ ከለ ጨምርና እንዘጥ። መቸም በጨዋታ መተጋገዝ ያለና የነበረ ነው።»

«ተበጀው፤ የዘፈን አመጣጥ ታሪክም በቃ ይኸው ነው?»

«ምን ይቀረዋል? በልኩት ላይ አገር ሲያክል፤ ያልታየን ይታየናል። የማያክል ከሆነ ደግሞ ያልታዩሁትን አያኝ ይሆናል። አንድ የሚያደንቅ ሽማግሌ በለለበት ተሰድጆ! እቴ አበባ!» ብለው ታላቅ እህታቸውን ተጠሩ፤ «አንች በይሆን ትንሽ አታግኘም? »

«በመጀመሪያ የወንድን በኩል የዘፈን አመጣጥ ስትጨርስ የሴት በኩል ምንጊዜም ወደ ኋላ ነው፤ እከተልሀለሁ። ያንተን በኩል ፍጆ፤ እኸ! ጠፍቶሀል መሰል አለኸኝ!»

«ያንች ነገር! መልከም! በ ኋላ ሲታይሽ ትገቢያለሽ! በወሬ አማረኛ ከመጣች (ዳንስኛዋ) ደግሞ የጣቢያን በኩል ዜማና ዘፈን የቀራው ቅዱስ ያሬድ ነው ይባላል። የዚህን ጨወታ መነሻ ሲያዩት ተመልሶ እኔ ከልኩት ጋር አንድ ነው። የተናገርኩት ሁሉ ይገጥማል።

«የየዳን፤ የደጆንን ተራራና ገደል ተጠግቶ፤ እላየኸውም? በዚያ ክባቢ አልፈህ አታውቅም? ለኔማ፣ መቸም ራብጊየ ነበር።

በያሬድ ስም ክርስቲያኖች የሰሩት መቅደስ ከዚያ ግርጌ ነው። ብዙ ታምር የሆነበት ጉደኛ ሰፈር ነው። ጨዋታ ከተነሳ ቅዱስ ያሬድ እስራኤል (ፈላሻ) እንደነበረ ግልጥ ነገር ነው፤ እሠ ብየ ባሳሳው እንዲያ ይመስለኛል፤ ወይም በሁለቱም ገጥ የቆመ (ክርስቲያንና ቤተእስራኤል) መሆን አለበት እላለሁ። እንዴት ማለት፤ የሆነ ታሪክ አለው። ክርስቲያኑ ከሰራው መቅደስ ራብጊ፤ ጥርቡ ገደል በየሰምንቱ ቅዳሜ እየተከፈተ የእስራኤል ልጅ መገኛ እዚያ ነበር። አሁን በኔ እድሜ የታየ። የአለቱ ሳንቃ ሲከፈት እኩል ቀን፤ በመልስ ሲዘጋ እኩል ቀን ይከፋ ነበር። የመዝጊያው እከፋፈትና አዘጋግ ያማረ ዜማ ነበረው። ታዲያ በሩ የሰው እኩል ማስገቢያውን ያህል የሰጠ ጊዜ እስራኤሉ የሰንበት መሰዶቱን እየያዘ ገብቶ ዝም ብሉ የሰንበት ድግሱ አለም ነበር።

‹ውስጡ የማይዘለቅ የሚመስል አገር! ልሂድ ብሎ የሞከረው ሰው ግን መቼም አልነበረም። ጠዋት ፀሀይ ቶኖ ስትጠልቅ የጀመረ የሚያልቀው ማታ አግር ስትከል ነበር። እንዲያ ሲዘጋና ሲከፈት ኑሮ በመጨረሻ ታጎለ።

‹አንድ በግ ጠባቂ የክርስቲያን መንጨረት፤ የልጅ ነገር! ጠዋት በሩ መከፈት ሲጀምር በዚያ ገድም በግ እያለቀመ ይገኛል። የጣን አመል ታውቀዋለህ፤ "የጅብ አፍንጫ ጥምብ ሲያሸት ከመብረቅ ይቀድማል" እንደተባለው፤ በዚያው ልክ በግ ጨሌ ከረቅ ያሸታል። እየተስገመገመ እዚያ የተከፈተ በር ሲገባ ህገንም አብሮ ይገባል። በግ ሆየ እየለቀመ፤ እግር እየተራመደ፣ ከበረ እየራቀ ወደአንጋዲው አገር ይገባል። የዚሁን ልጅ ከበግ መንጋው ጋር መግባቱን ያየ አልነበረም። በገባሁበት ተቃኘች፤ በሚያስወጣ በር እወጣለሁ ብሉ ልቡ አስቦ ኑሮም እንደሆነ አልታወቀም። የቅዱስ ያሬድ በር ሲዘጋ በግና ውሜጭ ሆየ እዚያው እንደተዘጋ ይቀራል።

‹ካለሰምንት ቅዳሜ አይከፈትም ነበረ አይደል? ሳምንት ሙሉ ልጅ እስከበጉ ሲጠፋ ባለቤት ሆየ ከፈሉን ሲያለቅስ፤ ከፈሉን ደግሞ ልጁ ከቅዱስ ያሬድ በረከትና ቃል ያመጣል ብሉ ውስጥ ውስጡን ሲደሰት ይሰነብታል። አገርም ውጤቱን ሊያይ ነቅቶ ጠበቀ። በሰምንቱ በር እንደልማዱ ተከፈተ። ልጅ ያለቅጥ ወፍሮ፤ በግም እንደጉድ ሰብቶና ደልቦ ወጣ። የበጉ ውፍረት ከጨሉው እንደሆነ ግልፕ ነበር። ልጁ የወፈረበትን ምክንያት እዚያ የተገኘ ሲጠይቅ፤ የማይታዩ ሰወች ሲንከባከቡት፣ ሲደክመው ዳሰውና ዳብሰው፤ ሲጠምነው አሽተው፤ ሳምንት ሙሉ የአትክልትና የፍራፍሬ ዘር ከምርጥ ምግብ ጋር ሲቀልቡት እንደከረመ ተናገረ። በግ መቅርቀር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ጠዋት በቀስቃሽ ያልተነሳበት፣ የስሜንን ብርድ ታውቀዋለህና በዚያ

ቅቱን ያልተመታበት፣ በግንም ቀበሮ ይጥልብኛል ብሉ ያልተሰቀቀበት ያን ሳምንት ብቻ ነው። የቅዱስ ያሬድ የተአምር በርም ልጁ በወጣ በሰምንቱ እንደዘወትሩ ተመልሶ አልተከፈተም። ታጎለ። ያሬድ ታዲያ በጣም ታሪከኛ፣ የቅሳንት ሰው፤ የዛሬ ቅዱስ መንፈስ መሆኑ ግልፕ ነገር ነው።

‹ያሬድ ዘፈንን የጀመረው ምልኪት ተከትሉ ነው፤ የመፍጠርንና የመቀኘትን ነገር ያነሳው ከትል ተነስቶ ነው አሉ። ሁሉም ነገር፣ ምክያት-ምክያት አለው። ንጉስ ዳዊት የበገናን ልቅና የተቀኘው በቤት ፍቅር ተይዞ፤ ያሬድ ደግሞ ዘፍ መውጣት አቅቶት ሲንከላወሱ ሲወጣ፣ እንደገና ሲወድቅ፤ ተመልሶ ቅንሽ ቀረቶኝ ሲል እንደገና ሲወድቅ፤ ምን ያለፋሀል፤ በጭንቅ፣ በመከራ፤ በመጨረሻ በጣም ደክሞ ያሰበውን ዘፍ በሰባተኛው ከዘለቀ ትል ነው ያን ሁሉ የሚነገርለት የዜማ ጥበበስንክሰር የተሰበመው። ያኔ አንተ ሁነህ ቢሆን ዋር ያንን ባለመያ ትል ደፍጠሀ ነበር የምትገለው። ግና፤ እንዲመለከተው ያደረገው የእግዚር ውቃቢ ነውና ከመግደል ይልቅ አፉን ከፍቶ ሲመለከተው ዋለ። የነበረበትን የአእምሮ ድድብና በትል ምሪት አጠዳው። የፍጥረት ልዮነት ይገርመኛል፤ ስለሆነም የያሬድ ዜማ የተቀኘው ከፍጥረቱ እንቅስቃሴ በማንሳት፤ የንጉስ ዳዊት ሊሳ፤ የቤት ወበት!

‹አሁን፤ ሌላውን ተወው፤ ይኸ ተዘዋሪው፤ የወንዙ፤ ሰመን ብጠራውስ ምን ይላል? እዚህ እንደሁ፤ ከየትኛው ሜካና ጃብጃባ የለበሰ ጥቁር ባህር አሊያም ሳጣ ገደል እንዲልተገኘ ነው? ፈፋእንኳ የሌለበት መናጢ አገር! ሰው ግን መናጢ ነው፤ የማይሰራው ነገር የለም። እምልህ፤ የወንዙ ፍጥረት ከበሮና ግቢንቶ ከኛው ቅንሽ ይበረታል፤ የፏፏቴው ምት ግራ እያጋባም እንደሆነ እንጃ! በጣም ሀያል ነው። መቼም ከኛው በጣም ልዩነት አለው።

‹ሀይል መፍጠርና ጉልበት ምንጊዜም በእጁ ነው። ይኸ ይሁን ከለ ይፈጠርለታል፤ እኛና የጅን ዘር የምንለያየው በዚህ ነው፤ እሱ ባፉ፤ እኛ በጉልበታችን እናድራለን። እኛ በጣም ለፍተን፤ እሱ ግን ሁን! በማለት። እግዜር እዚህ ላይ እጣ በማደል ተሰብቷል፤ ማን ያውቃል? እንዲያ ማድረጉ የመለበም ይሆናል፤ ነፋስ የሚሆን ነገር!.. የጅን ስልጣኑ የደረሰበትን ባየሁ እንዴት ሸጋ ነበር!› ሲሉ እህታቸው እንደመዳጨር ያጉቷቸው በድንገት ተተኩ፤ ‹አለኸኝ!› አሉ። ዜማዊና የፍቅር አጠራር ነበር።

‹ያንተ ነገር! ከኛ ስልጣኑ የወንዙ (ጋኔል ያለማለት ልምድ) መስልጠን ብዙ ይርቃል ብለህ ነው? ከዚህ ሳይሰ ልብም እላለክ፤

የጎደለብቅን ነገር፤ መቸም ፈርተነው ነውና የምንጥረው፤ እንዳልከው ይሁን፤ በልጦ መሰልጠን የጃን አይመስለኝም፤ ከነገረቀደም መዘወር የሚያበዛው እኛ ቀያልረበ ብለን በጠልነው እጠቢ፤ ፈርስና በሌላውም ይኸን በመሰለ ቆሻሻ ነገር ሁሉ ነው። ከልክስ ጃን የሚጥረው በኛ ተገንና ዙሪያ ብሎም በኛ ቆሻሻ ትራስ ነው። የሆቅ ሲሆን ፉከክረና ስራው ሁሉ ከኛ ጋር ነው። ከኛ ያየውን አስበልጦ አይሰራም አልልም፤ ይሰራ ይሆናል። ብዙ መላቅን ግን ተወው። የማናውቀው ነገር ኑር! በድንገት ሲገጥመን እንኪ መለመላ እርቃንስጋውን ነው የምናየው፤ የተለበለበ ግንድ!» ሲሉ፤ ያያ ተብጄ ፊቅ ተፍታቅቶ ተንሰራፉ።

«እቴ እንዴት! ውብ ብላሽል፤ ዉወትሽ የእግር መጣያ አለው። አንቺ ያልሽው እንዲያ ሆኖ፤ ራቅቶ መሆን የራሱ ፈሊጥና ጣእም ይሆናል፤ በኛ መልበስ ይሰቅ እንዲሆን ግን ያውቃል? እንዳሰው ነዲይ የሆነውን ገኖሞሽም ይሆናል፤ እንዳበለዙፉን በወርቅ ተንቆጥቁጦ ለብሶ የሚከሰት የጃን ዘርም ይገጥማል። የጃን ባህሪ እንዳሰው ብዙ አይነት ነው። እተዋ እንዳሰችው፤ አንተ ውብ አድርገህ ያበጃኸውን፤ አፍንጫ የሚነውኖ፤ ጀርሆን የሚጉትት ነገር፤ አካልህን የሚያስወብ፤ ሌላም ብዙ አይነት ነገር ይጥራል፤ ያውድግን ነገር እንደ ምሳሌ ወሰድ ለፍተሀና ቀልጭ አድርገህ ያናፈስከውን እህል ልትጭን፤ መጫኛ፤ አቅማዳና እህያውን ስታሰላ ጃን ሆኖ በጉን በማይታይሆና እንዳሉ ሰወር በሆነ አቅማዲ ተስፍሮህ ጃው ይሳል።... ያልሰፈርከው ነገር እንዴት መነሳቱን ተረዳኸው? ቅል ይሆናል፤ የሞኝ ጥያቄ! ግና እታበባ እንዳሰቸው አብረነው ነው የምንጥረው። ከምርቱ ሲጉድል ታውቀዋለህ። ብዙ መለኪያ አለው በዉዳው ጊዜ ዛላ እንሳሱና ክንድ አመነጣጠሉ፤ በድብታው ወገብህን እጠማመኑ፤ በክምሬ ድልደላ እግዚእ! ስንቅ ጫን ይጠጣ ይሆን? ብለህ የቷመጥከበቅና የክምሬን እርብራብ ተረግጦ ሲያንኩተው፤ በክምር ፍርሽው ደግሞ እየር ከለዛ እንስቶና እብጦ ስቅንሰንስው ከገለባው ይልቅ የፍሬው መፍጠጥ፤ በሬ ማሄዱን ስትገባ ደግሞ ማሽንህን አገላብጥ ስቅለው ፍሬው እንዳእሸዋ የበሬ እግር ሲገታ፤ መለኪያው ብዙ ነው። እኔ አሁን የከመርኩትን የጤፍ ክምር ባይን ግምት ይሆን ያህል ጫን ይወጣል ከልኩ በሰፍር የሚመጣው ከልኩት በልጦ ነው። ስቅገምቅ ጡር እንዳይሆንብኝ አግነህ አትናገርም። ሆድህ ግን የሚወጣውን ያውቃል።

«ከማጀት ወስዮ በተወከው የተሟሟተ እህል ባይቀር ይመጣብሀል። መልክም ሴት የተጨነቀችበትን ድቀስ፤ ምጥን ሽሮ፤ የተፈጨ ዱቄት - ምን ያለፋህል ለክራሞቱ ብላ ያስናዳችውን እጅ

የዋለበት ነገር፤ ለእፍ ግብዣ የደረሰውን ሁሉ በጉን ይሰልባል። እንዲህ ያለው የወንዝ ፍጥረት ሲገጥምህ ለዋቂ ደብተራ የምትከፍለው ወጭ አያሌ ነው፤ ያውም ጠንካራ ደብተራ ከተገኘ ነው።

«ሌላውን የጃን ባህሪ ስንሰልለው በጉ ጃንም ይገኛል። መልሰህ ያውድግን ታሪክ ወሰድ፤ ላውድግው እግግስ ብለህ፤ ውብ ስቅዳግስ አይነታ መቿዳሸው ይቀድማል። የዳገስከውን ብቻ መስዋእት አድርጉ የምትሰፍረውን ብዛት እንዲሰጠው ከማዩ ንጉስ - እግዚር፤ የምድሬ ባለቤት - አብሮ አዳግ ከሚኑ ቀሊ፤ ያበቴ ውቃቢ - የደንጉርሆው አደባር፤ አደራህን! ምርቴ የተከዜን እሸዋ ይሁን፤ በጭንቅ በኩል የሚጥረው ጭንቀት በኔ ይጥና፤ አጥግበህ የደስታ ፈረስ አድርገኝ፤ በእለም የተዘራህ ከሰው እጋኸ ሀይል ሁሉ እዚህ እውድግ ላይ በ-ረ-ኸ-ት እወርድ! ቅሰዋለህ። እያንዳንዱ ሀይል እቅፍቅፍ ስቅል በሚረጨው የምራቅ ዘለላ ልክ ከውድግው ላይ እንዲረግፍ ቅጋብዘዋለህ። ምራቅ እንዲያ አረብርበህ ከሰውን ደስታ የሚወደው ብዙ በጉ እመል የያዘ የጃን ዘር ሁሉ በቅርብ ያለ ይሆናልና እንደተማለልከው ያወርድልህል። ይህ በበጉ በኩል የሚሰለፈው የጃን ዘር ነው። ከዚህ ስታልፍ ደግሞ፣ ጥቁር ፍየል፣ ዳልቻ በሬ፣ ቀይ ዶሮና ሌላም ይሆን የመሰል በሚወደው ስእቅ ጣሉልኝ የሚል አለ። የበረው ዋጋ ይጉዳህ እንደሆነእንጂ ስጋውን የሚበላው ሰው ነው፤ ደሙን ብቻ ከጠራ አፈር ላይ ታፈስታለህ፤ ስጋም የሚሰልብ ይጥራል፤ ግና ያኔ አይኑ-አጥጃ ስለሚሆንብህ አይታወቅህም ይሆናል። ደም ሲሆን የመጀመሪያውን ጠብታ እንጃ ሁሉ አታፈስውም፤ ዉሻህ ምን ሊበላ? ከዚያማ ምን ቸገረህ የጠጣ ቢጠጣው! ሰው በእውቅ አላቅርብለቅ እያለእንጂ አንድ ነገር ስቅለምነውና ስቅለማመጠው ወደሰው ደም የሚተያይ ዉከኛ አረመኔ ጃንም አለ።

«የእተዋ ዉዋታ እውነት ይመስላል፤ ጥሊያን ብዙ ጋኔል አፍዋ፣ ከብረት በተሰራ ጋን እያስገባ ወስዶ የየበብ እውቀት አብራርቷል ብለን እናማለን። በግልጥና በዳባባም የተወራ ነው። እኔኪ እንዲያ በተደረገበት ቦታ አልነበርኩም፤ እተዋ "ጋኔል ባየው ይጠናል" ያልሽው ልክ ነው። ጥሊያንን በጃ ያሳሰና እምቢ ያለው ንጉሱንጉሱና በጣም ሀይለኛው አልሄደም። የሰሜኑ አውራ አሊያዝም ካለው የጃን መንጋ አንዱ ነው። ዛሬ በጣም አርጅቶ፤ ግልገል ልጁ ባንዳንድ ምሳያ ነገር፤ እንዴህልም በሰው ራሱን ማስተዋወቅ ጀምሯል ይባላል። ታዲያ አባቅየውን ለመያዝ አዳግ በተደረገበት የጥሊያን ሰሞን ለደፍን የሀገሬ ሰው፤

በሀልም፤ በግልፅ ጨኸትም ・ ዘፉን ከደንጊያው በማንቀጥቀጥና በማጋጨት አገር ፍርሽ ይሆናል ሲል ጥልያንም ፈራ። ያገር ሽማግሌም የሰላቶን ተባባሪ ደብተራ ተውተው ብሉ ጃንም ሳይሄድ ቀረ፤ አገርም አማን ሆነ። ግልገል-ግልገሉን ብቻ መውሰዳቸው በጃእንጂ አይነታው ቢሄድ ኑሮ የጠቢያ በረኸትና ሲሳይ ይጠፋ ነበር። በከፉ ካልሄደበት የማይተያይ የጃን ዘር አለ፤ እንደሁ እንደሰሜኑ ያለ አደባር፤ ዝም ብሉ ህይወት ጠባቂና በረኸት አውራጅ ጃን። እንደሁ ያለው ጃን ሰውን የሚሰው በምዘወርበት ጊዜ አቅዘወረ ነው። አበሻም ደሀን ስርአት ያውቃል፤ ስምሪትን የማያከብረው ደግሞ ጃልኛ አካሉ የጉደለውና የተጣመመው ነው። ሰው ጋኔልን በጉልበት ለበጉ ነገር ሲመራው አላየሁም። ይሀን-ይሀን ለዚች ሞኝ ፈረንጅ አትንገራት፤ እንዳልሆነች አድርጉ ነው የሚሰዳት። ግመንስ መቸም እንተን አላምንህም፤ ሁሉም ነገር እንደኔ የዘና ጨዋታ ነው የምታደርገውና ትንገራት ይሆናል፤ ግና ወደጃን አትተያይ በላት! ከጃን ጋር ተጫውቶ የረባ አላየሁም።»

«ጥልያን ጃን ቢጉትት እሷን ምን አስፈራት?»

«እንዲያ መች ወጣኝና፤ ጥልያን እንበለ ማንዷ (ባንዶ) መች የእኩል ሰአት ጉዳና ተራምዷል!» ብለው ታያይተን ተሳሳቅን።

ይሀን ጨርሰው የጉለቱትን ቢራ የያዘ የወረቀት ከባያ ነካኩት፤ ግና፤ ቀደም ሳይታወቃቸው እንጫልጠውት ስለነበረ ተኪውንና ከጠገባቸው የተቀመጠ የሴላ ቢራ መክፈቻ ፍለጋ ሲቃብዙ እሀታቸው እንደገና ጠረቻው፤

«አ ለ ኸ ኝ እንጂ!»

«ቶይማ እታብበ! ወይ ብየሸለሁ። እንቶ፤ ማን ነህ፤ እንዴት ነው! ቢራ አቅርብ መክፈቻ መንሰት እንዴት ያለ ትድረት ነው? በል!» ብለው ያፋጠጠበት ጉባል በለዘብታ፤ «አየዋ፤ ዘረ ነገር ረስተሀል፤ የሀበሸ የእጅ መሳሪያ በራስግርጌ ማገር ነው የሚሰገውና የሚንጠለጠለው፤ መጠረቢያው፣ ማጭዱ፣ መቸም የእለት ግብር መስማሪያህ የሆነ እቃ ሁሉ። እንደተቀመጥክና እንደተነሳህ ከምታነሳበት በታ ነው የምትጥለው። ረቅ የሚቀመጥ የቤት የሚሰጥር እቃ ነው። ታዲያ ግን፤ የቢራው መክፈቻ የተንጠለጠለበት በታ ጠፍቶሀል!» ብሉ ተቻቸው። ያመላከታቸውን የቶርኪ መፈርቀቂያ ሲያዩ ተንከትክተው ሳቁ፤ ስድብ እንዳይሆን እንጂ በጣም አንቧረቁ።

«ኧረግ የሰው ነገር! በመሳ አስተማርከኝ።» አሉት። ከጠረጴዛው ከንፈር ወደውስጥ ከተቸከለ መለስተኛ ችንካር ረዘም ባለ ዘለበት የተንጠለጠለውን የቶርኪ ማላቀቂያ ሳቡት። እየሳቁ

ሳጠገባቸው ጉባል ሰጡት። አሰከፍተውና ከማታነሸው መጠጫ ላይ እየሞሉ እሀታቸውን ጠሩ፤ «ባይ እንገዲህ፤ የውሰሳደፍንበት ነገር ሰልቷል፤ እተዋ የታየሽ ጨዋታ ምን ነበር?»

«በቅድሙ ጨዋታ መሀል ለሳ፤ ነገርን ነገር ይበጥልና አሁን ከተተራረብችሁት የሆነ ነገር መጣብኝ፤ እነዚህ ነጮች፣ እነሱ ከሚያደርጉት ነገር የተለየ ሲያዩ እያሙ አስቸገረዋል። ይሀን የጠርመስ ክዳን (ቶርኪ) መንቀያ ሌሳ ስፍራ ሰጡት፤ ባይጠጣም የክዳን መንቀያው ባደባባይ፤ እንደደበርቷ ጠላ ከማሪት የእንግዲ አይን ከሚያርፍበት በታ ላይ ሲቀመጥ ሰከራሞች ይሉናል። ይሀ እየተቿረጠ የሚመጣ የቀለብ ጉርሻ እንዳይቶም። የመቅበሪያውን ባለመከት እርፍራፉን አሰናድተው ሰጥተውናል፤ ታዲያ በዚያ፤ በዚያ ማስቀመጥ የወግ ይሆናል።»

«እቴ እንዴት "ሀልም ፈርቶ፣ ሳይተኙ አያድረም" ያለውን ጨዋታ አመጣሽው ጥናውን ጨዋታሽን ቀጥይ ይልቅ፤ ፈረንጅ እምቶ ከምን ልንደርስ ነው!»

«መቸም ልብ በለው፤ ነገረሀለሁ፤ አንተ ስጠጣ የመንጨረቅ ሁሉ በረሀብ እንዲያልቅ! የትድም ጨዋታህ ግር ያለ ነገር አለበት። የወንዙ መብት እሰከየት ድረስ ነው የምትለው? ይኸ ጠልቶ አልገባኝም»

«ምን ዳርቻ አለው ብለሽ ነው? ከኛው እግዜር ጋር በትልልክ ነው የሚዋረው። የራሱ፤ የብቻውና የአይነቱ እግዜር ሳይዋረው ይቀራል?»

«አየልኝ፤ እሁንስ ርቀት ሄድክ፤ ደግሞም ጨዋታ ስታጋጭ ያዘህ፤ እንዴት? በለኝ።»

«እንዴት እቴ እንዴት?»

«እንዲያ፤ እንዴት ብሉ፤ የተመኘኸውን ይመስልህ፤ ቅድም፤ ውብ ጃሮ በሚሰማው አይነት ተንቅንህል፤ እግዜር ሰውን ባንድ እንጣር፣ በተለየ ባህሪ መፍጠሩ፤ የጃንን ዘር በሌላ አይነት መስራቱ የመለበም ይሆናል ብለሀል። የጠየኩትም በዚህ ጨወትህ እገር እራምጃ ነው፤ ግና፤ እሁን ወደሌላ ታጠፍክብኝ»

«እንች የምትይው እንዴት ይሁን ነው?»

«እኔ ሳውቅማ የጃን ልጅ ሰውረት የገባው ተረማጭ ነዋ! በእራቱ እንጣር እግዜር የሰው፣ የወንዙ ደግሞ ከእግዜር ትእዛዝ የወጣና እኔም መንግስት ብሉ ያመጠና በዚህ ትእቢቱ የተቀጣ ነው። የምን እግዜር አለው ትላለህ? በመብረቅ ሲያሳድደው መስሉኝ የሚውለው? ሲዘንም ከዛፍ አትጠጉ የሚባለው ለዚህ መስሉኝ? አይጠረ ስለሚጠጋበት! ውሸቴን? አየልኝ።»

«እታብበዋ፣ እጊጉል ጨዋታ አመጣሽ! ይሀ እበባልሽማ ሌሳ

የታሪክ ጉዳና ያመጣል። በክርስቲያን በኩል ግፃ የተነገረ ነው። ሰደጣንም በደው ጋኔል ያው ጆኑን ነው። ስለሆነም እንቶ በምትይው ቢሆን እበታችን ይሁዳ ነው። ክርስቶስ በተሰቀለ በማግስቱ የተፈጠረ ታሪክ ነው። እየሱስን፤ በስልጣን ፉክክር ቀንቶ ያስመገረውና ያሰቀለው ይሁዳ ነው፤ ከመጀመሪያ፣ ይሁዳ ሊቀ መላእክት ነበረ፤ ይህን ማእረግ ያጣውና ጥልመት ልበሰ ተብሉ ጨለማ የገባው በዚህ ነው ይላሉ። በዚህ አንጣር ስትሄጅ ታዲያ እኛም ጋኔሉች ነን ማለት ነው። ምነው እንደዚያ ሆኘ በሆነ! እንደጆን ዘርግ ብስወር፤ ሀይሉ ሀይሊ ቢሆን ዋሮ እንደህ ያደባባይ መሰቂያ በልሆንኩ ነበር። ይህን የሚሚወትብኝንና የሚያናንቀኝን ፍጥረት ሁሉ በሰቅሀብቶ፤ መሰቀያ ቀርቶ በገራሁትና ሁሉም ነገር እማን በሆነ ነበር።

«የኔ ጨዋታ ሌላ አድማስም ይመታል። ቤትዮዋ ከስራ ሁለቱ ልጆቿ መሀል በመልከጥፉነታቸው የጠረጠረቻቸውን ከናላ ደበቀች። በጉብኝቱ ጊዜ ልጆችሽ እኒህ ብቻ ናቸው ይላታል.. እሱ ያልሰተውን ይጠይቃታል። ቤትዮዋም በመልስ እዎ ስትል፤ እለኝ ያልሽው የተመረቀ ይሁን! የቀረው ብኑን ይሁን ይላታል። ደብቃ ያስረገመችው የተሰራ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ነው ይባላል። እንደተሰወረ ቀረ። ሁሊም ሴት ሄዋንን ብቻ መስሎ እንዳትቀር፣ ሁሉም ወንድ አዳምን ብቻ ሁኖ እንዳይቀር እንደእትክልቱ ብዛት፤ እንደእንስሳው አይነት እንደሌላ-ሌላው ፍጥረትም እኸጉረጉረው። የደረደረው መሰ ይሆን ይሆናል። አዳምንና ሄዋንን ከመፍጠረ በፊት ያሰባሰው ነገር ሁዋ በሂላ የተጣደበም ሳይሆን ይቀራል? እትአበባ፤ ሰውን ሊሰራ ሲጀምር ከመጀመሪያውኑ እንደተልከሰከሰበት የምትረጂው ነው፤ አዳምን ፊጥሮ የሄዋን ጉዳይ የታየው በሂላ እንደሆነ በመፃሀፍ የተመዘገበ ነው። ታዲያ ይኸ ሰው የሚፈራው የተሰራ ዘግይቶ ነው፤ ቶሊ፣ ዘር፣ ጋኔል፤ ሌላውም ይህን የመሰለ ሁሉ።... ግና ማን ያውቃል ማን ነበረ?

«ታዲያ፤ ናላየን ግር ብሉት የወንዙም እግዚር እለው ያልኩት የመምታታት ንጥቀት ነው። የማይመስል፤ ብሉም የሚመስል በመሆኑ ነው፤ የሰው ወገን እንዳይባል ሰው አይደለም፤ ነፈስ ይሆናል። እግዜር የለውም እንዳይባል፤ በፃምና በፀሉቱ ጊወራት የሚደረድረው በገናና ምሰሏ በሀለቱም ገፃ ያሰባል፤ ሰው ነው፣ ሰውም አይደለም ያሰኘል። በገና የመጣው ከዳዊት ጀምሮ ነው ይባላን እስማለሁ። የጦቢያ ልጅም በገናን የሚጠቀምበት ለደስታ ሳይሆን ለፀሉትና ለምለላ ነው። የእግዜር ስም ማወደሽ። ታዲያ፣ የወንዙም እግዜሬን እያወደሰና እየተማለለ

ነው እልና፤ መልሽ በሌላ ገፃ ሲየው፤ ከእርግግናቸው ለመውጣት እግዜርን ምረቱ እወርደ፤ ይቅር በለን! ብለው የመማለልና እንደገና ወደሰውነታቸው ለመመለስ የመሰላይ ነው ብየ ማለቴ። ሌላው የልቢ አንጣር፤ ከኛ ጋር የመወደደር ዘይቤም ይሆናል ይላል። መቸስ ቀናተኛ አይደል! ገራ የሚያጋቦና መፃሀፍ እፃድቶ ያላቀረበው፤ ተቃርኖና እንበለእትጤ የተወው ነገር ነው። ከሰሱቱ ግን እንዱን ይሆን ይሆናል። የዚህ ምስጢር መዝብቲያ ጊዜ ዳግም የሚመስለኝ፤ ዱሬ፣ ማኪው፣ የሚሸሸግበት የውሀ ዘር ሁሉ እየተና ሲሄድና መግቢያ ሲያጣ ይጠፋና ነገር ገፃ ይደዘል፤ ጋኔልም አይቀርም፤ ስለጋኔልም ፍጥረት የሚያወራ አይቀርም።»

ዳንሰኛዋ፤ በገራ በቀኝ የተወራውን ልትመዝግብ ተቅነጠነጠች፤ ዳጋግማ ተመለከተቺኝ። መልሰ ነሲ ሂት። ግና፤ ትእግስቷ ትንፈሽ እያስውጥም፤«ለምን የፈት የፊቱን እትተረጉምልኝም?» አለች።

«በመጀመሪያ፤ እነሱ እየተናገሩ ለመተርጎም እያመችም፤ በሀበሾች ዘንድ መደማመጥ ዋና ነገር ነው። ሁለተኛ በቅርብ ከተናገሩት ለዳንስ ምርምርሽ የሚጠቅም እልሰማሁም። የሚያወሩት ትዝታ ነው። እርስ በራሳቸው እየተማገሩ ይመስላል። ወዳንድ እትጤ ለመምራት ጊዜ ይጠይቃል። ያ ደግሞ ራሱን የቻለ የምርምር መሰናዶ ነው። አሁን ክትር መጠየቅ በእደገታቸውና በልማዳቸው የፍርደቤት እዝ እድርገው ስለሚመለከቱት ጨዋታቸው ይቀረቀራል። ዝም ብሉ ማዳመጥ የመሰለ የለም፤ ሲሁኑ እንተዋቸው።» አልኩ። ፊቷ የሚያታልል መሰለና፤ «ሴትየዋ በጣም ተበትውና ሀይል ገዝተው ነው የተናገሩት፤ የወንድየውን በሂላ ትተረጉምልኛለህ፤ የሴትየዋ የፊት እሰራር ራሱ ዘፈን ነው የመሰለኝ» ስትል ነበበች ተበጆን ተጠሪ፤ እሷን እንዲያ ትቻት ጆሮየ ወደነበበች ተሰረ።

«እየልኝ!»

«እህ፣ እተዋ!»

«የልጅነት የጨዋታ ምርምር እናስቱሀና ነክከቱህ የጋሚየን ትዝታ ሁሉ ጉተትኸው።...» ብለው ሳይተገሉ እያ ተበጆ ጨዋታቸውን ቀጥቸው፤

«እንዴት ባለ? በሞቴ»

«ምነው! ጠላትህ እፈር ይብላ!»

«ውብ ጉዳና ገበሽ፤ ዘንግተሽ ነውእንጂ አንቺ ልትቀየር ነበር ድርጅታችን። ሌላ ወሬም በመሀል ሰጠሽ ነው ከጉዳና የወጣነው። በይ ጨዋታ ለዝናና ጊዜ ለማዋስጃ ነው። አንችም የጨዋታ ሰው ነሽ። የሴቱን ገፀ ጨዋታ፤ በሞቴ፤ አውርጅው እቱ አበባ!»

«ጉዝ የን አውቀኸዋል፤ ግና ለዚህ ነው የምትሞተው? አደራሀን ምን ያህል የሴት ነገር ብትወድ ነው?»

ነበበች።

የወጣትነት ዘገሊ አይናቸው ሞጭሙጮ፤ ያንን ለማላበስ የተሰራው ሽፋሽፍታቸው ተጨግዶ በበላዩ ተረገርጉቦታል። የኤሌክትሪክ መቅረዙ እየወጋ አበቸገራቸውና እጃቸውን ከወደቅንድባቸው ራስጌ እንገርበበበት። እቅርቢ ሁነው ለማበረታታት እንደሆነም እንጃ፤ ወለሉን እግክለ ለቡና ከዳሚኒነት ተሸከፋ የተቀመጡችውን ጉብል ተጠግተው፤ እንደደብር ዙሪያ ከበናቸው የተቀመጥነውን ሁሉ ባይናቸው ፈቀዱን። ለዚህ ምላሽ የሁላችንም ጆሮዎች ተከፉቱ። «በስሚን ከበቅና የገብስ ገለባ ጤስ የደከመ አይኔ የሽውን የመልክ ቀለም በልክ አላነሳልኝ አለ። ወይኔቱ ልጅታ! ልቤ የጉልማሳ፤ አይኔ ግን የተረታ ሁዋ ልቡከይኔ አልጋጠም አለ፤ የጨርቅ ቀለም ከየሰው መልክ ጋር በሀከል አንድ ሆነ፤ ከጨሰም አገር ተወልጆ በጤስ አለኩ!» አሉ።

ከዋና ጨዋታቸው ለመግባት ያድማሟቸውን ጆሮ ሁሉ ሊያዋዙ የተነሱበት መግቢያ ሳይሆን ይቀራል? ያንኑ አይናቸውን እርገብ-ርግብ አበኙት፤ ከላይ አጠግገው የሸለሉበትን እጃቸውን አውርደው ከጭናቸው ላይ አዘኑት። ያይናቸውም ቅኩረት ከጃቸው ጋር አብሮ ተዘና። ባት ያልነካው፤ ገለፋቱ በሰፊድ የወለቀለት የባቂላ ክክ የመሰለ፤ ብሉም ፍልጣፍልጥና ዘረዘር ጥርሳቸውን በጠባይ ሸርምመውና ግሪም አከናፍረው አበሙቱን።

ጥቁረት አላስከስተው ያለ ቾርችም ያንገት ውቅራታቸውን የቆዳ መሰብሰብ ተደምሮ ፍፁም ጊዮነቱን ሊቀማው ቢሞክርም፤ የንግግር እንደበታቸውን በጀማሪው ቃል ሊሰቅሉት ሲሞክሩና ጉድን ወደላይ የጠቀሱት አንገታቸው ሲቀና ውቅራት ደበቂ አስመሰላቸው። ብቻ፤ ሁኔታቸው እንዲያ እቅል ይሰቅላል።

«ሰማህ አለኸኝ! ዱር በብዛኛው የወንድ ሁልጊዜ የወንድ ነው የነበረ። ያን ይዘህ፤ በሴቷ በኩል ሲሆን፤ ነፍስ ያገባችው ነፍስ ከላገባችው፣ ከወደህ መንደር ያለችው የማደዋን መንደር ጉብል ትጠራለች። ይህች ጡቷ ያጉጠጉጥ የጆመረው ሴት፤ ለኩበቱና ለጭራሮው ለተማና ስብሰባ ባንድ ላይ፣ ከመቀነቷ በላይ ጠፍር-ገመዷን ታደገድግ-ታደገድግና በየማጀቷ ከዋለችበትና ከተሰናዳችበት መቀነጃጀት ጋር ተደምሮ የወጣች ጊዜ የሰርግ ድግሱን የምታሰናዳውን ያህል- ያህል ነው። ዱር የወንድ ነው ብለናልና፤ ከዚህ በመጣ መሽከፍ የሴት ነው። አመጣጧን ትጨነቅበታለች። ወንድማ እንግዲያ ምን ያውታል፤ የተበጃጀ ሴቅ ማየት- ተጥሉ ማንሳት ነው…» ሲሉ፤ አያ ተበጆን የእህታቸው ንግግር በጣም ነቀነታቸው፤ በመሆኑም አቷረጧቸው፤

«አበጅታ አመጣችው፣ እተዋ፤ በቸር ፍጆ! ሰድባሽ ግን ይቆይ!»

«በጥብጥ የሆንክ አሹከር፤ ተው እንግዲህ አታነቅፈኝ፤ ጣልቱት ነገር፤ ስታነቅፈኝ የጨዋታ እግርና እጅ እሰገመር ማዘበረቂ ያደላል። ታዲያ፤ ተጠብብታና በጣም እንደማመጥ፤ እንዳንራራቅ፤ መግ እንዳናቿርጥ ተባብለና መሀላ-ቀረሽ ድርድር አርጋ ነው በገፀ-ብገጧ የምትወጣው። ይህ ሁሉ የመለበም ነው፤ እንዴት ማለት ወንድ እንደቶመበት ነው። የወራት ምክንያትም ይዋረዋል፤ ወይም የማሽላ እሸቱ ወራት ይሆንና ይህን እሸት እንደዋልያ ያወላብ-ያወላብና በላዩ ላይ የተገኘ ሲሆን አሰር-ውሀውን፤ አሊያ አምቡውን፤ ይህም ይቅር የመከር ወራቱ ውሀ የሚያነሳው ሀይል ልዩ ነው። ምን ያለፋሀል፤ እንዲያ ሲሆን ወንዱ ሁሉ ምነው ፍጥረት ሁሉ ሴት በሆነ ይላል፤ ይቶምብታል! ግና እንዳሰበው የሚሆን የለም። የሴት ወደዱር መውጣት ፍርሀት የመጣው ይህን የወንድ የመንደግደግ ከመለበምና ላለመበለጥ ነው።» ሲሉ አያ ተበጆ ለማቋረጥና ለመተቸት አልተመቻቸውም፤ ከንገታቸው ተማዘው ጆሮ-ግንዱ ድረስ ተጠጉኝ፤

«ታውቃለህ? በቁንጅናዋ አገርን ኡኡ ያሰኘችና የተመነሸች ነበረች- ታያለህ አሁንም እንዴት እንደታመሰች? ዝም በል፤ አትማዳሀን ውብ አርገህ ዘርጋ- ጣፍ!» ሲሉ በጭንቅ ነበር ያዳመጥኳቸው። ግና የነበበችን ወሬ ብዙ ነገር አስተውኗል። ቢሆንም ጆሯችንን መልሰን ከሉበት ላይ ሁላታችንም ዳረግነው።

«… ለቀማ የወጡት ዝምድና ቢኖራቸውም የሚጫወቱት ነገር ሁሉ ማስመሰያ ነው፤ እህት ለእህትም በጨዋታ ምራትነት ትሰራለች። የገና ለገናውን አይቴ፣ በየት ነው ያለሽ፤ እህ! አትራቂኝ ብየሽለሁ፤ ዱር የሚሸፍነው ነገር አይታወቅም ትላለች

ይህቺ ወዳርን የናፈቀችው ጉብ ጉብ።

«ከሀሜተኛውና ከምትፈራው መንደሯ የራቀች ጊዜ የሚሸተው ነጠንት እያሉ ነው። ግና መፍራት አይቀርም፤ ሴላው ይቅርና ሴትን የሚተያያት ፍጥረት ብዙ ነው። ሀይል የማይገዛበት ፍጥረት የለም። ባለም ካለው ፍጥረት ሴትን የሚያከብር አንበሳ ብቻ ነው። ምነው እሱ ሰው ሁኖ በሆነ! ጀግና፣ ባለግርማ፤ ክብሯን የሚያውቅ። እንግዲያ ከንበሳም የአንበሷ አመል የቅል ነው፤ ሰለዚ ቀናተኛና ያገኘችውን ሁሉ ሳጥታ ባይ ፍጥረት ናት። መቸም ከወንድየው አንበሳ ውጭ ገመሮው ዝንጀሮእንኳ ሴት ለማባለግ ይተያያል። ሴት ብቻ ካገኘ ያሰበውን ሳያደርስ አይለቅም። ባንበሳ ግን ግን የተነገረ ነገር ነውና ምክሌውን አላጠኸውም ይሆናል አለኸኝ!

"ወንድ ይሞታል ባንበሳ፤

ሴት ሸላቸ ጋግውን በበሳ" ይባላል. ሀቀኛ ትርጉም ነው።»

የነበበች ጨዋታ ከወንድ ጉስግ እልፎ ወደቤት የፖለቲካ ንቅናቴ ሊያመራ ሲታጠው ታናሽቸውን ዝም አሰሰኛቸውም፤

«እተዋ፣ አሁንስ ፈር መጥተሽ ተጫግተሽ፤ ዋና ጨዋታሽን አቅርሽ፤ ጨዋታየን አቀረፈድክ ባቅይኝና፤ ያንበሳን ነገር አገነንሽ- በጣም ደጋገምሽው። የመጀመሪያ ጥያቄሽ አንበሳን ሲገድለው የሚዋረው ባለቀምጣ ወንድ መሆኑን አለመጥቀስሽ ነው። ጨዋታሽ አግረኛ የባበ ነው። ይህ የምን ይመስልሻል?»

«እንዴት? አለኸኝ»

«መልካም፤ እግዜር በበጉ ይጠይቅሽ። በመጀመሪያ ያንበሳና የሴት ጨዋታሽ የመናናት ነው። አንበሳ ይንታቸ ሂል። ባፍንጫው ነው ከንቀት ወሰኑ የሚደርሰው፤ ገና ለገና ከረቅ ግበሽ-ግበሽ ስትሸቱት አይኑን ያስዝባል። ወንድ ግን ብረቱ-ብረት ስሚሸተው ወደያው ይጠነቀቃል። ጀግና ወንድና አንበሳም ተከባብረው ይተሳሰፋሉ። እንዴት አደርክ ወንዱ! ስንለው በለዘበ ቃል፤ አንበሳውም የመልሱን ተጉሳም ያልፋል። ሰው ካልተጣለው አይጣላም፤ የቃልኪዳን ነገር ሆኖ ይመስለኛል አንበሳ የጦቢያ ሰው ስጋ አይበላም። የተጣላውን በመዳፉ ክርኑ ገድሉና የትንፋሽ ቅርታውን ግቶም አረጋግጦ እያገሰ ትቶት ይሄዳል። የወሸው በሽታ የያዘውና በስርቆት ጊዜ ጥቃቱ የደረሰበት ግን ምንጊዜም አብድ ነው፤ ሰው በልቶ ይሆናል። ሰውም ቢሆን በቅንዝርና ተነክቶ አእምሮው ከሳተ ያንበሳው አብደት ይታይበታል። ብቻ፤ የጨዋታሽ እናት ንቀት ነው። እንደምትናቀቁት በመሳ ነው የምትዋረት። ደብተራው አይደል ያንበሳ ጋግ ሸልተሽ ነይ ያላት! ጋግውን እንደሸለተቸ ሸልታ እምጥታለት

አላመሰገናትም፤

'በጣም ሞኝ ነሽ፤

ሂጅ ወደባልሽ፤

የማታስል ሙሳ እንዲያ ከጠጪሽ

ከንበሳው በላቀ ታስተኝዋለሽ ነው የሳቅ። በዚህ በኩል አልስደኝም። ሴትን በጣም አከብራስ ዝንጀሮ - የማይንቅ። አይደል? እቴ አበባ።»

የነበበች ደምፅ እልም አለ። ፈገግታ የመፍጠር አይነት ከንፈራቸውን ቢያሸራምሙትም በልክ ፈገግታ አልፈጠረላቸውም፤ አይናቸውን ወደወለሉ ጠልሰው ፊታቸው ተዘና። «... በማይቶንጥጠው ጨዋታ እየገባህ መች የምታጫወተኝ ሆንክና! ተጧጋች አባቅ የፈጠረሄ ነፍሱን ይማርና አየዋ (አባታቸውን) እንዲህ፣ እንዳንተ መግቅ አቤት! ብሎ የጠግለት ነበር። እሱ ግን የተጀመረ ጨዋታ አስከልቶ ነበር የራሱን ንባብ የሚያወርደው፤ እንተን የጉደለህ ጨዋታ አለማስከለቱ ብቻ ነው።» አሉ።

እህታቸው በተረታሁ ባይነት ይበሰውኑን በተበጀ ባይ ያልነበረ ኩራት ሜነባቸው። ከመቀመጫቸው እንደመነቃነቅ አሰኛቸው፤ «እንዲያ እንጂ! የንዴትሽን አግረኛ ወደጉን ተይ! በይ መቸም እንዳሸሽ ቀጥይ! ከጨወትሽ እናት ድረሽ፤ ፈርጅ የያዘ ጨዋታን የመሰለ የለም፤ እንችም የተያዝሽው ፈርጅ ስተሽ ነውና፤ በጥፋት ረገድ አልተጠጠንም።»

«ወይ አምላክ እስራኤል፤ ነበልባል መሆን! መልካም፤ በየት ግድም ነው የቆምኩ? የባልቴት ነገር!»

«በከረዳው እንጨት ለታሚ ግድም» አሉ ተበጅ፤ አንድ ቀን የእንስታይ ፆታ ግስ ከነእርበታው ብሉም ቅፅል በተባእታይ እንጂ በደንቡ ጠርተው አያውቁም፤ ሴቱ፤ ወንዱ፣ ባልቴቱ፣ ከረዳው.. እንዲህ እያሉ ነው የሚቀጥሉትና በታረመ ሰዋሰዋቸው የተማመኑት እህታቸው፤ «ይህ ጊደርና ወይፈን አዲብሎ ጥሪህ እኮ ብልግና ነው፤ ብታቆም ይሻልሀል፤ አለዚያ እኽ፤ ወዮልህ!»

«በይግ፤ ጨዋታሽን ቀጥይ፤ ምን ልደረግ ኑሯል? ሴትና ወንድ እኩል ከተባለበት አገር መስሎኝ የመጣሽው፤ በሌላው እኩል እንሁን፤ እንደገና ሴት ብላቸሁ ጥረን ምን አይነት ነው! በይግ!»

«ተጧጋች አሽከር ነህ አለኸኝ። እፃ! የመዳፈንና የጨቅልነቱን ዙረን እናየዋለን። ይህች እንጨት ሰባሪዋ ሴት፤ መጀመሪያ የተገኘውን እንሰሳታና ሰባሰባ በማጋመሻው ጊዜ ስራ ይቶግል። ጡትጡቷን መተያየት፣ የክረመብትን የናፍቆትና የስስት ጨዋታ ስታነሳና ስትጥል የዘፈን ግጥሞሽ ይመጧል። እንዷ እቶንቃኝ ትሆንና ሌላ-ሌላዋ ተቀባይ-ተቀባይ ትሆናለች፤ እንጨቱ

እየተሰበረ - እየተሰበሰበ፤ እየተጀመረ እየተተወ፤ እስክስታው በንድ ላይም ሆነ በየፊናው እየቀለጠ፤ የቃል መትረያና ጥና መሰልጠኛ በታም ዱር ይሆናል። የእውነት እንቅስቃሴህን የምትተያይበት ምቹ ቦታ ያ ብቻ ነው ብለህልና ይሁን! ልክ ጨዋወትሀል። እንደዚህ አገር ማግሸ የቤትህን ግድግዳ የሚጥሰ መስተዋት መቢያም ቢኖር ጥሮ እንጨት ልልተም የምትል ሴት አትገኝም ነበር። ግን በመቢያ የሰው መስተዋቱ ሰው፤ መተያያው ዱር ነው።

«ከጀመራ አዘብቾው ነው እንጂ ነገር መሸከፍ፤ በመግ ማስተመተ ወደ ሂላ ቀረ፤ ወይኔቱ ልጅታ! አ ኔ ን! አይ ወዲያ! ቢንፋን በንሸገር የቀረ፤ ወደ ሂላ የተተወ ጊዝ አናስተህ ልቢ ይሸፍት ጀመረ። አሺልህ! እንግዲህ፤ የወንድና የእንጨት ሰበሪዋ ሴት የዘፈን አቅም መፈተሻው ዱር ነው ተብብሎን የለ? አለችኝ»

«እንዴታ፤ እያ ብለሻል!»

«በመሰሪያ ገዋ የሄድክ እንደሆነ ማብጀት በጠቅላላ የወንድ ነው ገልጥ ነገር። የሚበዛው ክበሮ መች የቤት ገጥ ቢሆንም ልጉግ የወንድ ነው። ማሲንቆው፤ ክራሩ፤ ጥሪምባው፤ ነብር ጌታቹ፣ ወተቴ አዳንዛዝና ሰውን እማሹ ጭሸንት፤ እረ ምን ቅጡ ዘረዘረ እየቀረ ሄደእንጀ እምቢልታውና መለከቱ ሁሉ ያንዣብበል። የሰው ልጅ በነሲብበነሲብ የጠዋት እድልና ችሎት አለው። የጠገበ ጭሸንት አቅርበህ ንፋ ብትለው የማይሆንለት ብዙ ሲሆን፤ በሰበራው፣ በስንጣቃው፣ በአንከሳውና በጉግዳው ሸምበቆ አለብደ የሚጫወትም አለ። ልምድ ነው፤ ... የመልመድም ብቻ አይደለም፤ በፍ እስትንፋስ ቶቶ በፍንጫው ነፍቶ በጭሸንት የሚዘፍን ጉብል ብዙ ነው። ታዲያ እንደሰጦታው የፊተኛውን የዘፈን ቅሪት እያስቀደመ፤ ሲሰምርለት ከራሱ ሌላ ይመነጫል። ዘፈን በዱር ይሉሀል ያ ነው።

«ዱሬ ሰው የሌለበት፤

ምቹ ለጨዋታና ለብዶት። » ይላል መዘናት የሚወደው ሰው። »

«እቴ አበባ አሁን የገባሽው ወደወንድ ጉዳይ፤ ቀደም የወራሁት መሰሉኝ! የሴቱን በኩል ቀጥይ»

«አቃርመህና አልክስክስህ የነካካኸውን አጠራሁልህ፤ መለቀም ነውር ሆነ? በሌላ አንጣር "ማርጀት ጨቅላነት ነው" ብለህልና የሱ ቶሎም ይሆናል። ገመና መሸሸግ አይሆንልህ እየልኝ!»

«እት አበባ ሆድ ሆዱን በላሽው፤ ገና እምበሳ አይደለሽ፤ የሰጠውን አይንሰ፤ ያስንብትልን፤ አንችንግ ስከፋሽ አባይ በደፍኑ ይታረስ!»

«እምበሳስ ምን ያውቃል? በዚያው ደግሞ የበቶከው አባይ

ይታረስ ሰቶል... የጨዋታህ ብዘት፤ ግብጥና ሱዳን ተጥለቅልቆ እንዲፈታ ነው በሞቴ?»

«በደፍኑእኮ ነው ይታረስ ያልኩት! እት አበባ!»

«እሁን ደህና ደፋህ፤ በጣም ተጫወትክ!... በቤት ገጥ ሰትመጣ፤ የገርተከፈ ግድም ቤት ጥና መልመጃ ክበሮ ነው። ሲሆን-ሲሆን፤ ግድው የሸና ወሀ የሚወርድበት ኑሮ ይሆናል፤ የተልባና ኑግ ጭልቃ ማሽውን ገበታም ሆነ ፋጋ ታነሳና ከገደቦቹው ቅንጨ ባሀር ላይ ባፉ ደፍታ ሲላዋ አቻቷ ሁሉ እየተራዳቻቱ የእንብርክኩን፤ እ ደ ደ ም፤ እ ድ ድ ም፤ ሀ ድ ድም! ያደረገቸው ጊዜ ከገበታው እንጨትና ከወሀው የሚሰራረተው ድምፅ በመልስ፤ እንደንደህ፤ እ-ዱ-ዱ፤ እ- ሁ እ-ዱ፣ ድሪምግም፤ ዱሩኛ፤ ዱሩኛ፣ እንጃበሀ፣ እንጃበሀ! ሲልና በክበሮም ሰድብ ሲታወርድ ልብ ይሸቅላል። ጨብጫቢ ስልት እያገባ የከመረ ጊዜ ክበሮ እንሽ ወይም ሌላዋ የዘፋኝ ዘር የሆንች ኑሯ ይሆናል፤

እሽ በል ገዳያ ቅላለች፤ ተቀበ ዩዋ፤ እህ! ገዳያ! ሰቅልላቱ፤

"ኸላ ጉረመረመ አይበላም ነብር፤

እንደመቀነቴ በሸንጥህ ልዘር" ብላልህ እርፍ! ሲሉ የሰማች ሁና ይሆናል እንጂ፤ የወንድና የቤት ነገር ከምንም ያልተረዳችና ያልበለቀች ልቷሆን ትችላለች። በእንደህ አይነትና ይህን በመሰለው ጀምራ ድምፂን ስታነሳ- ስትጥለው፤ ስትሰብረውና ስትመልሰው ከቀረው የጨዋታዋ አይነት ጋር ተዳምሮ ሁሉንም ልዩ ወኔ ይጫናቸዋል። ፍጥረት በሰርግ የተሞላ መሰሉ ቀጭ ይላል። እስክስተኛዋ ቤት እያፈረች፤ መልስ ድፍረት ገዛሁ እያለች፤ እየተቅለሰለሰችም አለም ያልፋል።

«የቤት መጉበበል ሲመጣ ከውስጥ የሚገፋፋ ነገር አለው፤ አስቀድሞ ጡትሽን ደብቂ-ደብቂ ያሰኛል። ከሰው ጋር ሲሆኑ ብቻ አይደለም፤ ከበደ ሜዳ እንዲያ መሆን ያሰኛል። ከእቻ ጋር የሆኑ ጊዜ፤ ገልጦ እይቶ፣ እንዳገና ትግን፣ መልሰ ጉንፏን ልብስ፤ እንዲያ፣ እንዲያ ያደርጋል። ጡቱ ወጥቶ አልክመርና አላ ጉጠንጥ ያለ እንደሆነ ደግሞ ተያይዞ ወደወንዝም ሆነ ፈፋ ይወረዳል። ከዚያማ የውሀ-እናት ለሴት ልጅ ቃል ኪዳን የተፈጠረች ናትና ክንፍና ክንፏን ተረግጦ፣ እንደንትንራፈር ትይዝና ከጡቱ ጫፍ ላይ አፏን ስግታ የነዳደፈቻት ጊዜ ጡትን አጉጥጉጥ፣ አደግ፣ ተመንደግ ትለዋለች። በቤት መስየ እወጋሁት እንጂ... በጨወት እንዳልቶነጥጣችሁ እንጂ፤ ከባብሉም ቢሆን ደረቱ ማበጥ የጀመረ ጊዜ ጡቱን በውሀ-እናት ያስነክሰዋል። አንተስ ብትሆን ግሬራ ይዘህ የውሀ-እናት ልታነሳ ተከዜ ሰትወርድ ቀርተህል ይባል ይሆን? እነሆ ከደኝ- አለችኝ?» ሲሉ፤ "የልቡን የነገረት የሰለክሉትን

ያሁል ይለቃል" እንዳሉ እያ ተበጀ ብቻ ባይሆኑ አብዛኛው ሰው ሳቀሳቸው።

«እንዲያ እንጂ፤ የሁቅ ጨዋታ ሁቅ ኑው። አገር አውክቶ ተሰማግማልኝ። የዛሬን ማየሊያው ያ ግድም እድሜ ነው። አሁን የምናወራበት ሁሉ ከወፍጮ መንጠልጠል ከጆመሮች ቀይታ የሌ? ወፍጮው ሌላ የዛሬን መረጠሪያ ነው። ወላጅ ከመዳረ ዘገየገየ ሲሉ... መቸም የአገር ደንብ እንዳንዱ መላው ምጣቅ ነው፤ አበትየው የእክሲን ዘር ሲል፤ እናቲቱ ወቃቢየ እልወደደውም ብላ ስትመለስ፤ ጋሜዋ በመሀል ትደየናለች። እንዲያ ሲሆን የአቤቱታ መዝረፊዋ ወፍጮ፤ መደርደሪዋ ዛሬን ነው፤

"ጡቴ እንጠንጠ አበበ ሊያወጣ፤
ተው አባቴ ዳረኝ እመል ሳላወጣ"

መልስ ሌላ፣ ደግግ ሌላ ዳር-ዳር፤ ከፊት ቀንጆ ያወጣውን ግተም መነሽ አድርጋ፤ የወፍጮው ከመጆ ስምሪት ሲሰላና ዜማው ልክ ሲመጣ፤ ዱቄቱ ከቷቶ እየወረደ ሲታከብ የራሷን ደራሽ ግተም ከላይ-ከላይ እየጣለች ስራው ሲያልቅ እናቷ ሌላ የሚጨመር፤ ለመሰንበቻው እንዲሆን አንድ ድርጉ ጤፍ የለም? ያሰኛታል፤ ያላነሳቻውንና ያላሰሰችውን አለም ቀርታ ለመጨረስ እንዲያመቻት!

«ሁሉም በየፊናው ዛሬን ለምዶ የሌ? መገናኛውና መፈታተኛው ጉዳይ ነው። ቀን የደረሰላት፤ ቀን የደረሰበት ቢሉም ልክ ይሆናል። ወይም ለጡት የቷመጠው ከበሉ ይሁንና፤ ዳስ ይጣላል። የጉድ መፍያው ጊዜ ያኔ ነው። መቀነትና ቡሬ መሰኪያው ቀን ይለሀል ያ ነው። ሲቅሲቷ እንደየደረጃዋ፤ ያላገባችው በጋሜና በሳዱላ፣ ለወንድ የደረሰችውና ያገባችው በመሉ ጉፈረ ቅሆንና በመነከኪያው ነክታውና አበጣጥራው፤ አደሱና ቅቤው፣ እንዲያው ለይስመላው ነቁንቨ ተብሉና ለፀጉሯ ውበት ሰጥቶት፤ የነጠረውና የተቀመመው ኩል የአይኗን ከናፍርት አስምሮትና ከመሀል ላይ የጠራው ዘጌላዋ ወዲያ-ወዲህ ፍጥረት እየፈለገ ስትባዝን፤ በሌላ ገጥ ከማማቢሯ ግድም አሊያም ወረድ ብለህ ወደሸንጉቢቷ፣ ለአይነ-ስቡ መመለሻ ምልክት እንዲያወል የተሰራ ጊጥ የምታውልም አለች። ያንዳንዷ ልጃገረድ ፍጥረት የተለየ ይሆናል። የውበት እጅን ብቻ ከልቶባት በላይዋ ላይ ጥራቱን ሲደፋበት፤ ለአይነ-ወጊ የማስ መድሀኒት መላውና ጭንቀት የሷ ፈንታ ይሆናል፤ ብዙ ነው። የዳዊት ምልክት (የዳዊት ኮከብ) የመጣው አሁን ነው፤ መስቀሉን፣ የጨረቃ ምልክቱን፣ ሌላም የስእሊው እጅ እንደሄደላት ከማግባር ላይ - ለፊቅ ውበት፣ በእጇ ግድም ለጣት እጥታጥቅ መለያ ውበት፣ በእግሯም ሲሆን ለተረከዝ የውበት

መጨመሪያ፣ ለጥፍር አጣጣልና ለጣት አወዳደቅ ሁሉ አይነ-ወጊውን ወግድ የሚከለከል እንዳንገት ውቅራት የሚሰል ነገር ሞልቷል።

«የስእሉ መላ፣ አይን ወርዋሪውን ሰው ሁሉ በፊቅሀ ውበት ላይ እንዳይባዝንና አይኑ ከስእሉ ላይ እንዲወጋ ለማድረግ ነው። እግረ መንገዱን፣ የእጅስራው አጣጣል ውበት የሚሆነው አለ። ግና ለሁሉም አይሆንም፤ እንዳንዱ ሆን ተብሉ የውበት ማበላሽ ነው። በጦቢያ አውቶም ውበት ያበላሿል፤ እንዴት ማለት፤ አሁን ከፊቅሀ ላይ ጉድፍ ቢያርፍ የሰው አይን እህ! ብሉ የሚወድቀውና ማስተዋል የሚያበዛው ከጉድፉ ላይ እንጂ ከፈጣጠርህ ላይ አይደለም። ያባሉትን የሚባዝነው ጉድፉን ለማንሳት ነው። ያንዳንዱ ውቅራት መላም ይህን ከመሰበም ነው። ወዳንገት ግድም ስትሄድ ደግሞ በግልጥ የታወቀው፣ እንዲያው እንደመጠሀፍ ቅሸራ የሚሰራበት ውበት አለ። የጨዋታው ግተም ብቻ ይበቃል፤

"እንገቷን ብናየው ተጥፏል ስንክሳር፤

እንባለሁ ብሉ ወይ የገባው እሰር" ብሏል ያጠገቡን ሰው መቸገር የታዘበ ግተም አውራጅ። የጥርስ ውቅራቱ ድድን የመሸከፍ ብሎም ቁርጥማት ያለበት ይህን የመቀነሽ መላ ነው። ሴት በድፍን፣ ወንድ ጉራማይሌ ይነቀሳል። ተመልሶ ታዲያ ውበት ነው። መቸም ወደደጅ የመውጫውን ስልት ሁሉ ታውቀዋለህ፤ የቤት መጨነቂያዋ ኪነት ብዙ ነው። በጥልፍ ቀሚስ፣ በሞራው ነጠላ፣ ወንዱ ደግሞ በእጀጠባቡና በቡታንታው ተከፍሶ መከፈፈያውን የጠጉር ሸሽ የሚያባለው ያባልና እንእያ ከበሮ ለድየና ይቀርቧሉ። ዳንኪራው፤ ጂሉታውና ፉክራው በወንድ ገጥ፤ ከበሮና ጭብጨባ ከስልት ማጋቢት ጋር በሴት በኩል እየገነነ፣ በታል ቅንቀናውም እያስነከቸው፤

የኔ አበባ አበባ፤

የኔ አበባ አበባ ስትል እንዷ፤ ተቀባዩ እየመለሰ የኔ አበባ! ይላታል። የልቧ መሻቀል ክልክ ያለፈ ይሆናል።

የኔ ሬበባ አበባ
አበባው አበበ- የኔ አበባ!
ንቡ ገባልሁ የኔ አበባ!
እንግዲህ የአገር ልጅ- የኔ አበባ!

ግር ቅብባለሁ የኔ አበባ። ታብኛለች። የታሉን መታጠፊያና የደምቡን መዘወሪያ በደንብ ቀኝታ፤ የወንዱ መታመም ይተከና በምላሹ፤

የኔ አበባ፣ አበባ- የኔ አበባ!

የኔ አበባ አለችኝ- የኔ አበባ!
የኔ አበባደስ እሷ- የኔ አበባ!

እየጠቃቀሰች በእይንና በጥርሷ-- የኔ አበባ ያለት ጊዜ ለሰኛዋ መልሳ ሌላ፤ ወንዱ በመልስ ሌላ! ያለ ጊዜ በዳሱ የተበላው ፍጥረት ሰው፣ ጋኑ፣ ድስቱ፣ ጀንዲው፣ ጥንጫው፣ ገንቦውና ሌላውም የዳስ ቅራቅምብ ባንድ ገጥ፤ ከበቢውን የተጠጋው አእዋፍና ተባራሪ ፍጥረትም ሁነ ዜማ የሰበው አራዊት በሌላ ገጥ፣ እፅዋቱና የቤት እንስሳና ሌላም ለሰው የማይከሰት፣ ዉለግ የለበሰም ይኖራል፤ የከበባቢው በድን (ግኡዝ) ፍጥረት ነፍስ ገዝቶ ፤ ይህ ሁሉ ተጠቃሎ ፍቅርን እሽ ብሉ ይቀበልና ማበራታት እድሜ የጥጠ ይሆንና ዛፉ ሁሉ ከከበሮው ጋር አብሮ የዘፈን እየመሰለ፤ ቅጠሉ ከላይ ከላይ እየረገፈ፣ በታች አቧራው እየጠሰና እየተነሳ፣ እንዷ እልልል! ያለችው ጊዜ መነኩሴው ከምርኩዙ ጋር ሳይቀር ይቀላል። አለም ዘመንችና ዘፈንች የምትሰውም ያኔ ነው። ደህና ተጫወትኩ? አለኸኝ!»

«በ-ጣ- ግ! ወጣልሽ እንጂ! እንዴት የታያዝሽና የተነካሽ ኑረሽል በሞቴ?!...»

በቀል

ያያ ተብጀንና የነበበችን ጨዋታ ከልተን፣ የዛር ዳንስ ጥናቱ ሳይበክ ናዝሬትን ጠዋትን ለቀቅነው። ምሽትን ለሌላ ተተኪ ተግባር ተያየሁት። አንድ ስምንኛ ወዳጀ የናቱን ሞት ተረድቶ የሀዝን ጉዝጓዝ ከጠለ ሰንብቷል። ሁለታችንም የምንቀርበው ሰው ነበረና የሞት ነገር ነገም ለኔ ከሚል ልምድ፤ ብሉም በጊዜ ለመድረስ ከወረደብኝ ደከም ሳልወጣ፣ ከየረባሌም ወደቴልአቢብ መውረድ ታየኝ። ከጋዜጠኛውና ዳንሰኛዋ ምርምር እስተርጊሚንት የተቀበልኩት ራስ ምታት ወደእኪል መዛል አዘውሮኛል። ይህ ያሁኑ ሁኔታየ እንዳለ ሁኖ፤ ጋዜጠኛው በተለየኝ ጊዜ አብረው ሳጠፋሁት ጊዜ "ማከከሽ" የሆነ የእንግሊዞች ሥውንድ አሰፈርኖ ሰጥቶኛል።

ጓዛውን ጨርሰን ቴልአቢብ ያውቶቡስ ማራገፊያ ወረድን። ጊዜው አየከዳ በመምጣቱና ያውቶቡሱ መስመር እንዳይዘጋ ብሉም ታክሲ ከመከራየትና ብዙ ገንዘብ ከመክፈል ለመዳን ፕድፊያችን ልዩ ሆነ። አጋጣሚ ሆነና ወደራማት አቢብ የሚጓዘው አውቶቡስ ሊንቀሳቀስ የመሄድ ርቾትን (ጠፍቶ የነበረው መብራት እልም-ድርገም ሲል) ሲሰጥ አይኔ ከረቅ ስለያዘው፤ «ቶሰጆዋለሽ!

አውቶቡሱ አመለጠልሽ ያው! ታይዋለሽ? ያ መብራት የሚያርገበግበው መኪና፤ ወደሀዝን ቤት የሚወስደን አውቶቡስ ነው።» ስላት እሷ በረጫው አየለች። እንዳመርጥ፣ እንዳማከብበም እየደበሳለችሁ ተከተልኪት። ከራስ ምታቴ የተነሳ እንደሷ መሮጡ የሚየጣልኝ አልሆነም።

መግቢያው በር ደርሳ ከፊቷ የቆሙ ሰዎች እስኪሳፈሩ ሳንቲም ልታወጣ ስትታገል እኔም ደህና ተደረብኪት። እንገቷን ወደምበበው መብራት ጠንን፣ የሸንጥ ሸንጠጥን ወደመብራት ገዳል አድርጋ ደሀን ከገራ ጉኗ ተወሽቶ የጥለ የሴት ቅራቅምብ መያዣ ከፈዳ በመበርበር ተቸገረች። ሁለተኛ መክፈሏ አልታየኝም ነበረና (ቀደም ለታክሲው ከራይ የከፈለችው እሷ ስለነበረች)፤

«ዝርዝርአክ ነጂው ይይዛል፤ ሸርፍ የለኝም ቢል ያኔ ትገቢያለሽ፤ መጀመሪያ ግን እንሞክረው!» አልኪት። መልስ \ አልሰጠችኝም። መልስ ባለመስጠቷ ትንሽ ግር አለኝ፤

«ይህች አመሏ የማይታወቅ... ምን ነካት? እኩል ባለመሮጣ ወይስ የኔን ገንዘብ ናቀችው? መጠየቂ ግን ነውር ሊሆን ይችላል?... » አልኩ በሰከንዶች እእምሮየ ላይ የረገፈ ማሰላሰል። ጥገሹ ውስጠ-ሀሜት እንደነበረም አላጣሁትም፤ ግና፤ ያኔ ያልታየኝ ጉዳይ ነውና እንዲያ በከፊል አግኟት። የጀ ከሸንጣዋ ውስጥ ተዘፍቶ መጥፊን የተረጎምኩት በሆነ ተመክሮ ነበር፤ እንዳንድ ሰወች ገንዘብ ለሰው አይን አስጥተው ስለማይቶጥሩ፣ የነዚያ አይነትም ሁና ታየችኝ፤ በታው ጨለምባግ ነበር። ያን ያህል ዘግታኝ፤ እንገቴቷን ወደኔ መለስ፣ አይኗን ከይኔ ላይ ወርወር፣ እጆቿ እሸንጣው ውስጥ ተገታትረው ምገድ እንዳሉ፤ «የገንዘብ ሰረጢቴ!» አለች፤ በጣም ስብከ ያለ የቃል አወራወር ከመሆኑ ሌላ በጣም መቅቅና ብርድ ያለ ነበር። ከወቅሿት ጊዜ ጀምሮ፣ እንዲህ ያለ የተቀናና ለስላሳነት የፈሰሰበት የድምፅ ዜማ ሰምግላት የመጀመሪያየ ነበር። ጀምራ ለወዘፈችው ቃል ማጠሪያ፤ «እናስ? ሰረጢትሽ ምን ሆነ?» ስል መልስ አልሰጠችም። አንድ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መልስ ስትነባኝ ሁለተኛዋ ሆነ። በዚህ ጊዜ እንደፈተኛው እእምሮየ የሆነ ነገር ፍተሻ አልሄደም። ዝም ብየ "አመልና ጭራ ወደሂሳ ነው።" ይህ አንዳንዱ መልስ አለመስጠት አመሏ ሊሆን ይችላል፤ ከመለግመድ መክሰት የጀመረ። ለሁሉም ስንብሾ ልየው ጠበቅኒት። ጉርጉራዋ ቀጠለ። በርግጥ፣ ጥሏ የሆነ ነገር ይዘኝና ገርገርኝ ነውእንጂ ለጠየኩት የመልስ ምት እንደነበረ በጣም ግልፅ ነበር። መገረም ውስጡ ሀኪናየን እየቅቅቶት፤ «ሰረጢትሽን ሳውቀው የቅራቅምብ መአት እንደቅርሻ-ቅርስ ማህደር የተሰበሰበት ሲሆን በጣም ያበጠ ነው።

የምትፈልጊው ያንን ከሆነ፤ መደበስበስሽ አልገባኝም!» አልኩ። ደግሜ ደጋግሜ፤ «ኧ! ኧ ኧ... ማለቴ...ኧ ኧ!» ስትል፤ «ማለትሽ"» አልኳት።

«ኧ ኧ! ምናልባት ያዘው ብየ ሰጥቼህ ይሆን? ካልሆን ሁሉ እየው!» ስትል የሆነ ነገር የኤሌክትሪክ ንዝረት በእምሮየ ውስጥ ተመመ። በርብሬኝ ልላት ቃጥቶኝ ከምላሴ እናት ላይ ቀረ። ያንን ስቢ በምትኩ፤ «ያን ያክል ፎደር የሚይዝ ኪስ ያለው ልብስ በህይወቴ ለብሼም አላውቅ፤ አትልፊ፤... ከታክሲው ላይ ቀርቶ መሆን አለበት።»

ልንወጣበት የነበረው አውቶቡስ እንደገተረን ሹፌረ ደጋግሞ እየተጣነን ከተመለከተን በኋላ አስቀበከበው። የሚቀጥለው እርምጃ ታክሲው ወደቆመበት ሳይሆን ወዳራገፈን መሄድ ነበረና ወደዚያው አመራን። መራመድ ከልሆን እስከሆን ለመናገር እንደቻበባት ነው። ስንቃረብ፤ «ሲማሽ? ለታክሲ ስምሪት አስተባባሪ ከነገርሽው ገንዘቡ አይገኝም፤ ሰውየው እስኪመጣ እንጠብቀው፤ መጥቶ ሲቆም፣ ያለ ፈቃዱ ዘሎ ገብቶ ወድቋል ከምትይበት ከባቢ ተደምንመዋ፤ ከተገኘ አንስቶ መውጣት ነው፡ ካልተነገረው ጨለማ በመሆኑ የሂሳውን መቀመጫ አያየውም፡ የጣልነውን ብድግ አድርገን መውጣት ነው።»

«ምን ታውቃለህና ነው? ያመጣን ታክሲ በሄደበት ሊያድር ይችል የለ? ስለሆነም ገንዘቤን ተሳፋሪ ወስደው ማለት አይደል?»

አደብ የገዛ ጨዋታ ጀመረች፤ የምቀኝነቷ አይነት አለው፡ ገዴት የያዘት ተሳፋሪው ብቻ እንደሚወስደው ሲሆን ባለታክሲውን ግን ፍፁም በሀታዊ አድርጋ ተመለከተችው። «ሄይ! ስሚ! ባለታክሲው እየረሳለሚ ነው፤ የሄደው የየዲዮት አሀሮዋት ጋዜጣ አምደኛ የሰጠውን ጥራዝ ሊያደርስ ነው፤ (መሀል መንገዱ ላይ በመገናኛ መሳሪያቸው ሲቀባበሉት የሰማሁት ዜና ነበረ) ቢሮው በጣም ቅርብ ነው፤ ስለሆነም የሌሊቱ የመልስ መስመረኛ (ወደየረሳሌም) ስለሆነ በሮ ሲመጣ አስር ደቂቃ አይፈጀበትም። ገንዘቡን ካገኘ ግን ሀሳቡን ሊቀይር ይችላል፤ ምን አለፋው፤ ቤቱን ገብቶ ነው ለጥ የሚልልሽ። ለመሆኑ ምን ያህል ገንዘብ ይሆናል ከጠፋሽ የወረት መሳሜ ጋር የሄደው?» ከመልሷ በፊት በጣም ተረግጣ ተነፈሰች፤

«ብነግርህ በጣም ታዝናለህ!»

«ስትነግሪኝ የሚያልፍኝ ነገር ነው እንዴ?

«እሱስ እውነትክን ነው፤ በጣም ያሳዝናል፤ ወደሲበር ጥል ከምመለስበት ቲኬት ጋር እስከሆን ለገባሁት እዳ ማዕጃ እናቴ የላከችልኝ ገንዘብ... በቸክ ብትልክልኝ ዋር አይጠፋም ነበረ፤

በእግረኛ ሰው ልክ ው፣ ተቀብየ እንደከተትኩት፤ ከንተው ስማንያ ፖውንድ ጋር ተደምሮ ነው የጠፋው።» አለች። ጥያቄየን ግን ሞልታ አልመለሰችውም።

«እናስ፣ ስንት ገንዘብ ነው የምትይው?»

«የኔውን አይደል የምትለኝ፤ ስምንት መቶ ያሜሪከን ብር ይበልጥ ይሆናል አልቆጠርኩትም።»

የስምሪት መሪውን ጌጃ እንደቀረብነው ተንደርድሬ ተጠጋቸው፤ «አሁን፣ ስስት ደቂቃ ይሆናል፣ ከየሩሳሌም የገባው ታክሲ ሰውየውን ታውቀዋለህ? ወዴት ደረሰ?»

«የታክሲውን ቁጥር ይዘሽዋል?»

«የለም።»

«የሹፌረ ስም ግን ይባላል?» ሲላት፤ ወደኔ ዞረችና «ታውቀዋለህ? ክንዴ» ስትል፤ «የሰውየውን ስም እንኳ መጥራት ሌላ እዳ ውስጥ የሚጨምረኝ ይሆናል፤ ነገር ግን በርግጥ ይህ አስማሬ ያዝኛል ብለሽ ከመንሽ የታክሲው የመገናኛ የምስጢር ቁጥር ስድስት ነበር።» አልኩ። በተርበተበተ አነጋገር ስትለከሰው የመገናኛ መሳሪያውን የቃል ማንጠሪያ አደብ ገዝቶ ጨበጠው፤

«ስምን ፈልጋህ ነው ልበልልሽ?»

«የገንዘብ ቦረጢቴን ይዞ በ ረል።»

«ዝርፊያ ነው ወይስ ወድቆብኝ ነው የምትይው?»

«ሸልኮ ወድቆብኝ ነው።»

«ገንዘብ አለበት ወይስ ከረጢት ብቻ ነው?»

«ከስድስት መቶ ያሜሪከን ብር በላይ።» ስትል መልሶ ሌላ ነገር አልጠየቃትም፤ ደግሞ ደጋግሞ ጠራውና ሲመልስለት፤

«ከመቀመጫህ ጀርባ የተቀመጠች ልጃገረድ ጥቂት አረንጓዴውቹን (ዶላር ማለቱ ነው) የያዘ ቦረጢት ጥያለሁና እንባልኝ ትልሀለች። ካረጋገጥክ በኋላ ጥራኝ፤ ሳሁኑ ግን ሌላ ሰው ከመስመር ላይ እየጠበቀኝ ስለሆነ ወጣሁ።» አለውና ፀጥታ ሆነ።

ይኸኔ የገንዘብሽ መገኛ አክትሟል ብላት በወደድኩ ነበር፤ ግና መሰሉ የሚታያትን ሁሉ ነገር አድክማ ስለልጨረሰች አጥቂሬ ነህ እንዳትለኝ ፈራሁና ሁሉም ነገር ዝም ብቻ ሆነ። የዘገጠውን ያህል ዘግጦ «እንኳን የወደቀ ቦረጢት ቁርቶ የቀለፍ መያዣም አላገኘሁም» ሲል እንደያው ፈጦ ከዋለው አይኗ ውሀ ይጉርፍ ጀመር። የንባዋን ያለቅጥ መፍሰስ የተመለከተ ሌላ ከቅርቧ የቆመ ሰው፤

«ከማልቀስ ይልቅ የባለታክሲውን ቁጥር ተቀብለሽ ጣቢያ መሄዱ ይጠቅምሻል።» አላት። ተገቢ ጥቆማ ቢሆንም፤ በኔ በኩል

ግን እንዲያ ከማለቱ በፊት ጉሮሮውን ቢዘጋው ከመውጣት መውረዱ እድን እንደነበረ የማውቀው ሁኔታ ነበር። እንበየ ድርቅ እለና ሌላ የተስፋ ማእበል በሰራአከላቷ ተንሰራፋ።

ይህ ባለታክሲ ዳግም ሊጠነጠንበት የሚችለውን ሁኔታ በቅርብ ከመከታተል አንፃር ከተፍ አለ። ታክሲውን ግን አስይዞ አዳግሚችን ሆነ። ፖሊስ ጣቢያ መድረሻውን መንገድ ስታስብ፤ «ብቻችን ጣቢያ ወርደን የምናገኘው ምን ነገር አለ? ባለታክሲውን ጨምረን መውሰድ አለብን።» አለች።

«ፖሊስ ጣቢያ መሄዱን እንደፈለግሽ፤ ግን ሰውየውእኮ ገና ወንጀለኛ አይደለም፤ ደግሞም የከተማ ክልል መስመረኛ ስላልሆነ ወስደን ማሰተም አይሰራም፤ እንቺ የሚኖርብሽ ዝርዝር ሁኔታውን መመዝገብና ለፖሊስ ማመልከት ነው፤ ከዚህ ውጭ ልታደርጊው የምትችይው ህጋዊ መንፋት ሊኖር አይችልም።»

«ሰውየውን እልበ ጣቢያ ጦቅ ልበል እንጂ አል ሄድም።»

«እንዲያ ከሆነ፤ ሰውየውን ማናገር አትችይም፤ ፖሊስ ጥሬና ይሆን ሰው ፖሊስ ጣቢያ አዳርሰኝ በይ»

የቴል አቢብን 'ተሀና መርከዚቅ' የሚሞሉት እነሱ ናቸውና ተንደርድሬ ፖሊስ ጉትታ ስትመጣ ጊዜ አልፈጀብንም። ለባለታክሲው ሁለተኛ ወፍራም ገቢያ ተከፈተለት። በከተማ ክልሉ ስነ-ዳንብ መሰረት የርቀት መለኪያ ማትረን ከፈተውና ይርገበገብ ጀመር። ከሶስት ደቂቃ በላይ የማይፈጀውን ጉዞ እስራ እራት ደቂቃ አደረገው። ከየረሰሊም ቴልአቢብ ከከፈለችው፤ ለዚህ እርቀት የከፈለችት ታጠፈ። በብጫ የትራፊክ መብራት የማይገቡ ጥቂትና ከድሚያቸው የገፉ ሰወች ቢሆኑ ነው። በእርግጥ ባለታክሲወች ካልጠመሙና በፈታዳቸው የሚያደርጉት ከሆነ፤ በብጫው የትራፊክ መብራት መቆም ቀርቶ በቀዩም ስንጥቀው የሚያልፉ ብዙ ናቸው፤ ይህኛው ግን የብጫው የመጀመሪያ እልም-ድርግም መብራት ሊዳፈር አልፈለገም። ከሂላው የገተራቸው መኪናወችም ክንዱ ሁለቴ የጮሁበት ሁኔታ ነበር፤ "አውቶ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" እንደሉ አልገደደውም። የማያፈጥብኝ ቢሆን ኑሮ እንደህ ያለ የጥቅም ምሽት ገጥሞህ ያውቃል ወዳጄ? ብየው በወደድኩ ነበር! ግና ፈራሁ፤ እሷ ፊት ያወንታዊ መልስ ቢሰጥ እንደመረጃ ልትጠቀምበት ስለምትችል የሚደግፈው ተረብ አይሆንም።

እሷ ወንጀለኛውን በእጇ በመያዟ ስትራጋ፤ እኔን ውስጥ-እከሌ ከሚፋተገው እእምሮየ በሚዘራው ምትሀት ብዙ በሺተኛ ሀዋሳት ፈጠርኩ። ከሁን ጀምሮ የምከፍለው ወጭ ሁሉ አይሰማትም፤ የሚከፈልበት ነገርም ሊኖር ለመረዳት እትም

የምታገኝበት ሁኔታ በጣም ጊዜ የሚከሳ ጉዳይ ነበር፤ እንደገና ያችን የሪት እናትዋን ሁሉ ብላ የሚያምኗትና አዝነው ሌላ ገንዘብ የሚልከላት ከሆነ።

ሆንና በኔ ላይ ግን በብሶት ላይ ብሶት ይተራመሰብኝ ጀመር። ትስማማ እንደሆን በማለት፤ «ስማሽ የኔ እህት፣ 'ሳለፈ ክረምት ቤት አይሰረም' ይባል ፀፀትን የሚገስፅ ሀበሻ፤ ያጠፋሽውን ዶላር መልሽ አገኘዋለሁ ብለሽ እያለምሽ ከሆነ እንደማይሆን ነው የሚታየኝ፤ በመጀመሪያ፣ የሰራኢሉችን ያህል ዶላርን ያመለከ አታገኝም። በጣም ሰፊ አምልኮት! እናስነብተዋለን የሚሉትን ወረት የሚተብረት በዶላር፤ ያመቱ ባጀታቸውን የሚተምኑት በዶላር፤ መረግረጊያቸውም ሆነ የሲሳይ እፍ መክፈቻቸው ዶላር ሲሆን ሰርተው ከሚያወጡት ሸቂል ይልቅ ተቀልተው የሚያገኙት ዶላርም ይበልጣል። እንቺም ብትሆኝ ያደረግሽው ያን ነው። ሌላውን ተይውና በዚህ እገር በስማቸው የማይጠሩና ቢጠሩቸው ቅስረት ሁነው የሚታዩ ዶላርና እግዚአብሄር ብቻ ናቸው። በብራይስጡ እግዚአብሄርን ሞልተው አይጠሩም፤ ማህሪቃሉ ብቻ እንጂ። በዚህ እይነት ዶላርም ለምለም አረንጓዴ ቅጠሎች (ሀ-የረኪም) ነው ተብሎ የሚጠራው። ፖሊስታይንን ቅኝ የገዛ እንግሊዝ ነበር፤ ያገርሽ ፖውንድ ሳይከበር ዶላር ለምን እንደተመለክ ይገርማል፤ ከሰሞኑ የአሪደር መፈክር አትገነዘቢውም? ሸቂል ቀርቶ ሁሉም ነገር ዶላር ነው።» ስል፤ ሙትት ባለና በዘጊ ድምፁ መዘታ፤

«እውነታቸውን ነው፤ እምስት ሙቶ የእሜሪካን ብርና ሰማንያ የእንግሊዝ ፖውንድ ወደሸቂል ቢመነዘር የስንት ቀን ቀለባቸው ይሆናል!» ስትል ልቢ ጥራሹን ዘገጠ። እርፍ እንግዲህ፤ ዛሬ አልወጣልኝም ብየ ፀጥታ እንደዋጠኝ፤ ታሷን መጀመሪያ መስጠት ያለባት (ከሳሽ) እሷ በመሆኗ ቃል ተቀባዩ ጠራትና እኔና ሹፌሯ የፈረደብንን የዳር-ዳር ጨዋታ ጀመርን። የተሰዋወጥነው ቃል ስላልነበረ ምን ያህል የሷ ሰው መሆኔን ከማወቅም ሆነ ጠቅላላ ሁኔታየን ከመገምገም አንፃር ይሆናልና የተዘና ጨዋታ ጀመረ። ብቻ ብዙ አላስገፋሁትም። የሌላ ጉዳይ ባይሆን ሁለቱ ያስደረብኝ የውስጥ ጥላቻ ስለገፋኝ ጨዋታየ ሰልቶ ሊወርድ አልቻለም። በተራዋ፣ ለፍልፋ ስትወጣ ባለታክሲው ተራውን ሊያደርስ ተጠራ። ተከታዩ ነገር ጨነቀኝ፤ «እንግዲህ ምን ቀረን፤ እንሄድም እንዴ?» አልኩ፤ እሷ የምትለውን ለመስማት ፈልጌ፤ «ሰውየው ከመግባቱ በፊት ለምን አልነገርከኝም? ፖሊሱ ሂጅ ብሉ መቸ አሰናበተኝ። ደግሞም ምን ሊወጣ እንደሚችል ታውቃለህ? ባለ ታክሲውን ከጠየቁት በሂላ ፍንጭ ሊገኝ ይችል ይሆናል፤

አትቸኩል።»

ባለታክሲው ወርዶ ሲወጣ የጠበኩት ስንብት ነበር፤ ተንጠራራሁ፤ በድንገት «በ! ጆንጆ፤» አለኝ ወታደሩ፤ እኔ በብልግናና ምግባር ባነሰው አመለካከት ያየሁትን የሲብ ጠቱ ጥቅሽ እየጠቀሰኝ። ለሱ ሊዋረኝ የሚችለው ክብር መልጭ ብሎ አለተ። ብቻ፤ ወታደር ነውና ትእግስቴን ውጬ ገባሁ።

«ቁጭ በል! ወንበሩን ሳበው፤ ተዝናና።» ሲል የታደለኝን ወንበር ወደእግከያችን ጠረጴዛ አስጠግቶ ተቀመጥኩ። ጠረጴዛውን ሲደገፈው በቀር ጃንሆይ አቀማመጥ ተቀመጠ፤ ጡቶቹን መረባቸውና እፍፍጦ ያየኝ ገባ። እውራ ጡቱን ከተመረበበት አነቃንቀው። ይኸኔ እእምሮየ መታመስ ጀመረ።

«እ እ፤ ይህ ነገር አላማረኝም፤ የተደረተብኝ ድሪቶ አለ መሰል?» አልኩ፤ እንዲያው ፍርሀት ሲጀምረኝ።

«ደግ! ና፤ እንጀምር፤ የምታውቃት የት ነው?»

«እዚሁ፤ እስራኤል ውስጥ።»

«ይህ አልጠፋኝም፤ ስለትውውቃችሁ ንገረኝ።»

«የፈላሻ ዳንስ ልታጠና መጥታ ተዋወቅን።»

«ለመደነስ ወይስ ስለ ዳንሳችሁ ለመፃፍ?»

«ከሆነላት ሁሉንም ማድረግ ትጠላለች እንዴ? የፈላሻ ዳንስ ስትደንስ ግን አላየሗትም።»

«ምን ማለትህ ነው፤ ዳንሳችሁ በጣም አስቸጋሪ ነው እንዴ?»

«እሷን ሁዋ መገመት ቢያዳግተኝም፤ በኔ በኩል ግን ከብደቱ አይታየኝም፤... አብሮኝ ያደገ ነገር አይደል፤ አንተ እስራኤላዊ ዳንስ ያቅትሀል እንዴ?» አልኩት። የጥያቄው ሁኔታ እንዲህ እናገረኝ እንጂ ዘፈን የሚባል ነገር ስልሉኝ አያውቅም። «እሀ! ገባኝ፤ በዚህ ጨለማ ለጉዞ ያወጣችሁ ነገር ምንድን ነው?»

«ሁለታችንም ወደሀዘን ቤት እየሄድን ነው።»

«የልጂቷን የገንዘብ መያዣ አጠፋፍ እንዴት ታየዋለህ?»

«ጠፋኝ ከማለቷ በቀር የተጨበጠልኝ ነገር የለም።»

«ከታክሲው ላይ ነው የጠፋ ብለህ ታምናለህ?»

«ወስዋ ነበረ የምትለውን ጊዝ ጨምሮ ለማየት ባልችልም ለጉዞው ልትከፍል ስታወጣው ያየሁት የገንዘብ መያዣ ጠፋ ማለቷ ከታክሲው የሚያርቀው አይመስለኝም።»

«የአንተን ኪስ በትህክል ፈትሸኸዋል?»

«ምን ማለትህ ነው?»

«ማለቴ፤...ኧ... አንዳንድ ጊዜ ያደረከው ነገር ይረሳል።» ሲል፤ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ከኪሴ የነበረውን ቅራቅምብ ከጠረጴዛው ላይ ዘረጋገፈ «ይህ የምታየው እቃ ሁሉ የኔ ነው

የሚመስለኝ፤ ጥራትና ቅየው።» አልኩ ከመጠን በላይ ራሴን ጠርጥረው።

«የጠፋውን እቃ ቀለም የሚመስለል ነገር አይታየኝም፤ ደልቅ የያዘው ገንዘብ ቁጥር ምን ያህል ነው?»

«የጠፋበት የውጭ አገር ወረቅ ነውና የያዙትን ሽቀል የመቁጠር ግዴታ ያለብኝ አይመስለኝም።»

«ግሪም ነገር። ከዚህ አገር ከመጣህ ብዙ ጊዜ ሆነህ?»

«አራት አመት።»

«እብራይስጥ እንዴት ተማርክ? በጣም ለምደሀል!» ብሎኝ፤ በሰጠሁት ታልም ሆነ ባልሰጠሁት ጭምር የዋስትና ሪርግ ግጥም አድርጉ አስፈርጦኝ፤ ብሉም በበስተኛ ሌብነት ጥርጣሬ ተመዝግቤ (አንዳኛው ሹፌሪ ሲሆን ሁለተኛዋ አብረውን የተሳፈረና በሉሉበት በሽፌሪ የተወነጀሉ የስደስ እድሚ አካባቢ ሴት ናቸው።) ከእኩለ ሌሊት በሗላ ወደተነሳንበት አቢይ ጉዳይ የሌሊት መስመረኛ ታክሲ ፍለጋ ወጣን። ያልጠበኩት ስእል ሁሉ መፈጠሩ ከግንዛሬ ሊፈጠር የሚችለውን ስእል ሁሉ አስረሳኝ። ሌሊ ታክሲ አስጠርቶ ከኔ እስኪርስ ድረስ የሚያዘንበውን የመቅጠሪያ ባንቲም ከመክፈል ደልቅ ሌላ ፖሊስ ፈላጊ በው ያመጣውን መኮናተር ይቀለኝ ነበር፤ ግለቴ ከዚያው ብቅመጥ እስር ደቂቃ አይበልጥም ነበር፤ ግና፤ መስጥእትነቴ ግለቲያ አጠ። አራቱን ቀጊ አሳልፌ ባንድ ጊዜ የጠራችው ታክሲ ሊወስደን መጣ።

ስድስት መቶ ብር ከሁለት ሳምንት ተኩል የሚያሳልፉት ቀለብ አይደለም። በኔ አቅምና ምጠና ሲመዘንና እንዲህ ያለ የተሳከረ ሁኔታ ካልገጠመኝ በቀር፤ ገበያ እያዘጋሁ ከወጣሁና መንገድ ዳር ከተጧጧተ እህል ካልተልከሰከሱ ስድስት መቶው ብር ለስድስት ወር ተኩል በደንብ በቅቶ ያበላኛል። አንድ ቀን ሳላዘጋ ሰርቼ የማገኘው የ ወር ደመወዜም ከዚህ አያልፍም። ታዲያ ደሀቹን እምብርት የነሳትንና መቀነቷ የላላ ስድጎእደግ ልጃገረድ ያስከመኝ፤ ተራቀቅሁ ያልከበትና ራስወዳድነቴ የሌነበት የበሰጠት መሳየ ነበረ። "ዳየት" (የውፍረት ንቅህ) እንድትገባ በውነትሽ ሰሞኑን መዝኗል ልሳት እስብኩና ተመልሽ ባጤነው ግን "ዳየት" የምትለው እስከንገቷ ድረስ በልታ ማስታወኪን ነው። እንዲህ ያለ የሚያርበተብት ጊዜ ሲገጥማት መጀመሪያ መውደድና ጠብ የምትገጥመው ከእህል ጋር ነው። ዙሪያየን ሁ-ያለ ወበርተኛ እዳ ከበበኝ። መጨረሻ የተረዳሁት ነገር ያ የተቀበልኩት የእንግሊዝ ፖውንድ ከእዳ የሚያወጣኝ ባይሆን እጥፍ ድርብ እራጣ የጫለብኝ መሆኑን ነው፤ ግራም ነፈስ ቀኝ ጋዜጠኛው በጣም ተበቅሎኛል!

"ናይጄሪያዊ" ነኝ።

የሙሴ ተልእኮ ሁሉንም ቤተእስራኤል እንበቶ ሳይጨርስ መክሸፉ ብዙ ነገር አልከሰከሰ አስቀርቷል። ከዚህም የመነጨውን አንዳንድ የስራ መዛነፍ ለማስተካከል ጥረቱ የቀጠለበት ሰሞን ነበር። ቢያንስ የተነጣጠሉ ህፃናትና ወላጆቻቸውን ለማገናኘት ይደረግ የነበረው ጥረት አልበረደም። ይህን አስመልክቶ፤ አንድ ምእራባዊ የውጭ ድርጅት «ሙቶ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ይሁዳወችን ባሰባኩት ጉዳና ወደእስራኤል ሳወጣ ነው» ብሎ ለጊደኛየ ፅሁፈት ቤት ስልክ ይመታለታል። የዚህ ጥሪ ባለቤት ከእያ ተበጀ ጋር ኬንያ ላይ የተጣላው ተዘራ ነው። በምን ሊተባበር እንደሚችል ጥያቄ ሲያቀርብ፤ «በመጨው አመት ያደሰ ኘሪዚደንት እናወዳድራለን። አሁን መንበር ላይ ያለው ሰው ለዳግሚያ ምርጫ ለፈፋ ጀምሯል። በማህበራችን ስም ልንጠቀምበት ፈልገናል፤ እንድንመርጥህ ህበሾችን ወደእስራኤል አውጣልን ብለናል። የቀረን ጉዳይ የኛውን እሽ ካደስ ካስወጣን በሂላ ጠቅላይ ሚኒስትር ሽምእን ፔሬስ የምን ያሰሰባኩት ሰው አመጣችሁብኝ ብለው አላውቅም እንዳይሉና ሌላ መዘዝና ጣጣ እንዳይመጣ ፈቃዳቸውን ለመቀበል ቢሯቸው ዘንድ ግባና ማሶማግኘትህን አብስርልን» ይሉታል።

ረፋዱ አይነታ የቢሮ ሰአት ነው። ቴሌግራም የታጀበውን የውጭ ስልክ ዘግቶ ትንሽ ከቅማማ በሂላ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮውን ሀሉ ደላል። በገሪቱ እንደተዘረጋው ሴት የቢሮ ፀሀፊ የሚያበሰጭ አይገኝም። ከጀርባ ላይ ነው የሚበኑት፤ ደግሞ የጠራ ጨቅጫቃ ነው። ባጋጣሚ የጠ/ሚ ፀሀፊት ደግ ቀን ያልጉደለባቸው ሆነው፤ ሰሙን ጠርቶ «ጤና ይስጥልኝ» ሲል፤ በሌላ አጋጣሚ እንደሚወቁት ሰው ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጡ። ቀጥሉ የጠራበትን ምክንያት ተናገረ «ከጠ/ሚ ፔሬስ ጋር ለግንኙነት ቀጠሮ ይመዝግቡልኝ» ሲል በመልስ በተከታዩ ቀን እንዲጠብቅ ሆኖ ስልክ ይዘጋል።

በጣም ነገረኛ ሰሞን ነበር። ታሪከኛው የኢትዮጵያ ይሁዲወች የየሰሳሳ አንድ ቀኑ ተቀምጠህ እድም (ሰላማዊ ሰልፍ) ወገብ ነበር። ያደማው ዋና አቤቱታ «ግርዛትን ተውን» የሚል ሲሆን በውጭም ሆነ በውስጥ ብዙ ንትርክ አስነስቷል። ውጭ ከተቀመጠ ህያ ሁለተኛ ቀኑ። በመንቻክነት በቢሮውም ሆነ በህዝቡ ስላልተወደደ ኢትዮጵያዊ ይሁዲ የመሆን ስሜት ልዩ ነበር።

የስራኤል ህዝብ በዚህ ጥያቄ ላይ ከሁለት አልፎ ብዙ አቷም

ይዘበታል። እንዳንዱን መሰረት የያዘ የፖለቲካና እእምሯዊ ገምጋሚ ወደጎን ትቶ፤ ተቀምጠህ አድመን በቅናትን መልክ የሚቃወሙት ይበዛሉ። «ሰላሳና አርባ አመት በንተመፕ አንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተን እናውቅም፤ ይህችን የእለም ህዝብ ያስቸገራት አገር ቅባንት ወጥተው ምን ታወርደ ብለው ነው ይህን ያህል የሚጮሁት?» ያሉም ጥቂት አይደሉም። ምን ችግር ገጥሟችሁ ነው ሰላማዊ ሰልፍ ባቅወጡ የቀራችሁ? ብሉ ለጠየቀ ህበሻ ግን መልስ ያጠጣቸው ብዙ ናቸው። ከሁኔታውም መጠነሰብ ብዙ አድማስ ይመታል፤ የሰራተኛው ፖርቲ (ማእራህ) ጠቅላይ ሚኒስትሩን ገለልተኛ አስመስሉ የስደተኛ ሚኒስትሩ ቤተእስራኤልን ደግፈው እሪ እንደሉ ሲያደርግ፤ "የሙበት እስጠባቂ እንቅስቃሴ" (ሻሉም አክሻብ) የሚባለው (በገሪቱ የፖለቲካ መድረክ እንዳር በግራ ፅንፍ የሚታወቅ) ፖርቲ ደግሞ ከሰላማዊ ሰልፉ ገብቶ ገምበር ቀደም ጠሪ ሁኗል። "የምን ለቅስ ለምን ይበጃል" እንደሉ፤ የሚታደምበት የህይማኖት ክፍል፤ «ተመልከቱ! ኢትዮጵያውያን መረታታቸውን አረጋገጡ፤ ከኮሚኒስቶች፤ ከፀረ ይሁዲ ህይማኖት ሀይሉች ጋር ሲሰለፉ፤ እኛ ህበሾችን ያልናቸው «እሪትን ተማረና ተመራመረ» ሁዋ ባለ እኛን ከስበው፤ እግዜርን ከከደ ሀይል (ግራ ሀይሎች በሙሉ) ጋር ተሰልፈው መጡብን፤» ሲል በሁለተኛው የፖለቲካ ትንቀናው «ኢትዮጵያውያን የሚያውቁት ምንም ነገር የለም። ሰላማዊ ሰልፍ የወጡበትን ምክንያት ጠልቀው አያውቁም፤ መፈክራቸው የተደራጀው በኮሚኒስቶች ሲሆን፤ ያለማወታቸው ዋና ምልክት፤ ይህን ያህል ቀን ድንኳን ጥለው፤ እያፀዳን የምንዋርበትን ቅድስት እየረሰሱም በቆሸሸ ማራከሳቸው፤ የሰላማዊ ሰልፉቸውን ገደብ ተንትነው ቤታቸውን አለመመለሳቸው ነው።»

ሁኔታውን ከውጭና አውጭ ለሚመለከት፤ ብመለከከት መስንጠቅ የስራኤላውያን ብቻ አይደለም፤ ህበሾችም ከሁለት ተሰንጥቀዋል። "የሰክኑት" ክፍል የሰነበቱና የተማረ ያላቸውን ሰወች በድርጅቱ መዋቅር የሚሰሪ የትርጉም ስራ አበልተኛ ስለደረጋቸው፤ የሚሰረበት ድርጅት ፀር በመሆን ከሰላማዊ ሰልፉ እንዳይደረቡ በስራ መተክሉ ይገታቸዋል። መተክሉም ሰላማዊ ሰልፉን ማክላሸት ጭምር ነውና በገምበር ቀደም በታኝነትና አሸባሪነት ያሰለፈው እንዚህን አበልተኞች ሆነ። ሰላማዊ ሰልፉን በሚመራው ቡድንና ባበልተኞቹ መሀከል ያለው ልዩነት እንደኛው (የሰክኑት) ግርዛትን ያፀደቀ መሆኑ ነው። ብዙወቹ የዚህ ወገን ሁኔታውን በ"እዛኝ ልብ" ይተቹታል፤ እዝነታቸውም " ያሁኑ አልገረዝም ማለት የባሰ መዘዝ ያመጣል፤ በጣም የዘገየ

ጉዳይ ነው፤ መጀመሪያውን ከደፈረንና አብዛኛው ከተገረዘ ሁሉም ከዚያው ቀጥሮ ነው።" የሚል እቿም አላቸው።

እንደህ እያለ ነበር ተዘራ በጉን ከጠ/ሚ ፒረስ ጋር ቀጠሮ መቀበል የፈለገው። የቴሌፎን ቀጠሮውን እንዲንጠለጠለ በጣም ከተፈታተነው የግል ጉዳዩ ገባ።

በስራው የመጣ እየረበሰኚ ሲሆን ፈልጉ የሚከራይ ቤት ፍለጋ መቃበዝ ከጀመረ ሰንብቷል። መንግስት በማግኘ የሚከፍለለት ቤት ሀይፋ ቢኖረውም፤ ወደየሩሳሌም ለመዛወር ግን ጊዜው ገና ወጣት ነበር። አንድም ሀበሻ ገና ያልሰፈረበት፤ ሁለተኛ ተዘራ የሚመራው ቤተእስራኤላዊነክ ማህበር ከመንግስት ያልተጠመነ በመሆኑ የጊዳ ቤት (የሀይፋውን እንዳለ ዘግቶ) ፍለጋ የጀመረው ለዚያ ነው። ከዚህ ጋር የሚያያዘው ችግሬ የቤት ኪራዩ ውድነትና ቤቱም ያለመገኘቱ ጉዳይ አልነበረም፤ የሚያከራዩ ሰወች የሚጠይቁት ከወሰን ያለፈ የጥርጣሬና የዋስትና ማጠሪያ ነበር። ረከስ ያለ ቤት የሚገኘው በአረቦች አከባቢ ሲሆን እዚያ መንደር በክራይ በሁለት በኩል አይመችውም። በይሁዳውያን በኩል የሚያስጠይቅ፣ ባረቦችም ጠንኛ ጉረቤት ሁኖ ሊታይ አይችልም። ለረዢም ጊዜ ለመከራየት የወር ገቢው ዝርዝር አይፈቅድለትም። በይሁዳውያን ሰፈር ለመከራየት ከፈለገ የወር ገቢው ዋና መመዘኛ ነውና በዚህ በኩል የሚኖረውን አግራሞ ዘግቶበታል። ብዙ ሰው እንገቱን እየነቀነቀ ሲመልሰው እንደመጨረሻ አግራሞ ያደረገው «ቱሪስት ነኝ» በማለት ለጭር ጊዜ (ከጆ ላይ መክፈል) የሚል ተስፋ ጥሎ መዞር ነበር። ይሆንም ምርጫ የሚበጠብጥ ሌላ ነገር አልጠፋለትም፤ የቶዳ ቀለሙ ብዙወችን እያስበረገገ የራስ ምታቱ መሆኑ የየቀኑ እሮሮው ነው። በዚህ እለት ከዙረቱ አብረው እንድጋራ፤

«አንድ የኪራይ ማስታወቂያ «ዘ ጀረሳለም ፖስት» ላይ አይቻለሁ፤ አብረን አይተነው እንምጣ፤ በወሽቱና በማደራረደሩ ትረዳኛለህ» ብሎ ሁለታችንንም አድርገነው በማናውቀው አይነት ተሳብበን መስመረኛ አውቶቡስ ላይ ወጣን። ተዘራ እንደገጠመው ካንድ በግራና በቀኙ በኩል ተጠማዝ ወርደ ከተከሸው ላይ ፀጉሬ የወደቀ ድፍን ጥቁር-ለበሸ ሰው (ኦርቶዶክስዊ ይሁዲ ከሚባለው የሰው አይነት) ፊት ቀጭ ሲል በጣም ቀፈፈኝ። «ተዘራ አሁን ከላጠኸው ስፍራ እዚህ ደብተራ ጉን መቀመጥህ ምን ይሆን?» አልኩና እሱን ትቸ ከጀርባቸው ከፍ ያለ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ። እየሩሳሌም ቂስች የሌሉበት ቦታ ማግኘት ዘበት ነው። የፈራሁት የዚህን ሰሞን ሰልፍ በሚመለከት ጭቅጭቅና ንትርክ ማንሳቱን ነበር። ግና ጊዜ አልፈጀበትም። «ታዲያስ!

ጀንጆ» ሲለው፤ ተዘራ በመልሱ፤ «ምስጋና ይድረስ ው!» አለ፤ ቶኩር ብሎ የፍርሀት እያየው። «ሀበሾች ናችሁ፤ የሰላማዊ ሰልፍ ውጤታችሁ እንዴት ያለ ሆነ? ከተቀመጡ አድማ እየተመለሳችሁ አይደል?»

«ከሰላማዊ ሰልፍ አልሄድኩም»

«ለምን?»

«መጨታወቁ ቀሰል ከማብዛቱና ከመሰልቸቱ ሌላ ምንም ዝና አይፈጥርም ብየ ነው፤» አለው። ከመሰልቸት የመጣ ቢሆንም፤ ብልግና የተመላበት አቀራረብ ነበር። ሰውየው ትእግስት ገዝቶ በልክ ቂስ ሆነ። ተዘራ የመጀመሪያውን ጥያቄ ሲመልስለት፤ ከቅንጃ ባጥንኛ ቶርቶሮ ጋር ሲከፍት ጉብጦ ታገለ። እስኪከፍት ግን ዝም አላለም። «አየህ! ሁሉም ያልፋል፤ ትእግስት ብቻ ያስፈልጋል።» ሲል ጠቱን ከወራ ጠቱ ጋር አወብሮ ከከፈተው ቶርቶሮ ጥምብሆውን አውጥቶ ለጉጠ። «ታጨሳላችሁ? (ከተዘራ የላይኑን ሸሚዝ ኪስ ፈጦ፣ ፅሁፉም ሰርቶ የሚነበበውን የሲጋራ ፖኬት አይቶታል) ሲጋራ ማጨስ ቅዱሚን ይፈታተናል፤ በተለይ ቅስና ላለው ሰው የማይገባ ነገር ነው፤ ትፈልጋለህ?» ብሎ እጁን ሲዘረጋለት ተዘራ ጥምብሆውን ይቀበላል ብየ ጭራሹን አልጠበቅሁትም ነበር። ፈቱን ከፍተር-ፈታ አደረገና ጋባዡ ሲያነባ እንዳየው አድርጉ ቶንጥሮ ለጉጠው። በተዘራ አለቶመም፤ ወደኔ ዞረ። «ትሸለህ?» ሲል፤ ራሴን ነታንቼ «አመሰግናለሁ» አልኩት።

ተዘራ ይህ ቂስ ያደረገውን ሊያደርግ የለጉጠው ጥምብሆ ድዱን በጣም ቶጥቁጦት ተቸገረ፤ እንዲያማክረኝ ያለመደው ነገር አፉን ሲከፍት ለንግግር የማያመቸው ሆነበት። ደግሞም ከኔ የማይተናነስ አፈራም ነው። እንባው ተንጠርፍፎ አይኑ ፈጠጠ። ነገሬ የምራቅ እጢው በመነከቱ ጉንጩን የሞላውን ውሀ ልዋጠው-አልዋጠው በማለት ተቸግሮ ኑሮ ነው። ሱዳን ወስዮ እንደህ ያለ አመል እንዳለ ቢያውቅም፤ የጥምብሆ ጭማቂ ሲተፉ አንጆ ሲውጡ አላየም። እዚህ አውቶቡስ ላይ እንዲያ ማድረግ ሌላ ነገር የሚያስጋብዝ አሊያም ማህበረሰቡንም የሚያስደብ ሆነበት። ሰውየው ደግሞ መደረግ ያለበትን ጉዳና አልሰጠውም። በዚህ መሀል ይህ ቂስ ለማናገሪያ ጥምብሆውን የሰጠው ይመስል የሂሳቡን ጥያቄ መደርደር ሲጀምር

«ተዘራ፤ ሰውየው ሲናገር መልስ መስጠትህ አይቀርም፤ እንደማይህ ከሆነ- የለጉጥከው ያልተመቸህ ይመስለኛል ለስላሳ ወረቀት ወይም መሀረብ ሰብና አፍንህና ጠርገህ አውጣው» ስለው፤ እጁን በቅፅበት እንዴት እንደላከውና መሀረቡን እንዳወጣው

ለማገናዘብ ባልቻል ሟጥጦ በመልስ ከኪሱ ከተተው። ይህን ሲያደርግ ቄሱ አላየም። የጥምባሆ ቧምቧን እያዘጋ የነበረው ቄስ እኔ የቆረጥኩበትን ንግግር እስከልቶ ከተዘራ ጋር ውይይቱን ቀጠለ።

«እርምያስን ታውቁታላችሁ?» አለ፤ ተዘራ መልስ ከመስጠት ይልቅ ፊቱ በድንገጤ ተወናብዶ ፀጥታ ሲውጠው፤

«አሀ! እዚህአካ አዲስ የእብራይስጥ ስም ነው የምትቀበሉት፡ የቤተሰብ ስሙ ታመነ ይባላል፤» አለ ቄሱ።

ተፈራ ራሱን ያውቀዋለሁ ነቀነቀለት። የሀበሻ ስም ከሆነ በይታወቅም አውቀዋለሁ ማለትን የመሰለ ነገር የለም (የጠራው የቄስ ስም ነውና)። እለዚያ ሌላ የጥያቄ ጊዝ የሚያበነባ ይሆናል። የጀመረውን ሲቀጥል፤ «እርምያስ ብቻ ባይሆን ሌሎችም በጣም ጊደኞቹ ናቸው፤ እስተማሪያቸው ብሆንም አብረን ብዙ እናስልፋለን። እረፍት ሲሆኑ እቤቴ ድረስ ለጨዋታ ይመጣሉ። በጣም ጥረወች ናቸው፤ ሳልጋብዛቸው ከተፍ፤ እንመጣለን ባይሉ ለገቢያ እንደወጡ እንዴት ዋላችሁ ነው የሚሉት።» አለ። እየስደበን መሆኑን የተረዳን መሆናችንን የተረዳ አልመሰለም። ለተቸው ያመመን ዝርዝር ተዘራ ምንም መልስ ባይሰጠው፤ «ይገባሀል! የዚህ ሰልፍ ጉዳይ እኔን እልፎ የናንተንም ቂሶች (እሱ የሚያስተምራቸው) ግራ እጋብቷል። ሀይማኖትን የሚመራው ቄስ ተቀምጦ ተራው ሰው መምሁ የማይገባ ነገር ነው። ብዙ ያሳሟላችሁት ጉዳይ አለ። የይሁዳዊ ጠመንጃውና በትረ እራቱ ነው፤ ታውቃላችሁ፤ በእብራይስጥ የተፃፈ የሀይማኖት ነገር ይዛችሁ አልተገኛችሁም። የሳም ልጅና ስጋውን አቀላቅላችሁ ትበላላችሁ፤ ይኸም ይቅር፤ የጋብቻ ነገር የባሰው ጉዳያችሁ ነው። ደም ተበላሽቷል። አየህ! እኛ ሞሮኮወች ከዛብላንካ ነው የተወለድኩት፤ ባንድ ይሁዳዊ አስተዳደር፣ ባንድ ቅጥር ግቢ ተከልክለን ከማንም ሳንቀላቀል ደማችንን ጠብቀን ነው እዚህ የደረስነው፤ ስለዚህ ደም ጠብቆ የቆረና ያልቆረ እንዴት ይጋባ! እስራኤል መጥታችሁ ኢትዮጵያ እንደነበራችሁት ከማንም እንቀላቀልም ልትሉ ነው እንገረዝም የምትሉት? የዚህን ሰልፍ ትርጉም አብራራልኝ!» ሲል ተዘራ ቅእገስቱ ከዳው፤ ቢሆንም አልበተም፤ ጥያቄውን ቀጥታ ከመመለስ ይልቅ፤ ቄሱ ያቃረነውንና ያላጤነበትን ትንተና ለመግቱ ተጠቀመበት።

«ከማን ጋር እንድንቀላቀል ፈልገህ ነው? ሞሮኮወች ደም አለማቀላቀላቸው በምን ይለያል! መልካችሁ አረብ፤ ቋንቋችሁም አረብ...» ሲል ተዘራ፤ በውየው የተጠየቀውን ሁሉ መልስ ወደጎን ተቶ፤ «ራብ ለመሆኑ መቼ ነበራችሁ ጅንጅ?»

«የናንተን የሀይማኖት ትድረት የሚግሬት ቂሶቻችን በኛ ቤት ራብች ናቸው። ራብ ማለት ቀርቶ በግረኛው ቄስ መባሉ ነው ራብ የላችሁም ያሰኘን?» ሲል ተዘራ ቄሱ ጉልበትና ፍጥነት የተመላበት ትንተና ጀመረ፤ ጊዜ እንዳያቋርጠውና ባይነግረው እንዳይወርድ በመኻከል፤ «ትሰማለህ «ጅንጅ» (ቡራቡሬ ለማለት) ብበት ሊዋራችሁ ይችላል፤ ግና እገሬንም ባህሉንም ባትለምዱት በመንፈቃችሁ እሬታ አበዛችሁ። በስንት መከራና ችግር ከጠላት ጋር ተቀጣቅጠን ያቀናናት አገር ናት። ታያለህ! እኛ በድንኳን ወደያ ተጥለን ከሽከናዚወች ጋር ስንት ብጥብጥ አልፈናል። እነሱ ተደምን ብለው ብዙ ጉድ ሰርተውናል። እናንተ በፋራዳ ማለት ናችሁ። እምላክን አመስግኑ፤ በሰላም ጊዜ ነው የመጣችሁት። ሀይማኖት ቢዋራችሁ (ይሁዳዊ) ባውደ-አመት በወርጭና በፀሀይ ከውጭ አትቀመጡም። ይህ ሁሉ ከመፅሀፋችሁ የጉደለ ቢዋር ነው፤ ተሳሳትኩ ? እስራኤል ውስጥ ሙሆ አድማጭ ለማግኘት የወታደርነት አገልግሎት ቀድሞ መስጠት ያሻል። እናንተ ግን ከዚህ ሁሉ ገና የደረሳችሁ አይመስልም።...»

«ስንት አመት በወታደርነት አገልግለሀል?» ብሎ ተዘራ ጠየቀው። ቄሱ በመልስ ትክ ብሎ ተመለከቶት፤ «የቄስ ውትድርና ሀይማኖት በህዝቡ ዘንድ እንዲፀና፣ ሰላምና ብልፅግና እንዲወርድ መፀለይና ይህን በመሰለ መራዳት ነው። በሀይማኖት በኩል፤ ስለ እሬት ትርጊሜ ብዙ አስተምሬያለሁ፤ ይኸን እዳረኩ ማለት ነወር ይሆንብኛል እንጂ፤ በተራችሁ የናንተን የሀይማኖት መሪወች እያስተማርኩ ነው። ይኸ ታዲያ አንድ በጣም ትልቅ ውትድርና አይሆንም እንዴ ጅንጅ! አይበቃኝም?»

«ውትድርና የሚሄደው ሁሉ ሀይማኖተኛ አይደለም ማለት ነዋ? ለዚህ ነው ተገረዙ የምትሉት?»

«ቄስ ይወተድራል ስልህ የጦር ሀይሉ ቀኝ እጅ መሆናችንን ስነግርህም ነው። አገልግሎት የሚሄድ ቢያንስ ከናቱ ይሁዲ የሆነ ነው፤ እናንተም ይሁዲወች ናችሁ፤ ግና ጋብቻ አቀላቅላችሁ ይሆናል ተብሎ ነው፤ ዘጠኝ መቶ አመት ስትሰደዱ፤ ያም የተሰደዳችሁት በሁለተኛው የቤተ-መቅደስ ፍርሽ ከሆነ ነው፤ እለያ ሁለት ሽህ ዘመን ተሰዳችሁ ስትዋረ፤ ይህን ያህል ጊዜ ስትዋረ መጠራጠር ይጥፋን ብለህ ነው?»

«ያልከው እውነት ይሁን፤ ሁሉም ተሰዶ ነው የዋረ፤ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን፣ እናንተም ሞሮኮወችን፤ አሜሪካዋችም እንዲሁ መሰላቸውን፤ ሯሲያና የመንም እንዳምባላቸው፤ ሁሉም የነበረበትን ከባቢ ሰው ነው የሚመስል። ይህን እንዴት ታየዋለህ? ጨዋታህ በጣም ይገርማል፤ እኔ ግን

ምንም ይሁዳዊ አይደለሁም፤ በጥቅረት ተነስተህ ብዙ አመራኸኝ፡ ናይጀሪያዊ ነኝ።» ብሉ፤ ሰውየው ገና በማንጋጠጥ ላይ እንዳለና የወሰጥ መገረሙን ሳይጨርስና ቃል ሳይወረውር፤ ተዘራ ወደኔ አንጋጦ ተመልክቶ «በሰበካ አንድ ፈላሻ አጥምቄና በክርክርም አጥቅቸ መጤሁ ብሉ ቤቱን ሆ እያለ እንዲይገባ አንድ ሰው ጉድ ሰራሁ? ይች ናት ቡሪ፤ እንዴትእክ መሰለህ በድንገት ወጥታ የመጣልኝ! ...» ብሉ ሲደረድር መገረሙን የጨረሰው ቄስ የሚናገረውን እሰልቶና አጢኖ፤ «ናይጀራያዊ ነህ። ይህም ጥሩ ነገር ነው። እስራኤል የማታስተናግደው የሰው አይነት የለም። እዚያም ይሁዲወች አሉ፤ በተራ እንደናንተ ይመጣሉ» ሲል ተዘራ ከወንበሩ ሊነሳ እየተንቆራጠጠ «ትሰማኛለህ? አንድ የማይገባኝና የሚገርመኝ ነገር ??»

«ምን ይገርምሃል?»

«እሱ ፀጉርህ የሞርክ ይሁዲወች መሰያ ይሆን?... ይኸን እንተወውና ለጠ/ ሚ ሽሚር የኢትዮጵያውያን ግርዛት ሲያልቅ ልጆቻችን (የገራዦች) የሚቀለቡት ነገር አይኖርም፤ ስለዚህ ናይጀሪያወችን አምጡ ብላችሁ አመልክቱ፤ ለኛም እርዳታ ይሆናል። ናይጀሪያውያን ሲመጡ እኛን ከመገረዝ ትተውናላችሁ፤ እሊያም በትግሉ ያግዙናል።...» ብሉ ሲወጣ መልስ አልጠበተም ነበር፤ ሰውየው ግን ቅፅበታዊ መልስ ነበር የሰጠበት።

«ጅንጅ ሰማ፤ ናይጀሪያዎች ሲመጡ የምንገርዛቸው አብረን ነው፤ ያኔ አንተም አበል ትሆናለህ፤ የማታ ማታ፤ ነቢዩ ሲመጣ በየሩሳሌም ላይ የማይሰበሰብ ፍጥረት አይኖርም፤ ናይጀሪያወች ቀድመው ከመጡ ከ ጟላው የሰው ግፊፊ ይድኑ ይሆናል፤ አንተ ግን ናይጀሪያዊ አትመስልም! ፈላሻ መሆንክን ለኛም ያልከው ምስክር ነው» ሲል የተዘራ የጮገት መከላከያ ተንሿለጠበት። ጨርደናልና ሹፌሬ በሬን ዘጋው።

ወደቢሮ ስንመለስ በይደር የቀጠረት የጠቅላይ ሚኒስትር ፀሀፊ፤ የቀደመን የሸረ መልእክት ትተውለት አገኘ። «ጉዳዮ ከጠቅላይ ሚኒስተር የሚደርስ አይደለም፤ በመልእክቱ ላይ የተወከሉህን ሰው የሚመለከትና በባቸው የሚያልቅ ጉዳይ ነው። እባቸው ከቅግሚ በላይ ነው የሚሉት ሁኔታ ሲኖር ራሳቸው ወደጠ/ ሚኒስትሬ በቀጥታ ያቀርቡታል።» የሚል ነበር። ተዘራ በመገረም፤ «እየህ ክንዴ፤ ቢሮክራሲውን ሊያስተምረን ሰስት ደረጃ ሰሰጡት! ወደኔ እንዲቀመጥ ማለታቸው ነው እኮ። ይኸ ያስፈልግል የሚባል ሰው ማን ይሆን? ሰማህ ክንዴ! አፈን በፀጥታው ከመከራቱ በፊት ይህን እቶ እስፈፃሚ የሚባል ሰውነትና ማንነት ሳጣራ።» አለና፤ ቀትሬን ተንተርሶ ወሬ ደሰጠኛል ሳላቸው ሰወች

ሁሉ «ሀሉ» ሲል ቆይቶ ከንድ የሚዛናባቸው ብሉም ስለ ዲሬክተሬ ጠልተው ያወቅ ሰው የሚከተለውን ሀተታ ይቀበላል።

«እቶው በዚህ የቀውጢ ጊዜ መንግስት (መንግስቱ በቢጊን መውረድ የተነሳ በሁለቱ ፖርቲወች ከዚያ በፊት ባልታየ ሁኔታ የተዋቀረ መሆኑን ለመግለፅ) በሊኩድ ፖርቲ በኩል ለስልጣን መደራደሪያ በስደተኛው ቢሮ (ሚኒስቴር) በዲሬክተርነት ከተቀመጡት አንዱ ክንፍ ናቸው። የኢትዮጵያ ይሁዲወች ጉዳይ በሌላ አበይት የአገሪቱ ጉዳይ እየገባ ስለበጠበጠ ሁሉም የሕናንተ ጉዳይ በርሳቸው እንዲያልፍ ተወስኗል። ስለሆነም የጉዳዩ ተገቢ ሰው ናቸው።» ይሉታል። ቀጠሮ አስመዝግበ በሰስተኛው ቀን (ለቀጥር እኔንም ጨምሮ) ጓዘው ወዳስፈፃሚው ቢሮ ይሆናል። በእውነትም በጉዳዩ ላይ እኔ ብቻ ነኝ አይነት ተንፈራጠወብቶ አገኘናቸው። «ምን አመጣችሁ?» አሉ ያልተነገራቸው ይመስል። ተዘራ ለጠቅላይ ሚኒስትሬ ፀሀፊ ያስመዘገበውን መልስ እንዳለ ደገመላቸው። የሰሙትን ባለመደሰዙ፤ «እስፋውና እንወያይበት። በኔ በኩል ማለትና አለማለቱን ለመገመት ስለጉዳዩ የበለጠ አብራሩልኝ። የትኛው አገር የሚኖሩ ሰወች ናቸው ፈላሻ እናውጣ የሚሉት?»

«ቡድኑንና አገሪቱንማ ገና የደረሰክበት ጉዳይ አይደለም። የመጣሁት በሰም በኩል አድርጊ ጠ/ ሚ ቢሮ መቅረብ እንዳለብኝ ስለተነገረኝ ነው።

«ማን እንዲያ አለህ?»

«ጠ/ ሚ ሽምእን ፔረስ»

«ከባቸው ጋር በቃል ተነጋግረሀል?»

«ፀሀፊያቸው ቃላቸውን የሚፅፉ መሰሉኝ?» ሲል፤ ሰቀው፤ ሊያናግሬት ተንደረደሬ «የሊኩድ ፖርቲ እናንተን በሚመለከት ብዙ ታሪካዊ ስራ ሰርቷል። «ማእራህ» ያን ያህል ስልጣን ላይ ሲንፈራጠጥ ያሳስታወሳችሁን ያህል፤ በዚህ አጭር የሀላፊነት ዘመን እስገራሚ ስራ ነው ያከናወነው። የናንተን ሁሉ ነፍስ ያዳኑ ምናሄም ቤጊን ናቸው። አሁንም ሌት ከቀን ነው የምንሰራ፤ እቡቴእንኪ ማሪፊያ ጊዜ የለኝም፤ የቴሲፎኑ ጥሪ በጣም ጭንቅ ነው፤ ግን አይደክመኝም፤» አሉና እዚያው፤ ሳይ፤ «ያቀረብከውን ጥያቄ በሚመለከት የማይሆን ነገር ነው። ተሰምቶ የማይታወቅ ነገር። እስራኤልን በሚመለከት፤ መውጣትም ሆነ መግባትን የሚመለከተው የእስራኤል መንግስት ብቻ ነው። ከኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ ከሌላ ጋር የሚደረገው ጉዳይ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሬ በኩል (ይስሀቅ ሻሚር) ነው። እኔና እናንተ እኩል ነን፤ የምናውቀው ነገር የለም። ግለሰቦች በመሆናችን በእንዲህ ያለ

ጉዳይ ጠልቃ መግባት የለብንም። ይህን ጠንቅቃችሁ ማወቅ አለባችሁ። ከዚህ በተረፈ ግን በማንኛውም ጊዜ ቢሮየ ክፍት ነው፤ ሳታንኳኩ ብትገቡ ይቻላል።» ብለውና ተሰናብተናቸው ስንወጣ ተዘራ። «ሁለት ክንድ ይሻላል የሚሉት ሀቅ ነው። ቢሯቸውን ለቀን እንደወጣን ከሰፈፉት መሀል አንድ ቁም ነገር ተገንዝብን። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚሉትን ራሱን አስችለን እንሞክረው። የሁሉም ሹም ልብ እኩል አይደለም፤ እዚያ ደግሞ የተለየ ተቃርኖ ሲገጥመን እኛም ተመሳሳይ እንፈጥር ይሆናል። ድል ባንመታም ሌላ የሆነ ተመክሮ ይዘን እንወጣለን።» ብሎ ሲተች የሰጡት መልስ አልነበረም። ይህን አባባሉን በተግባር ለማየት፤ መጀመሪያ ጠ/ሚ ቢሮ ሀሉ አለ። ፀሀፊዋ ከመቅፅበት:

«ጉዳይህ ከምን ደረሰ?»

«ከዳሬክተሯ ጋር አልተስማማንም። እሳቸው የፈለጉት ልንገራቸው የማልፈልገውን ምስጢር ለማዋጣት ነበር። እርስዎ እንዲሉኝ ወደጠ/ ሚኒስትሯ ላከኝ ብላቸው፤

«የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ (ሻሚር) ናቸው የሚፈልጉህ፤ ይኸ የሻሚር የስራ ድርሻእንጂ የጠ/ሚኒስትሯ አይደለም። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኛ የስራ ድርሻ ነው፤ ጥምር መንግሥቱ ሲቋቋም የተደረሰ ስምምነት ነው ብለውኛል። በዚህ ምክራቸው መሰረት ወደሻሚር ስደውል ፀሀፊያቸው፤ ለጊዜው የሉም፤ ሲመለሱ ይሆናል ብለው ዘጉብኝ። ምን ይመስልዎታል ብየ ነው አሁን ስልክ ወደስዎ ያነሳሁት።»

«እንዴ ጠብቀኝ፤ ጠ/ሚንስትሯን ላናግርልህ፡» ብለውት ከመስመሯ ለፋታ ከተሰወሯ በኋላ፤ ተመልሰው፤ «ስማ፤ ከዚያም ብትሄድ መልሱ አንድ ነው። ዳሬክተሯ የነገሯህ፤...» ብለውና ወዘፈው ተወበት። በእርግጥ፤ ከስልኩ ላይ ብዙ ጊዜ መጥፋታቸው ዳሬክተሯ የወሰኑትን ለማጣራት እንደሆነ አላጣነውም። «ዳሬክተሯ ምን ብለው ነገረውኛል? ወደውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ሂድእክ ነው ያሉኝ! የማወራወት ይኸን ነው። አሁን እስዎ የሚሉኝ ሚስተር ሻሚር ሲመጡ ጠብቀህ ሂድ ነው?»

«ቆይ እንዴ፤ እንደገና ጠ/ሚኒስትሯን ልጠይቃቸው!» ብለው አሁንም ገና ቴሌፎኑ አልተዘጋም። ተዘራ እስክርቢቶውን ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ እንዴ ያሳምጠው፤ እንዴ ይለቀለቅበት ጀመር። የእውነት ይመስላል፤ ከቆየበት ቆይተው «መልሱን በሚቀጥለው ቀን ትቀበላለህ» ብለው የስልክ ጨዋታ በዚያ ያልቃል። ተዘራ በዚህ ጉዳይም ሆነ ቤት በመፈለግ የሆነውን፤ ከዚያም የቀጠለውን ያወቅሁት አልነበረም· የለሁም።

ማመልከቻ

ቴል አቪብ! የሰፈረ ወለል ከኔ ያስደረውን ወለትና ዝና በባቸውም ላይ ውሉባቸዋል። ከውቶቡስ ወርደው ተሰሰምን። መጀመሪያውኑ ሲቀጥረኝ ለባለወል ጨዋታ ከማለታቸው በቀር ጉዳያቸው ወደት እንደሚያመራ ባለመረዳቴ፤ «እያ ተበጀ፤ መዳረሻችን ወደት ነው?» አልኩ፤ ነገሯ ወገ አደረሰኩ ብየ ነበር፤ ግና የሰራሁትን አ/ነገር ዘብጠው እኔ እንዴ ሁለት ሰው ሆንኩ፤ እዚያው ላይ የሚተቻቹበትና አድማጭ። «ምን ይላል ይኸ! የምንሄድበትን አያውቅም እንዴ?... ዘወር ያለች፤ የተጠዳችና ሜታ በታ ፈልግና እዚያች እንቀመጣለን፤ ዘሬ አያሌ ስራ የምትሰራ ነህ» አሉ።

«መልካም፤ ሸመልያን ልቀበለኝ!» አልኩ፤ እጁ አስተድሞ ከበትሯ ላይ አርፎና ጨብጦ እንደለቀቀት ፊታዳቸውን እየጠበቀ። ለማረጋገጥ ባብኩት፤ አጠንክረው እንዲያዙት ነው፤

«ይልቀቁት እንጂ! ተቢ፤ ምንድው? የጤና? ትድረት የሚያደንቁ መሰሉኝ?»

«የዘኛ ቃመስኝ ነበር፤ ያበትአደረጉ አልረባኸውም፤ እግዜር ያክብርህ፤ ከደረክው ይቀጠርልህ፤ ግና፤ የለም በትሯን አልሰጥም - እየሄድኩና እየተመረኮዝኩበት ነው። ተወው፤ ግዴለም!» ሲሉ፤

«ግዴለም ግለትክ የተለመደ ጨዋታም ይሰማል፤ ይህ ግድርድርናያ "ጉንደሬ ተግደርዳሪ" እንደሉት፤ "ዘር ከልጓም ይስባል" እንደተባለው እንዳይሆን፤ ነገሬስ በየዳና ጉንደር ብዙም በልይነት የሚጠቀስ አይሆንም፤ ይበሉግ፤ ይኸው ከማረፊያችን እየቀረብን ነው፤ እጅዎን ይፍቱት፤ ይልቀቁት!»

«አንተ? ይኸ ሰው ከልቡ ነው። ከሰው በላይ ያውልህ! በእውን ባድርገው በትልግ፤ ምን አለበት፤ ባንተም ቢሆን ያበትትርስ ለልጅ ታስተራለህ። ወብ ነው። እሄ የኔ ነገር! ልጅህ የትኛውን ሽመል እንዳልቆረጠ ነው? ይኸ ነገር፤ እየቀለድክብኝ ይሆን?» አሉ፤ "ብንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ እእምሯቸው ተጋገተባቸው? በጣም ጠረጠረኝ።

«ልጅ ገና በትር ስለማይቆርጥ ያሁኑን ባለሽመል አታክብር አለበት እንዴ? ልጅ በትር በለለበት ሲወለድ በትር ማስያዝም አይለምድብኝም፤ እያ? ተቢ፤ እንግዲህ ማንን ሲመታበት ብየ ነው ቆመጥ እንደቆርጥ የማስብበው!»

«ይሆን አይደል የምፈራው፤ አሁንም ስደበኸኛል፤ የቅሉንቱ

እሚቴ አስራ አራት (እም 14) ጌታ ዘረ በጆሊ በሄድ፤ በንት ጥቃት ወረደ!» ብለው፤ ምንም ያልጠመምኩበትን አማረኛ የሮሮ መግቢያ አድርገው ተረቡኝ። ገና የጨዋታ ቂታቸው ያልተናጋ ሁኖ ነው መሰል! ደሀን ጥለው፤ «ግና ተባረክ! ሁለት በደል ልብ ድልህ ነው፤ የሚያውል ስራ ልትሰራ ሽመሊንም አሸክምኩህ፤ በል፣ ቢሆንም ረድኤት ነው፤ በፈቃድህ የምታደርገው ስለሆነ መክንን ለኔ፣ ጥድቀትም ባንተ አይሆንም።» እንዳሉ፤ ከሂሳ እየተከተልኳቸው፣ በቃል አቅጣጫውን እየቀየሩኝ ወደሚገረፈያው ቡና ቤት ስንጠጋ፤ «ደብሉ፣ ተቤ እሱን- ደረጃውን ይሜውቅ!» አልኳቸው አልደፈር ቢሉ ተመልክቸ።

«እየ መከራዬ፣ ይኸ ነው ያደከመኝ፤ ካሳጡት ስፍራ፣ በየገዳሉ ቤት ደጭፈና የሚከቅመት ደረጃ ልቤን አፈሰሰው። የቤት አሰራር ብልሀት ያለቸ በጣቢያ ብቻ ነው። ከነገረቀደም፣ የጣቢያ ጉጆ አሰራር፤ ዘር፣ ዘር ብሉ ያየር ቅነፈሳው ሺሚያ የለበትም። ከንዱ ቤት የወረርሽኝ በሺታ ቢገባ፣ እዚያው ቤት የተከማቸውን ይፈጃልእንጂ፣ ሌላው ቀብጦ ካልሄደ አይበክልም። እዚህ፤ ተመልከት! አንድ ከሳለ ይፈጀዋል፤ ካሳጡት በታ፤ አይወደ ያ!» ብለው፣ ደረጃውን ሲሜው እገር ሲነቅሉ ተረብኳቸው፤ በመብረቱ አባባሉ የከቸው ነው፤ «ይህ የምን ይመስለዎታል ? አገር እንደብቃ ብለው አስበው (እስራኤሉች) እንዳይሆን ??» ብዬ በጣም ስትብቸው፤ «ውብ ተሜወትክ፤ የማትረብ፣ ቅንሽ መንደር፣ መናጢ ቅንሜ!» አሉ። ቢያማርሬም የሚደዘበ ፍቅር ይዚቸዋል። ስድባቸው ሁሉ ፍቅራዊ ነው። ከደረታቸው ገፋ፣ ከመቀመጫቸው ጉብደድ፣ እጆቻቸውን ገርበብ አርገው ደረጃውን እተፈተፉበት። ከእምሬቸው ጋር የሚደጠም ነገር ብቻ ሳይሆን ያነተፋቸው ነገር ሁሉ ያናገራቸዋል። የሆነውን ነገር ሁሉ ሳይተቹበት ማለፍ ዘበታቸው ነው። አንድ ማማበኛ ከሌላ ሊለይበት የተጨነቁበትንና ኪነት የፈጀበትን መልክም ሆነ፣ ባንድ ቃል አብደናጉውን ያወጡታል። ታዲያ ያንም ደረጃ አጋምሰው የአረፍት ፋታ ስርተው ገቱኝ፤

«እሁን- እዚህ እንደበየዳና ጃንአሞራ ተረተር ከደረት ገትሮ ከመተው፤ እንዲያ ገድመን፣ ወገብ ለወገብ ጉድን ቢጠርበውና ቢያመጣው ልቤ አይፈለም ነበር፤ ጆል ደረጃ፣ ጆል ስራ! በጣቢያ፣ የደርብ ቤት ያሰራር አማረኛ ሌላ ነው፤ እንዲያም የሚሆነው የቤትሰር በሚያጥረው የተከዜ ከባቢ ሰው ሲሆን ነው። ምድሬ ቤት ያጌዘ፣ የጆንደና የእሁል ነክ ማስቀመጫ ጌታ ይሆንና ከላይ ደርቡ ያው ቤት ነው። እዚህ ታዲያ ስራው የቅል ነው። እዚህ የተወነወነ መሰል፣ በዘወትር ምንም ጉዳይ የለሰው

ስራ-ፈት ጉድጊድ፤ የጥልቀት ማየል! ሳንዳት፣ ገና ለገና፣ የፍርሀትና ያስር አረፋት በንብ ይጥላል ተብሎ ፈጦ መተበሪያ! ጣራውን ከፈለሰው የሚቀር ይመስል! ግና በፍርሀት ጥበብ የተያዘች አገር ናት፤ ቤት ሲናድና ሰው ከውስጥ ሲታፈን የሰው ጠረን መፈለጊያ ወሽ አላቸው።» እንዳሉና እንደተንከረፈፉ ወጥተው፤ ተከትያቸው ገባን። የቤቱን ውስጥ መሰል ባይናቸው አሰሱትና በጣም ተቅበዘበዙ፤

«በል! በየት በኩል ነው የምናርፈው? ከተሳሳፊው ለመዳንና በጭርታ ለመጫወት ያቺ ጥጊ ያማረች ባትሆን አትቀርም» ብለው፤ ወደማእዘኑ እያመለከቱና እየመረኝ ሄደን ተቀመጥን። ቀጥለው፤ «በል! ሸሂም ቀርሰም አምጣ በለው! የምትሸውን ሁሉ እዘዝ! ንገረው! እኔንስ መቸም መሰሚያ ይገባውና አይሰማኝም። ይህ ዱልዱም ምላስ!» አሉ ገና ከደረጃው መውጣት የመጣውን ትንፋሽ ሳያባክኑና አቅሳችን ሳይረጋ። እንዳሉትኤ እሳቸው የሚጠጡትንና የኔን ሸሂ አዝዤ ስመለስ ከውስጥ የኮት ኪሳቸው፣ የጥጥ ማደመጫ ብረት መሰል የተሸበለለ ነገር ሲያወጡ፣ ከገጭ ስራቸው ተስጉ፣ ከታች ኩታቸው ገፍተትና ፊታቸው ተጨፍግጉ ሲታገሉ፤ ከወገቤ ተሰቤ፤ «እያ ተብጆ፣ ልብስዎ ከታች ጠልፎትክ ነው» ብዬ ኩታቸውን ከወረቀቱ አለቅቄ ስቀበሳቸው መልሰው ሀይል ባልመጠኑበት እጃቸው መንጥቀው ሲወስዱት የንጥቀት መሰለኝ፤ እሳቸው በዚህ ባለጌ መሰል ሀይላቸው የተሰማቸውን ማንበሳሰል ባልቻሉ፤ ዘርግተው ዲመጡት። «ጆል ስራ! ያ ተረፈእክ ነው እንደህ ስከበልለውና ሲያሽሞለመለው የዋለ፤ ለመንግስት የሚገባ ወረቀት እንዳይቅራፈድ ብሉ… ማገሸእንኪ ባንተ መጆመሪያ፣ ባማረኛው ማደረጃና መልመጃ ስለሆነ ቢታጠፍ ምንም አይደል። ግና መቸም፣ የመለበም ነው፤ እንተም የጠዳ ሲሆን ቀለም አጣጣሉን ትጠብቃለህ።

«በል! እንግዲህ፤ በባዶ ሆድና ባደረ አፍ፣ የራበር ነገር አይመችም። በጣቢያ ሲሆን ቡና ፈልቶ፣ የቡናውን ምረት ለመሸር በቅቤውና በማሬ አልሶ፣ ማጆቢያ ቀርሱ በየቤውና በቅቤ ኩርፉ ተሲብሶ፣ እጅና ምላስን ስታራውጠው ማዘን ልክ ይመጣል። ቅቤው ሀይል ያስነሳል፤ ቡናው ምላስ መስብሰቢያና ሀሞት መሸከፊያ፣ ማሬ ለዘ፣ ወበቅና በጉክጉ ማመንጫ ነው። እፍከን ሸረው፤ ከሰዋ! እሀል መድፈር አይሆንልህ፤ ባንተ እድሜዬ ጥጋቤ የትና የት ነበረ፤ በናንተ ጊዜ ግን ዘመኑ የብረትና ጋራ አልፎ የሚወነጨፍ ደንጊያ የከዘበት ብቻ ሆነ። ለጡንቻና ለፍንጆ ስጋ ዋጋ አልሰጠው አላችሁ፤ የቀለም ዘመን ሁኖ ቀለሙ መጥምጦ ወረሳችሁ። ሚሊዮን ጉልበት የሚፈጀው ስራ ሁሉ ባንድ ጣት

እየተረገጠ ስንት ስራ ተሰራ። ልብ ብለህ አስበው! የጌብኑ (ፎቅ) መውጫ፣ እንደጉድጓድ ወሀ ቀጅ ከላይ በገመድና በከንድ የሚሰብ ቢሆን ስንቶቻችን በስራ እናልቅ ነበረ። የሰሜኑ ገደል አርሽ ስንት ሰው ነው የጨረሰው። ግና የሬቱ ወደ ሂላ እየቀረ፣ የሂላው የሬቱን እየገዘው መሄድ! አሁን፣ ገም ብሉ፣ ጊዜ እንድ አይነት ብቻ ቢሆን እንዴ ይለመድና እንደሀ በመደናበር ቅጥ እናጠም ነበረ»

«ምን ማለትዎ ነው? ዘመን- አንድ አይነትና ወብ ሁሉም ነገር አንድ- ጥሬ ብቻ ይሁን ለማለት ነው?»

«እኔ ተብጀአንኪ ጆል ከደሀና አልለየሁም። በሁለቱም ገጥ የለመደከው ቢሆን ግለቴ ነው። በመጣኸው መንገድ ግን ደስታ ያለሀዝን፣ ግር ያለእረቅ፣… ባል ያለሚስት ምን ዋጋ አለው? እግዜርአንኪ ሰይጣንም ባይሆን የምንረዳው ነገር- ሰይጣንን ባይመዳደረው የሚደግፈን ነገር አልነበረም»

«እንዴት ባለ አማረኝ? ተቢ እዚሀ ላይ ወዋታ ተወሳደፈብወት መሰል!»

«ቀዋታ ነው የተናገርኩት፤ መወሰደፍ ያንተ ነው። ሰይጣን ለሰው ልጅ ታማኝ ጊደኛው ነው፤ ምንጊዜም ቢሆን ሰይጣን የገራ ቀንጂ በሬ ሲሆን እግዜር የምትለው የቀኝ ቀንጂ ነው። ሰይጣን በገራ ይሰለፋል ስለሆ፤ ሀያል ስራ ያለ በዚያ ገጥ ነው። ሌላውን ተወው፤ ከደንበር መሰስ ላይ የገራው ማነቂያ በሬ የቀኙን ማነቂያ በሬ በገበብ ብሎም በብርታት ቧልገፋው መሰስ የለም። እኔ የምልሀ ግን ያልረበበ ነገር በዘ፣ በረታና አየለ ነው» ሲሉ፤ ከሌላ ቅንተናቸው ጋር ተያርዋው ቢታየኝም ወምረ ልጋፋቸው አልፈለኩም፤ ወብ ሽወዳ ነበረና ይበታቸዋል። «ሌላ ወግ አስገብተን ዋናውና የመጣንበት ተግባር ተረሳ፤ አንዳንድ ነገር ባንሰው እየተሰነቀረ። በል! እንግዲህ እሱን ወረቀት ዘርጋና ከቢም ይኸው! የምልሀን የማመልከቻ ወዋታ የምትጀምር ነህ!»

«ይሆን ሲዳመጥና ሲደየን የዋለ ወረቀትዎን ተዘርጋ፣ አትዘርጋ! የመጀመሪያውን ዳመጠ ማፍረሽ ሌላ ዳመጠ የምወለው ጉዳይ የለኝም፤ ብርእም ሆነ ወረቀት አለኝ፤ ተማሪክ ነኝ ተቢ!»

«እደራሀን እንዴት ተመቸተሀል? የምንጥፈው ታሪክ ጭምር ነው፣ አንድ ክቢ ይፈጃል፤ የያዝውን ክቢ ክከሳኸው ለሂላ አይዋርሆም።»

«ሲያልቅ ተገዝቶ አይተከም ያለዎት ማን ነው? ሱቅ በደረቴው እረቅ ነው እንዳይሉና እንዳልስቅብዎት!»

«ወንድሜ፣ ካንተ ጋር ማን ይሟገታል? በብዙ ቅብዳላለሀ ብየ ሀሳብ በደርግ ይሆን ያሀል መግቶ? በል፤ ወረቀቱ ባንተ በኩል

ይሁን፤ ይህ ባገር የተመረጠና ኩታራው ክኪሉ አወልቶ ለመወሰድ ቅገሉ መኪራ የሆነ ብረትለበስ "ክቢ" ምን ይመጠለታል?» አሉ። እውነታቸውን ነበር፤ ሸጋ "ፓርከር" ይዘዋል። እንዳልጉዳባቸውና እራሳቸውን የመቻል ቅገል ተሸማገለን ስንወርስ የመመሪያ መንደርደሪያቸውን አስቀደሙ።

«ልብ ብለህ ስማ! የክቢ" መርገጫሀ ጊዜ ገና ነው። አንተን ለዚህ ስራ የመረጥኩህ እህ ብለህ ስለምቅበግ ነው። መጠፊንግ እንግዲያ ተረፈ ልጅም ያንገበግበዋል፤ ግና፤ ስራ ከመስራት ይልቅ በፍጆት እንገለያያለን። ከመስማት ይልቅ ከንግግሬ ጉዳፍ የማውጣቱ ጥረቱ ያይላል፤ ከዚያ የሚተርፈው ኩርፊያ ሆዶን ይበጠብጠዋል። ልጅን በጣም እወደዋለሁ። ለሱ ብየ ነው የተሰደድኩት… አንተም በጣም ዋና ልጅ ነህ፤ መወሰድ ሰም ነው፤ ልጅ ማለት ፍቅርና መዋደድ ነው። የምንገርህን ሁሉ አትተው። እጅ መሚራን እንዳሰኪለኛው ሳይለምደው ይቅርእንጂ የነገር አጠጣል፣ የቃል አገባብ ድብትርና የኔ ነው። "ራብር" ጠሀፊ ሁሉ ይህ በዚህ ይገባ ብሉኝ አያውቅም፤ የቀን በዜት እናስገባው? እንጂ። አንድ ዋና ነገር፣ ባንተ በኩል የሚዋር ትርጉም ነው፤ የዚህን አገር ባህል አትሰተውምና አንዳንድ ከኛው ጋር የማይጣጣም ሲወስድ ያሀ! በለኝ፤ እንዳልቀና በሬ የጊዝ ሸር እንዳልስትና እርሸህ እንዳይበላሽ! ያዝ እንግዲህ!» ብለው፤ ማሰብ የመጀመርና የማንሰላሰል ይመስላል፤ አይናቸው ከጣራው ድፍን ወለል ላይ ተንጠለለና፤ «አየ ስራህ ብዙ! አይኔ የሚያርፍበት ቅጥ ከሌለው ላይ! ጣራው ከወለሉ በሀኪል አንድ። የቤት ስራቸው ሳጭር ጊዜ በችኮላ የተጠለ የሀብሻ ዳስ ነው።»

«አያ ተብጆ፤ ልብናወን ባዩት ላይ ከበተኑት የማመልከቻው ሀሳብ ይሸክፍልያታል?» ብየ አቋረጥኳቸው። «እውነትክን ነው፤" ልብ ካላየ አይን አያይም ይባላል። ልቤ ነገር ሊያብላላ ሲያግቶር አይኔ ከልብናየ ቀድሞ ካልረባ ነገር ላይ ጣደኝ። ሁለቱ ባንድ ሲመጣ፣ አይን ወደልብ ይጋበና ለሀሳብ አሰሳው አብሪ ይሆናል። ያኔ የምታየው ሁሉ እንደማታየው ይሆናል። ሰው ሞኙ፣ ያኔ ማያው አይን ነው ብሉ ስንጥር ከዛ ጉላህ ቢለቅበት አይሰማሀም። ከሰብከው ላይ ልብህ ይጠልቅና ሀልውህ አይታይሀም፤ ቸኩልክበኝ እንጂ የልቤን አይን ሳጊመት ነው የነበረው፤ ቢሆንም ወብ ነው የያዝከኝ።

«በል!

«ያዝ እንግዲህ፤

«ቀን ጥፈሀል?»

«እንዴታ! ጥፊያለሁ»

«በል እንግዲህ… ግመልከኝ ለክቡር፤ ለተከበረች፤ ክቡር የእስራኤል እገር ጠቅላይ መንግስት፤ የሊኩድ "ባርቲ" ዋና መሪ አቶ ምናሄም ቤጊን።

«ጌታየ ሆይ!

«ሰላምና ጤና ለስዎ ይሁን!

«ክቡር ሆይ፤ እግዜር ለሹመት ከመረጠው የእስራኤል ልጅ ሁሉ፤ ከንጉስ ሰሎሞንና ከንጉስ ዳዊት በመለስ ችሎታና እርጋታ የክቡርነትዎ መሆኑን በማረጋገጫ ደርሰንበታል። በዚህም ልቀትዎ፣ እግዜር በዘጠነኛ አይኑ የተመለከተውን የጠቢያ እስራኤል እይተዋል። ይህችን ያምባክ እንድ ገብረት እገር፤ ከዘመን ዘመን ሸር፣ በስዎ እእምሮ እልፎ የዘመናት ምልባችንና ስግደታችን በክቡርነትዎ ሀሊና ተሰምቶ፣ ስንመኝት ለነበረችው ቅድስት እየረሰለም ግግሽ እከላችን መጠጋት ለስዎ መታደል፣ ለኛም እልፈት ነው። የእሱ፤ ያምባክእስራኤል ታል ከመሬት እይወድቅም። በመንፈስ ተንሰራርቶ፣ የረቀቀ እከልያን ሰርጓ፤ ከሌላው ምድረእስራኤል ጋር የጠቢያን እስራኤል እኩል በማድረግዎና ጠቢያን በማቷጠርያ ግዛትዎን አሁንም ያሰፋው፤ ከፍ ያደርግዎ እንላለን። ጠቢያን ያነባ ክቡርነትዎ ብቻ ነው፤ ያልደገፈንን ረቂተው፣ ከግሪክ እስራኤል ጋር ተጋግዘው፣ ወቅያዊሱ የየብስ ጫካ ሳያገድ እሽሎክሉከው እዚህ ስላደረሱን እግዜር ከፍ ያርግዎ፤ እለሁልህ ይበልዎ፤ መቸም መላክተኛ ነዎትና። እኛም ስለስዎ በኩል በመሆን በፀሎትና በምለላ እንገኛለን።

«ምድር የጠቢያ እስራኤል ደስ ብሎታል። በጣም ያመሰግናል። የስዎን እላማና "ብላን" በመረዳት እንዳንድ ልቢ የታየውን ስጠቅመዎ በደስታና ባክብሮት ነው። የጠቢያ ልጅ ታሪክ (ቤተእስራኤል) ካባቶቻችንና ከቅድመ-እያቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ፣ በደጋጉች ጥናት እንደደረሰንበት ይሁዳ ዋና አባታችን፣ የነገር ግንዱ በመሆን ከዚያ የነፍስ አባታችን አብርሀም ሲዋለድ ደግሞ ያእቆብ እያለ ዘልቆ፤ ዘረ ይኸው የተረባውንና በለም የተዘራውን፣ እዚህም ቅድስት እየረሰለም የተሰበሰበውን የእስራኤል ልጅ ሁሉ ሁኗል። ይህም ሆዋ ሙሴ በትክሉም ሆነ በመልኩ የጠቢያ ነው። የጠቢያ እስራኤል መልክ ነው የነበረ ይባላል። መጥሀፍም የመረከዘ ታሪክ ነው» ሲሉ የሆነ ነገር ናላየን ነጠቀው፤ «እያ ተበጀ፤ ገና ለገና ምናሄም ቤጊንን ላለምን ብለው ሌላ የመግቶ ዘርፍ እንዲደፈጥረ፤ የሙሴ የዘር ሰራግንድ ይሁዳዊ እይደለም፤ እንደኛ የተገረዘው ባርባ እሙቱ ነው፤ ግብፅ ነው የነበረ፤ ይህም ሆዋ ጥቁር የሙሴ ሚስት እንጂ ራሱ

ሙሴ እልነበረም። "ከደጡ፤ ወደግጡ" እንደሉት የፈላሸን ይሁዳዊ እለመሆን ለሚጊገቱ ሰወች ሌላ ሰምነኛ ታሪክ ከስዎ ሲፈጠር ታየኝ። ከመንግስት ቤት የሚገባ ግመልከኝ ይቅርና ደብዳቤም እይጠልም፤ የምንጠቃበትን ቀዳዳ እስዎ እይጠረጥሩም?»

«እሀ! ምን እይነተ ያልስግሁት ጨዋታ እስነሳህ፤ ያልከው ነገር መጥሀፍ የተመረከዘ ነው ብለህ?»

«ከመፅሀፍ ላይማክ ግደበሰበስ ሞልቷል፤ እነሱ የሚተርኩት ጉደፍ የለውም ይባላል፤ የሚምግታቸው የለም። እስዎ ግን እንደዚህ ያለ ታሪክ ሲያስነሱ ጠማግ ብልት ነው የሚያወጠብት፤ ከዚያም ይጠያሉ። ዘራርፈው ይወነጅሉያታል። የነሙችን ያህል መዝረፍ የለመደበት የለም»

«ብርዛለው ገለጠበጠኝ፤ እለ ከቅግል ላይ የደከመ ሰው፤ ምን ይላል ይኸ! መግቶ ከመጡ እረታቸዋለሁ፤ የመፅሀፍ መግቶ ከሆነ፣ ግብፅ ላይ ባሪያ ያልነበረ እለ እንዴ? ይህን ሀሰት ትላለህ? ያኔ ያልተነካከና ደም ያላዘነቀ ነፍስ ይዋራል?… ግን ወብ ብለህል፤ ይኸን፣ ቀይተን ከሚያወቅ ሽማግሌ ጋር የምናጧምተው ይሆናል፤ ከልሆነም እዚህ መዝገብ እናወጣዋለን።

«በል፤ ያዘ እንግዲህ፤ ሌላውን እንግፋ! በል!

«የጠቢያ ልጅ ወልደትና ዝርያ ከብዙ ያመጣል፤ ከስራኤል ንጉስ ሰሎሞን በንግስተ ሳባ እድርጌ ቀዳማዊ ምንይልክን እግር መጣያ ሰርቶ፣ ምንሊክ ደግሞ ሲረባ ከዚህም ከዚያም ልጁም ያሰበሰበ እስከእጤ ሀይለስላሴ ድረስ ጠቢያን ባንድ እስተዳደረል። የእስራኤል ልጅ ሸረት የመጣ፤ በግልጥ የሆነ፤ አሁን በመንግስቱ ሀይለማርያም ነው። ግና፣ ፈትም የነገሩትን በሙሉ የክርስቲያን ስብከት ስለፈታቸው ቅድረትን ከኛ ሰርቀው፤ በግብር ግን ከኛ እርቀው የወጡ ሆነው ታይተዋል። መንገዱና እስራኤልነት ባንድ እልመጣም።

«የእስራኤል ልጅ ሳስተዳደር፣ ለመንግስት ስራ፣ ለፍልሆና ብሎም ለሌላው ግብብነት ነገር ሁሉ የተሰራ ነው። እምልክቱን ቢከዳ፣ የጠበብ ነገር እያጠውም። እኔ ቴድሮስ የቷራ እስራኤል ናቸው፤ የዋናው ፈላሽ የዘር ጋን መገኛው ከዚያ ነው፤ ቷራ። ከሰለሞን በኩል እይደለም ይሏቸዋል፤ ግና የነው ፍጥረት ሁሉ ከእስራኤልነት ያላነሰው ነገር የለም። በደህንታቸው ጠልተዋቸው ነውእንጂ እስራኤልነት ለቴድሮስ በጣም ቅርብ ነው። እናታቸውና አባታቸው ክርስቶና በተነሱ ሰሞን የተለወጠ እንጂ። ስማ ከንዴ ያጡ ቴድሮስን እስራኤልነት ምልክት እንተ እንዴት ታብራራዋለህ?»

«እያ ተበጀ፤ አሁኝ ነገር እመጡ፤ የባቸው ፍልስና ደግሞ

እንዴት ብሉ፤ በየት አድርጌ አደራምን?»

«እንዴት አጠያየቅ ታጠብቃለህ? የዘር ግንዳቸውን መቁጠር ትችላለህ እንዴ? እኔ የማጫውትህ በምልክት ተነስቸ ነው! በርሳቸው የወደፊያ በስቲያ ይሁዲት የምትባል ንግስት ነገሠ-እስራኤል ናት፤ ምድረ ክርስቲያንን መድረሻ አሳጥታ፤ የሚሰበሰብበትን ቤተክሲያን ሁሉ ስንት አቃጠለች፤ ቴድሮስም ቢሆኑ በትክክል እንዲያ ነው ያደረጉት፤ ግና ተራኪው ብዙ ነገር ወምርቦበት፤ ብዙ የሚብራራ ነገር ይቀረዋል። ንግስት ይሁዲት ግን፣ የክርስቲያኑን በስራኤል ላይ ፊርሽት ለማብረድ የዝር መስክተኛ መሆኗ በጣም ግልፕ ነገር ነው» ብለው ድምፃቸውን ገደሉትና፤ እንደማሽከሽከም ቃጣቸው፤ ነገራቸው መፃፉን እንዳቆም የማድረግ መሰ። «የሴት ብርቱ፤ ታሰኛለች እንቱ ይባላል። ሴት ስትቆጣ ወሰኝ አይደለች፤ እግዜር ከመረጠው አውቆበታል! ወፈወፈችው» ብለው፤ እንደገና እዚያው ላይ ድምፃቸውን አገነኑት፤ «ዋናው መረጃ ስሟ ነው፤ ከዚህ ይገባዋል፤ ወይም ይህ የስራኤል ስም አመጣጥ እንዴት ነው? ብሉ መጠየቁ አይቀርምና የዚህን ማብራሪያ መፃፍ ወረተትና ጊዜ መግደያ ነው፤ አታስገበ። ያዝ እንግዲህ! «ከዚህ በመለስ፣ የስራኤል ልጅ በጦቢያ አገሩ በሚባል ነገድ ስም፣ ያበቶቹን ቿንቿ፤ የነአብርሀምና ያቆቢ..» ብለው እንደገና ድምፃቸውን ወደዜማ ቀዥት፤ «የናት ሆድ ዥንጉርጉር፤ ይስሀቅ የያእቆብ ወንድም ነው። ግና ያብርሀም አንድነት በነሱ አልታየም። እስራኤላች አብርሀምን ጠቅሰን ያቆብን እናስከትላለን፤ ይባቅ ሌላ በመሆኑ እንወምረውም። ይስሀቅ የያቢር አረፋትና የሌላው ሰው ዘር ሆነ። እስባሞች ከያቆብ ይልቅ ይስቅን ያከብሩታል።...በል! ዋናውን ቁም ነገር፤ ያዝ እንግዲህ!

«የጦቢያ እስራኤል ያብርሀምንና የያቆብን ብሉም እነሱን የተከተለ ሁሉ ቿንቿ፤ አሁንም ሙቶ የተነበውንና የስራኤል ልጅ የሚናገረውን እብራይስጥ፣ በዚህም የተፃፈውን ኦሪት ዋና በማድረግና የህዝብ አውራ በመሆን ዋር፣ በዝቶና ተባዝቶ እልፍ ቢሆን አይተው የቀናበት የክርስቲያን ወራሪዎች ጦርነት ገጥመውት ብዙ አለቀ። በጣም የበረታ፣ ባለም ያልነበረ ጦርነት ነበር ይባላል። እኛስ መችም አልደረስንበትም፤ ይባላልን እንሰማለን። በጦርነቱም አገሩ እስራኤል ሁሉ ተጠቃ፤ ብዙውን በመስቀል ባረኩት፤ የዚያ ምልክት የክርስቲያን እማኝ ሁኖ በድፍን ጦቢያ አገሩ እየተባለ ይገኛል፤ ከማረኛ ይልቅ አገውኛ ለእብራይስጥ ይቀርባል። በጦርነቱ ቢጠቃም፤ እምቢ ብሉ ያልተሰጠው ይኸው ዛሬ ፈላሽ የሚባለውና ያበቶቹን ሀይማኖት

ጠብቆ፣ በሀይማኖቱ እንደብረቱ ፀንቶ የቆየው ነው፤ እዚህ የመጣነውና ለመምጣትም መንገድ የተዘጋበት። ፈላሽ የሚባለው አጠራርም ከዚያ ጦርነት ውድቀት የመጣ ስያሜ ነው። ከገው መለየትን፤ መግድ መባሉንና ከእርስቶ-መሬት መነቀሉን ያመለክታል። እላምንላቸው ሲል ፍልስ፣ ፈላሽ ብለውት ስምም፣ ስድብም ሆነ።

«በገውና በማሮች መሀከል በተደረገው ጦርነት በብራይስጥ የተጠፈ የኦሪት መፅሀፍ ሁሉ ለክርስቲያን ከመነው ጋር አብሮ ብሉም ከወራሪው እጅ እንደገባ ቀረ። ስለሆነም በሀይማኖቱ የፀናው እስራኤል ሁሉ በቃል ያጠናውን፤ ከሰውሰው በዋና ከህናቱ ለቅም ኦሪት በግእዝ ተጠረዘ። ከዚያ አገውኛ ተርቶ ግእዝ የእስራኤል ቿንቿ ሆነ፤ ተመረጠ። ዛሬ፣ ይኸው፣ ከሞት የተረፈው የስራኤል ልጅ በየኪሱ ሳይቀር መዝሙረ-ዳዊትን ይዞ እቤት ጌታየ እንዳለ እዚህ ለመድረስ የበቃም አለ፤ ብዙው ግን አሁንም የፃን የመጨረሻ እርዳታ ይጠብቃል። ነገር ሁሉ ወደግእዝ ሲተሳለፍ፣ ከዋናው የእብራይስጥ ኦሪት የተተወ ወይም የተረሳ ነገር የለም። የቀረ ቿንቿው፤ እብራይስጥ ብቻ ነው።

«አሁንም እንደሆነ! የጦቢያ እስራኤልን እንደማርሳት የሚያንገበግበው የዋናው መፅሀፈ ኦሪት በቤተ-ክርስቲያናትና ገዳማት መቅረቱ ነው። በእጅ ለማድረግ ታክተን ቀርቷል። ክርስቲያኑ ሁሉ የኛን እቃ እንደመንፈስ ያየዋል፤ እያነቡት ቿንቿው አይገባቸውም፤ እንዳይከፍቱትም ይቀበፈናል ብለው ፈረሱ እንደሞተበት ያውሊያ ጊዝ ተከድኖ እንደተቀመጠ የታወቀ ነው። ከፈሉም ያይዋ መጫወቻ ሁኖ ባይጠፋ አልቀረም። ያለውን ግን በውቅ፣ በታ-በታውን ለመጠቆም የኛ አባግ ቢሆን በቸር ከመጣ ለዚህች ቅድስት አገር የመንፈስ መጨመሪያም ይሆናል ብለን እንገምታለን።

«ጌታየ፣ ሆይ! የመጊጊታችን ምልክቱ መቅደሳችንና የመሰያ ጨሳችንን ቤተእስራኤል በማለት ሰውም የስራኤል ልጅ እየተባለና እስከዛሬ ሳይጠፋ? ያ ሁሉ ጦርነትና ሞት ሲወርድ ያልፈረሰ መቅደስ! ሌላ ዋና ምልክት ነው። ፈላሽ ቢሉንም፤ መቅደሳችንን በመጠበቅ ስድባቸውን ከጉዳይ ሳንጥፍ እንደሰወ ያለ እጋዥ እማኝተን ፈላሽ አቅባሉን እስራኤሎች ነን በማለት ያለም ጠሀፊ ሁሉ እስተጋብቶልናል። በኔ ገጥ አንድ ስህተት ሆኖ የታየኝ በስም እርዳታ መታረም ያለበት፤ ተማሮች በመባባቱ ሰውን በመስጊዳችንና በመንደራችን ስም መጥራት መቻሉቸውን ነው። ቤተእስራኤል መስጊዱና መንደር የሚሰራበት ክበብ ሲሆን፤ እማኙ ግን እስራኤል ሲባል ኘው የቀረው። ከኛ መሀልም ቢሆን ራሱን

ፈላሽ ማለቱ የልማድ፣ በቀልድና በተረብ ተጋብቶ ቀርቶ ነውና እንዲያ ነው። ይህም ገብቶት አሁን እያረመ ይገኛል። የገማ ነገር ተሎ ካልጣሉት ሽታው ተሎ አይጠፋም፤ ብዙ ዘመን ይበክላል። እኛም ተበክለን ኖሮ ነው።

«ስማ አንድ ክንዴ!»

«ምን ወይ? እያ ተብጄ»

«እዬ ወዲያ_ ዝም ብዬህ ነው! አንድ ነገር ከልቤ ተጣዶ፤ ይሆን ልጠይቀው ብለህ?»

«ምን ሊጠቅሱ ፈለጉ? ወገን»

«ወገን ደብልህ! እሺም፤ ከወዲህ፣ በጣም ከመሸ የመጣ መዘዝ ነው። ግራኝ መሀመድም ትላንትና ነው መቢያን ከፍሉ ያሰመነው፤ እኔማ፤ ከልቤ ላይ፤ ወለል ብሎ የሚታየኝ ነገር አለ»

«ይናገሩትና ይለይለት፤ ደግሞ ሰው በሌለበት!»

«ሰው በሌለበት አትበለኝ፤ ልንመዘግበው መሰለኝ?»

«መልካም፤ ያልረባ ጥቅስ ከሆነ ሰው ባይሰማ እንገለፍለን ለማለት ነው፤ ተቤ»

«ክርስቲያን የሚባል ነገር የመጣው ከክርስቶስ ጀምሮ አይደል? ከዚያ በፊት የነበረ ክርስቲያን ኑሯል ብለህ?»

«እያ ተብጄ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ የማውቀው ዘለላ አረፍተነገር የለም። ግና፣ በታሪክ ገፅ ከቶት፤ ይሁዳዊነት - ከይሁዳ፣ ክርስትና- ከክርስቶስ፤ እስልምና- ከመሀመድ፣ ሌላ ሌላውም ለዚያ እምነት ከቶመሰት ሰው ሞት በኋላ የተፈጠረ ነው ቢባል ይመስላል። ተመላኪዎች ሰዎች ይመስሉኛል»

«ልክ ነኝ፤ ነው፤ ልክ ነው የተሰማኩት፤ አንተ ያልከውም ትንሽ ይታረባል፤ ሰው ይመሰክል ግን አትበል፤ የሚልከው እግዜር አይደለ! መቼም፣ እያ! ልክ ይመስላል ነው። በየሱስ ነው ክርስትና የተጀመረው፤ የሰው ሁሉ የመጀመሪያ፣ አይነታው እስራኤል ነው፤ ፊትም የነገርኩህ ነው። እስራኤል ያልሆነ ነገር አጉልና ከንቱ፣ የማይሆን ነገር ነው።»

«እና? ይህን-ይህን ጥቅሰው ነው የሚሉኝ?»

«ወብ ነገር ኖሮ፤ ይህ እመዳም ነጭ ሁሉ የጥቁር እስራኤል የለም የሚል፣ የቅ አባቱ! ደማባዝም ሁሉ፤ ለዚህ ደግ ሰው (ቤጊን) ደስ እንዲለው ለማስበም እሰቢ ኖሮ! ከያዙነው ታሪክ ጋር ግን የገር መጣያና ማራመጃ መሰላል የሌለው ሆነ። አንተ! እየነደደኝ፤ ቀጥቶ ይመጣና ከንጉሴ መሽም፣ ሆዱን ማረሀረህ፣ መርርሸት፣ መርርሸት፤ ወይኔ ያጠ ልጅ፣ እንዲህ ወደማታ ነድጄና ተታጥየ ልጥቅ!» ሲሉ፤ ትንሽ ባቅ ቢጤ ሲፈታኝ ተመለከቱ፤ ከንፈራቸውን ፈርተቅ እንደማድረግ አድርገው በይናቸው ሰለሉኝ፤

«ምን ወደህና ወዲያ ሆዱን ይዞ ይንፈረፈራል? እሩቱ! ተ-ን-ፈ-ቅ-ፈ-ቅ፤ የኔ ንዴት ደስ አለው? የልጅ ነገር! አንተ ጥታት መች ይገባሀል፤ ተሉ-ተሉ ከሳስረዳን ነጮች ባፍ ከፊት እየተደሰ አስጥገረውናል። ነገራቸው ሁሉ ዘዋሬ ነው የሆነብኝ፤ ባንድ በኩል የሚሰብኩትና በሌላ በኩል የሚያደርጉት በጣም የተለያየ ነው፤ ምን አለብህ፤ ባቅ! በልእንጀ፤ ሽረ ምን ነው ያስቀህ?» ብለውና የተቆጡትን ተቆጥተው፤ የሳቅሁበትን ለማወቅ ቋመጡ። ፊታቸው በረድ- ልመና፣ ከንፈራቸውን ፈርተቅ- ከፊት አለና የታችኛው ከንፈራቸው እንደመሸከፍ፣ እንደመዛል ያጣው። ባጭር፣ የፊታቸው ሁኔታ ከሚኪሸጒት ወደዘር የሚወጣ ቃል የሚጠብቅ መሰለ። በንባ የዉገገ እይኔንን እንዳማተርኩባቸውና ንግግሬን የሳቅ እስትንፋስ እንዳጀበው፤ «ተቤ፣ አሁን ምን አለበት ቢተውኝ፤ እንዳንዴ ዝም ብሎ ይሳቃል፤ እናም ሁልጊዜ ሳቅ ጤና ነው ይላሉና_ ማለፍ አያውቅም?»

«በቁም ነገር ደህና ሰው ብየ ጋብዤና አስመጥቼ? ዝም ብሉ ከሚዲ የሚስቅ፤ እብድ፣ አሊያም በእብድ ጎዳና ሲገባ ሸገግ ያደረገው ይሆን ይሆናል። አበድኩ በለኝና ወረቀቴን ጠቅልየ ቤቴን ልሂድ፤ ኡ-ም-ባ-ክ-እ-ስ-ራ-ኢ-ል! አታወርደው አስደንጋጭ ነገር የለም! ሳቅህ መጣራት ያለበት ነገር ነው፤ ሳቅ ጤና ቢሆንም የዉነት መሳቂያ ማብጀት አለብህ» ሲሉ፤ አሁንም እስትንፋሴ በሳቅ እንደተያዘ፤ «ስማ ወገን! አንዳንድ ነገር ይገርመኛል፤ "ዝር ከልጊም ይበቡል" ብለን የል፤ እኔ ጠ/ሚ ምናምን ቤጊንን ብሆን ቀሮ አሁን ከያያዙትና ሊጠቅሱት ሞክረው ለመተው ከፈረደበት ሀሳብያ በመነሳት፤ በርግጥ ቤተእስራኤሎች ያለጥርጥር ይሁዳዎች ናቸው ብየ ያደባባይ አዋጅ አውጅ ነበረ»

«እንዴት ባለ አግረኛ ተንስተህ ነው ለዚህ አጭርና በጣም ቀልጣፋ አዋጅ የበቃህ?»

«ልንገርዎ!፤ ወደዚያ እየመጣሁ መሰሉኝ፣ ቀዝቀዝ፣ እረጋ ይበሉልልኝማ!» እልኩ፤ ይኸኔ ገጠመኝና ቀንጠጥኳቸው፤ ስቸኩል፤ እሳቸውም እንዲያ ነው የሚሉት። ባልስተካከላቸውም ላንድ ጊዜ ምት ሆነኝ። ብልግናም እንደሆነ አውቀዋለሁ፤ ግና ስለምዝናናባቸው ምንም አይደል።

«ባንዳንድ ነገር እንዴ ከንዱ የሚሉት ይመስለኝ ነበረ፤ ሁሉም ያው ሁዋ ነው ያገኘሁት፤ እነሱና እስራኤሎች፣ ልክ አንድ ናችሁ። ይሁዳውያን በሙሉ ለማለት ትንሽ ቢያምጠኝም እስራኤሎች ግን የቅም ይሁን የቅ፤ የሆነ ሰው ብዙ ሰው የሚያስደንቅ አሊያም ልዩ ስራ የሰራ፤ ይንጣም፣ ይቅባም፤ በግድ ይሁዳዊ ነው ይሉታል፤ አደስ ነገር የፈጠረ፣ የላቀ መሪ፣ ዝነኛ

የአምርት ሰው፤ የታወቀ ጋዜጠኛ፤ ሌላም ሳብዛኛው ያልመሰለ ነገር የሰራ፤ የኛ ሰው ባይሉትም ገና ለገና ስሙ ሲጠራ ይሁዲ ነው? ማለት ልምድ አለባቸው። መሳሹ አይደለም ከለ፤ ወደፖለቲ ምርምር ይገባሉ፤ ተመርምሮ ፍንጭ ከታጣ የለም ይሁዳዊ ነክነት ያለው መሆን አለበት ማለት ግዳቸው ነው። ይህም፤ ክርስትና ይነሳ፤ ሌላም ነገር ይሁን ምንም አይደል። ከሮኔል መሀመድ ጋዳፊ፣ ሰሞኑን በግሪኮችና በእስራኤሎች ላይ በመፈከራቸውና በመዛታቸው፤ እንዲህ ያለ ድፍረት የያዘ ሰው የሆነው ቢያንስ በናቱ ይሁዲ ቢሆን ነው ብለው ይጊገቱባቸው ገብተዋል፤ እናቱ ሴባል ደግሞ ዋና ነገር መሆኑን አይርሱ፤ የየሱስ አባት አጨታማቂ ቢሆንም ይሁዳዊ መሆኑ እናቱ ጠርታ በመታወቂ ነው ማርያም። ስለሆነም የይሁዳዊነት ዋና መመዘኛው አባት ሳይሆን እናት ናት፤ በሴት ላይ የሆነ ያልሆነ ስለሚደርስ ብሎም ወንድ መድረስ እንጂ መውለድ አይችልም ከሚል መሰበም ይመስለኛል። የነጭ ስም ብዙ አይያዝዎት እንደሆነ እንጂ ብዙ እጠራለውቶ ነበር፤ አበበ ቢቂላ ጋላ ነው (እርም ብላቸው አይገባቸውም፤ እነቸው የሚያውቁት እንዲህ ነው) ግና የቤተእስራኤል ጋላነት እስከሁን የተነገረ ነገር አይደለም፤ በግልፅ የሚታወቀው ብሎም እስከሁን የተነገረው በትግሬና በደፍን ጉንደር ብሎም ከሳስታም ትንሽ ያመጣል ነው። ግና አበበ ቢቂላ ለብዙወቹ የገድ ፈላሽ ነው። ስለሆነም የስም መጨነቅ አጉል ነው፤ ጠ/ሚ ምናሄም ቤጊን፣ ይሁዲ ያላሉት አለም አይገኝም። ይገባቸዋልና አጉል ተጨነቅ ብየ ነው መሰቴ። አጉል የወረቀትያ መፍጃ ነው።»

አሉኡ ሀይል መፍጃ ብላቸው አምባጓሮ እንዳምንፈጥር ስለታየኝ። ለመከርከሚያ፤ ደግሞም ጨዋታ አሰመርኩ የማለት አይነት፤ ሊቀ መንበር መንግስቱ ሀይለማርያምም ከቀናቸው ይሁዲ ይሆናሉ» አልኩ፤ በዚህ ፋታ ግን ስሁተት መግቢቴን አውቄዋለሁ፤ ተሰፋኝ የወረወርኩት ጨዋታ ነበርና በጣም እንዲሚመቸኝ ረዳቸው። እንገታቸው ጠነን፤ አይናቸው ከጠረጴዛው ጠርዝና ከግድግዳው መለያያ ገድም ላይ ቶከር አለ፤

«እ-ራ-ቶ! ያንተ ጨዋታ! የሀይለማርያምን መንግስቱ ያህል በእስራኤል የተከበረ ማን አለ? ከሞት ይጠብቁታል አሉ፤ እንዴእጤ ሀይለስላሴ በሉሞንነቱን ስሳወጁ ይሆን? ያንተ ጨወታ! ቤተመንግስት የገባ ያው ምንጊዜም ሰለሞን ነው፤ ቴድሮስን እሳ የሆም፤ ስለሞንነት የለውም ቢሏቸው እየረሳሉምን እንዴውና እንዲለው ገና ለገና ከእንግሊዝ ጋር ደብዲቡ? ደምገዲቡ ቢሉት ልክ ይሆን ነበር፤ ታዲያ ሲገፋ ነፍሳቸው አለፈች፤ እንዳርሳቸው ብሳንግ "የጠቢያ ባል፤ የየረሳሉም እሙኝ፣ የገብርየ

ክንድ፣ የመደህኒያለም ባሪያ ብለው መፈከራቸው ጠቢያ ሲቀናሳቸው ቀጥሉ ወደየረሳሉም ለመሻገር ነበር። የሀይለ ማርያም መንግስቱን ያህል?... ማንገስ የሰሴ ከሆነ ማርያም እናቴኮስ ምን ይሳናታል። ይሁንም ለተረብ እንተወውና የሀይለማርያም መንግስቱን ያህል ቢንከባከቡን ኑሮ የቅና የቅ! እገር እማን ሆነ ማለት ነበር። የእስራኤል ነክነት በይፋር ነው ነፍስ ግብታና እንክብካቤ የሚሆነው? እንገዲያ የመንግስቱ ስራ መክብ፣ ግና ዘብና ነፍስ ጠባቂ እስራኤል። የማታ ማታ በሰው እንቶርጥም፤ "እሆያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም" የተባለውን ተረት በግልጥ እያየሁት ይሁዳዊ አይደሉም ይለኛል! ይልቅ አጉል ጥቅስ እምጥተህ ሀሳቤን በሙሉ አሳጋኸው፤ የመንግስቱ ሰሎሞንነት አልጋው ሲጠና፣ ቅብ ቅዱሱን በግልጥ ሲቀምስ የሚታወጅ ይሆናል፤ አልጋ ጠና የሚባል ያኔ አይደል! እስከዚያ ድረስ ደግሞ ሰሴነቱን አትርሳ፤ ከነዚህ በስቱ ሰሰቾ ከምቶቿቸው ሰወች የቅኛው ነው የእስራኤል ዘር? እንዱ ዋና እስራኤልነት ነበረው ይሉኛል»

«የምን ሰሴ ነው የሚያወራት?»

«ያስተማረን የደርግ ከድሬ ነው፤ ይኸ ሳንተም ጠፋህ እንተስ ያው ደርግ አይደለህ፤ ተማሪ!» ሲሉ፤ በውነት ከሆነ "ከድሬ" የሚለውን ባይጠሩ ኑሮ የምረዳቸው ነገር አልነበረም፤ ስለገባኝም «እዎ ግርከስ ይሁዳዊ ነበር» አልኳቸው።

«በሙን ደግመህ አስደዘኝ!»

«ግርክስ።»

«ልክ ነው የተማወቅኩ! እንድ ጊዜ ያስያዙኝን የሚገባ ጨዋታ አልረሳም። ይኸን ጨወቅ ያነሳሁት መንግስቱ ቢሆንም ሰሴነቱን አሳጣውም፤ ሰሴነቱን ደግሞ እስራኤልነት አያጣውም። ስለሆነም «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ግርክስ (ግርክስ ለማለት ፈልገው) ቢለው ልክ የሚመጣ ይሆናል። ዘርዘር ክእስራኤል የሚወጣ ነገር የለም ያልኩህ ለዚህ ነው። ሀይሉም ቢሆኑ ቀስ በቀስ.. እንዲያ ነው ያደረጉት፤ ያንተ ጨዋታ ድንኩርኩር ነው፤ በል ይልቅ ውሀ መሳይ ከፍየ ልምጣ! ለሽግግሉ ፊኛ መቋጠር የማይበጅ ነገር ነው፤ በየት በኩል ነው የዚህ ገንዳ (መፀዳጃ ቤት) መውጫውና መግቢያው?» ብለው የተቀመጡበትን ሞባሳ የሁለት ሰው መቀመጫ ወንበር ሊለቁ ሲንፈቀቁና አልፌያቸው ሲል፤ «ጃል ስራ! ላንድ ሰው ይሆን ያህል መደብሽ! ከነገረቀደም ከርፍራፉ (ጠረጴዛ) ለግቶ፤ ክበዱው አይገፋ! ቢሆንም ደግሞ በየሱ መርጥ ልክ እንድ ባንድ፣ ከፊት ከፊት እደርጌ ቢሰራው ምን ነበረበት?»

«ለብዙ ሰው ከተሰራው መቀመጫ ላይ የተቀመጠበት እስኪ ንገሪኝ፤ አባ ዘራፍ!»

«ያንተ ዉሻታ! ቡና የሚጠጣው ሰው በዝቶበት ነው ከላጣው በታ ይሆን ሲገኙምልኝ የሚለው? የድሀ መጋኛ በረቱን ያህል ሰፋቱን አታየውም! የነጋዴ መላ ጠፍቶኝ! ገም በል! ነገር አልሰማችሁም።»

ከደረታቸው ገፋ፣ ከወገባቸው መታ፣ ከመቀመጫቸው ቀረሁ እስኪታወና እጃቸው ተንገበ ቶመ። በር ፍለጋ አምባሉሊ ፃኝ፤ ለሚፈልጉት እርዳታ መስገሚንና አለመድረሱን ቢረዱ ለብ ጣታቸውን ቀሰረው፤

«መከፈያው በዚያ ነው መሰል? ነው ብለህ? ነገረግ ከውስጥም ያሰቃል፣ የቤት መቀመጫና የወንድ መክፈያ የሚባል ተበጅቶ! ና! ልጁ፣ ና! መምጠሁ አልቀረም፤ ከቤቱ ገብቶ ቢተፈቅዱ፣ አንዷ ነጭ ቲፕ እንዲትደዘኝና እሬ ብላ መሳቂያ እንዲትሆን፤ ነገረሽ፣ በሰርጅታ ጋንጃ ብለው የሚጥሉ፣ ሴቶቹ ናቸው ብለው አስፈራርተውናል። ጥልቶ ከተረፈው የቤት መንገ ይሆን ያህል ጥልቅ መላ መመለል። ና! መቸም፤ "ከልጠረጠረ ይመነጠራል"፤ ለሁሉም ና!» አሉ፤ ያስጨበጡኝን ወረቀትና ብርእ እያንከላወሱ ነበር የዘገየሁባቸው። በገራ በቀኝ ብለው በደንብ አጠርተውና ተመላክተው ገብተው፤ የፈጅትን ጊዜ ፈጅተው ተመልሰው ወጡ። «ሰማሁ ከንዱ! ያንዳንድ ነገር ሁኔታ በጣም ይገርማል፤ ትድም ያልከው ነገር ነው፤ ከዋናው የመቀመጫ ክፍል ጀልቅ የሽንጉው ቤት (ሽንት ቤት) ተዳት ይበልጣል። ሲመቹ፤ ከጃርቢዋ ላይ አፈፍ እንዲልከበት የሞን ከብት (የጋማ ከብት) ፈተት ብሉ ነው የሚወርደው። ራቴ ሆዴ፤ አንዳንድ ነገራቸውና ስራቸው በጣም ልክ ነው። እንደሚዲው፤ እንደነፈሽው»

«ተቤ፣ ስለምን ነው የሚያወረኝ?»

«አይገባውም? የሆድ እቃ ጊዝ መጠያው እንጋዳ ማለቱ ነዋ፤ ሽንጉ ቤት አሳማሪዎች ናቸው።» ብለው ዉሽታቸው በጣም ቤቱን አቃወረው። አውቶቡስ ጠቢያ ያሉ መሰለፃቸ? ልባቸው ታየኝ፤ ግና ሌላ ታሪክ ውስጥ ይገቡና የምንተመገብትን ጊዜ ስለሚያራዝሙት አይኑን ያፈሰሰብንን ቡና ቤተኛ ሁሉ፣ ዙሪያ ፈገግታ መግቢው ልመለስ ስቃረብ ሊያናግረኝ የፈለገ እስራኤላዊ፤ ወደኛ እስቀደሞ የዘረጋውን የቀኝ እጅ ጣቶቹን ወደመዳፉ መትቶ እናጠረና፤ አይኑን ፈጠጥ አርጉ፤ «ፈላሽዎች?... ልክ?... አልተሰባቸሁም አይደል?» አለ፤ ባለመደ የስራኤላዊያን የንግግር ስልት ሲበዛ ጉልበት ያነሳና ብሉም በኢትዮጵያውያን ትሁትናና አክብሮታዊ አቀራረብ አንፃር በለሀብት ቀም! ያስኛል ያስፈራል።

አደስ አልነበርኩምና ያ ዝሌፈያ መሰል አቀራረቡን ቸል አላልኩትም፤ «አዎ፤ ልክ ነህ!» አልኩት። የኔ ድምፁ ለሱ እዛል ከነበው ሰው የመጣ ነገር ነውና፤ የታሲ መድከም በተናገርኩት ላይ የተጠራጠርኩ መሰለውና «አይደለም? ምን?» ብሉ ጣቱን ገሪና ቀኝ ዘዋወረው። በርግጥ የጥቅስ ቿንቿ ነው፤ የትኛው? ምን ለማለት? እንዴ? ወዴት? ስንት? ሌላም ሌላ ጥያቄ ነገር ተኪ ነው። ሆኑና፤ ከትክረት አልቶጠርኩትም፤ እንደሱ በሀይል ባይገራም፤ ድምጼን ከፍ አደረኩት፤

«ልክ፤ ልክ ነህ!»

«ስንት ጊዜ ሆናችሁ? በሰሞኑ አፈሳ ነው የመጣችሁት?» ሲል፤ እያ ተበጀ ብዙ ያወራን መስሏቸው፤ «ምን ያወራል? ይህ ደዷ። እፉ አደብ ግ!»

«በሰሞኑ ንሸ (አፈሳ) ነው ወይ የመጣችሁት ነው የሚለው»

«አግዜር ያንሳው! ምን አበቱ አገባው? ቅጡ ቅጡ አረብ ይመስላል፤ ይኸ ነው የሚደብል፤ ሁሉም አንድ አመዳም። እበብ ገላ ሁሉ። የኛ ቢሆን የሰው ከሰው መለያው ብዙ ነው፤ ዳማ፣ ቀይ፣ ጠቆር ያለ፣ ሽምብራ መልክ፣ እንዲያ፣ እንዲያ እያለ ይለያል፤ እንግዲያ ድፍን ጠቢያግ ዝም ብሉ ጠይም ነው የሚባለው። ቢጠቀርጢቀላ ዝም ብለህ ጠይም ነው የምትለው። እዚህ ታዲያ የምታየው ሁሉ አንድ ነው፤ ችክ። በልማ፤ ሊያበላዝነን ነው፤ ይህ አውታታ!» ሲሉ በሁለት ችግር መሀል ገባሁ፤ ይሁንበት ብየ እነቸውን ተወት አድርጌ እሱን ከጀመረው ዉሻታ መዳፈያ ሳደርሰው አድል ሰጠው፤ ሀበሾች በፍፃኔት የሚደጠይቁት የመሰለኝን ነገር ሁሉ፤ «አድሜህ? ቤትህ? ሚስትህ? ደመወዝህ?» ሌላም ሌላ ጥያቄውን ከመቻል ጋር መለሸለት ለተረፈው ግን ይቅርታ ጠይቄው ወደኛና ስራቸው ተመለስን።

«በል፤ እንግዲህ!

«ክቡር የየረብሉም መቅደስ ጠባቂ...» ብለው አቿረጡት፤ ድምፃቸውን ገደል፤ ገምባራቸውን የሸሸ ሹበታቸውን መዳረሻ ደንበር የመዳሰስ አይነት ለበና መሀል ጣታቸውን ገጥመው በበራቸው ላይ አንሸራተው፤ በክንዳቸው ጠረጴዛውን ተደግፈው ፊታቸው ከፊቴ ሊገጥም ቀርበ፤ «የየረብሉም መቅደስ አስከባሪ፤ ልጅ ምናምን ቢጊን ብንለውስ ደስ ይለው ይሆናል፤ ሹምን ሲያወድሱት ነው ጉዳይ የሚሞላ፤ ይሆን ታስገበው?»

«እያ ተበጀ፤ ቤጊን የሰሜን-በየዳ የመንደር ምስኔ አይመስሉዎት፤ ከየረብሉም አልፎ የትና የት መስለውት የሚያበሉት፤ እጤ ሀይለ ስላሴን ልጅ ሀይል ስላሴ ብሉ የጠራ ማንን ያውቃሉ? እንዳሉት ቤጊን ይቅርና ቴወድሮስእንኳ ስንት

ተመኝተው ነበር የሄዱት፤ ምኞት ነው የገደላቸው፤ ቢጊን ከዚያ ያለፉ ሳይሆኑ ይቀራሉ?»

«ነገር አመጣህ፤ ያንንግ ቀደም የነገርኩህ አይደል፤ እንግሊዞቹ ቴድሮስ "የጦቢያ ባል፤ የየረሳሌም እጮኛ" ብሉ እንደደገመ የልቡ ሳይሞላ ቀረ፤ እሱማ ከዚህ ደርሶ ቢሆን ኑሮ ነጭ እያስፈረመ ሲያስገባኝ፣ እኔ ነበርኩ እያስፈረምኩና ወሸላውን ሁሉ እየቆረጥኩ የማስገባው። ግና የቴድሮስን ነገር፤ እግዜር ይሁን ባይለው፤ እኛን ደግሞ ይበደሉ ብሉን ነው እየረሳሌምን ሰላቶ ወሮ የቀየን። ሌላው ምበለቲክ" ሽርደዳህ ግን አልጠፋኝም፤ ያንተ ትረካ፤ እገሌ ሸንጐ ነው፤ ቢጊን ሱሪያና ጆርዳን ነው የሚወስው፤ ለበዋንንግ ወርሰታል። የምንሰማው ነገር ነው። በውትድርና ያለ የጦቢያ ልጅ ሁሉ ወሳጆን አሳብ አስገብቷል። ሁሉም ነገ በእጃ እንደሚሆን አላጣሁትም፤ በእስም የተዘራው እስራኤል ሲሰበሰብ ይች አገር የት ብላ የምትበታ ልትሆን ነው? እያዋዙና ጊዜ እየፈጁ በጆ ማድረግ የነበረና ያለ ልምድ ነው። ዳንበር ከሰራህ ግሬን አትርሳ። ባለም ያልተገፋ፤ ሳንድ ከበብ ህዝብ ብቻ ተሸብቦ የቀረ መሬት የለም። አንዱ አንዱ ሲገፋና ሲያጥር፤ ሌላው ሲያክበክብ ነው። በጫዋታ በኩል ስታየው ግን አንዱ ትገፋና እንዲያዝከው እርጋ ትላለህ፤ ውሉ ሲያድር ይረሳል፤ ሌላ አመል እስኪበቅል ያንተ እጅ እንዲሆን ይቆያል። በጦቢያው የርሽ ዳንበር ግራሬ አይነት አማረኛ እየው። ከጉልበት ያየለ ነው ይዘታን የሚያገኘው፤... በጦቢያም ቢሆን መጀመሪያ ጠበረ ከልክል ሳር ታጭድበታለህ፤ በሁለተኛው ፈልመህ ትተወውና ዝም ብሉ ከርሞ አሁንም ከልክል ትተወዋለህ። ባራተኛውና ባምስተኛው የበሳንጋራህን ጭንከርናና ልፍለፋ እባልፈህ ገምስህ እህል ትዘዋለህ፤ እንዲያ፣ እንዲያ እያልክ ልብህ ሌላ አዲስ ዳንበር እያወጣ በየሌሊቱ እያለመ፤ ግና የውነት ከሆነ፤ የሰው ዳንበር የለውምና ዳንበር እንዳልክ፣ ለመጨረሻው ዳንበር ሳትበታ ትሞታለህ፤ ልብህ አንዱን ሲይዝ ሌላውን ነው የሚመኘው። የመሰረት ጫዋታ ያነሳህ እንደሆን ወትሮ ያ ሁሉ እስራኤል ነው የነበረ። ከዚያ እልፍ፤ በግብፅ በኩል የመሲን ግረጊያ የሲናይ ተራራ፣ እረቱን ያጠበቅን፣ አረብ ሁሉ የኛ እጀ ነው ሊል እምሮታል። በስንት ድብድብ ነው የቀረ፤ የጠማሸው ነገር ነው። ይህ ሁሉ አልጠፋኝም። እየረሳሌምን የዚህ ሁሉ መናገሻና መናኸሪያ ለማድረግ አይደል "ብላኑ" ታዲያ እንግሊዞቹ ቢጊን ማስሽ እእምሮውን በዚያና በዚያ ከልስደደው፤ ይህ ዙሪያውን ሊቀራመታት ያሰፈሰፈ አረብ ልጆቹን እያዘደራቸውም። ከልቤ የገባው ጫዋታህ ግን ልጅ ማለት

ያገሰዋል ያልክ ውን ነው።

«በል ይልቅ!

«የየረሳሌም መቅደስ ጠባቂ የሚለው ብቻ ይበቃዋል።

«አሁንም እንደሆነ፤

«የጦቢያ ልጅ፣ ሀይማኖቱን ለማስጠበቅ በቆራጥነት ሲጋደል የኖረ፤ ብሉም እሪቱን የመከፈልት መከራቻና መውጊያ በማድረግ ተጋድሎውን በፀሎትና በምንና እያገዘ ከእስፍ እርዳታ ደርሷል። እየረሳሌም፣ ሁልጊዜ ከፍ እልተለየችም፤ ምንጊዜም በምስራቅ ነው የኖረችው፤ ከስራኤል ልጅ እልፎ፤ እስከም ብቻ ራቱን ትንሺ ወደመካገመዲና ዘወር ሲያደርግ በቀር ሌላው ጉድ ሁሉ በታሉ የሰውን ኪዳኗ መሰረት፤ መውጫና መግቢያ የሆነ በር ሁሉ፤ የሰውን ቀርቶ የጠብት በረት ባይቀር የሚሰራው በየረሳሌም እድግስ ትሁከል ነው። ፈላሻ ግን... ከፉ እልወርድ ያለ ታል ገጥጦኝ ተደይኝ ልምቶ ነው፤ እስራኤል በለው።

«የጦቢያ እስራኤል፤ አሁንም እንደሆነ፤ የጠር ነገር ባዘበትም ሆነ በሰንበት፣ በውሉ መቶ ጊዜ እየረሳሌምን ከራቱ እድርጉ እንደተሳለመ ነው የኖረው፤ ጦቢያ ያለውና ገና የመምጣት ተራ ያልደረሰውም ወደየረሳሌም እድግስ በመሳለም ይገኛል፤ ወደኛ። ምንጊዜም ያዝዘ ራስጌና የመስጊድ ግንባር በቅዩዩዋ ወደእየረሳሌም ነው የሚጠለው»

«ይስሙ እንጂ እያ ተበጀ»

«ቀጥል! ከንተ ጋር ነኝ»

«ያሁኑ ጫዋታም መሰረተ-እያያዙ... እኔን ሲረዳኝ የደጃፍም ይሁን የጠረቤበር እሰራር ረገድ የመጣው እማገስ (ነፋስ) ለመብጠ በተፈጠረ መስ ይመስለኛል። ያውሉ ነፋስን እመጣ ለብቻ ይተውትና፤ በጠዋቱና በማታው መጋቢያ፤ እንደሁም በሌሊትና በቀን ማጋመሻ እምብርት ሰእት እማገስ እዚሪው ሀይል ይበረታል። ይህም የሚበዛው ባግቢ ከከብ መውጫና መግቢያ በመሆኑ፤ በሁለተኛ ረገድ ያለት እንደሆነ ደግሞ ከቀጥታው የጨረር ምታት፣ ብሉም ከዚያ የሚፈጠረው ሙቀት ለቤት ጊዜ ሆን ለትጂኑ፤ ከቆንጫው መፍላት ለመዳን ከምስራቅ ሽረፍ መደረጉ፣ ከምእራብ በኩል ደግሞ መተገኑ ለዚያ ይመስለኛል። መቸም እብዛኛው ቤትን በደጃፍ ሊገባ የሚችል አውሬ ነፋስ እንዳይፈነቅለው የመጠበብ ነው፤ ታዲያ የእትዮጵያ በራፍ አሰራር የመጣው ከየረሳሌም ያምልኮ ፍቅር ነው ማለትም የሚመስል ጫዋታ ይመቻል? በርግጥ፤ የጠንደትን በኩል የምክራከረም አይሆን ይሆናል፤ እንዳሻም!»

«ጠልቀህ ባታየው ቀርተህ ነው፤ የልጅ ነገር! ይሆንንግ!

እግዚር ከመጀመሪያውኑ የተለመበት ነገር ሁኖ ነው። ለየረሀሉም ታልሺዳን ሲገባ ለሰው ምችት ይገባው ብለህ ነው? እየረሀሉምን በምክራት ቢያዋር እውቶ፤ እንግስን በደቡብና በሰሜን ቢያበዘ እውቶ ነው። ከሉ የሬጠራ ብልሀት የሚወጣ ጉዳፍ ነገር የለም፤ ጠሞ የሚታየው በሰው አይን ነው፤ ያም ሰው የመረዳት አቅሙ ትንሽ እየሆነ ነው። መችም ጠበር እስራር ብልሀትና ትርጉም የተጫፈ ነው። በምክራት ስልህ ደግሞ ትንሽ ሽረፍ፣ ወደቀኝ መታ ያደርገዋል፤ ደጃፍ መታሪው። በትህክል አይነ-ብልጧን፣ እየረሀሉምን የመተያየት መስ።

«በልግ፤ ነገር አልሰትኩም፤ እዚህ ባደስ አንተ ስተህል፤ እያሰጋኸኝ፤ የስትክ ይመስለኛል። በውነት እንጢር ግና እኔን ያስለበምኩ መሰሉህ ነውና በጣም ወብ ነገር ነው»

የስጡኝን የመጠየቅ መብት ልጠቀምበት ከመፈለግ ብቻ ሳይሆን በሆነ አጋጣሚ የቢተእስራኤል ተመክሮ የተነሳ ጭቅጭቅ በማስታወስና ብሎም ባያ ተበጀ ማብራሪያ እየተደጋገመ ሲነሳ ያየሁት በመሆኑ የመጣው ይምጣ ብየ ተከታዩን የማከሰሽ (መዉረሽ) ጥያቄ አቀረብኩ።

«መልከም ይኸ እንዲዘህ ይሁንና፤ ባሉት ልርጋና፤ የምንናና የገዳም ነገረወ ብጥብጥ ያስነሳል። በብዙ በታ፣ በገዳምና በምንና የሚያምን ክርስቲያን እንጂ ይሁዳዊ አይደለም ነው የሚባለው፤ አንዳንድ ደህን ያወቁና የተጨነቀ ቤተእስራኤላዊ ሰው ይህ የገዳም ነገር ይሽፈን ሲል ሰምቻለሁ። ስለሆነም ይህ ለምናሄም ቤጊን የሚገፍ ነገር ለዋዋቹ ራብችም ይደርሷልና መዘዝ ያበዙብናል። እንዴት ይታየመታል? ይህን ማንሳቴ፤ ከየፍነው ውስጥ እንድም በቂ ማብራሪያ እንደሰጠበት አሊያም የሚከሳ ነገር ካለ ደግሞ እንዲከሉት በማሰብ ነው»

«ይህች ናት ጨወት! ጨወት ብለህ ዝም! ግለፈያ! በጣም ግለፈያ! አንተ፣ እኔ ያንድየ ባሪያ፤ ይህ ጆልና የሚያደርገውን የማያውት ሁሉ እንዴት ተበሸቀጠብኝ? ምን ይላል ይኸ? ሰው እንደሁ ራሱን ከሌላው የሚያጣልጠበት ነገር፤ እውነት ከሆነም አበሸቅጦ፤ ካልሆነ ደግሞ ያልሆነ ነገር ፈጥሮ ሌላውን ሰው ማራከስ ይወዳል። ደግሞም ሳሜት የተሰራው ጥቂት አይደለም። ብዙ ነው። ገዳም፤ ምንና ብል፤ ምን ይመጣል? አንተ! ምን ይመጣለታል? መንጋ በሽታ ጠማቂ ሁሉ እለች እክስቲ! እየ በዚህ ውዝፍ ስራ ላይ ልታስለፈልፈኝ የምታመጣው ነገር ሁሉ መብዛት፤ ግና አልተወው!

በሽታ ጠማቂ።

«በወናናቷ የተሞላች እክስት እለቻኝ፤ መወነን ቢሉህ ደግሞ ባደ መወነን አይደለም፤ ከግብር-መያ የመጣ መወነን ነው። ውንንዋ የተሰራው ከተነገረለትና መልክም ነኪራ ያመጣውን የናሜ ገመድ ያዘል በልክ ከሚበጃጅሳት ባልትናዋና መያግ እጇ ነው። እገድም በቀጧ የዘራረፈቸውና የመጠንቸው፤ ስድ የጣደቸው፤ እንዲያው ያገፈሰፈቸው ነገር ሁሉ እንዴት ስትጨነቅበትና ስትጠበብበት ብትውል ነው? ያሰኛል። ለምህ እንዲ ከተነሳ ብታበላሸውም ተመጋቢው ዝም ብሉ ያመስግንሀል፤ የሚገመው ይመስለዋል፤ አለመጣም ቢሰማው ደግሞ እውቀህ ለዚያ ጣእም የቀናኸው ይመስለዋል።

«ታዲያ፤ እንዲከስቴ ያለ ግብርና መያ ያለው ሰው ደግሞ ከማህበር አይጠፋም። ማህበር ገብታ መጀመሪያ፤ የአደል ነገር፤ የማህበረ የመከፋቻ መብረሺያና ማህበሩን ያቀም! ብሉ መመረቂያ ተራ የቢ ይሆናል፤ በእጇ የሰላም ሆነ በስሚ-ስሚ ባልትናን እንደሰራው እንደምትሰራው ያውታልና መችም ወሰኑው ልክ ነበር፤ የማህበር መከፋቻው የቢ ሆነ።

«ወጡን ከንጀራው፣ ጠላውን ከብርዙ፣ ብሉም ከፍትፍቱ ራቱ "እንደሉ የማእድ ፍቅር ማንሸውን ሁሉ ጉዝጊዙን፣ ሰኔሉን፣ አጉዛ አጠጣሉን፣ ከጉዛ ስር የሚመቻቸውንና ዳር መከፈፈያውን ሙፈ ባንድ ረገድ፤ እደሚ የዋጠውን ሴት ከጉበጉቡ ሴት መተመጫ መሰፈሪያውን ሁሉ ገጥብገጥ ምንም አልቀረው፤ በጣም ግለፈያ እሰኝታ የገባውን የቤት ማህበርተኛ ሁሉ እነሆ! ስንበትን እንደህ እንደምንጨቅሳት ትጨነቅልን፤ እቤት ቅበለን! ብላ ትቀበለዋለች። ታዲያ የማህበርተኛ ሁሉ አቅል ይሳከራል። መችም የሆነው ሁኖ እጅ ይባርክ! እየተባለ ብተና ይሆናል። ባለተራ አይቀር አይደል? የሌላውን በውል የጠጣ እንዳንድ ደሀ-ባጋጣሚ እጅ ያጠረውእንኳ ለፍፎ (ለምኖ) ቢሆን ይከፍላል። ታሉ-ኪዳን ስለሆነ፤ ደግሞም በማጣት የተነሳ ከሰው ጋር በጨዋታና በዝና እንዳይለይ የማለት ትድረት ነውና፤ ልፈፉ ሲሆን ባለሰብ ዩ ሰውም ከደሀው ልመና ከራት ስለሚሽምት መስጠት ባይፈልግም ዝም ብሉ ይሰጣል፤ የሀብታም ሀብታምነቱም ደሀው በዙሪያው ሲያገበግብ ነው።

«ደሀነትም መምሚው አይታወቅም፤ ባይታሰብ ቤት ይታጣል፣ ከብቱን በሞነኛ ያየር፣ ብልሽትና ለውጥ የወረርሽኝ በሽታ ለቶበት ምጥጥ ያደርገው አይታወቅም፤ ችግር፤ ነገም ለኔ

ከማለት ልምድ ብሎም ደሀውን ከሀብታሙ የማባበቂያ መላ ሲበል እጣሁ ብለህ ስትለፍፍ እንኳ ይገኛል። ግና፣ ያክስቴ ማህበር አጣጪ ያጣው የህል ዘር አልነበረም፤ ሌላ የማይለፈፍ እህል እንጂ ባልትናና። የታዘበ ሰው "እርሸው ከላግረ፤ ደበው እያምርም ብሎ እንደተጫወተው። ከገቢቿበት የቤት መንጋ ሁሉ እንደትእንኳ ሙያ የመጠለት ትጠፋለች። አራተኛ፣ አምስተኛ፣ ስድስተኛ፤ እያለ ፅዋ በተራ ሲከፈል ከንደኛው አንደኛው ማህበር ቤት ይሸል ይሆናል- የሚመጣው በማለት፤ ደግሞም፣ ተደም የከፈለችው እንዲማረላት እየቆጠረች የየእለት ባለተራ ከፋዮዋን ደብዛ ስለምታግ ብዙ ነገር ይሸፈናል።

«ትር ሊልህ የቃጣህ ይመስለል፤ ጨዋታየ አልተግባባሁም መሰል… ከልታግ ተግሬ፤ ለሌላ ስትሳትኑ ይኸ-ይኸ አይታያችሁም፤ ተሞልቶ የተቀመጠ እቃ የምትደፈትም እንደህ እንደሌት የዋ ስትዛብሬ ነው። መልከም፤ መቸስ እንዴ ጀምረነው የል፤ እንቀጥል፤ በጠራሁልህ ውብ ነገር ሁሉ መልስ፤ ቤትህ አልባብ-አልባብ ይሸተትና እንደኔ መግት ይጣልብሀ። ባሳንጋራሁም አንድ አሳቻ የኒቢጡ መናጪ፤ ችጋራም ደህ ይሁን እንበል። ለምሳሌው እንዲያመች። ታዲያ ፍርድ ቤት ወጣን፤ አንተ ባለሲሳይ እኔ ደሀ። አንተ ልጊም አስበህ፤ ጃዋ ጥለህ፣ በነጠረ የቅቤ መጠመምጠሚያ እየታጀለ ሲሸት የነበረ ጠጉርህን ፈትተህ፣ ጥቅርሸ ሸሽህን ጥለህ፣ ይህን ጉፈሬህን ነክ-ነክ አድርገህና፣ በግሬ እቃ በቅሉ ሸልመህ። አረማመዱ በተገራ ልጅህ በቅሉህ እየተሳበ፣ አጃቢም ይዋርህል፤ ባለሲሳይ አይደለህ እበላ ያለ በጠገብህ አይጠፋም፤ መቸስ ብቻህን ሀብታም አትሆን፤ በሰው ብዛት ነው ባለጠጋ የምትሆነው»

«አያ ተበጀ፤ ምሳሌያወት በጣም ከበደኝ፤ እጠረደዱኝ እየመሰለኝ ታመሰኩ… ጥያቄየን ይመልሱ፤ ደህ ሀብታምና ደህ የሚል ምሳሌዎችን ደግሞ በሌላ ሰው ይቀይሬ፤ ጥያቄየን ቀጥታ ይመልሱ!»

«እነሆ! አልቀይረውም፤ ወደመልሰሁም እየመጣሁ ይመስለኛል። ምሳሌውን አልቀይርም ግለቱ እንዲገባህ፤ የዝና ጨዋታ አቀራረብ እንድትለምድ ነው። ተመልከት! መከባበር ያለ ነገር ነው። አሁን እወራ ተራኪው አንተ ብትሆን፤ እኔን በደሀ፣ ራብክን በሀብታም አትመስለውም። ሲሳይን ሁሉም ይወደዋልና ባይዋረውም ስትመስለው የሆነ ይመስለውና የውስጥ ደስታ ይሰማዋል። ውስጠ አከሳቱን ታስመቸዋለህ። አንተም ፍቅር ትገዛለህ፤ ገባህ?» ሲሉ ፈገግታ ወምረ የመስማማት እንገቴን ነታንቅሁላቸው። ኩራትና አደብ ተጭነው ወደጀመሩት የሙግተ ታሪክ ገቡ። እኔን ያቀነጠነጠኝ ግን ስለሴት የዋ ቀጥታ እንደናገሬ ነበር።

«አንዳንድ ነገር በመሀል እየጠነቀርክ፤ ከምን ደርሰን ነው ያቆምነው?»

«ተሟጋቾችን በየፊናቸው ሲያስወጡ ሲደረድሬ ነው

የቆመት። የደህውን ሰው አወጣጥ ገና አልነኩትም»

«ደህ? ምን አለው? በትሬ ወደል ዝግጢ፤ ጥቅና መዋር ምንጊዜም ከጁ፤ ውሉ መግቢት ከጉልበቱ ነው። አጥቂ ሲሰልሰው በሌላ ነገር አቸገሬዋለሁ አይልም። በፍንጅና በቶ ብሎም በበትር እያያዙ ነው የሚተግመነው። 'እያያዙን አይተው በትሬን ይቀመታል' የሚባለውም ለዚህ ነው። ልብሱም ሁልጊዜ መናራም ነው። ሌላም ቀንም የሚለብሰው ያንኑ አይደለ? ታዲያ ጋቢውን ከበትሬ ተሸክም ፍርድ ቤት ከተፍ ይላል። በግሬ ሲሳትን ከንተ የኩራ በቅሉ ይቀድማል። አንተ ታዲያ በመከበር አሊያም በገብ ተማምነህ ይሆናልና የመጣኸው፤ ግና፤ እስጠጠን አታውቅ ይሆናልና እንደከብቱ አገር መከተሉ መሰሉህ ከ ሂሳ ስትንተረፈፍ በታል አቀራረብ ለገብ መስጠትና ለመገልበጥ ባቅበታ በመጀመሪያው ፈደል መልዋ አድርጎ አስበፍልፎ፣ ልብ ስትገዛና መክሬ ሲከብህ በማታስገለብጠው ሁኔታ አሰርህ 'ወረቀትና ጥኝ ያሲያዙትን አይለቅም' እንደሉ… ዛሬስ ከወረቀትም ያግሬ ብዙ ያዥ ነገር ተፈጥሯል፤ በተሰብገርጋና በቴብ አስገብቶ፣ ገልብውን ጠይቶና ተሸልዋ ወደአቀበትም ይሁን ቁልቁለት ቤቱን ጅው ይላል። ይኸ እንጣሚ የሚሆነው፤ ደኛው ያንተን ባለጠጋነት ካለማወቅም ይሆናል፤ ከወቶ ግፉ በመጀመሪያው ፈደል ደህውን ይጠመዋል። ለምን ብትል አንተ ከሲሳይህ ጭነህ እንደምታመጣለት ያውቃል። የመግቶ ነገር ብዙ ዝና አለው። ሁለት የሚቻቻል ባለሲሳይ እንኳ አንዱ አንዱን ያጠቃዋል።

«ሁለቱ ሰዎች ፍርድ ይጋጠማሉ። በመሀሉ መግት ቀርቶ የገብ መስጠቱ ፉክክር ለደኛው ይወርደለታል። ደኛውም በጣም ሽለጠነ ኑሮ፤ ቀደም ሲል ጠሳው (ከግራ ተኝ) እንዲለ ሁዋ የመዝጊያው ፈደልና የመጨረሻው መፈለግያ ተከታዩ ቀጠሮ እንዲሆን ቁልቁሳ አስነፍቶ ይናገራል። ይህን ያወቀ ግራ ተኝ ተሟጋቹ ገበኛ በትለው ያምራል። አንዱ መለደ ብሎ ሸልንጉን በእጁ ይጭርና ከደኛ ቤት በጊዮ አስገብቶ ምንም እንዳልሰራ ከፊደሉ በታ ይወርዳል። ሁለተኛው ጅግና በቅሉውን አሸልዋ ከፊደል በታ ይደርስና በጉን መሳከተኛ፤ በቅሉ ለገብ ማምጠቱን ለዳኛ ጀሮ ሹክ ያስኛል። ያንን አድርጎ በቅሉዋንም እንድትታይ በዚያ በሬቀ ፍርድ ቤት ከጊዳ አልነበር! እንዲያ ይሆንና ደኛም ቀጣቸ ይቀርብና ደል ጣለ ብር ሰውየ ነው ብሉ እርፍ ይላል። እያ ቅርቁሩ ባለበቅሉ ደግም፤ ደኛው በቅሉ ለገብ ያመጣ መሆኑን ያልተረደ መስሉት፤

«ጌታየ፤ ምነው ለግኝ ባያራ ግጭ ብየ መጥቸ እንደህ ሰሰረኝ ሲለው ደኛ በመልስ፤ እንኳን ለግኝ ሲቀመጥ መፍ ሲጮህ

ያልሰማ ብር ብሎ ቀደመህ ብሎት ነገር በዚያ ይዘጋል። ታዲያ የዚህ ልምድ ስላለ፤ ገንዘብ ከሌለህ የባሰንጋራሀን መጠጊያ መንገድ ተሎ-ተሎ ብለህ መድፈን የነገር-አዋቂነት ነው። ሁሉም ነገር መላ-መላ አለው።

«እየህ! የኔ ነገር አንዱን ይዤ አንዱን ነው፤ ጨዋታ ለጀምር አንዱን ጥየ አንዱን ሳነሳ ነው። አለመን ሁሉ የከሳሁ እየመሰለኝ፤ አንዱን ሳልጨርስ ሌላው የዳር ጨዋታ መጥቶ ከልቤ መሸም፤ አንድ ቃል ለጥል ሌላው ጊዜ መከተል፤ በዚያው መሄድ መሄድ፤ መጀመሪያ ያነሳሁት ጨዋታ ሲታወሰኝ ደግሞ ለመመለስ እስከመርሳት ድረስ ደርሷል። ከረሳህ ደግሞ ጥልቀቱ መገኛ የለውም። እንዲያውስ ምን ብለህ መለከት ሲታይህ! የጠየቁኝ ከዚህ ከመለሱ ለለተኛቸው ቤት ሆኖ ባለ.. እኔ ታዲያ.. አይ ወዲያልኝ! ከገር ተሸግሬ ጠቢያ፤ የቀረ ነገር! ከጊዜ ደግሞ ተመልሽ ከምንልክና ከአባ ገብረሀና ጊዜ ጨዋታ። አእምሮ ሰክሬም ነው። ሰያሚ ተሳስቷል፤ ምነው ማለት ያዙሽ ነሬትና የጠላ ሀይል ሳጥር ጊዜ ከዳንኪራነት መዳን ነው። ሰያሚው ሳይመስለው ቀርቶ ነው እንጂ የመጠጥ ስካር ሰሳምና ሰው መውደድ ነው። እኔ እግዜርን በፍቅር የምተያየው የስከርኩ እለት ነው። ባዘቦት ቀን ግን ምሬት ይበዛል።

«ሴትዮዋ አሁን ግማሽ ስካር ላይ ነበረች። ምነው ማለት ሞቅ ሰብኳት ሌላውን ነገር ረስተዋለች። በእለም ከባተ የበለጠ ጉልበታም የለም። እብዱን ሁሉ ተመልክተው፤ አይተኛ፤ ሲዘር ሲዘር መዋልና ማደር። የሴትዮዋ አወዳደቅም ሀይል ነበረው፤ ግው ብላ ነው የወደቀችው፤ ቀደቶ ይስማት ካልሆነ ስትወድቅ አልተሰማትም፤ የሰበከን እኛን ነው፤ እንደሷ አልተሳከርንም ነበር።

«ታዲያ አይቶ ነበረች። የብዴቷ ታሪክ አለው። በጣም ረገሮም ታሪክና በብዙ አመት የተገነባ የፍቅር እብደት!.. አውራ ብለኸኝ የል?» አሉ። በሬተኛው ወሬያቸው ብዳከምም አንገቴን ነቃንቅሁላቸው።

«እየህ! የውነት ከሆነ ከሀዘን ቤትም የሚጨወት ጨዋታ ነው፤ ሰውን ከእዝነቱ ይለያል። ማንታቲያም ጭምር ነው። ተመልከት እንግዲህ እኔ ስጀምረው ሴቱ ከወደንዱ ሲያርመኝ እየመሰለ በጥያቄም እያንተራሰ መተባበሬ እልፈቶ ነው የሚሆነው። ጨዋታው እንዲደደናቶፍ ግን አደለ ገቢውን ለቅብ ደራሽ ያደርቀው በል! ደግሞም እዚህ ካዘኑ መሀል መብቅ ያስጀመርኩትን ሰው አልታሸ መጥቶ ባልቅብ ሲል አያምርበትም። የቢቂና የለቅሶው ግጭት እጊገል ሬት ይፈጥራል።»

ከወ..ነቸው መታ አድርገው ከተዘረጋላቸው ፍንጃል አፋፉን ለይተው በጣታቸው ዙሪሽ አቀረኝ ያዙትና ከንዳቸው አጠፍ ብሎ የፍንጃሉን ከንፈር ከከንፈራቸው ለማዘመድ የቡናውን እንፋሉት ይከለክሉባቸው ይመስል የግንባራቸው ስጋ ከፍቶር-ፊታ፤ አይናቸው ጭልመስመስ እያለ ደገመው ደጋገመው ጨመደ ዱትና፤

«ኧረዲያ! እጅ ይባርክ፤ የሀዘን ቤት ቡናም አይመስል፤ እጅ እለጠጣቸውም መስል? ያለውን ሰው የማስተበቃት ሳይሆን የተደበረ ወቃቤ ማፋቻ ተብሎ የዲጊስ ቡና ነው። በጣም የተሰማማ!» አሉና በድንገት ወደኔ ሳብ ብለው ከንፈራቸውን ከጆሮ-ግንዴ ገድም አስታከኩት። «እየህ! አስተናባሪው አይገደው አይደል! ባለቤቶቹ እንደምታየው የወግ ሊያደርሱ ተከፍለው ተቀምጠዋል። የዛሬ ጊዳ በርባሪያቸው በሙሉ ባድ ነው። ሁለተኛ ጉዳት የሚጉዱ አይመስለውም በእንትርት ላይ ጆሮ ደግፉ። እግዜር ሰውየውን ሲበርብርባቸው፤ ሰው ደግሞ ያን ተከትሎ በሰላይ ብርበራውም አጠደፋቸው፤ ዝም በል ዛሬ አይሰማቸውም፤ ሁሉም ነገር እየተብራራ የሚሄደው በሀዘን መውጫው ነው.. ሀዘን ጂሉ ብሉ የሚጋባውና የሚያንሰተሰታቸው ያኔ ነው፤ ሰውየውን ከንበረታቸው ለይተው ሲያዩ።»

ሰኔ ያሉትን ሀሜት ጨርሰው የቀረውን ቡና እንሚለጡና አተላው የሚሰራውን ለእል ሲያዩ ማንጠፍጠፊያ አፈር አለመዋረን ሲረዱና ሰሚንቶ ብቻ ሲሆንባቸው፤ ዙሪያውን ባይናቸው ተንከራተተው፤ የቀረ ቡና እንዳለው በማስመሰል ዥዋውንም (አተላ) እንዳገና ጠጡት። ባዶውን ፍንጃል ዘቅዝቀው እያኑት፤ ጠብ ያለ ነገር ግን አልነበረውም። ይህንን አድርገው እንደዘወትሯ አገር በግልፅ እያያቸው የራሳቸውን ፍንጃል በራሳቸው እየጠነቆሉበት እንደሆነ ሊያዩ አልፈለጉም፤ በጣም ዝግ አድርገው ባየር ላይ ወደከዳሚዋ እስጊዙት። ሁንም-አልሆነ የተሰራውን ለእል አጥርተው ሲመለከቱት ሰርቄ አይቻቸዋለሁ። በመሆኑም አሁን ወደተደገሰበትና ዙሪያ እምባሉሌ ወደዋለበት ጨዋታ ተመለሱ።

«እንያ አይቶ ነበረች። ዘሬ ቅባንትን ሳይሆን አይቶ ነበረች እልናት። አይወዲያልኝ፤ ይኸ ህይወት ማለትእክ! በል መቸም፤ ታዲያ፤ የተከታይ ወንድም ሚስት ካብሮ ማደጉ ጋር ከእሁት ቀጥር ናቀ። እንዲያውም እንዳንዷ አይቶ ከሀትም ትልታለች፤ የተባረከችውና ሰው የምትወደውን ካጋጠመህ ማለቴ ነው። እለዚያማ ወንድም ከወንድም የምታታትርም አይቶ አንዳንዴ ይገጥምሀል። ከእሁት ትልታለች ያልኩት ወገን በጣም ያናግራል።

እህትህን ለሌላ ስጥተህ ነው በምትኪ እብረህት ያሳደከት ፍጥረት የምታመጣው። እህት ምንጊዜም ኑሮዋ በውጭ ነው። ለከለ-መጠን ከደረሰች ሌላ አገር ልታቀና ትሄዳለች። አብዛኛው ወንድ ግን ከተወለደበትና ካደገበቅ የእባቱ መሬት ላይ ነው እንዲዋርከው የሚሞተው። ሴት ግን ያገባችው ሰው የመሬት ደሀ ካልሆነ በቀር ወደእበቷ መሬት እትዘምትም። ዛሬ ግን የዚህ ነገር ወደየት እንደሚያመራ ገና አልጠራም። መሬት ምንጊዜም የመንግስት ሀይለግርያም ነው ተብሏል። ግና እህት ወብ ናት፤ እርታ እንደመሄዷ እብሯት የተሰደደው የዘመድ ፍቅር እብሯት ከርሞ ስትመጣ ስጊቱ ልዩ ነው። በዚህ የተነሳ "ዘመድ በረቅ ያምራል" ይባላል፤ የሌላን ጠብና ቂም በሽምግልና ያስታርቅታል፤ በመሬት የመጣ ጠብን ግን ወገድ ብትለው እይሄድም፤ ሆድ አይደል!

«ታዲያ የሁለት ወንድማማች ግቡት ሲጠጣው በወንድማማችም ፍቅር እብሮ ይሰፍናል። አንደኛዋ ባልትና በሰመረለት ጊዜ ገንበም ይሁን ቅል፣ የተከሸነ ድስት፣ ሌላም ነገር ሁሉ ቢሆን የሁለቱ ባሉች በሌሉበት አይከፋትም። በሁሉም ዘንድ ፍቅር ለመሰበቅ፣ ግብዣቸውን ድንገተኛ ለማድረግ ውድድሯ ከልክ ያለፈ ነው። አንደኛዋ ግባስል ሲታያት መጀመሪያ የምታጤነው ያማገሱን እቅጣጫና እንፋፈስ ነው። የተሳሳረው መንገደኛ ሰው እፍንጫ ሽታውን እንዲያነሳበት ስኔሱን፣ እገዛውን ብሉም ይህ እልበታት ከለ ደግሞ ነጠላና ጀንዲውን ገልበ፣ አየር እንዲዘወርበትና ትሂን፣ መጀሊ፣ ብሉም ቀንጫ በመቀት ሀይል እንዲይፍ ታስበ በምታሮ እርቀት የተሰራውንና የተማገረውን ግድግዳ ትከትረዋለች። አመለጡ ሽታ ቢሄድበት ምንም አይደል፤ ለየንፍሱ ሁሉም ያበስል የል? የድግስ አይመስልም። ደግሞም፤ እጅ የሚያደልበት ነገር ሁሉ በእውቅ እንዲይነስ የማድረግ ብልሀትም ነው። ምን ያለፋሀል መጨነቿን ያለግባወቅ ፕረት ነው። እመለፕ ጠረንም ክፋት አለው። ብንብን ሽታ ስልሆነ እሳሬውን በጣም ነው የሚበጠብጠው። እፍንጫየ ያዘው፤ እልያዘውም፤ እመለጠኝ እያለና ናላው እባዘረ ያልፋል። ጨዋታየን አገኘሽው? በተለይ ለራብውና ከባለመያ ለራቀ መንገደኛ ግለቴ ነው።... ገጥሞህ እያውቅም?» ሲሉ መመለሱን ቅቸ በሳቅ ስወረር ተመለከቱኝ፤

«እንተ እግኝቸሀለሁ! ቢሆንም የዛና አይደል! ግየትን የመሰለ ነገር የለም። ጨዋታየ የገባህ ብታውቀውና ቢደርስህ ነው። ለጨዋታ ስሆን ልብ እትበለው»

«ተቢ፤ ምን እልኩያ? የስደቡኝ አይመስለኝም፤ መሳቴ ብቻ...?»

«ተግባብተናል፤ ይልቅ ይባርክህ! ባማንወም ሆነ እዝመራ

ስለሳ የሚገዛው ወንድ ሁሉ ወደቤት ከመመለስ ላይ ዘገምገም ይላል። ጠሀዩ እየሞቀና ጠዘው እረግጦ ተፈገን ማንሳት ሲጀምር ድስቱ ከመቀቅ ይበርዳል። የውጭው መጋል ከጠሀዩ፤ የድስቱ መበረድ ከባት መራቅ ነው። ይገባሀል! ወዳጄ፣ ታዲያ ወስምቢያውንና ድስቱን በመሀል ያማገረው ወጉ-እንወቅ ተገምስ ሲገደም ለበ ያደረበት የጌትሬ ስቀላ ይመስላል። እያሌ ስእቅ በጥናቡግና ወሀ፣ በክርክም ሳቅ የተደየነው ሽንኩርት ከቅመሙ ቀለም፣ ከደርሙ ስጋና ከቅቤው ለኸቅ ገዝቶ የሚያመጣው የጠረን ሀይል ዝምብ ይገፋቅራል። የነጠረ ነገር እይደል? ዝምቡ አይቀርበውም። ዝምብ ቆሻሻ ነው የሚወደውና እንደህ ባለው ግብብ እከባቢ አይደርስም። ይልቁን በእበዛበውና በእጣቢው ይበዛል። ሌላውን ተወው፤ ስኳርና ማር ጃል ነገር አይደል?»

«እንዴት ብሉ እያ ተብጂ?»

«ምን ቢጠራና ቢነጥር የሺፈተ ዝምብ ሆ! እሰኝቶ ጥምብ እጥራውን ይጠራውን ያህል ነው። እዚህ ላይ የውጭ ሰው መመለሽ ጊዜ ደረሰ። በውጭ ያረፈደው ወንድ፣ ቀኝ እጁን እያወጣ፣ እንበለ-ቡሪ ያገደመውን ጋቢ እያወናጨፈ ዝም ብሉ ነጣ! እንደኔ ያለ ግራኛ ከሆነም በቀኙ በኩል ባንድ እጁ ግረራ በሌላው መወደሪያ ጭራውን እያወናጨፈና እየታማወበተበት ይደርሳል። ወደላም ግራከብ ነበርና የወጣው በትረ ጭራው ስለሆነ ቅመጥ የለውም። በጭራው ነው ከብቱን የሚነዳው፤ ከብቱም ቢሆን አንድ ጊዜ ከባለቤቱ ጋር ማደርን ለምዷልና እንኳ በቀር ተወምርበት የቀጠ ደምፅ ሲወጣ ይብረገረጋል። ሆን ብሉና አውቆ ይታዛዘዋል። ይህ የማወራህ እንግዲህ ባንዱ ወንድ በኩል ያለውን ነገር ነው።

«ባለቤት ቢሆንም ወንድ ልጅ ከደጁ ቆይቶ ሲመለስ እንደደረሰ ዘሎ ከቤት አይገባም። በጣም ብልግና ነው። ከወለል የተልከሰከሰ ቿንቅራና... የምትሳበስም ሴት ትሆናለች። መቼም የቤት መንግስትነት በሴት በኩል ያደላል። እጊጊልና ተሰቶህ ከምድጂ እግርህን ስድ ስታራጥጥ እንዳንዷ ሀይለኛና ከስታራ ቤት ስድቢ ጭንቅ ነው፤ ምን አይነት መዘርጋት ነው? ሰው ሁሉ በልክ ተሸከፎ መቀመጥ እያውቅም እንዴ? ትልሀለች። ከእንዲያ መብል ያድንህ። ሴት ምንጊዜም የተሸከፈችና የተቀጣች በመሆኗ እሷ በዚህ አይነት የምሳሽ ስድብ አትገኝም። ይሆንም ተወው፤ የቤት መቼም ሀይለኛዋ ትበዛለች፤ የግብ ፈታድ ለመቀበል በተዛነቡ ግድም ይልከሰከሳል። ከቤት ውስጥ የማይሆን ነገር የለም ብየሀሁ፤ የዳወረ ደሮ የደፋው ይዋራልና ይሆን አይነት የቤት ገመና ለመሸሸግ ግብ ግለት የቤት ነው፤ እንተየ ግብ

እንጂ መልክን የመሰለ ነገር የለም። ወንድ ልጅ እርግትን የሚማረው ከሴት ነው።

«ገበ! መልክን ትኩረት ያደረገው ወንድ ታዲያ አስቀድሞ ለምልክት ኧ-እ-ሀ-ሀ-ሀ -አገሮቹ መወደሪያ ጭራ ተቀበሉን ይላል። አንድ ሚስቱን እንደድፍን አገር ይቆጥራትና ራሱንም እንደሚልዮን ሰው ይቆጥረዋል። እኛ ማለት መቀጠሪያ ወሰን የለውም። አንድን ብዙ አድርጎ የመጥራት ነገር ልምድ ከማፈር የመጣ ነው። ሴትም እንግዲያ ግልጥ ነገር ነው፤ ብዙዎቹ አፈራም ናቸው። እንደነውርም የሚቆጠርበት አገር-አገር አለው። ዝም ብሉ አንቺን አይደለ! አንተን አይደለ! የሚባበል ጥልቷል። ሰውየው ታዲያ የመጣሁ ምልክት በጥቶ የለ...

«የረፋድ ራብ በጣም ያፍተለትላልና የተሰናዳችና በማብታ ሙታ የነበረች ሚስቱ እንደገና ነፍስ ዘርታ ምነው! በውጭ የምትቀሩ ናችሁ እንዴ? አገር በጣም አማን ነው፤ ግቡ! ትላቸዋለች እየሄደችና እየተራመደች። በተራዋም ምልዮን ሰው አድርጋውና ያረፈደበትን ሰበት በክብት መወደሪያ ገመዱ አሳልፋ ልትወጣው።

«መሰሰም የለውም፤ ግና የሰውነቷ ስብከት፤ የያዘውን ጭራ ስትነከው እሱንም ይለብከዋል። የተሰታት አስመስሳም መዳፉን ገድም ትነከዋለች። ታዲያ ትቀበለውና ሲሰ የዋ ባለበት እንዳፀና፣ ሁልጊዜ እንዳለበች እንድትዋር እምሳኪን በምስጋና ድርደራ ልትወድረው የሷም መወደሪያውን ከገረራው ላይ ለማዋል እያጓጓተች፤ አለሞቸ፤ ቢስ አይያችሁ፤ ወላችሁ ግቡ፤ ከራቴ በናንተ ላይ ነው እን-ት-ፍ-ት-ፍ-ት-ፍ ትልበታለች፤ ከገረራው ላይ፤ እንዲያው ለደስመላና ለደስታ መገለጫ ያሁ-እንጂ እሀል ያልቀመሰውና የጠመነው ምሳሲ ምን ምራት ሊወጣው።

«ትኩሱ ወተት እስኪበረድና ግማሽ የጥንስስ ዙረሽ እስኪጥል፤ የምድጃውን አይነታ ጤስ ከሚቀበለው መሪ ውንግራና ድመት ከማይደርስበት ተንጠራርታ ትሰቅለዋለች። ቅቤና ጤስ ለገረራው ይበጃል። ወተቱም ተሉ መቀት እንስቶ እንዲያዘርና ወደመገፈጃ እንዲገለበጥ ይረዳዋል፤ ታጥዋ ለማታው ጥጃ እርከቢያ እንዲደርስ የመሰበም ጥበብ ነው።

«ታዲያ ባንድ ገብ ወንዱ አይገባም፤ በሁለተኛው፤ አትገባም እንዴ? አንተን አይደለ! ብላ ድምፁን እንደጥና ጠሪ ትጎትተዋለች፤ ወዲጃ የሚቀራ የእስላም ክታበኛ ደረሰ ይመስል የድምፁ ውበት ፍቅር ይጠራል። እስትንፋሷ ይነግርሀል።

«ባልየው በበኩሉ በኩራት ይታሸል፤ የራሱ የሆነ የፍቅር መስሪያ መሳ ይዋረው ይሆን የል? ታዲያ ልቧን ሊሰቅለው፤ ም-ን-

እኩ! ደርሴ፡ የፍየል ግልገሉ በዚህ በኩል እወራ ጉዳና አበጅቶ ንበቹን ጠባይ የሚነሳብኝ ባይሆን ይቀራል? ችፍርግ፣ ጡንጅት አሊያም ከሴው ለሹታው ውብ ነው። ከሽሌው ከቅርብሽ ነበር-ቀንሺ ብትጥይበት ያስጥለው ነበር። ግልገልና ዶር እትሙ ከጭራር አያልፍም ይላታል። እሱ እንዲህ እያለ እሷን ከወስጥ እንደሙዳይ የያዘውን ቤት ከመሀል ላይ አግከሉ በተዘነቡ እምባሉሌ እባረ የፍቅር ዳቂቱን ይደግምባታል።

«የተንከሉ፤ በዚያው አይቱን ከሬቅ ይጠራና ክርቀቅ ያወራል። ሚስቱ ግን ድምፁን ብቻ ምግቡና ቀለብ ታደርጋለች።

«አይቴ! ምነው ደሀና? አይተ የዋጠች ድመት ይመስል የጎረሰሽው ነገር አለ መሰል? ሌላ እንዳይባል ባልሽ ገና ከረፈደበት አልተመለሰም። ይኸው ገና በግዶው እየወረደ ነው። ይቅርታ ድምፅሽ በጣም ተሰወረብኝ ብየ ነው ሲል አይቱ በመልሱ፤ ያንተ ቀልድና ተረብ መግጫው አይታወቅ፤ የጎረሰኩ ብጉርስ ነወር አለበት? ጠሀዩ ያልሄደ መስለህ እንዴ? እየዘ አትርሰ፤ ሴት ያለጉርሻ የምትዋረው ትልቅ ሀጢአት ሲወርድባት ነው። በልግ ይልቅ ወደዚህ ግባ! ትዳሬ እየመጣ ነው ብለሀል። ቡና ማጠብ ጀምሬያለሁ ስትለው፤ መችም የሴትን ውድድር ታውቀዋለህ.. ውድድር ወደፉክክር ከልተለወጠ ጥቅሙ ያይላል። ያልሆነውን ሁሉ ያናግራል። ስለ ፍቅር አይነት ውሸቱ ሁሉ ይበዛልና ግረራ ተቀብ ዶዋና ባሏን ከጥጂ የያዘችው ሴት፤

«መሸሪቷ የጤናሽ ነው? ቀድም ባትናገሪ? እዚህ እኔ ቡናውን ከሰቶ ላይ ከዋልኩት ስንት ጊዜ ሁዋታል? ስትል፤ የሴትን መላ ቤት ታውቀዋለችና፤ እናቱ! መናገሬ መቅደሜ መሰለኝ? ከኔ በፊት እንኳንስ ቡና ሊቆላ ቀርቶ እዚህ ያረፈደው ቶሎም አልተናገረ። ብረት ሲንኳኳም አልሰማን። በዚህ የቀርቀሮ ዘመን፤ እንደወዲያኛው ዘመን በረጅቱና በገል ጣድሽው ልበል? በይግ ያንቸው ቡና ጠሀይ ምላሽ ይሆናል። ደግሞም እድግ እሬሪ፤ ቀድሜሽ የተሞሸርኩት እኔ ነኝ፤ አይደለ አማቸ! ትላቸዋለች እሷን ትታ ወደእሱ። እገረ መንገዷን የልክ የልኳን ነገራት፤ የትልቅ ቤት ምንጊዜም ግንባር መሆኑን አሳምራ ረትታት ስምምነት በዝምታ ይወርዳል።

«ባቱ እየተንበለበለ፤ ቀድም ፈልቷል ተብሉ የተቀሸበት ቡና አሁን ተጣደሁ፣ ቶየሁ እያለ ከመንገድ ላይ ያለውን ወንድ ለመጠበቅ ሁሉም ነገር በመላ ይታሻል። ቀድሞ የመጣው ወንድ እንደተባለው ከወንድሙ ቤት ገብቶ ከተጉዘጉዝ መደብ ላይ ተቀምጧልና እንደ የቡና መወቀጫውን ብረት አሊያም መደቆሽ እለሉውን፣ ሌላ ጊዜ መቀጫ ልጁን፣ እጣኑን ከፍንጃሉ ስታገጥና

ስታጥዋል፣ ጀበናውን ስታስቀልቅ፣ እንዱን ስትጥል ሌላውን ስትጀምር፣ ቡናው ፈልቶ የቀረበለትና እግሯ ብቻ የሚሰለፍበት ይመስላል። የተሰራ እንዷም ጥና ነገር ገና የለም። ተቀማውን እንደሁ እያታለለችውና እንዳንድ መጠመሪያና ማላዘቢያ ቃል እየወረወረችለት እሱም እየመለሰላት፤ ከውጭ የቆየው ወንድ በድንገት፤ መቸም በድንገት በለው፤ ኧ-ና-አ-ፈች ሁ! ይላል። ቃል መስያ ተብሎ የተመደበውን ሙሉ ሆኔ ሁሉ ይነሰዋል። እንዲያው በመዘታው እሰስሁ ነው ደሀና አረፈዳችሁ ማለቱን የምታውቀው። ይህኛው ወንድ ታዲያ ዘሎ ነው የሚገባው። መጀመሪያ የገባው ወንድም ከበቢውን አሰልቶታልና ከ ሂሳ የመጣውን ደጅ ላይ ቆሞ የግባ ቃል እስኪቀበል መደየን አይገጥመውም። ሴት መልከስከስ የምታበዛው ማንም የለብኝም ስትል ስለሆነ አሁን ግን የገባው ሰው አሰናድቷታል።

«የተቀመጠው ገቢው ያረፈደበትን ያዘመራ ሰላ ወሬ፤ ጃርቶን፣ አይጡን፣ የፍልፈሉን ከወፉ ሁኔታ ከጠየቀውና ያም ከጠምጠው በ ሂሳ የሚሰቃቅሰውን ልጥም ሆነ ያረፈደበት ገመድ በግድግዳ በማገሪ ከሰጠ በ ሂሳ ታናሽ ወንድሙን ነወር እሰኝቶ ሙት ይቀመጣል። የወንድ ዘር ከመደብ ላይ የዙፋን እጂ ይጥላል። ሴቶቹ ያረፈደበትን ለማስመሰከር በቀራረብ ስልፍ ቤቱን ያዘፍኑታል።

ተቸናፈጥ የታናሽ ሚስት፤ ዘገምገተ በማለት ነጠላዋን ትሳበሰውና፣ በንድ በኩል እየከተረችው፤ ያመለጠው የድስት እክል እየታየ፣ እንዳንዱም ማስተመጫ ስሬቱ ሌላ ነገር እያስመሰለው፤ መቸም፣ እንድ ሙብ ነገር ይዛ ከሸን! ከይቷ ማጀት ዘው ትላለች። በለማጀቷም ሆዷ የሚያውቀውን እውቶ እያጉረመረመ እፏ ግን ሌላ ጨዋታ ይቀራል፤ ከሰው ማጀት? ዘሎ ጥልቅ፤ የጠፋሽ ነገር አለ እንዴ መሸሬት? ትላታለች ፍቅር ማስጠመኛ የእውቅ ንግግር ነው። ብታውቅም እንዳላወቀች ዝም ብላ ትጠይቃታለች። ከድስቱ ሙቀት ጋር የሚሄድ የበረደ እንጀራ እንዳለ ጠይቃ ያወንታ መልስ ስታገኝ መደላደል ይከተላል። ትኩስ በትኩስ አይሆንምና ወጥ ትኩስ ሲል እንጀራው ሙቀት የጠላ መሆን አለበት፤ ከዚያማ ምን ልበልህ! የምታገባትን እጢርታ የአርፈሽ ተቀመጡንና በቤቷ ሁሉም የኔ ፈንታ ነው መብልን ተቀብላ የዚያን ማጠጫ ምን አይነት ናት እቴ! መርዳት ነወር የሰበትም፤ ደግሞም የቤት እንግዳ አልተፈጠረም ብላ ታዝናናትና ቀላል ቀላሉንና ከፊቷ የሚታያትን ሳት መቶቡቶሰም እንድ ሙብ ስራ ነው። በዚያ-በዚያ ትራዳታለች። ቡና እንዳከዳደሙ ተከደጥ አራት ሰው ልጅ፣ ጭጭ-ምንጭጭ በሌለበት፤ ወሽና ድመት ግን

ምንጊዜም አብሮሀ ነው፤ የጦቢያ ሰው ከመጉረሱ በፊት ጉርሽ ለማይናገር እንሰሳ ማደል ያስተደማልና ቤቷ አስተደግ ትለበምበታለች።

«አሁን ታዲያ ግድ አይደል! ግብር መስራት ሲጀምር የሁኔታው ነገር ልዩ ነው። ከፍቅፍቅ ፊቱ የሚገባለውን መሳ የምታገኘው ያኔ ነው። እንዲያ ሲጨነቅበት ከዋሉት እሁል እግጊት ሌላ፤ ሲያንስ መጠበቂያ እንጀራ ማቅረቢያ ቀለምሽሽ፣ አይነታ ግብር ማግቢያው ሞሰብ፤ የድስቱ አፈጣጠር፣ የባት ልብሉ የእንጨት ማንኪያ ተዳምሮ እንድ ፍቅር ይሆናል። ለዚህ ማከያ ደግሞ ግድ መቅላቱ የማይገባኝ ልምድ ነው። እንደሁ እያለ ነፍስ ያገባው ሲከረተረት እንተ እግዜር እትሁን፤ ልብሁ ነው የሚሰቀለው። ነፍስ ያላገበው ከታራማ እንግዲያ ደርሶ ነው የሚዘነጥለው፤ ይህን ያወቀ ዘሎና ፈጥሮቆ ከልያዘው በቀር። ታዲያ የቤቱ ባለቤት... እህሉ ቀርቦ የል?

«በል እንጂ ከንዴ? ግባና ቅረብ ወ! ይለዋል። ግና፤ እንግዲው፣ ምንምእንኳ ወንድምና ጉረቤት ቢሆን በጆ ብሉ ዘሎ ከበው ቤት ከተሰራ ግብር አይበርከም። ቅስና የሌላቸው ቢሆን ጨዋው ጨዋውን ይገራዋል፤ ልምምድ የመስጠት። ታዲያ ትልቅየው ትንሽየውን ያበራታዋል። ይህ ቢሆንም እህል በተሉ ሰልቶ መቅረቡ በጣም ይዘገያል። ሴቶቹ የቀረበውን ፉክክር ሲመለከቱ ከንዳቸውን ከታጠፈው ገልበታቸው ቀጥለው ቁመት እንዲጠረው ወንገሪ ያጠጥሉታል። ከንፈሯቸውን እንደወፍ ማውጫው እንጀራ እያጠባለሉና ያሽጊጠጡ እየመሰለ፤ በሚሰራረቅ እይን ሲመለከቱት በልባቸው የሆኔት ናዳ የሚያወርዱ ይመስላሉ። ጨዋታውና ዝናው የሴቶቻቸው ስለሆነ ከፉክክሬ የሚወጣ መውደድም አለና- እንዲያ ነው። ምጣት ክርክር ካለፈ በ ሂሳ ሁለተኛው ዙር ጊዜ መገደያ ይጀመራል።

«እሁሉን የሚቀርበው ሰው ከጨዋታ እለም የተፈጠረ፣ ምኞት ሁኒናውን በጣም የደወረው ከሆነ መጀመሪያ ግብር ገቢውን አይን በግዱ እናቱ ላይ እንደሸረፈት እንዲሽከረከር ያደርገዋል። አይን መጀመሪያ የሚያነሰው እንቅብቃቤን ነውና፤

«እግዚእ! ማዳችን ጠረከት አድርገው እስቲ እንተ የሰራ እል አምላክ ብሉ እጁን በላዩ ላይ ያንከራትትበታል። ከማእከሉ ላይ ሲያወለው የሚይታይ ምሰስ ከመሬት ወገቶ ሞሰቡን መሀል ለመሀል ቀዶ ወጥቶ የደገፈለት ይመስላል። አይኑን በሙሉ በማእዱ ላይ ያስተረጥዋል። ያልኩህ ለዚህ ነው። እንዳንዱም ሞሰቡን ነቅንቅ፣ ነቅንቅ ያደርገዋል። እህል ያን ያህል ተከምሮ ቀርቦ፤ የአብርሀምንና የሳራን ማእድ የጠረከው ጌታ፣ ይህንን

ግድም በረከት ያወርድበት፤ የወጣ ይግባ፤ የታመመ ይዳን፤ በሚጠባ መሀል ሰላም ይወረድ፤ ደመናውን የበልግና የሲሳይ ዝናብ ፈጣሪ፣ ወሀቦን የመቶቅና የቡቃያ ጉልበት፣ ወረታዋን እንስሳት በቸር የሚበላከበት ቅሁን። ለሰብና ቀጤ ግን እግዚር በእውቅ ጋርዷት ዳኛንታም ቅሁን። በቸር እንዳነጋኸው ለሊሊት በቸር አብቃን። የከርም ሰው ይበለን፤ ያረገዘ ይወለድ፤ ያልያዘውን ማህጠንም እንዲይዝ አድርገው። ሀገንና እምቦሳ የሚገናጋበት መንደር ይሁን… እያለ፤ የታየውን እስኪወርስ ይቀጥላል። ማገሹ ሰድብም ነው፤ እርግዝና እምቢ ያለቺ ሴት ከሆነች ከዚያ የምርቃን ማእድ ከምትገኝ መሟን ብትወል ይሽላታል። ይህ ሁሉ ተሸክፎ በንድ ሲመጣ ከ? እስከ የሚደብል የሀል ፍቅር ይወርዳል። ይህ ሁሉ መሳ ፍቅር የመስሪያና በሀል ላይም የመታገስ ልምምድ ነው።

‹ከሀል ላይ የሚሰቅን በለሳውም ሰታናም ይሆናል። የጉንደር ሰው እንኳን በራሱ እጅ የሰራው ማእድ ይቅርና እገር ጥሉት እንግዶነት ቢሄድ መቶ ሳይገለገል ማድ አያሰራም። ስለዚህም ነው "ጉንደሬ-ገደርዳሬ" የሚባለው። ጋባዡ ሰው ምን ያሀል ቆራጥ እንደሆነ የማወቅና የመፈተን መሳ ነው። እውነተኛ ጋባዥ ሰው ከጋቢ አሰባቡ ቢነገርህም ደጋግሞ ማጠራት የተገባ ነው። አንዳንዱ ሰው በይሉኝታ ብቻ የሚዋር፤ አንዳንዱም ያልታሰበከ እንግዳ ስለምትሆን እንዳዳረስከ ልገልግልህ የሚል አለ። ስድ ገብተህ ያደግልህን እድምቶልህ ከወጣህ በኋላ ባምንት የሚተክዝ ሞልቷል። ከዚያ አልፎ ምንው የመጠበቅን እገር ሰብሮት በሆነ፤ የበላው ቅወከት ይሁነው! ብሉ ይረግምሀል። እይዳርስም እደብልም፤ የሆድ ሀዘን እድሜ ይበጥሳል። በሸታ ሊለትብህ ይችላል። ለራሱ የብዙ ቀን ቀለብ ብሉ ያስቀመጠውን ወይም ያበጀውን ነገር ከውነህበት ስትሄድ ደንጋይ አደበላ! ታዲያ በግብር ነገር እርጋ ማለትን የመሰለ ነገር የለም፤ ያ ሁሉ መታሸት ከወረደ በኋላ ተደም እንደነገርኩህ ከጠገቡ ያለውን ፍጥረት እፍ ሸሮ ነው የራሱንም እፍ የሚሸረው። ወሽ-ድመት፣ ሚስቱ፣ ሌላም የታየውንና ሲደየን የዋለውን ሁሉ በመጀመሪያ ያጉርሳል። የጉርሻው ልኪታ በደረጃ ያድጋል። እንደመቢያ በሀል የተቀጣ አገር የለም! የዚህች ሴትም ዳብ እንቅና እብደት ይሆን እይነት ሀይወት ያለፈች በመሆኗ ነው፤ እማቿ ቢሆንም ከወንዶቿ አብልጣ የምታየው፤ ያመለኛ ጊዜ ጊዷ ነበረ!

ሸንጐ

ቀቅር እከባቢ የተጠነሰሰው ሸንጐ በተገኙት ሽማግሌችና በተወጣጡ ወጣቶች እስራ-ሰለቀን ተንተርሶ፣ ከዘን ቤቱ በጎደና ክፍል ተጀመረ። ለሊቱን እንደከሄድ የተደረገበት ምክንያት ነበረው፤ በወቅቱ ቤተእስራኤሎች የቡድን ማህበራት ቀጥር ወደሰር የደረሰበት ጊዜ በመሆኑ፤ የሚቃረኑና ከመናከከር የተነሰ እብረው መቀመጥ የማይችሉትን ሰዎች የማሰወገድ መላ ነበር። ይህ በንዲህ እንዳለ፤ የዚህ ድንገተኛ ሰብሰብ ተሳታፊዎች በሙሉ ወዳንድ ማህበር ያዘነበሉ ሳይሆን አብዛኞች የሀዘንተኞቹ እቅራቢች በመሆናቸው፤ የቀረት የተፈጠረ ማህበር ቢፈጠር የማይገደቸውና ይልቅ የህዝብ ጉዳይ ነው ከሏቸው የትም ለመገኘት የሚችሉ መሆናቸው አጋጣሚው ልዩ ነው።

ስብሰባውን በቡና ከፈቱት። ወደይቱ እንደከሄድ ከቀነቀኑት ጉረምቦች መሀከል አንዱ ጉሮሮውን ሰሎ፤ ሊዋር የሚገባውን የስብሰባ መስመር በራሱ የመግቢያ ቅኝት ተነተነ። ሲጀምር የንግግር ዘይቤው ለገጠሬዎች ብሉም ለሽማግሌች እንዲረዳ ተጨኔቀ፤ ቃል እዘራረፉና መዚቃዊ ቅኝቱ ልክ ገጠሬኛ ሲሆን ለከተሚ·ቀመሰች በጣም ደብሮ ታየን። ጊዜ እየሸሸው ሲሄድ፤ የመሸማቀም ይሁን የስሜት መነከቅና የመዘንጋቅ፤ ከዚህም-ከዚያ (ከገጠሬውም ሆነ ከከተሜው) የንግግር ስልት ሰብቆና እላግቶ ጉራማይሌ ሆነ።

‹እያችሁ! ወገን፤… ዘመዱ! የዋለብንን ንቅርክና ብጥብጥ መሰል ነገር እንደያ ወቅሳ ሳለን እሪክ-እሪክ እንለው ነበር። ብጥብጡን የሚያደነው ነፍቡያገባ ጣልቃ ገብቶ ነበረ። የዚህም ብጥብጥ መነሸ የተዛበና መስተካከል የሚዋርበት ነገር ኑሮ ይሆናል። ጠልቀን እስከምናየው ልበለው! ወደችግር ቅንተናና ሂርዥር መግባት የገባ እው ስለሆነ የገጠን እንደደርሻየ፣… ቆይቼ የምጫወተው ይሆን ይሆናል። ሳሁኑ ግን ጥቆማ ብቻ ይሆናል። እንደችግራችን መብዛት የሰው አይነቱ በዝቷል። ባንድ በኩል ከማዶ ያመጣነው ጉንደሬ፣ ቅገሬ፣ ኢ.ሀ.እ.ፓ፣ ተ.ሀ.ት፣ ደርግ በማለት፤ ከዚያ አልፎ የሸዋ ፈላሽና የጉንደር ፈላሽ የሚባልም በተማሮች ገድም በቅሏል። ቅገሬዎች ሽዋም በቀሉ ከተከዜ በመለሱ ያው ቅገሬ ናቸው፤ በዚህ ረገድ አይታመም። በጉንደሮች በኩል ቡድነኝነት ዋና በሽታችን ሲሆን፤ ሁለተኛው ልዩነት እስራኤል የጠቀለው የሰው አይነት ነው፤ ነባር፣ በሱዳን የመጣ፣ ቀጥታ በደስ አበባ የመጣ፣ እንገረዛለን ያለ፣ ግርዛት አይሆንም ያለ፣

የመርገም ጉጅ ከልተሰራ የሚል፤ ዘወር በል! የምን መርገም ጉጅ ይባል? በጠቢያ ቤት ልጅ ብቻዋን እንደቶሸሸ ድሪቶ፤ ያው የከረፋ ደም እንደነካ ወርቅ በረሀ እየተጣለች መከረኛ ይበቃል የሚል፤ ከዚህ የናጠጠው ደግሞ "ፍየል ከመድረቧ፤ ቅጠል መበጠሷ" እንደሉ "መ-እ-ራ-ሆና "ሲ-ኩ-ድ ፓርቲ" በማለትና በመለየት በፈረንጅ የልደይት ጉዳይ ገብተው አበሻውን ሊያቋርሱት የሚጠጣሩት የሰው አይነቶች ናቸው። ዘሉ ፈረንጅ ሊሆን የከጀለ ሞልቷል።. ወገም ሁሉ፤ ሰው ሁሉ በጣም ወናና እየሆነ ተቸገርን።

«ሁሉንም ጠልተን ስናውቅ መሆን የሚችል.. ከወትንበ እንዲያም አይሆን ነበር! ገና ለዉያታውና ለምኞቱ ማለቴ ነው፤ " የንቹኩል-ቹኩል ቤት ግድግዳው በንብሎች እንዳሉት ይህ የረጫ " ፓርቲ" ነክስ ከግታት ላይ ብቻ ይገለናል። ስለእስራኤል እምባክ ብለን ወቅታዊ ከልሆነ ተግባር እየተደረገብን ይህን ምክንያት የገጠር ህዝብ ከተወሳሰበ ችግር እናስገባው ብጥብጥ የከዘው በምሁር አከባቢ ነውና። ለሚጉዳን ሁሉ ተመቸነው፤ ባንድ ከመሆን ተከፋፍለን ጠላትን ሁሉ ባንድ ገጥ አሰለፍነው። " በመጀመሪያ መቀመጫየን" ብሏል ዝንጀሮ ለሰው የትምህርት ተረት ሲያወጣ፤ የማበዛው ነገር የለም፤ የሚል ልዩነታችንን ለጊዜው በየኪሳችን ሸጉጠን አሁን "ድር ቢያብር፤ አንበሳ ያስር፤ አንድነት ሀይል፤ መከፋፈል ግን ድክመት!" ብለን ይህን ስብሰባ የሚመሩና የሚመዘግቡ ይመረጥ። አንዱ ከሌላው በማይበጅና በነወር ጉዳና መጉንንታተልና መነከከት ባይኖር. መቸም "አማረኛ እንዳበጀሽ ቅበጂለሽ" እንዳለው የታዘበ ሰው፤ አማረኛን ባንድና በበጉ ከላዩት ከመቶ መዋደቂያ ያደርባልና ሰሚም ባይዘርብት፤ በከፉም ቢታየው በበጉ ገጠ እያየ፤ ተናጋሪም ባይዘወር ተመቻቸተን . ማን ያውቃል? ከውብ ማሰሪያ እንደርስ ይሆናል። አበቃሁ፤ አመሰግናለሁ!» ብሎ ሁላችንም በይኑ ፈቀደን። ንግግሬ እያ ገዛኸኝን ስክለከለ ሊናገሬ ተኩት። «ከፍትፍት ፊቱ የተባለው ጨዋታ በልክ የተሰራ ነው። በጣም ብርሀን ልጅ ነህ። ጨዋታን ስቀው ከያዙት መዳረሻ አይጠፋውም። ያማረ ጨወት! ወብና ጀምረሀል፤ በዚያው ልክ የምታስኬደው ይመስለኛል፤ ከምኞትህ ተረዳሁት። ተማሬ ከቀለም የተነከከ፤ ነገር አይጠፋውም። በል! እኔን የሚታየኝ አንተ በትመራው ነው፤ ሌላው የሚነቅፈኝ ከሆነም ገልጦ ጨዋታ ነው የተያዘው፤ እንሰማ!» ሲሉ አስተናባሪው ተደናገጠ ፊቱ ተሸበረ፤ የማማቢሪ ደም ሀዋሳት ተወጣጠረው፤ «እያ ገዛኸኝስ፤ ነገር አመጡ! የማልችለው ቀንበር ጣሉብኝሳ በሞቴ? ድርሻየን የፈፀምኩ

መሰሉኝ፤ መስብሰብና መንደርደሪያ መስጠት ያንድ ሰው ስራ፤ ስብሰባውን መምራት የሌላ ነው። ልምድም የለኝም፤ ባብዮቱ (እቅዩዕ'ያ) ወይይቱ በደርግም፤ በኢህኢፓም የነበረ ይምረቅ፤ በነሱ ያምራል። እኔ አገር የተወኩ ባዬ ሀይለስላሴ ነው። ይቅርታ አድርጉልኝ፤ እሳ ወትም ማለት ነወር የለበትም!»

እያ ተበጀ፤ በእውቅ ተረብ ማወጣት፤ አንዳንዴም የገራገር ጨዋታቸው ነገር የሚጭርና አታታሪ ንግግር መፍጠር የታወቀባቸው አመል ነው። ከራባቸው የመነጨ፤ ሹርክትና የተታረነ ሀሳብ ተተባይነት ሲያጠባቸው ማሳበሸና ማሸሳለኪያ አወጥተው እንዲዋጉባቸው በማድረግም አውራ ናቸው። ከዚህ የተነሳ ይመስላል፤ ሌላውም እንደባቸው ታላቅ አታሞት፤ አባገቶና ሸውዶ ማለፍ የሚችል ይመስላቸዋል። ሰውየውን እንዲያ ገዛኸኝ ሊያጥሁት አልሞከረም። «ምን አይነት ጨዋታ አመጣህ ተሚ? ልዩነት ዝርዝሩ ያመጣህ አንተ፤ የሚበጅ አይደለም ያልከው አንተ፤ ተመልሰህ በዚያና በዚህ የነበረና ያልነበረ ማለትህ ጨዋታችን በእውነትም ባንድ እንዳማይዘልቅ ስትነግረኝ ነው። የደርግና የኢህአፓ ጨዋታ አይነት የመጣው በፈረንጅ አገር አይደል? አንተም በዚህ አገር ብዙ ዘመን ስትኖር በጋዜጠውም፤ ቢምንም የለመድከው ነገር ሳይሆን ይቀራል? ፈራሁ! ሞዴን ባርባር አለኝ!» አሉ። ሁሉንም አስደንግጠው ከዚህም ከፃቸው ድንጋጤ ተፈጠረ። ወዲያው መልሰው ፈር ሊያስዙ ከፊታቸው ላይ ፈገግታ ደፉበት፤ «ወሰታ ተማሪ፤ ልቅሽልክ ስትል እስያዝኩህ! ይልቅ ገፋማ፤ በል! ምርጥናውን እኔም ፈቅጃለሁ!»

ተጨንቆ የነበረው ፊቱ ተፈታ። ተማሪዎቹን ሳቅ በፈንታው ረታን። የልኩን ንግረውታልና እሱም መልስ አልሞገታቸውም። ሁሉም ተስማምቶበት አበባው ራሱ በሊቀመንበርነት፤ እኔ በፀሀፊነት እያ ተበጀ የዋሉብኝ ወለት ነበርና ተሸምን። ተነፋራ ሁኔታና ወቅት በመሆኑ ከመናገር ፀሀፊነቱን የመረጥኩት ባይሆንም፤ የወሰድ ዳሰታ ዋጠኝ፤ የተፈራራ ምሽት ነበረና በቀጥተኛ የትችት ምልልስ ወስጥ ከመግባት የዳንኩ መሰለኝ። ከፀሀፊነቱ የሚመጣብኝ መዘዝ እንዳለ ግን ሳልጨምር ነው።

የመጀመሪያው ስም ማስተዋወቅ ነበረና፤ የእባ፤ ኢዮብ፤ ገዛኸኝ፤ አልአዛር፤ ዳቢድ፤ እባይያስ፤ ተበጀ፤ ጋዲ፤ ጋድ፤ ይሁዳ. የሚሉ በከፊል ለሀበሸ ያልተለመዱ ስሞች ሲቀባቀሉባቸው ለዥማግሌው በጣም እንግዳ ሆነ። የማን ዘር ነህ? ማለት በእባ ይሀቅ ይጠናልና በመገረም የስም ትውውቁን ንባብ ቆረጡት፤ «ይቅርታ አድርጉልኝ፤ ያንዳንዶቹ ስም ገራ ሆኖ አልተያዘኝም፤ የማንቱ አባቶቻችን (ነገደ ይሁዳ) ስም እንዳገና ለማውላት

የተሰየማችሁት ዘይቤ እንደሆነ አልጠፋኝም። ግና በለመድነውና በኛም በኩል ያበቃ አደር ብለን ያደግንበት አለና፤ ያበቃ ስማችሁን እያከላችሁ። ልጅ ያበቃ ስም ማንሸ ነው፤ ከነማን ዘር ጋር እንደተቀመጥንም እንወቀው፤ ቀደም የመጣና ያላገኘሁት ደዋሪልና ከሰው ጋር መተዋወቅ የደንብ ነው፤ ወዋታ ካልወጣልኝ ደግሞ ይቅርታ እጠይቃለሁ።» አሉ።

ግና ከመግቢያው የሰበሰበው ሰንበሬት ቅጥ አልደዘ አለ። ለዚህ ወረፋ የተቀባቀለበትና ልመና መሰል አስተያየት ብሎም ግዳጅ መልስ ለመስጠት ሁሉም ሲቸገር አያ ተብጄ ከመቀመጫቸው ነቅነቅ ብለው ዘረፋ ጀመረ። «እየ ገዘኸኝ፤ የማይሆን ወዋታ ልትገጥድ ተነሳህ፤ እሁን እንደገና ሰው መቋጠር ከጀመርን ቡና የጠጣንበትን እቅድ ሰንፈጅ ነገ ማለት ነው፤ እኔ የምለው ግን፤ ይሆን የተበደለ ሰው ተወን ነው። ቅርጉመና ምስያው አይገባንም፤ ሰው ማለት ቷንቷ ነው። የጠቢያ ልጅ... እናትና አባት ሰው ሲያወጡ በምልኪት ነው። የሰውን ሰው ተውት፤ ወሸውን ሲጠሬእንኳ አይነትና አግረኛ አለው። ቀን-አልፎ፤ ቀጠሮ፤ ማዘንጊያ፤ ቀለበት፤ ቀን-አይበስ፤ ተመከሮ፤ ዘመድ-አየሁ... ኧረ በስንት ያስኙታል። ይህ ሁሉ ታዲያ ከምልኪትና ከቅርጉም ይመነጫል። የሰው ልጅ ሲሆን የሲያገው ምልኪት ስፍር አይገኝለትም። ቡለቾሬ እግዚአብሔር፤ ቡንቡት ያቅማች ሁ፤ ብሎ የለመነ የኔቢጤ፤ የቶሎ ተማሪም ይሆናል፤ የሚጠልለትን ቀራሽም ሆነ ድርጉ ጥሪ፤ የታል ኪዳኑን ጥለ ወለቶ ሲሰጠት - ሲሰያችሁ ይለምልም፤ ዘራችሁን ያበፋው፤ ብርሃን አይንሳችሁ፤ ምንጊዜም ስጡ፤ የዋለባችሁ አይጠቀም፤ ከፋሲክ አይለያችሁ... ሌላም ብዙ ብዙ ጥሬና ዳስ የሚያሰኝ ነገር ይላል-ለተሰጠው ቀራሽ መልስ። ታዲያ ተማሪውም ሆነ የኔቢጤው የሚለው ነገር ሁሉ ሰም ነው። እንዲያ ሲሆን አንዷ ቤት በዚያ ቀራሽ በተሰመነበት ገድም ልታበርክ (ምጥ) የተጣደች ኑሯ ይሆናልና ተማሪው ከዘረፈው ምርቃን፤ የታያትንና ዳስ ያለትን እንስታ የወንድን በገጡ፤ የቤትንም በገጧ ሰው ቅለፍጣለች። መቸም የሰው ምልኪት ብዙ ነው፤ በህልም፤ በተክል፤ በዘመን እመጣሽ ነገር፤ በተዘዋዋሪ ሹም። ደስ የማሉ በሲሳይ ምኞት በኩል ስያሚው ህብታመ ሲል፤ በሞት በኩል የተጠቃው ደግሞ በታቢል፤ ተረፈ፤ ቢራራ ብሎ የምሳለትና በምኞት የተጠቀመ ደግሞ ተመስገን ይልና ጠሉትን በዚህ ፈጅቶ ከመስጊድ ደጃፍ ዘወር የማይል ሞልቷል። ምስሳውን ልጁን በጠራ ቁጥር የተወጣው እየመሰለው። መስጊድ የሰለቸውም እንደምክንያት ይጠቀምበታል። "ወሀ ሲወስድ አሳሶቶ ነው" ይበላልና ህይማኖት ሲቀርና

ሲለመድም ምክንያት እየተፈለገ አይደል? ነው... አሁን እዚህ ቤት ስንት ሰው ይገኛል፤ መስጊድ ደጅ ብቅ የማይል ተማሪ። ለዚያም የሰው ንግድ ጠፈ፤ በለመድነው ቢነግዱእንኳ ቅርጉመ ይገባንና አገር መስማማቱና አለመስማማቱ ይታወቅ ነበር። አንድ ሰው ሰለየም የተፈጠረው ሳንድ ሰው ነው። ሰው የሚቀየርበት ጉዳና የለም ማለቴ አይደለም። አመል ያወጡ ሰበ፤ ሰው በግፍ የገደለና ከገር የሸሸ፤ ከለምብታኝ አገር ያመለጠ፤ አለምብታኝ (ገዳም) የገባና ይሆን የመሰለ ሰው ይቀይር ይሆናል። እዚህ መሀል ነፍስ የገደለ አለ? በጠቢያ የገደለ እዚህ አይደኘምና ሀሳብ አይግባው። እየፈለሉም መገባታችን የምንና ነው የምቅሉ ከሆነ አለማፈር ነውና እንስማችሁ። ዱር ጥሉ ምንና በከተማ! ይሆን የበደር ሰው ተወን፤ አሁን ከመሀከላችሁ አለማየሁ ብሉ ቢጠራ ልቢ ቅድድ ይላል። ከሰው ደስታ ይገኛል። ቢገባኝና ምስያውን የማገኘው ስለማሆን። የማይገጥመንን ነጭ ሰው እያነሳችሁ ግራ ገባን ብሎ በግልጥ መናገር አይሻልም ገዘኸኝ? የቅድመ-አያት ስም ስየማ ከምንገባ?»

በተከፈተባቸው የዋህ በር ገብተው ቀጭታቸውን ተወጡት። ሌላ ነገራቸው ግን ከመጀመሪያ አበባውን የዘለፉትን ያህል ቢትን ከሁለት ሰነጠቁት። ስማቸውን የቀየሩት አስተያየት ለመስጠት ቢቋምጡም ከመወያያው ርእስ እየወጣ ጭቅጭቅ እንዲፈጠርና መሬቱ እንዲደግር እንዲያው ቅእግበት ዝም አሉኛቸው። ያበባውም መስመር አስጠባቂነትም ደህና ረዳን። አያ ተብጄን ግን የቀለለ ነገር ቀሏቸዋልና ከተዘና አቀማመጣቸው ሌላ ፊታቸውን ከህዘን ቤት ያልሰነበተ ወዘና ጣለበት።

በጣም አስቸጋሪ የሰበሰበ መግቢያ ነው። ከተማሪኛው ያማረኛ ቷንቷ ወኔው በጣም ለፈሰፈሳ ነው። ከዚያ ደህንቱ በላይ፤ በዚያቸውም ጠብቶና ተፈራርቶ፤ እየለቀመ በመሳ የሚናገር ሲሆን፤ ጊዜ በባዶ በመከላት እንደኛነትን ያዘ። ገጠር ቀመሰቸ በጣም ነገና ገልፅ ናቸው። በምርጥ ታሳት ፅንሰ-ሀሳብ ማድማት ይችላሉ፤ በዚያው ልክ ለታል ብልቶ በማወጣትም የሳቁ ናቸው። እንጀቶ እርር-ድብን የሚያደርገው ግን ከመወያያ ርእስ ዘብጦ በመወጣትና ነገር እያያዙ ርእስ በማስፋት፤ ከሆድ የሰነበተ ብሶት በመቅራት የመጣባቸው መለኞች መሆናቸው ነው። በጊዜ እብክኝነት ባይወነጀሉም የወይይት ባህር በማስፋት ከነሱ አይገመም ያስኛል። ይህ ብቻም አይደለም፤ እንደመጠባቸውና ያበቷቸው የሚዘርፉት ቅኔትን አስተያየት አንዱን ከንዱ የሚያናክስ ሆኑ። የተሳጠው ፈቱን ሲከመዝዝ፤ ከመሳጠቱ ነፃ ነኝ የሚለው ወገን ፊቱ ለመሰመ። መሳቅእንኳ ችግር ነው። ግና

የውስጥ ሰቆ የፊት ወዘና ፈጣሪ ነውና፤ ውስጥ-ለ ውስጥ መተራረድ ነገሰ፤ እኔም ምቾት አጣሁ። ለሁሉም የመጨረሻውን ያበጀው። ሰባሳ ደቂቃው ርእስ በማፍከት አለቀ። አንዱ ሲነሳ ሌላውን እየመለደ ዝርዝር በጣም በዛ። ቢሆንም፤ ይህ ብዙ ሲበሰል የዋረ ሁኔታ ሁሉ በመሰንዘሬ፤ የሰበሰበውን አባላት ለማናያት ከመበታቱ ሌላ፤ ጉጉትና እንድነት ሊፈጥር የሚችል አጋጣሚ ይታይ ጀመር። ጊዜው ወጣት ሆኖ ብዙ በያስደመደምም፤ የእስከሁኑ እኔ ቀደም እንደፈራሁት አልሆነም። መሪው አጀንዳውን አስወመተኝና አቢይ የመነጋገሪያ ርእሱን አዘረዘረኝ፤

-የጊቾ የመተበሪያ ቦታ ውዝግብና ግርዛቱ፤

-ኢትዮጵያ ውስጥና ሱዳን ስለቀረው ህዝብ አመጣጥ፤

-የኢትዮጵያ ይሁዲዎችን ታሪክና የዘር ግንድ አወራረድ መተንተን፤ በዚህ በኩል የተፈጠረውን የሀፈዎች ግምት መምታት። የመጨረሻውን ነጥብ ስወረውር፤ እያ ተበጃና እኔ በጣም ተያየን። በሰውየው ዋት የተቿረጠውና ለምናየም ቢጊን ሊያስገቡ የተነሰበት ማመልከቻ ይዘት መጀመሪያ ይኸ ነበርና። የሁለታችንም አእምሮ ተዋህደ፤ አይን ከመለዋወጥና ከፈገግታ በቀር ቃል አልወጣንም። የቀረት ሌሎች ችግሮች የወሬ ማዳበሪያ፤ መቅኖና ማጣፈጫ ሆነው መሪው መንደርደሪያውን አቀነቀነ። የንእሱ ርእሶችን ተራ እንገላብጠናቸዋልና ቅንተና በታሪክ በኩል ሆኖ ወደተሰጠኝ መዝገብና ብርእ እንገቴ ተደፋ። አበባውም ጀግሬ እታች ሆነ፤ «ከምናየውና ከምንሰማው ታሪካችን በብዙ ተከፍሏል። እቺም መወሰድን ለ ሂሳ ቅቸ፤ ከሚበለው ጥቂት ሳስተደችሁ። እታውቀም የማለት ሳይሆን የውይይቱ ባህሪ የሚጠይቀው ግዴታ ይመስለኛል። ከልተናገርን ተዉብጥ ወል አይዋርም። የመጀመሪያው የሰሎሞን ዘሮች ናቸው የሚለን መገን ጉዳይ ነው። እኛም ይሁዲዊ የሆን ሁሉ የሰለሞን ዘር መሆኑን እናውቃለን። ግና፤ እኛን እንዴት ለዚህ እንዲሰጠጉን እንየው፤ በሁለት ይከፈላል፤

«-ንግስተሳባ ከሰሎሞን የወሰደችው ምኒልክ ረብዞ ይኸው ቤተእስራኤልን አረባ የሚለው ቢሆን በገረዷ በኩል የሆነውን ግን ገና አልተወራም። ሰለሞን ገረዷንስ በተራ አድርጌ የለ? ለንገሬ የግርድና ምልክቱ ለሰበ የተከሰተ ይሁን እንጂ ለሰሎሞንማ እንግዲያ ሁለቱም ያበሸ ሴቶች ነበሩ። እዚህ ላይ ታዲያ ዝባኤው ልብ ማለት ያለበት፤ ምኒልክ በአባቱ እንጂ በናቱ ከደሳ (በውስጥ ጨዋታ እንደቀልድና ማዝናኛ እየሆን በንዳንድ ሰወች የሚጠቀስ ቃል ነውና አበባውንም ለምደበታል) አይደለም። እዚህ ላይ ንግስተሳበ የሀበሻ ንግስት ናት የሚለውን

ገፕ በእምነት ይዠ ነው። ሳበን የኛ ናት የሚሏት ብዙ ናቸው። ይሆን ታሪክ እውነት ለማስመሰል ወሰታ (ጉንደር ውስጥ የቤተእስራኤል መንደር) በተቿቿመው ያሸንጉሊት የጅ ስራ የሰለሞንን ቅንዝርና የሚተርከውን የክርስቲያኖች ድርሰት በመጠቀም የጭቃ ሳጥን አየሰራ የሁለቱን አብሮ መተኛት ታሪክ ለኛ ታሪክ ሰርተውታል። በቶሳው ገድም (ጠገዴና ወገራ፤ ወልቃይትና አርማጭሆን) የመጣችሁ ይሆን ስራ ጭራሹን አልሰማችሁም ይሆናል። ግና ጉንደርም ይሰራው ቅንጌ፤.. ኧረእንዴያውም ቅገሮች በዚህ አይታመም! ብቻ ግን፤ በራሳችን፤ በፈላሽ ስለተሰራ የኛ ታሪክ ሆኖ ከጨዋታ ገብቷል። ይሆን አንድ ያልጠራ ቅረኛ ብሳችሁ ያዙ።

«-ሁለተኛው የሰሎሞን ጠንቅ ደግሞ የኢትዮጵያ ይሁዲዎች አመጣጥ ከምኒልክ ሳይሆን፤ እናቱን እንዲያጅቡ ከተላኩት አሽከሮች የመጣ ህዝብ ነው የሚለው ግምም ታሪክ ነው። ሁለተኛ ልብ በሉ! ያ የሆነው ያፍሪካ የበሪያ ንግድ ከመጀመሬ ብዙ ዘመን በፊት የሆነ ነው። ቤተእስራኤል ሙሉ በሙሉ እንዴት ጥቁር ሆነ? ከጊዜ ብዛት አየር ለወጠው? ምንው ግብፕ አልጠቆረ? የሚዋረው ከተንቀለቀለ ጠሀይና በረሀ መሀል ነው። እንደግብፕ በረሀ ያየለበት አገር ብዙም የለም። አንድ አባይ ብቻ ነው ወዝቸው፤ ፈፋ የሚበል ነገር አያውቅም። በመሆኑም ግብፕ አልጠቆረም፤ ፊት እንደነበረው.. ኢትዮጵያዊ ከቅላት በጣም ያነሳ ልጅ ሲወልድ ከግብፕ የተሰረተ የሚመስል ልጅ ወልደሀል ይባላል። ቅላታቸው የዋረ፤ አሁንም እንደነበረው ያለ ነው። ይሆን ሁለተኛ ልብ በሉ፤

«ሌላው ገጡ-ታሪክ፤ በመጀመሪያው አሊያም በሁለተኛው የየራሳሉም መቅደስ ፍርሽ በግብፕ በኩል ተሰደን፤ ሌላ ሌላው በያድማሱ ሲበተን፤ በየመንና በሱዳን ገድም ስንልከሰከስ ቶይተን መርጊያችን ኢትዮጵያ ሆነ የሚለው አንጣር ነው። የዚህ መረጃ አቅራቢዎች ደግሞ፤ ቤተእስራኤል ወደኢትዮጵያ የገባበት ምልክቱ እለው፤ ለምሳሌም ቿራ፤ በብራይስጡ የሆነ ዛፍ ስም ነው.. ምናልባት የሰበ ዛፍ እንዲይሆንም ፈራሁ። ታዲያ ተራኪዎች፤ ይህ በበጊምድር በኩል የተገኘ ምልክት ነው ሲሉ፤ በቅገራይ በኩል የጉጡ ስም ሁሉ የተበየመው የቤተእስራኤል የሱዳን አወራ በረፈበት ሁሉ እየተጠራ ነው። ያእቆብ፤ ጊዴወን፤ ዳዊት እያለ መቸም አበራ ሁለት ይደርሳል ይሉታል፤ እንዲህ ብዙ ቦታ ተሰይሟል፤ በዚያ ገድም የነበራችሁ ታውቃላችሁ። እኔ ወደቅገሬ ተሻገሬ አላውቅም።..» ብሉ ሊቀጥል፤ እያ ተበጀን ሸነጣቸው፤ ከጠየቀው የስም መጥራት እርዳታ ሊገቡ መስሉኝ ሳለ፤

«መሰረት የያዝክ አሽከር! ውብኛ እያጣደህና እያበጠርክ ያዝኸዋል። የጣልከው ስም በቂ ነው። በልማ ይልቅ የቀረውን ዉሎትህን ግፋልኝ» ብለው ጉልበት ሰጡት። ሲቀጥል ሲያቅማማ መልሰው ተደረጉሰበት፤ «ወይ ጠባይ! ዙሪያው የታጠረ ነገር፤ ያልሰማሁት፣ ሰር ያለው መቶት ሁሉ ብቅ አለ። አብራራው የሆንክ አሽከር! በል! ወደመዳሬያ እየተያየህ ግፋ! ማሰሪያንና መሽከሬያን የመሰለ የለም» አሉት።

«እያ ተበጀ፣ እርጋ ይበሉማ፤ ገና ሰስት አይነት ትረካ ይቀረኛል፤ ከመጀመሪያ የጠቀስኩት ነው፤ ሁሉንም ልጫሰው፤ ሂሳ ለመበስት የሚያመች ይመስለኛል!» አለ አበበው፤ እሱንም የውስጥ መታመስ እንደሰቸው ሚን-ሚን እያስተነፈሰው።

«እንዲያ ብለህ ልቤን አረፍት ስጠው፤ ዙሪያውን አጥረህ እንበለ-ውል ሰትተወው መዳረሸ አጥተን የቀረን መሰሉኝ ነበር፤ ሰስት ካለህማ አንዱ የኛ ታሪክ ይሆን ይሆናል፤ በጣም ጣፋጭ የሆንክ አሽከር፤ እንደህ ጨዋታ የምታውቅ መሆንህን እስከዛሬ አላሰማሁም ነበር፤ ኧረገና! ወይ ሰት መሆን?» ብለው እኩሊታውን ተሰብሰቢ አሰቆቅ። እኔንም የሆነ ነገር እከሳቴን ሁሉ ወረረው፤ እንደማሳብም ቃጣኝ፤ የነገር ሰ-ሰኛና ቀለዋጭ ናቸውና አደስ ማመልከቻ ፀሀፊ እንዳገኙ ጠረጠርኩ። የሚያስርፈኝ ቢሆን ብየ የብልጠት ደስታ እከሳቴን ወረረው። አበበው የቀረውን ሰስት ሊከሳ ከተደናቀፈበት ጀምር ቀጠለ፤ «ሊሳው የታሪክ ረገድ ዳግም፤ ራብኑት (የእስራኤል ይሁዳዊ የሀይማኖት መሪወች) ያቀረቡት የመሳ ታሪክ ነው። የሰረብን ብለው የቀለለ ይሆናል። የኢትዮጵያ ይሁዶወች የተመዘገበ ታሪክ የላቸውም፤ በሀይማኖታዊ ልምምዳቸው ብዙ ነገር ሰተዋል። አንዳንድ በጉና ጠንካራ ጎን ቢኖራቸውም፤ "ሀላኻ" (ቃለ-ህግ) የላቸውም፤ በተጨማሪ አንዳንድ በይሁዳዊ ሀይማኖት የሌለ ባእድ ተመክሮ ጨምረው ተገኝተዋል፤ በየጊዜው የታረመውን ደግሞ አላረመም፤ ይህ የሆነው ለብዙ መቶ ዘመን- በግምት ዘጠኝ መቶ አመት ይሆናል፤ ከዋናው ይሁዳዊ ምንጩ-ህዝብ (ሚይን ሰትሪም) ተነጥለው ያለምንም ግንኙነት በመኖራቸው ነው። የተሸሸለውን ህግ አላገኙትም። ስለሆነም የይሁዳ ዘር መሆናቸው ሳያጠራጥር፤ የተጣፈ የታሪክ መዝገብ ይዘው ባለመገኘታቸው ከጠፉት አስራ ሁለት የይሁዳ ነገዶች ምልክት ጠፍቶ የቀረ ዳን የተባለው ዘር ነው። ስለሆነም ዳኖች መሆናቸው የሚመስል ነገር ነው፤ የሚሉት የራብኑት ወገን ናቸው። ይህ ቅልጥ ያለ ስድብ ነው፤ እንዴት ማለት የዳን ዘር ከታሪኩ እንፃር፤ ዛሬ ለኛ ማራጊያ ሰበል ሊያሰባብሱት ቢሞክሩም በጣም የተናቀ ነገድ ነው፤

ሊነግሩን ፈርተው ካልሆነ በመገት አንጻር ከሆነ፤ ስሌሞን ከንግስተ-ሳባ ገረድ ወልደ ያረባቸው ቢሉን የለየለት ነገር ይሆንና ብዙም የምናፍርበት አይሆንም ነበር። ልክሳ አንድ ቀርቶኛል፤ እገር ጫብል!

«የመጨረሻው ባለ መንቶያ ታሪክ ነው፤ በመንታ ያለትን ሰወች! የኢትዮጵያ ይሁዶች በመልክ፣ በገፅታ፣ በቀለምና በሌላም ሰራቸው ከሌላው ከሚገን ኢትዮጵያ ህዝብ የሚለዩ አይደሉም። እንዲያውም መሰረታቸው እገው ነው። በመሆኑም ከአረቢያ አሊያም ከሆነ እቅራቢያዊ ክበብ የዘመተ ይሁዳዊ የሀይማኖት ግዛት አስፋፊ የተየራቸው መሆን አለባቸው። ከአረቢያ የመጣ ሰበኪ በሀል ያምራል፤ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የንግድ ግንኙነት በዚያ በኩል የጠና ነበረና። ያሁኑ በሚናዊና መሀል አገር ሰውም ከአረቢያ የፈለሰ ነው ይባላል። በመሆኑም ሀይማኖታቸው እንጂ ደማቸውና አጥንታቸው ይሁዳዊ አይደለም፤ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ነው። የተሸከመት ወኔም ይሁን ብሄራዊነት ሀበሻዊ ነው። ይህን አንዳንድ የኢትዮጵያ የጉባ ጠቢባን የተቀበት ጉዳይ ነው። እስራኤሉችም ይህችን ለማጣራት ከብዙ ኢትዮጵያዊ "ፕሮፌሰር" ደጅ ታይተዋል። የሀበሻው ጠቢብ ዶግም የጠልጊ እኔን ደፋ!.. በጠቢባን የተሰጠብን ትችት፤.. ጥቀግ ብለው የለየለት ይሆናል፤ እስሳ ያለ የጊዳ ጠጊግ! እንግዲያ በደባበይ ወጥቶ ትረካውን ባልሰማንስት? ፈላሻን እስራኤላዊ ማድረግ የሚቻለው ሀበሻዊ ወኔውን በመግደልና ወደእስራኤላዊ ወኔ እንዲቀየር በማድረግ ብቻ ነው ብለውልናል "ፕሮፌሰሮች"። ግና፤ የምንወጠውንና የምንተፋውን የወኔ ቅመም መቶጂ ምኒልኩን (መለኪያ) ግን አልተናገሩም። ማን ያውቃል?.. ይህ ያልሰማነው ይሆናል። በርግጥ ይህ የተያዘብን ጉዳይ ነው። በያንዳንዳችን ላይ የሚያዘረትን አገም የተረዳ እስከሁን አንድም አላየሁም። ከፎቅ የሚወድቁት እንዲቀሉኝ፤ ከምንም ወኔ የሌሉ ናቸው። ወዲበሽ የሚጠጋ ህጥቅ ይባል ይሆን? እንጂ! አገር እንተ ታውቅ። በኔ በኩል ግን "ይውጋህ ብሉ ይማርህ" አማረኛ ነው። ሸሰታ መንግስቱም ቢሆኑ ህዝቡን ተሰረቅሁ ቢሉ የጨቀ አይነታ ጨወታ ይችው ናት፤ ያልተሰወጡች ፈላሸ ሁሉ፤ ጁው ኢትዮጵያዊ፤ እምነት ግን እንዳገር የግል ነገር ነው ያሉት።

"ሌላማ እንዳይወሯረ የሚኒሰት ነገር፤ የሀይማኖት ነገር ማንነት ከርእዮተ አለም ጥራታቸው ጋር የሚያጣላቸው ይሆናል። ቢሆንም ገጥ የያዘና የተሸከፈ ንግግር ነውና ከራብኑት ግዛት አንጻር የማያሸማው የመንገ ሀተታ እንድደ የሚገለኝ አይሆንም. በለላው ከተከደንና የምርጫ ነገር ከተነሳ ማለቴ ነው።

«የዚህ ሁለተኛ ዘርፍ ከየመን ይሁዲዎያን የረገፉ ናቸው የሚለው ወገን ነው። ይህን ገጽ ሲያትቱት፤ ከኢትዮጵያውያን ጋር በመጋበት ገፅታቸው ተለወጠ ነው። የፀጉራቸው መከርደድ ዋና ምስክር ነው። የመናውያን በብራይስጥ ቋንቋ አረታቸውን ይዘው ተገኝተዋል። ኢትዮጵያውያን ግን ለምልክት የተገኘባቸው የመፅሀፍ ነገር የለም። ይህ ከተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል እንደም በድንገት ወጥተው በዚያው ቀርተው፤ በኋላ ጠቢ. እንደንገድ ባለ ነገር የሀይማኖት ጊዝ ሳይዙ እንደወጡ በዚያው ተመችቷቸው ድንኳን ጥለው ለምደው አሊያም ያልተጠሩና ባንዳንዶቻችን (ቤተ-እስራኤል) እንደሚባለው ከክርስቲያኖች ጋር በተዋጉ ጊዜ መፅሐፋቸውን ተቀምተው ይሆናል። ገራም ነፈስ ቀኝ፤ ደግቸው የጠራ አይደለም ብለው ለግርዛት የዳረጉን የተንታኞች አፈታሪክ ነው። ሁሉንም በንድ የሚያያይዛቸው ደግሞ የመጠሪያ ስማችን መብዛት ነው። ከይላ፣ ቤተእስራኤል፣ ጠይብ፣ ቡዳ፣ ፈላሽ፣ ቅማሪ፣ ጉንደሬ ይህም ለብዙ ምርምር ዳርጉናል። በኔ በኩል አምስት አደረኩ። ከያንዳንዳችሁ ደግሞ ምን ያህል እንደሚወጣ ምን ይታወቃል? ግና አንድ ጊዜ ፋታ ስጡኝ፤ ኡሁ! ተታጠልኩ!» ብሉ ወሀውን ገፎ ሊጠጣ ሄደ። «እንጀራ ይወጣለት፤ ጨዋታውን እንቀልቅሉት ልቧኑም በወሀ ጥም ተንቀለቀለ፤. ኡሁ! ያስጠጣል። ንቢግ በቅምህ፣ ስንበት ታቅምህ ለኔም አምጣልኝ፤ እሱ ተታጥሉ እኔንም አታጠለኝ።» ብለው፤ ተበጀም ወሀ ጠየቀ፤

እያ ተበጀ እንደተነበዩት፤ እያንዳንዱን ነጥብ እየነካከና እየመዘኑ በበጉ ስላልጨረሰው፤ የብዙወቻችንን አእምሮ በመዘው። በሌላ በኩል ግን ይህን የዋረ የታሪክ ውዥምብር የመጨረሻ ለማየት የመጓጓት ሁኔታ በመጠቀ አከባቢ የተተነተነ ቢተነተን ውሀ ቢወቅጡት እምቦጭ እይነት ቢሆንም፤ በሸማግሌዎቹ ግን ይህ ስብሰባ የተሰፋ ጭብንጭል የሚሰጥ መስሉ መታየቱ ከፊታቸው መዘናት፤ ከመንደርደሪያው አቀራረብ የገዙትን ሀይል በመገምገም የተነበይሀባቸው ሁኔታ ነበር። እበበው የሱን ጠጥቶ ያያ ተበጀን ወሀ ይዘ ተመለሰ፤ «ጉበዝ፤ በሉ! በሰአት ከመቷጨት እንድንደርስ ሸማግሉች በቅንነና እየተራዳችሁ፤ ይህ ልክ ነው በዚህ ምክንያት፣ ያኛው ልክ አይደለም? በሌላ ምክንያት በማለት፣ በተጨማሪም ያልተነካ ማብራሪያና ታሪክ ካለ በማውጣት ለፀሀፊው ደግሞ እንዲመቸው. ከሁላችንም ችግር የሚቆርበት እሱ ነው። ይህን እውቀን በሀሳብ እሸክክፍ የሚራዳው የያንዳንዳችን ከንፈር በመሆኑ፤ ከንፈር አለታቀም የተናጋሪወች ይሆናል። እደራችሁን፤ መዝረክረክ እንዲታበዙና

የስብሰባ መሪነቱን እንዲታቀቨኩ፤ የስብሰባ ስነስራትን የሚያስከብረው ተሰታፊው ነው። እያንዳንድህ ከርእስ ውጭ እየወጣህ ብታተፈቅፍ የምስድህ እይሆንምና ባለስልጣን እንዲታማርሬ፤ ነገረስ፤ ተይዘ ያለው ጨዋታ ባለስልጣንንና ባለጊዜን የማግረር ነገር ነው» ብሉ፤ እበበው ቀልደኛ ቢጤ ነውና ተሰብሳቢውን አዘናው።

ተከስተ ቀጠይ ባለተራ ሆነ። «የተዘረዘረው አጅንዲ፤. እንደኔ ከሆነ. ስንክስር ቢሆንም አንድ ነው። ሰንቲም ሁለት ገጽ ቢኖረውም ዘርዘር አንድ ባሁሪ፣ አንድ አካል ነው። ልዩነቱ የገጽ ገፅታና ስእል ብቻ ነው፤ ሳንቲሙ የተሰራው ከብር ከሆነ ሁሉም ብር፤ መዳብም ከሆነ ሁሉም መዳብ፤ ቅይጥም ቅይጥ ነው። ግርዛትም ጠጣ፤ የመታብር በታ ተነስገን፤ መጀመሪያ ይሁዲወች ነን ወይስ አይደለንም? የሚለው ግልፅ መልስ ካገኘ ነገር ተጠቅልሉ ተከወነ ማለት ነው። እንዲያ ሲሆን ግን ብር፣ ግን ነሀስ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚያ መልስ ለመድረስ ደግሞ ነጭን ባንድ በኩል፣ ፈላሽን በሌላ በኩል. ገራኝና ተገራኝን በየገጡ መጀመሪያ እንጥሮ ማየትና የየራሱን ጉድ ማውጣት ፍቱን መድሀኒት ነው። ላይ ለላይ መላጨት ግን ዙሮ መላጨትን ያስከትላል። የፍልሚያ ነገር የሚመጣው ከዚያ በኋላ ነው፤ ፍልሚያ በመጨረሻ ይታያል።» ሲል፤ ያያ ገዛኸኝ ፈት ልውጥ፣ አይናቸው ፍጥጥ እንዳለ አቿረጡት።

«በወብ አይነት ሲተረክ ውሉ ያሁኑ አይነት ጨዋታ ግን ጉዳና የሚያስብረን ሳይሆን አልቀረም፤ የግርዛት ዜና በገጡ ሲነበብ መስሉኝ ወደሌላ ሁሉ መድረስ የሚቻለው!» ሲሉ እለበል አጠቀና መድረክ መሪውን እየተመለከተ እጁን አወጣ። ንርምርምታው ስለበዛ ፈታድ ሲሰጠው ጊዜ ፈጀበት። «እኔ በግርዛት በኩል ያለ ነገር ቀድሞ ለማናበብ እለሁ።» አለ ከተከስተ ጋር በጣም የሚዋደዱ መንታወች ነው የሚመስሉትና የጀመረውን አቿርጦ በዚያው ላይ ከንፈሩን እያሻራመጠና ሰባ ባቅ አጠቀ ቅንሽ ሊያበሸተው ሸተ። ሲሉቻችን ባላለምነው ጉዳና የመናገር እድል ከተከስተ እና ወደእለበል ተሸገረ። ተከስተም ዝም አለ። እለበል የገዛኸኝን ቅእንዝት ግጠትና ፍርሀት ተጠቅሞ ገና ለገና ከመንደርደሪያው ላይ እንዳለ አስቀረበት።

እለበል፤ የድምፅ ቅኝቱና ቃል አጣጣሉ አድማጭ ይስበስታል፤ የቅንነና ዘይቤው፣ ነገር ማታረንና በንዱ መሀል ሌላ የተጣደበትን ቅኩስ ነገር በመደርጉስ ከያ ተበጀ ይልቃል። የሚያታርነውን ሁኔታ የሚያስብሰው በሚሰራው ቀልድና

ከፍትራዊ ስድብ ጋር በማጣጣም ነው። በዚህ ስጦታው ሰማን ከሚሉት ይልቅ እንስማው የሚሉ ያደላሉ። የወንዳወንድነት ወኔ ሞልቶናል የሚሉት ግን አይወዱትም፤ በለከፋቸው ቀጥር ቤት እጫዋች የሚል ትዕል ሰም አልፏልፎ ከሚያስቅባቸው ቀልድ ለመዳን የሚጠቀሙበት ማስፈራሪያ ነው። ግን በጤና ባላንጣነት የሚታያዩት ጥቂት ናቸው፤ በተደማጭነቱ ብዙ ሊያቆሽሽቸው እንደሚችል ያውቃሉና። ይሆን ባሁኑ ለዚህ ጊዜ የተመኙሁት አልነበረም። ቧልቱን የመፍራት ባይሆን፤ እንደበተቃሉ ለስለስ በመሆኑ በሰዎች ላይ እንቅልፍ እንዳይለስድባቸው በመፍራቴ እንጂ። ቢሆንም ተራውን የሰጠው ሊቀመንበሩ ነውና የያዘውን ያንገት ላይ መሀረብ (ሻርፍ) ከፍንጁ ላይ እየጠማጠመና እየፈታ ተጫወተበት፤ አፉን አጣምሞ አይኑ ወደሰማይ ተከፍቶ፤ «ያሰሉኝን የሰው ተራ ተሸምቼ፤ ልናገረው ያሰብኩት በነነብኝ፤ በንዱ ጀምሬ እየቶየ ይፈስልኝ እንደሁ ልሞክረው፤ እንዴ ገብቾ የለ፤ መውጫ የለኝም! መልከም… በመጀመሪያ በጥያቄ እንየው፤ እዝህ ካለነው፤ ብልት ለምላጭ ያልሰጠ ስንት ይሆናል?» ብሎ፤ እንገቱን ደፋ አድርጎ በዚያው በመሀረቡ በተጠነጠነው ከንዱ ጫፍ የታሰረውን ሊቡና መሀል ጠቅን አጫፍሮ ከፀጉሬ ስጦ እንደሚደ ተጠቀመበት። እንደገና ቀና እንደማለት ብሎ እኪሸሚ ልጃገረድ ታየውን አይነት ወደተብጀ አትኩሮ ፈቀዳቸው። ዝግ አድርጎ መልሰ፤ «እየዋ ተብጄ በናንተ ግድም ሰው ሁሉ ከግርዛት በደህና አምልጧል?» ሲል ተብጀ በተደናበረ ፊታቸው፤ «አንተ ደህ ድምባዝም! ደህ ማጋጣ ምን ይላል? እንደሱ እየተጉተትኩ የገባሁ መስለው? ይህ አይነት ጥያቄ በኔ እንዴት ተነሳ፤ "አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል" ይላል ፊቱ የተበላሸበት ሰው። አንተ አንተ ልጅ ሀሳብ የሚወድቅልህ አልመሰለኝም፤ በጣም ተቸግረሃል።» አሉ። ዘመዳቸው ነውና ከልክ ያለፈ ዘለፋት፤ እሱም የባሰገውና የተዘናው አይቶ ይሆናልና እንዴት ሊጠቀምባቸው እንደከጀለ እንቶቅልሽ ሆነብን። ንግግራቸውን በፈገግታ ካስከሳ በሂላ ቀልደኛ ፊቱን ልጦ፤ እንደገና መልሰ ዘና አደረገውና የሞተውን ድምፁን የበለጠ ገደለው፤

«እየዋ! ካልተገረዝክ መፈክርህ በጣም የተገባ ነው። የድልአንጂ የጥቃት ፈከራ አላደረክም። የጥቃት ፈከራን ለመጠናት የሚያደርጉ ቢኖሩም ሲያምርባቸው አላየንም። በኔ በኩል ደግሞ መጠየቂ የልክ ነው። ነገር ይብራራ ተብሎ ነውና የተቀመጥነው፤ መብራራት ከጥያቄም ይመጣል። እንተን ለጥያቄ ማስቀደሚ ደግሞ ስለምዝናብህ ነው። የግርዛት ጥያቄ መልስ ከዚህ ቤት ይገኛል። እያንዳንድህ የተገረዝኩ በምን አይነት መንገድ

ነው? ብለህ ብትጠይቅና ጠልተህ ብታይ የምታገኘው መልስ የበጉ መደረሽ የለውም። እናም የዚህ ጥያቄየ መልስ በቅርብ ከተገኘ ይህ ንዝናዝ ሌሊት ሳያልቅ እንተኛለን፤ እለዚያ ግን ተቀምጠህ፤ ወለግ እንደለበስክ፤ ወለግውን እንተ ሳትከሳው እሱ ከልቶህ በመሀይ ጊዜ ሌላ ወለግ ትገባለህ። በመሀይ ከተኙ ምንጊዜም ወለግ ነው። ከዚህ በተረፈ ግን ከንግግሬ የተነሳ የተከፋ ቢኖር ይቅርታ፤ እጅ እነሳሁ!

«የግርዛት ታሪክ የጀመረው ጥንት ነው፤ ገና ለገና ፈላሽ ወደሰራኤል ሊሰብ ልጊም ሲበጅ፤ ነገር መበከት ሲጀምር፤ ገና ከገበታው ላይ እንዳለና ከሸንኩራው ላይ ሳይወድቅ ነበር የመበጫ ምላጭ የተሳለብን። ክርግ እንግዲያ ከምኑ ላይ ሊያወሉብን? ጥንት፤ ገና በስምንት ቀን የተቆመጠ ብልትዛ መሰእንኪ እስክርባ እሙቱ ያሳደረገው ነገር! መበጣቱን የተሰገመልን፤ ጋንጃ እንዳያዘው በሬ እኛእንኪ የታመመ ደም ያለብን አይመስለኝም፤ እንዳሉት መጥቶር የደም መበላሸት ካልሆነ። የደም ግቢረን የተፈራረመልን የራሳችን የፓለቲካ ሰዎች ናቸው። በሀበሻ ታሪክ የመጀመሪያ አድርባዮች! ሀገብ በጀምላ ለማፕረድ የደም ግብር ያዘጋጁልን ወንድሞቻችን! በቋንቋ ታጠፍን እንዳደሉ የፖለቲካን የቋንቋ ገመድ ወጫሊ ላይ የበደለ እገር ላይ ነው የተወሰደን። ምን ያደርጋል! ሲባላሹ ደግሞ ገዋ የያዙ መበላሸት ወብ ነው። የነዚህ ምሁራን ግን በግልጥ ለወበጠ እጅ የጤና ያወቀህ ግዘው ሰምምንት ፈርግ ነው። እንዲያው ፈረንጅ እገር ሲባል ብርቅ የመሰላቸውና ለመምጣት የቿመጡ። የፈላሽ ወደየረሰሌም መምጣትግ እንግዲያ በሰምምንት ሳይሆን በፈቃዱ፤ በሰው ፍላጐት ሳይሆን የእግዚር ቃል ሲደርስ እንደሚሆን አውቀነው የዋርነው ጉዳይ ነው። የኛ ሰዎች ግን ከዚህ ወረዱ። በትንቢት በኩል፤ ጊዜው ባለመድረሱ፤ የሱዳንና የግብፕ በረሀ ገርግሯቸው የተመለሱ አባቶቻችን ብዙ ናቸው። እነዚያ ታዲያ የደም ግብር ለመክፈል የተሰገመትን ወል አልሰማንም። ወደጣቢያ መልስ ያደረጉት የመጣፊ ትእንቢት ባለመድረሱ እንደሆነ ሁሉም ያውቃል። ሀሰት ብትሉ ነገር ጠቅልሉ ይበላሻል።

«የምናገረው ነገር ሁሉ የፈጠራ አይደለም። ዘመድ የሚነካብህ ሁሉ እፍጠህ እንዳታየኝ። የነጭ ሁለ-ነገሬ በመዝገብ ነውና፤ እሁን የመጣው ሰው ሁለተኛ ግርዛት ለምን ተብሉ! ሲል በመልስ የቀረበለት ታምር የመጣኸው ተገርዘህ ልትገባ ነው፤ ሸሞችህ የፈረመበት ወረቀት እለን ብለው ጉድ እየ። እከሌ ብየ ስም መጥራት እሁን ትንሽ ይግልዳል፤ ነገር ሲከር፤ የተፈራረመና

የማናውቀው ሹም ተብየ ሽወኪያ ተጨዋች ሁሉ መጋለጡ የማይቀር ነው። ይመጣል።...» እንዳለ፤ እያ ተብጆ ነገር ማጧያጧያስ ይወዳሉና፤ ሌላው የሚናገረውን ያዝ በለው ማለት በላቸው ላይም መዘዝ እንደሚያመጣ ማየት ዘበታቸው ነው።

«የሆነ ነገር ከሌ.. ብቻ ያልሆነ አትናገር እንጂ፤ የሆነውንማ አፈንዳው! ነገር ሲበላሽ ዝም ብለህ ታይ እንዴ፤ እዚህ የተቀመጥነው ነገርን በጥልቀት አይተን ከሆነ ማስሪያ ልንደርስ መስሎኝ?»

«ቅይማ አየሁ፤ መቸም በታየኝ ሁሉ እየመጣሁ ነው። ከላይ በጠቀስኩት ታሪክ መሰረት የስራኤል የሀይማኖት እመራር በሁለት ተከፈለ። ግማሽ መንግስት እንሱ ናቸው። የእሽክናዚው ዳኛ፤ የለም፤ ቢገረዙም ከመሰረታቸው ጥቁሮች ናቸው፤ ስለዚህም የጥቁር ይሁዲ ተስምቶም ሆነ ታይቶ አይታወቅም» በማለት አንድ ገጥ ሲይዝበን፤ የስፋራዲ ሰወችና የሀይማኖት መሪወች ደግሞ፤ «ፈላሾወች፤ ከስረ-መሰረት ይሁዲወች መሆናቸው በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሷል። መፅሀፈ-እሪት ላይ "ጦቢያ" በሚል የቦታ ስም የሚጠቀሳቸው እነሱን ነው በሚል ከኛ ጉን ሁነው በማልጥ ደግፈውናል። የሆቅ ነው፤ የኛ ሰው "ጡ"ን እንደ"ጦ" አንብቦ "ጦቢያ" ብሎት ነው። ሰፋራዲወች ታዲያ በዚሁ መግታቸው ገፍተው በሚዚር ቃልና በምደባው፤ ጦቢያ ከገር ሁሉ በዘጠነኛ መጠቀሷ በቂ ምስክር ነው። ይሆም ይሁዳውያን በምስራቅ አፍሪከም መዘራታቸውን ይጠቁማል። እኛም እናምንባቸዋለን አሉ። ይህ የስፋራዲወች የድጋፍና የፍቅር መግለጫ ነው። ግና ይህ እግዚር ማለት ይገርመኛል፤ ይሁዳውያንን የፈጠረ እግዚር ሌላውን ፍጥረት ሁሉ የፈጠረው አይደለም ይሆን? በጣም ነው የሚገርመኝ፤ ይሁዳዊ የሌለበት አገር በመፅሀፍ የማይጠቀስ ይሆን?... ግና ደግፈውናልና እግዚር ይባርካቸው። ከሌላው አተላ ቀቢያችንና ከሚያጋጁን እጅግ ይሻላሉ። ይህ የመፅሀፍ ጥቅስ በሰፋራዲወች ልብ ባይበል ኩስ እንደነካ እንጨት እንታይ ነበር።

«ከስ እንዲፈር ነው፤ ሀበሾች መፅሀፍ ቅዱስ በእብራይስጥ ይዘው አልተገኙም፤ ሰንና ወተት አቀላቅለው ይበላሉ፤ ገራዝቻቸው ሴቶች ናቸውና ሌላም ተጠቅሰብናል። እዚህ ላይ ብዙ የሚጠየቅ ነገር አለ። ሰንቶቹ ናቸው እብራይስጥ ሲናገሪ የዋረት? በደንብ ሊጠቀሱ የሚችሉ የመናውያን ብቻ ናቸው። የመናውያንም በገቡበት ጊዜ የተገለባበጠሽ "እመድ በዱቄት ይለቃል" እንደሉ ይሁዲ አይደለቹሁም ተብለው ነበር። ጥቁር ሁነው በመገኘታቸው! የየመናውያንን ሰቃይ ሀንዶች ተኩ፤ የሀንዶችን እኛ ተካን። ይሆን ጅል ነገር ተሸክመው፤ በቻይና፣ በኬንያ፣ ናይጀሪያ...

እዚህም ይሁዳውያን አለን ባላለው ሁሉ.. ኧረንዲያውም ከአስኪሞዎች ሰፈርም.. ያንን፣ ያንን አገር በተራው ገፋፍተውና ከቤታቸው ምን አይነት የዘረኝነት ጊዜ እንደሚፈጠርበት ባይነግረ፤ እየጉተቱ ፤ እርፎ የተቀመጠውን ሁሉ እዳና ጭንቀት ይከቱታል። እለም ብልጥ ቢሆን ከኛ ተምሮ በዳነ። እንግዲያ ለራስ የማስብ ነገር ብታነሱ የሚያስርፈን እዱስ ነገድ ቢገኝ ለኛ እርዳታ ነበር፤ ሌሎች በኛ እንዲረፉት።

«ሰጋና ወተት አቀላቅለው ይበላሉ መባላችን የጉድ ነው። ሀበሻ ቢታማ በእሰር ወሆና በጭንጫ አጠባበጡ ነው። እኛ ሰናወቅ በወተት የሚታማ ድመት ነው።.. አቀላቅለንም እንብላ፤ ይሁን፤ ከጊሽና ብቅል ጋር ነውና የምንጥረው የሚጎረብጠንን የሳም -ልጅ ዘር እሰርወሀው እመድ ያደርገዋል፤ ሆድ አይጎጥጥም። ብቅልና ጊሽ ሰጋና ወተትን ማበራየት ይቅርና የብረትና የገል ሽንኩራ ሹሀላ ሁዋ ይበላል። የሰጋና ወተትን መለያየት ከሆድ ባሀር ላይ ስለማይጠጣም አይደል? ሰጋ በልቶ አንድ ሰአት መጠበቅና ወተት ማስከተል! ሌላ ምን ትርጉም አለው? በሴት ይገረዛሉ መባላችንም የድድብና ነው፤ በጦቢያ ከወንድ ልብ የቤት ልብ ይራራል። በብልሀትና በምላጭ እያያዙ፤ ከልጅ በመታረብ ሴቶችን ያሚወዳደር ፍጥረት አይገኝም። ቢከፋም ከልክ ያለፈ ችሎወና ቢመራቸው ነው። ይህ እንደተጨበጭ የማል ተመክሯችን መታየት አለበት፤ ወንድ ጨካኝ ነው ብለሀል ተብየ እንዳልከሰስ፤ እያወቅበትም፤ የበሰውን እጊጉል በታ ላይ ይሸነትፈውና ለሞት ስለሚያበታ ይመስለኛል! በራሱ ውን ቂስ ቀጥ ይሰጣል፤ ሴት ምላጭ ትጥባለች፤ ይህ ታዲያ ምን ስሁተት ሁዋ ሊታይ ይችላል? እዚህ ውስጥ ከተቀመጣችሁት ሰንት ሰው ነው ጨክኖ ምላጭ ከብልት ላይ መጣል የሚችል? እገር ይሆን የመከራከሪያ ነጥብ አንድ ብለህ ሰጣ።

«ሌላው የመገኘት አይነት በየዘመኑ የተነሳ ቂላቸው ሁሉ ያነሳው የቃልሀግ ተብሉ ነገር አይገባኝም። በርግጥ እንደዚህ ያለ ቃለ-ሀግ የሚባል የለንም ብንል ምን ይመጣል! ወደፊትም ከነሱ ጋር ስምምነት ብንደርስ አይጥመንም። የኛው ቂስ በስክረና ሞቅታ በዘረ ጊዜ ሁሉ የእሪትን መሪና ነባር ሀግ ሳያበላሸው ስለቀረ ነው ? ባይነታው እንደነበረ ይዘን በመገኘታችን ነው? ተበላሽተው ያገኘናቸውስ እነሱን! ይሆን መበላሸት ለመሸፈን ያለ የሌለ ጉልበታቸውን ተጠቀሙብን። ይሆን-ይሆን እዚክልካቸው በደንብ መንገር ያስፈልጋል። ራዲዮኑ፣ ተሌቪዥኑ፤ ጋዜጣው የነሱ በመሆኑ እሳማዘን ብሏልና በደንብ ትግል መደረግ አለበት።

«ሌላ የሚታየኝ ነጥብ ደግሞ ጥቁር ናችሁ የሚለው ጉዳይ

ነው። ይህ ከቀለም-ቀለም ንዝቶ፤ ለዛና ውበት ያልፈጠረበት ሽሉ-ተማሰል ገላ ሁሉ አሰቶናል። ንገረኝ! የትኛው ሀበሻ ነው በየቀኑ አጓዛ እየጠቀለለ ከሚጣበስ አሸዋ ላይ ከጠሀይ ላይ ሲቀቀል የሚውል? እኛ ነን ወቅያዋስ ዳርቻ ላይ እርቃነሰጋችን ስንቀቀል የምንውል? የሙገት አይነት ከሆነ፤ የሰው ገላ እንዲያ ከመጥሀፍ በሌለ ቅጥ ሲያራክስና ሲያስመርቅ የሚውል ሀበሻ ነው? እንዲያ ባለመሆናችን ስድብ በዝቶብን እራቁትን ለመታየት የቤቴ ልጆች በልምምድና ወርቅ በመቀየር መከራ በልተዋል። በየደቂቃው ወንድም አለም ና እቴቴ እየኝ፤ እንዴት እመስለሁ በመባል ስታመስ ነው የምውል። ከጠሀዩ ጠበሰ ሲመለሱ የጠንዛና ድመት ከርቶ የተወው የሞተ-በፊታዴ ገብት ነው የሚመስሉት። የሰው ልጅ ገላ እንዲያ በጤና ጊዜ ሲቀረፋ ማየት ይገርማል። ባለመጥቆራቸውና በታችነት ሰሚታቸውን አገር እንዳይበሳበቸው እስቀድሞ በር የመዝጋት ነው። ፈረንጆች በመሳና በዘዴ ነው የሚዋረት፤ የሚፈታተናቸውን ነገር ዘወር ባለ መንገድ ሲያደርጉ ተወዳዳሪ የላቸውም። ጠላነው የሚሉት ነገር በጣም የሚወዱትም ነው። ጠላን ማለታቸው ሌላው ኩራት እንዳይሰማው ማቻቻያ ነው። በተፈጥሮው እንደኔ የተቀባውን መጥላት፤ መልስ ቀለሜን ለማንሳት በሰተ-ገሞራ ጠሀይ መቀቀል.. ባያውቁት ነው እንጂ ከጠሀይ ይልቅ ነፋስ ያጠቁራል። ጠሀይ፣ የውስጥ እሸቱን ማውጫ መሆኑን ሲቀቀሉ ውለው ሲመለሱ ከሚገፈፈው ገላቸው የምረዳው እኔ ነኝ። እብብም ገላውን የሚያወልቀው በበጋእንጂ በክረምት አይደለም። ያጠቆረን ነፋስእንጂ ጠሀይ አይደለም። እንዷሉት ግብጥ በበረሀ ብርታት አልጠቆረም። ታዲያ ባውቶቡሱ፣ በሚዲያውም ሁሉ የዚህ ልዩነት ነገር ሲታየኝ ቶዲ ቀለሜን ትክ ብየ እየውና የጣቢያ ንፋስ ውሰህ ግቢ፣ ተመስገን ብየ ሳምሳም ነው የማደርገው፤ ከራሲ ቀለም ላይ ያቅራራ ፍቅር ተባፍሮብኝ ያርፋል፤ ፍቅረንም የሚያሲዙኝ እነሱ ናቸው! በሞቴ፣ እንደኔ ያለ እብደት እናንተንም ይስርቃችሁ ሄል ይሆን? እያስያችሁ ባሙት፤ ብዙ ሰው ታናድዳላችሁ።

«ግፋ፤ ቀጥል! ካላችሁ "መታፈር በክንፈር" ይሏልና ሌላውን አለማክበር ራሰም አለመከበር ነው። የመበላለጥ፣ አንደኛውን አንደኛው የሚያጠጥለው፣ ነጭ ጥቁርን ይሁዳዊ አይደለሁም የሚለው ከሆነ፤ ስለቶን እምበሰብሰ በመመልከት እናቴን የሚያክል የሰው ዘር የለም። ስለሆነም አደባባይ ይዢት እወጣና ተያይዘን ገደል እንገባለን። እስራኤልም እስራኤል አትሆንም። ወኔና ወንድነት ከሆነ ዳግም አብሮን የሚኖር፤ እራሳቸው ያስለጠኑን ነገር ነውና የሚጨንቀን አይደለም። በመጨረሻ ግን

ሀሞትና "እታ" እንዳንጠለጠለ ይታያል። እለምን ገዘሁ ያለ ነጭ ሁሉ ይታዘበው፤ መዋደቂያው ባይታወቅና ባይነገርለት ያሞራ ራት ሁኖ የቀረው ስለቶ ዘመድ ሁሉ ያውቀዋል። የነጭ መከራራትግ እሁንስ መች አለቀና! ደቡብ አፍሪቃ ላይ የሚሆነውን ማየት ይበቃ የል! ቅሌታቸውና ከብትነታቸው ያየለ ነውና የመጨረሻ ውርደት የሚቀበሉት እዚያ ይሆናል። አንዳንድ ንጹቴን አትፍረደበት፤ ምነው ማለት አያቴንና ወንድሙን በገድ ተን እንበለ-ተባሪ ያስቀራቸው ጥልያን ነው።

የሆነ ሁኖ የመከራራት ነገር ሲነሳ በጣም ይመጣብኛል፤ የትኛውን የሀይማኖት ምግባረኛ ሊጠራልኝ ነው፤ እነሱ ስለሞዋቾ እኛ መዳረሻችን ባይታወቅ የቀረ የተባልነው? ዘጠና ታሪክ ይጠጣልን የተገባው?... ስለምን? ወይስ ዳዊት? የትኛቸው ናቸው በሀይማኖት ምግባር የሚጠየቁት? ከንጉሥ ሳባና ከገረዷ ላይ የደረሰው በደል በዘሬው ሀገ-መንግስት አይነት ቢሆን ያለውድ በመግለስና በባለጊነት ያስቅል ነበር። ሲተኛ በማይከደን አይኑ አጥብርብሮ አይደልእንዴ አይኑን ሲዞጋ ተኝቷል ብላ ተጠንቅቃ ውላ በውድቅት የተጫወተባት! ይህ ያለውድ ድፍረት አይደለም? እገር ምን ትላለህ? ንጉስ ዳዊትን በምግባር እንወስዳለን እንዳይሉ፤ እኝደሱ የቶመበት ሰው በታሪክ አልሰማሁም፤ ቅንዝረኝነቱ ወደፋሸሽትነት የለወጠው እሱን ብቻ ነው። የሰው ሚስት ተኝቶ ሰው ካስገደሉት በታሪክ የተመዘገበ የመጀመሪያ እሱ ነው። አቅም ቢያጥረው፤ እግዜርን ና! ወረድና ሰው በቶንጨራ ገደለ እርዳኝ ብሎ በገና የደረደረ፤ ብሉም ያለቀሰ ዳዊት። መፅሀፍ እንደያዘው እንፋረድ ከተባለ በመጨረሻ የተገዳደማት ቤት ፍቅር ልቡን ሲያጠዝተውና እንዳገቢያ ቅቤ ሲያቀልጠው፤ ባሏን፣ ታማኝ ወታደሯንና ግዛት አስጠቂውን የታወቀ ጦረኛ እናቱን አስብሉ አስገደለ... ዳሞ ለጨዋታ!

«በመሰማማት ረገድ የሆነ እንደሆነ ግን ሰው አይሰማ! ይሁዶች ስንባል እልም ያልንና የወጣልን እመንዝራዎች ነን፤ የሀይማኖትን ምግባር በፍተወስጋ በኩል አታንሱብን ብለን እንደምንባሌው ቴሎም ዝም፤ መጥሀፍም ዝም ብሉ ቀጭ ማለት ይሆናል። እለዚያ ግን የሚያራክሰኝን እኔም እኩል አራክሰውና በደልም እኩል ይሆናል። እንዴተጣፈው እግዜር ለዳዊት ሀይልን፣ ለሰለሞን ጥበብን መስጠቱ ልክ ከሆነ፣ በእሪቱ የተፃፈው የእመንዝራነት ማገጃ ወሸት ነው፤ በእግዜር ያልተጣፈ! ለተራው ሰው አታመንዝር፤ ለንጉሱንጉሱ ግን እንደሸው፤ ከእግዜር በታች በምድር የሆነ ቤት ሁሉ የሱ ይሁን ማለት ነዋ። በጦቢያ ሲሆን እኩሌን በድልልን ብለን ከመወለድ ይልቅ የበረታብንን፣ በልሆነ

ነገር የሚተያየንንና ምቀኛችንን ከቤት አወሰው፣ አብርደው፣ ልብ ስጠውእንጂ ገደለው፣ አጥፋልን አንልም። እኔ ጨዋታየን ይኸው ፈጀሁ! እናንተ ስትጫወቱና ያልታየኝ ደግሞ ሲታየኝ በነጻ አጠራቅሜ ወደመጨረሻው ሰዓት እንነሳ ይሆናል። መጀመሪያ ግን እያንዳንዱ የተያዘ-የተያዘውን ይጣል።» ብሎ ሲጋራን እንደገና ነካካው። ከሽማግሌዎች አካባቢ ጭንቀትና የፌት መታመስ ይታይ ጀመር። እርካታ እያ ተብጃን ብቻ አጠቃ። ሴት በማብዛት አጫፍሮ ቢደብደባቸውም የዘቸውን የቤት ዘራፊነት በፍፁም የነካ አላስመሰሉትም። ያለበል ዘረፋ የቀረትን ሽማግሌዎች የጠበጠበት ምክንያት ለዘመናት ሲወርድ-ሲዋረድ ታሪክ በቅድስናቸው የሚረገረግባቸውን፣ ስማቸው የብዙ ሀገናት መጠሪያ የሆኑትንና ቅኔ ከዜማ የተደረደለቻው ሰወች መንንተልና መሬክስ ገራ ስለጋባቸው ሳይሆን ይቀራል? አበባው ሁኔታው ፈር እየለቀቀ መሄዱን ቢረዳም፣ በዚህ ሁኔታ አለበልን ሊዳፈረው አልፈለገም። ጉምጉመ እያ ተብጃን ምችት ነሰቸው፣ የጀመረው ጨዋታ እንዲደሰናክል ስለሰጉ በፊታዳቸው ትችት ጀመረ።

«ወይይት አላቸሁት? ፍልስፍና፣ እውቀት፣.. በግልፕ የቶሉ ተማሪ ከተንጠለለ የጠረሀ ገንት ሳይ፣ ከለመለመ ያትክልት ስር መልከም ነፋሱን እየማገ ያወረደው የምርምር ዘረፋ ነው። የፌተኛውን ተናጋሪ ከሂለኛው ማመዘን እታተኝ። አለበል ፈዘኛ ይመስለኝ ነበር። አሁን ይዞት ያለው ማጣናትና ዘይቤ አቅሊን በጣም ነካው፣ ጨዋታውን አቶቆልመመት። በወረቀት የሚቀርብ መገት ነው። ጥንትም የጦቢያ ልጅ በተፈጥሮው አዋቂና ነገር በላች ነበረ፣ ነክተውት ቀርቶ እንዲያው ያወርዳል፣ ያን የነበረ ባሀሪ ከዚህ ቤት አገኘሁት፣ የታየውን እስኪወርስ ጊዜ ስጠው» ሲሉ አለበል ይሀን ቀዳዳ ተጠቀመበት። «የሚቸን ሰው ያቀበበር መገት ያመጣው አለመገሪዛቸው ነው። እንደቀበረ የተሰማመበት ስራ መጋለጥ አለበት.. በለም የተነገረላቸውንና የተነገረባቸውን የዘረኝነት ተቃውሞ ያገነዋል ከሚል የተነደፈ መሆኑን አላጠሁትም። በተጨማሪ፣ ፈላሽ አለመቅበረ መዘዝና እመዕ ይፈጥራል፣ የቀረንና ያልገረዘነው የፈላሽ ቁጥር በጣም እነስተኛ ነው፣ ቢንጫጫ ቷጫ አይከፍትም፣ ሁሉም እንደተገረዙ ቁጥር የማለት ተንኮልም ነው። ይሀን እኛም ጠርጥረናል። ያቀበበር ወሰኔ ለኔ ላለበል ቢሰጥ የሚቸ ሰው እስክረን ከዚያ የነጭ እፅም ጋር አይታጉርም ነበር።»

ሲጀመር ጀምሮ አለበል ላያ ተበበል የተመቻቸው ተቻ አይደለም። በመንደርደሪያ የሚሰጠው የነገር ገርፊያ የወደፊት ንግግሬ ጭማቂ በመሆኑ እያስወረፈ አስቸገራቸው፣ ስለሆነም፣ ከንዳንድ ጊዜ በቀር በማያስስቱት ተሸሽጊ ባሀሪያቸው ታጅበው አለበልን ማየት አታታታቸው፣ የሽከረና የጉረና ድምፅ ረታቸው፣ ሊያለበልሉ ቢያስሉም እሽ አላላቸውም። በዚያው የሽከረ ድምፃቸው፣ «ልጅ አለበል እንዴን ስትሽፍን በሌላ በኩል የታቀት ቀዳዳ እያወጣሀ ተቸገርን። እኛም ብንሆን "ጉይ" ከመታበሩችን አናስገባም። ሚቹ እዚያ መቀበሪቸው ተገቢ ነው። የኛም ደንብ ስለሆነ እቡ-አል (ይሁዳ) ያልሆነ እንተብርም ማለታቸውስ የንፅሀና ወደመታብር ወራጆችን የማጣዳት ነገር ነው.. በታውን የማስከበር። ታዲያ ያሁኑ ጨዋታሀ ወደደጅ አይወጣ። አለዚያ ነጮች ተቀብለው ይቶለመሙትና ሂላ ለማታናት ቅገሉ በጣም ሀያል ይሆናል» ሲሉ፣ አድምጧቸው ብሉም ቅጉ-ያጣ ፈገግታ ከለተመን በ ሂላ ቀጠለ፣

«የሀበሻ ብቻ መታብር ተከልሉና ተብጆቶ፣ እኛም ከመታብሩችን ሰባቶ አናስገባም ብንል ንፅሀናው የበለጠ አይሆንም ያለወት ግን አለ? በግዚር ፈታድ የሞተን ማንኛውንም ሰው ፀሉት አድርሰን በመታብር መኪያችን እስጠግተን መቅበር፣ ፈላሽ ባለመሆኑ የማጥለላቅና መታብር እንዲያራክስ የማሰብ ሳይሆን ሌላ የታረመ ምርምር የያዘ ጀርባ አለው። ያ ማለት በቁሙ ባለ ያመነበትን ለመጠበቅና በድኑን እንዲፈልስ (ፈላሽ እንዲሆን) ላለማድረግ ነው። እኛ ግን ከዘር እስከዘራዘርታችን ይሁዲወች ነን እያልን ዋረንእቶ ነው ነጭ እየረበሰም ላይ መታብር ያቶሽሹ ያለን። እያ ተበበል ጨዋታየን በደንብ አላዩትም፣ የጦቢያን የቀብር ትድረቶም የታሪክ ጀርባ ስተው አይተውታል።.. እያ ተበበል አይፍረ፣ 'ሀቅን ተናገሮ ከመሸበቅ ግደር እያስነውርም።» ሲል ተበበል ለማብራሪያቸው ተተኩ። «እንዲያ ስትልግ ልዩነት ቀጠለ፣ ባበሾች በኩል በረታ ማለት አይደል? ልዩነት ይጥፋ ከሚል ጨዋታ ላይ መስሉኝ የተቀመጥነው! ምን ትላለሀ ልጅ አለበል?» ሲሉ ልሳናቸው የተጠራጠረ መስሉ በጣም ተሰባሰበ።

«ሰው፣ እያ ተበበል! በዚህ አገር ስላንድነት ከሰበክ ይልቅ ስለልዩነት የሰበከና ልዩ መሆንን የወደደ ሰው አንድነትን ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል። ልዩ መሆን የያንዳንዱ ሰው ሀልም ነው። ከፈረንጆች ጋር በንድስይ መዋር ከተፈለገ ወገዱ፣ እምቢ፣ አትቅረቡን ማለት እንዲቀርቡን ያደርጋል። እበክቻሁ ማለትን አይወዱትም። ይሀ በማንኛውም ወቅት የታጠቸው ሀመም ነው፣ ቀላል ምሳሌ ቢፈልጉ፣ በጢሮው ሂደው አይተው ከሆነ፣

ከለመንና ከተሰማመጠ ይልቅ የሙኾ፡ ጠረ ፤ውን ከጉዳይ ፈጣሚው ሰራተኛ ላይ የገለበጠና የተሰደበ የልቡን አድርሶ ቤቱን ይገባል። እንዲያ ያለው ተጋሬ ትልቅ ምስጋና ከጀርባው ይነገርለታል፤ ይከበራልም። የተመታችው ባለሙያ ሰራተኛ ጠረጴዛውን በገለበጠ በሰምንቱ ሲሄድ አምበሳው! እንኳን ደህና መጣህ! ብሎ ብዙ እዲ የሚከሳ ጉልበታም የገንዘብ ቀሊዱን (ቸክ) ነው አኩርታ የምቅስጠው። ከዚህ አገር መኖር የፈለገ ወንድ፡ ጉብዝ መባል አለበት። ጉልበትና ተጋሬነት ትልቅ መመሪያ ነው። ከትሁትነት ይልቅ ሀይል በጃእያ ይኑር! በጅ የሚለያት ከሆነ ይሞክረ፤ እውነቱን ካልሆነ አለበል ምን ብሉኝ ነበር ብሎ ው ባደባበይ ይመኝ፤ እፍረ ከቤት አልወልም።

«በተሰራው እለም ነጭ የፈለገውን ወንጀል እንዲሰራ፤ ጥቁር ግን ነጭ ሌላውን ለመገየድ የሰራው ትእግስትና ምግባር የመማሪያ ት/ቤት እንዲሆን እግዜር መደብታል ያለያት አለ እንዴ እያ ተባባል? ያም ሆኖ የሰረትን ምግባር የሚያከብረት ቢሆን እንታማ ነበር፤ ምግባሪን ያስከብረታል እንጂ አያከብረትም። እነሱ በፈጠረት ዝባዝንኪ እኛ እየተተራመስን ለራስ መመለሜና ያለድሜያችን መሸበቻ እየሆነ ደየነን!.. እሰቡት፤ ከዚህ አገር ከደረሳችሁ ሰንት እንደነጣችሁ!.. ሽበት በሽበት። ይልቅ የታየኝን ልወርስ፤ በተራችሁ ስትናገረ እኔም ዝም እላለሁ! አታደናቅፉኝ።

«የጣቢያና (አለበል "ጣቢያ" የሚለው እንዳንዴ እንደቀልድ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከገጠሬወቹ ጋር ለመመሳሰል ካልሆነ "ለ"ንና "ፐ"ን የማናበብ ችግር የለበትም) የሌላ ሌላው አገር ይሁዲ ልዩነት እንደህ እንደጀመርነው ተፈጠረ ተባለ። እረ ለመሆኑ እኛስ ጥቁር ሆነ፤ አሽከናዚው፣ ሰፋራዲው፣ ሞሮኮ-አልጀሪያው፤ ፈረንሰይ-ጣልያኑ፣ አሜሪካ-ካናዳው፣ ግብጡ-ቱርኩ፤ ሌላ ሌላውን ሁሉ ይሁዲ የሚያሰኘው ምልክት ምንድን ነው? የተገተረ አፍንጫቸው ነው ቅሉኝ ይሆን? በዚህ በኩልስ ቀትራራ አፍንጫ ይሁዳዊ ነው ከተባለ ሰንት ይሆናል ቀትራራ ተብየው? ሰንት ጉማዳ አፍንጫ ነው የምናየው። እዚህ ላይ፤ አፍንጫ እንሰናል የምትሉ ካላችሁ መስደቢ እንዳልሆነ ይታወቅ፤.. ሸክም የሚወድ ይኖር ይሆን? ነፋስ በየቦታው ሞልቷል፤ ከርቀት የሚያስኬድ ነገር የለም። ደግሞም የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና የሚባል ዘመን አመጣሽ ስራ ተጀምሯል፤ አፍንጫችሁ ቢረዝም ያገር ሀኪም አክሳቢ ነው የምትሆኑ አይጠፋ!» ብሎ ሲዛበት ተከስተ የትችት ተራው በአለበል ያሳግበብ ማምታታት ተቀምቶ በሽቆ ነበረና እዚህ ላይ ሊለክፈው ያለ ሊለቀመንበሬ ፈታድ ተዘለለበት።

«ገምገ እፍ! እዚህ ላይ ጨዋታ አልወጣልህም፤ ደፍጣጣ አፍንጫወች ናቸው ስለለከኩ ያየናቸው፡ ማይክል ጃክሰን ረጅም አፍንጫ አልነበረውም፤.. ከስእሉ ላይ ማየት ነው!» አለው ሁለቱን ክንደቹን ከተራጠጡት ጉልበቶቹ ላይ አስደግፎና ጀሮወቹን በመዳፎቹ ደግፎ ተመልካችን በሚያዘና ሁኔታ ተስሎ። አለበል በመልስ፤ «አንተ ያልከውም ይሆናል፤ ብዙ የረዘመም አጥሯል፤ ወብ አድርገህ እንብዘበ!.. ወራንታ እፍ! ቢጠግኑስ ያንተን አፍ የሚጠግኑበት መሳ በሰረ፤ ሁሉ ሲያዳምጠኝ ያንተው ዘሉ መግባት የምን ነው? አሁን ያለሀበት ተጠፋኝ። » ብሎ ቤቱን አስቆ ቢወጣለት ወደጨዋታው ተመለሰ።

«እኔ ሳውቅ በ"ቶራ" እምናለሁ ያለ ሁሉ ይሁዳዊ ነው። ከዚህ ውጭ ግን የቀለም አቀባብ ሀይማኖት ከሆነ መላው አፍሪካ በሙሉ ተበድሏል. መቸም ሀይማኖት በመበደር የተበደለ ህዝብ ነውና። የደቡብ አፍሪካው ደገዞሞስ ቱቱ ከፈረንጅ የተቀበሉትን ነጭ ማቅ አውልቀው ልጣቸውን ለብሰው ብረት ቢታጠቁ ኑረቸው በጣም የቀና ይሆን ነበር፤.. እንደኔ ቢሆን ማስቴ ነው፤ እነቸውማ እንግዲያ አንዴ እንደቀና የትደሰት ፈረስ ተይዘዋል። ትክክል ሀይማኖት ማለት ማውለቅ ብቻ ነበረ. የእኔ ምርጫ። ምነው ማለት፣ ከቅድሙ እያት ይቅርና ካያታቸው ያልደረሰ ትርስና ብሉም ያሳወቁት እግዚሀር አደከንናቸውም ብየ በማሰብ አይነት አማረኛ ነው። ተሰስተሀል የሚል እግዚሀር ከመጣ ደግሞ፤ የቀለምን ነገር አስወግድ፤ ይህ ሀሳብ የማደበጅ ከሆነ ደግሞ ቀስተ ደመናውን ከሰራሀበት ቀለም ሁሉ አንስተህ አረንጓዴ ሰው፣ ሰማያዊ ሰው፣ እያለን ተብሉ ይጠየቅ ነበር፤ በዚህ ካልተስማማ ደግሞ ሌላ ድርድር ይሆንና እለም እኩል ሆነች ማለት ነበር. ደቡብ አፍሪካ ላይ ያለም አንድነት ተመስርታ ቁጭ እግዜር ቢወርድ።»

«አረንጓዴና ሰማያዊ ሰው ቢታከል ዘረኝነት ይጠፋል ያለህ አለ እንዴ? ጨዋታ ዘዋሪ በትለኝ፤ እዚህም ላይ ጨዋታ ተበላሸብህ፤ የምንሰማህ አይነትም አልሆንክ አሊው፤ የፈለሽን ታሪክ ብታወራ ይሻልሀል፤ ይኸ ከውጭ የምትሰበው ዝባዝንኪ ቅራኔ ውስጥ የሚከትህ ነው።» አለ ተክስተ፤ አሁንም ከስነ-ስርአት ውጭ በመሆን አለበልን ሲያበጨው።

«ጨዋታ አልወጣልህም? እኔን ደፋ!.. ስማ!.. እግዜር የሁሉን ነገር ባህሪ ሲያበዛ የቀረው ነገር ቢኖር የሰውን የመልክ ቀለም ሲያድል እጁን ማጠጡ ብቻ ነው። ለዕጊረዳ ከሰጠው ያበበ ቀለም አይነትና ብዛት ሰውን ግን በሁለት ቀለም ብቻ ይደደይነዋል። የደጋውን የዕጊረዳ ቀለም ከቆላው ይቅርና ከወይና-

ዶጋው ላይ አታገኘውም።. ከሀይማኖቱ ብዛት የሚገኘውን ሰላም አትመለከተውም? ሁለቱ የሀይማኖት አይነት ቢታገር ከሌላኛው ጋር ሰላም! ቅብብላለሁ። የቶዲ ቀለም ግን ጠቆሮ መንጣት አሊያም ነጥቶ መጥቶር ብቻ ነው። የምታየው ነው፤ አንተ ነውን ቶሚፕ ስትለው እሱ "ኩሽ" ይልሀል። በጥቁርና ነጭ መሀል ብሜ ሰው አለ የምትል ከሆነ ደግሞ በሁለቱም የሚደየን ህይወት ነው፤ አንዱ "ድቅል" ሲለው ሌላው "ንፍፕ" ይለዋል። የብሜውም የራሱ የሆነ ኩራት ይኖረው ይሆናል. ካንዱ ቤት ሲለቀስ ከሌላውም ይለቀስልና። መቸስ በየቤቱ የማይታጣ የሰው አይነት የለም። እኔ እንዲያ ነው የሚታየኝ፤ ቢገባህ ይግባህ፤ ባይገባህ ደግሞ እንዳሻህ፤ እኔ ግን አረንጊዴ አሊያም ሰማያዊ ሰው ቢሰራና ባለው ላይ ቢታከል ብዙ የጠመንጃ ትግል ያስቀር ነበር። ይልቅ ጨዋታየን ልጨርስበት አታደናቅፈኝ።

«እምቢ፤ የሰው ዘር ማለት እኛ፤ ምንጊዜም ነጭ ብቻ ነው፤ ጥቁር፤ መጋዝ ሆኖ ነው የተፈጠረ ከሉ ክሀበሻ ጋር አልተዳደረም ማለት ነው። መነከከት ሲመጣ የኔም አመል ይሸምብኛል። ደግሞም ከሚዳ ተነስቶ አይደለም። "አባ ጉርጊሪ ዘንዶ ያወጣል" ይባላል- የዚህን ጉድጊድ ነገር ያነሳነውም ሆነ የቶፈርነው እኛ አይደለንም። የ"ሉሲን" ታሪክ ልንገራችሁ። "ሉሲ" ስል ግራ አይግባችሁ፤ በጣም ያሸከፈፈች፤ ያንድ ዘመን ጣቢያዊት ቤት ናት። ዝንጀሮነክነቷም አላት ይሏሉ። ዝንጀሮ መቸስ ሰው በዶር፣ በገደል ሳለ ያው ዝንጀሮ አይደል የነበረ. ታዲያ "ሉሲ" ያፅም ስም ነው፤ የሰው አጥንት። በሰይንስ የሰው ህይወት ተመራማሪ መረት ቶፈረወችና የቆረ አፅም ፈላጊወች ነጮች! የሰው መፈጠሪያ መጀመሪያ በታ አፍሪካ ብሉም ጣቢያ፤ በኬንያም ግድም ነው ማለት ጀምረዋል። ነገ ሲቶጫቸው የሚለውጡት ካልሆነ። የውሸት ነገርም አይደል፤ እስካሁን ድረስ፣ በሌላው አለም ከተገኘው የወደቀ አፅም ሁሉ የበለጠ እድሜ የቆረ፤ ያንዲት ሀበሻ ሴት ቅሪተ-አካል ነው። ከዚያ ያረጀ ግን ገና አልተደረሰበትም .. በዚያው ግድም ይገኝ ይሆናል። የሚገርመው ግን.. ቶፈረዋ ነጭ ናት ብያችሂለሁ። በመሆኗም፤ የተቆረደ የወልድ ቶሲና የቆረ አፅም ውታቢ አናግሯት እንደሆንም አልታወቀ፤ ያወጣችውን አጥንት ወደዘር.. አሊያም ድንገል ሁና መታ ከነበረችም ወይዘሪት አፅም፣ በቀጥታው አነጋገር ሲሆን ደግሞ እመት ጣቢያ ማለቷ ቀርቶ፤ የቶፈረዋ እናት ይሁን ያያቷ ስም እንደሆነ አልታወቀም.. መቸም "ሉሲ" ብላው አረፈች እፅሙን። ሀበሻ አኩርፎ "ሉሲን" ጥሉ ድንቅነሽ ማለት ሲጀምር ወደሌላ ዜማ ልትለውጠው ሞክራ ሳይሞክላት ቀረ። ግን ዙሮ-ዙሮ

ያው ከ"ሉሲ"ነት አልወጣም። ይህ ማለትም፤ እንዲህ አይነት ነኝ የማለት ነገር ከተነሳ ማለቴ ነው።.. በኩሌታም ይሁንበት፤ የሌፋቷ ዋጋ ይሁንና እንዲያ ብላ ትስይመው። ምነው? ማለት፣ እኔን ደስ አሰኝታኛለች፤ እሷ በታወጣው ኑሮ ሀበሻን አፅም አውጣ ብትለው ይቅበጭህ፤ ሲያስቀብረኝ ነው አፅም አውጣ የሚለኝ? ብሎህ ነበር የሚያርፈው፤ ሀበሻ የፈጠጠ አፅም ሲያይ መርጥ አሊያም መቅበር እንጂ፤ የተቀበረ አፅም ማውጣት ቅስፈት ነው።

«ታዲያ፤ እየረሳሁም በነዚህ አበጣሪወቻችን ግምት ሰው የተፈጠረው፣ በማይና መሬት መዘርጊያው ታል የወጣው እዚህ ነው ይሏሉ። እነሆ! የሰለሞን ቤተ-መንግስት እየተባለ፤ የተገነተረ ሆነ፤ አልቶ መብፍርት ዘመን የቆረ ታሪክ፤ «የእንክሊ መንደር እየተባለ በእስራ ሁለቱ የይሁዳ ነገድ የሚጠራው ነገር ሁሉ እንደ አፅም ያወጣልኝ። የመበሳለጥ ነገር ከተነሳ ጣቢያ የሁሉም ፍጥረት እምብርት አገር ናት ብየ የምመሀና አገርን ወገድ፤ መንጋ ተቆረደ ሁሉ ብየው ነው የማርፍ። ያልታሰበ ነገርም ገና የሚታሰብ ይሆናል። የመከበር ሲሆን ግን መኩራራት ደግሞ ብልግናችን ነው እንወደውም።» ብሎ ሳበቱ መንቸርፈፍ ሲጀምር እያ ተባባል አለቀቁትም፤ ይኸኔ ዘለው አልገቡም፤ ጣታቸውን በፈራ-ተባ እወጥተውና ፈታድ ከሊቀ መንበሩ ተቀብለው ነበር ከለበል የመገቱ መልስ የገቡት፤

«አንተ አሽክር፤ ከሁሉም የበረታህ ሆንክ፤ "የተቀመጠብትን መንበር እር እይለቀልቀም ይላል የተባበመ ሰው፤ በኔ በኩል ሁሉንም ነገር የምታጠፋው ነው የመሰለኝ። ነገርህ፤ ወደትንክስ እንጂ ወደመፍትሄ የሚያመራ አይመስልም። ገና ለገና ከንዳንድ ነጭ ዘንድ ነቀፌታ ደረሰብኝ ብለህ፤ ከተጧጧፈ የጥቁርና ነጭ የቀለም ጦርነት ውስጥ የምታስገባን ነህ። እንዲያ ያለ ሁኔታ ቢፈጠር ቀድሞ ላንተ ጠብ-መንጃ የሚሰጥ ሰው የታመመ ነው። ከእንዲያ ያለው ሁኔታ እግዜር አይገጥመንህ። የነቀፍከው ነገር ሁሉ የኛን ታሪክ ነው።. ጣቢያ ላንተ ምንህ ነው? የሰው መፈጠሪያው፤ አይንታው የእሬቱ ታል የወረደው እየረሳሁም አይደለም ቶለኝ? ይለብኛል።. በልና ጣቢያ በየትኛው አምባ ላይ የጥፈረቱ ነገር ተወራ? የትኛው የእሬት ታል ወደቀ? በልክ! መሊ የበከበትን ተራራ ግራው! ይህ አጉል መግት።»

«እያ ተባባል፤ አልገባያትም። እግዜር ፍጥረትን ለመጣል ምን ከመሬት አስወረደው? መሬትን ለመፍጠር ከሌላ ነገር ላይ መሆን አለበት፤ ያንን ነገር ደግሞ ገና በጥናት አልደረስንበትም፤ የማወራወት የጥናት ነገር ነው። ጤፍ ሲዘራ ከላይ፣ ከክንዱ

አጠነነ አልነበር፤ የሚታየኝ እንዲያ ነው፤ ደግሞም እሱ በሚል ነገር ተነስቶ ሳይሆን በሚታይና በሆነ ተመርኩዤ ነው። በመገት እንጢር ይዩት፤ ተራርቀን ተያየን መሰል ጋሽ ተበባል.. ነውር አይደል! የተጠራና የበለተሚስ ቂስ ልጅ እኮ ነኝ፤. ባልጌ ታየሁዋ እንዴ?» ብሉ በጣም ሸለጋቸው። ቢሆንም ይህ አይነት መቿቿም ይመጣብኛል ብሉ የገመት አልመሰለምና፤ በጣም ነበር የተደናበረው። በሁለቱ መሀከል እያ ተበጀ ተተኩ።

«ተባባል! ለምን ትቸኩላለህ? የምናጠራውን ሂሳ እናጠራዋለን፤ የተናገርነው ሁሉ ከወረቀት ላይ ይወድቃል ማለት አይደለም»

«በሱ እእምሮ ከዳረ፤ ከወረቀት ላይ ባይወድቅ ቲም ማለት ይህ አይደለም እንዴ ተበጀው?»

«አንተ ገዛኸኝ ተወእክ ነው የምልህ፤ ጨዋታ በጣም አከረርከ፤ በዚህ አገር፤ ሰው የታየውን መናገር ይችላል፤ በዚህስ አይቀየመትም፤ እንዲያውም ማናገር በጣም ይወዳሉ። ይልቅ ይህ ተማሪ ሁሉ የሚያንበለብለውን ታሪክና መገት ነገ ለኔ ብለህ አትሰማም ? ነገር የሚበላሽ ከሆነ ማወቅህ ውብ ይሆናል፤ ትጠቀምበታለህ፤ ሰላም ከወረደ ደግሞ ዝም እንዳልክ ከንተ ጋር ታስቀረዋለህ፤ እምነትና እምልክ የግል ነው ቢሉ አልሰማህም? አለበል ያመነውን ቢያምን ምን ገደደህ፤ ኩነኔ የሱ ይሆናል። የመገት ነገርን ዝም ብለህ እንደኔ አትቃርምም ይልቅ? አደባባይ ላይ ብዙ ጠሀይ ያልተመታህበትና ለክማሪ የብርሌ ጠላ ያህል ያልከፈልክበት የመገት ችሉትና የውቀት ነገር ስታገኝ ዝም ብለህ መሸመት ነው።»

«ጋሽ ተበጀ ምነው እያወቁ. ፤እምነት የግል አይደለም፣ እኛን የገድ መምሰል አለባችሁ» ከመባላችን የመጣ ብጥብጥ መስሉኝ እንደህ ያስቀመጠን! መንጋ-መንጋ ልጅ እምጥተንና ከዚህ በትንን፤ ገጭታ የሚያበቅል ነገር በኛ ሲብረታ ከጀል ነገር ይደርሳል ብየክ ነው.. ቀደም በተደረገው ጨዋታ ነሙች እየቀደሙ ጉድብ በማብጀት ወደር የሳቸውም መባሉ ከልቤ በጣም ተጥፏል። ጨዋታውማ እንግዲያ፤ የዝና መሆኑንም አላጣሁትም።»

«ለልጅ ወጣጭ አታስብ፤ በንግርት የመጣ ነውና ያመጣው አምላክ አይጥለውም።» ብሎ ተበጀ ለተባባል መልስ ሰጡ። ያለበል አስተያየት በዚህ አለቀ፤ የማደሽ ቡናና ሻሂ ሲባል፤ የመፀዳጃ ቤቱም ተራ ተጨማሪ ትእይንት ፈጠረ። የወጣት እሜሾች ጠብ ከበረንዳው ወደቤቱ ተትጉለጉለ። ቡና እደላው ትንሽ አላጋንና ለመቀጠል ተንጨበጨበ።

የመሸጋገሪያው ትንተና ሰጭ አሁንም እበባው ሆነ። «ጃግና ሰው፤ እያችሁ ወገን፤ ባለማዊ ሀይወቱ የተከበረ፣ የተጠራና መታፈሪያ ነው። ቢሞት ለቀሪው ትውልድ ቅርስ ጥሉ ነው የሚሄደው። ሞቶ ተመኝሀ አትበሉኝና. የሆነ ነው። ይህ ያየዋ እምሪ (ተስቶት እንጂ ሰውየው ታምሪ ነው ይባሉ የነበረት) ማለፍ ከቀም ነገር የሚያደርስን ይመስለኛል። መጨረሻውን ያብጀልንና በጣም እያነታታን ነው። ሳየዋም ቢሆን (ሟች ሰው) · ከመልክም ሹቱ፤ መልክም ሰም ይሏልና፤ ጥሬ ሀወልት ተከሉ ማለት ነው። ዘመድ አዝማድ፣ ወገን በሙሉ የማማከራብት እርምጃ ይሆናል። ከንጨት የተጠረበ ሀወልት ሳይሆን ከለት ተመልምሉ የወጣ ጥርብ ነው። እለም ካልጠፋ አይጠፋም፤ የረሀውን ጥርብ ሳልበሳ ብሉ ዝም ነው።

«አሁን ታዲያ ሰውን ሁሉ የምጠይቀው ጉዳይ፤ ችግር ማንሳት ብቻ ሳይሆን የዘርፍ መቿጠሪያ ማብጀት እንዳለብን ነው። እሊያ ከፈትከፈት አዝንተን የሸመነው እየተበተነ ሁሉ-ነገራችን እንዲያልክሰከስ። ወደመከርከሚያ እንድረስ።.. ዶክማችሁ መስል?» ብሉ እንደጨረሰ እያ ዘላለም በለተራ ሁነው ትንቀናውን ተቀበሉ። ያለበል የጨዋታ ግፊትና አለመጠቅለል እንደተባባል ገና እንደከነከናቸው. መሰለው ታዩን፤ በቡናና ሻሂው ወቅት በጣም ተረብሸ ቀልድ የተቀባቀለበት የቃል ልውውጥም ያደረጉት ከሱ ጋር ነበረና ከመተማመን ይልቅ አለመጥጥ አይሉባቸዋል።

«ለምን ደከማችሁ? ያበኝህል! ጊዜ የቆረጠው የመዋት (ጠበል) መንገደኛ የተወጨና ከተመደበ አገልግሉቱ ወጥቶ የተጣለ የቅል ሸንኩራ ይመስል ከዙሪያ ማንብ ስር ተቀምጠ የፈረንጅ ራስ ሰቶጥር ሰወልም አልደከመኝ። ያገሬ ልጅ ጨዋታ ሁሉ በጣም ርቶኝ ከርሞ.. ሊደክመኝ ይቅርና ብርቅ ሆነብኝ። የተያዘው ጨዋታ በጣም ታምር ነው። ከቃል የሚዘረፍም አልመሰለኝ፤ እንዲያው ከመጠፍ የሚነበብ እንጂ! ግብይ። በገጠ፣ በኔ በኩል ነገር አጠራ፣ ግልጥ እየሆነ ሄዷል። የገበረ ነገር- ከንግግር ያዘ ያደርገኛል፤ የምትሉትን ለመደገፍ ግን አንድ ምሳስ እሆናለሁና ወወት በናንተ ያምራል። ተባረኩ!» ብለው ሀተታቸው ቁምጥ አለ። ብዙ ሀተታ የሚሰጡ ነበር የመሰለን፤ ግና እሳቸው ድጋፋቸውን ሰጥተው እባ ሰማኸኝ ሊናገሩ ተተኩ።

«እንደሁም ያስ የለ! ሆኖም እያወቅ! ሰው ሁሉ በጨዋታ ትንታኔ ከኔ ምን ያህል ርቆ እንደሄደ ያየሁት ዛሬ ብቻ ነው፤ እገር ከጥሬ ገድ ላይ ነው የጣለኝ። ይልቅ፣ እስከሁን ያደርጋበት መዝገብ ይነበብ. የቀደመን በደንብ ቀርፆን የተረፈን እንደገጨምር . ከዚያ ወደፊት ይገፋል። በጣም ብዙ ቁም ነገር ወደቀና፤ ከላይ

ከላይ ስትሸመብኝ ከራሴ ውስጥ የያዝኩት ቅጡ ተጣፋብኝ፤ ብዙ ነገር እንዳገባ ግን ሲተራመስ ይሰማኛል።» ብለው የሳቸው ክዘላለሙ ያጠረ ሆነ። ይኸኔ፤ አይኔ ፈጠጠ። በንዴህ ያለ መንገድ ይመጡብኛል ብየ ያሰብኩት ሰው አልነበረም። የፈጠጠ አይኔ ቢፈጥም የምለቀቅ አለመሆኑን በደንብ ነበር የተረዳሁት፤ ሁሉም በጉጉት አየኝ። የወሸንገርኩትን እንብቤ ስጨርስ እያ ተበጆ አይናቸውን እንደጣሉብኝ ቀረ። የያዝኩትን ግን እንብቤ ጨርሻለሁ። ሌላ ሰው ሳይቀድመኝ፤

«ተቤ፤ የጤና! የተበለሸሸ ነገር ተገኘብኝ እንዴ?»

«በቃ?.. ያደርጋበት ይኸው ብቻ ሆነ?»

«ምን ቀረብኝ?»

«ምን ቀረ? ይለኛል? ምን ይቀርብኛል ብየሀለሁ? ስራም አልሰራሁ! ከልብሀ ከሆነ የምትጫወት፤ አይነታ ታሪክ አልተመዘገበም። የነስሎሞን፣ የነዳዊት፣ ግን አላቸሂት ያችን አፅም?.. የሷን ትንተና ሁሉ ከመዝገብ ላይ አልጣልከውም። ይኸ ነገር አልሆነም.. ካንዱ ቢስት ሌላው ነው። ካልሆነ ረዳት ይጨመርለት።» አሉ። በርግጥ ይሸር ግለት ከብዷቸውና እኔን የሚያርቅባቸው ሁኖእንጂ በጣም አናድጃቸዋለሁ። «ዋና ከታቢ ብየ መርጬ፣ በጨዋታ ልቡ ያልተነካ ሰው አባልፌ ጉድ ተሰራሁ!» አሉ፤ የጉስመኝን ግላሲያ ባቅ የተተባቀለበት አስተያየት ወምረው። የሳቸው የዘልግድ መላ ተጨምሮ፤ ሊቀመንበሬ የበለጠ መሸፈኛም ሰጠኝ፤

«ካንዱ ሁሉን ነጥብ ጠቅልሉ ይዘታል፤ የተባለው ሁሉ የሚገባው ሲረቀቅ ነው። ካንዱ መዝጋቢእንጂ አርቃቂ አይደለም። ያኔ ብዙ ሰው ይታክልበታል።» አላቸውና ብዙውን ተግሪ ፈገግታ ወረረው። እነቸውን ግን የመራው ሸንገላ ባያረኩቸውም መልሰው መናገራቸው እኔን በጣም ሊቶነጥባቸው ስለሚችል ዝም አሉ።

የትንተና ፈንታ ድግሚያ ስተካ ሆነ። ነገር መሸብለል ያውቃል፤ አቅጣጫ ለማስያዝ ሆን ተብሉ የተሰጠው ነበር ግለት ይቻላል - «ያለፈ ትንተና ሁሉ ወደፊት ይጠቃለላል። የምንደረደረው ወደሚታየኝ መፍትሄና አቋም ይሆናል። አሁን እንዲያ ነው አቋም!

«የምን መልክ ልታሲይዝ ፈልገህ ነው? መልክ ማሲያዝን እንተዋለን ብለን... የምናወራው የግዜር ስንክሳር ነው፤ እግዚሀር ምንም የተለየ መልክ የለውም ብለን መስሉኝ የምናወጋው? መልክ ማሲያዣ መስሉኝ አገር የፈታ! ስንክሳሬ ደግሞ፤ በውን እንደስንክሳር ከተቆጠረልኝ፤ ጆል ነገር እንዳታነሳ መፈናፈኛ ቀዳዳ ያልሁትን ሁሉ መድፈኔ ነውና ይህንም ጨምረህ ተረዳ።

«የከርከር ነገር ወትሮም እንዲያ ነበር። በበቴ አድሜ ጊዜ የሁለት ጉረቤታም መግት የሚያልቀው በፋይሉ ጥዜማ ከቤት እንደነበረ ነው። ጠዋት ከዳኛው ፊት በየገጣቸው የሚያቀርቡትን የቃል መከላከያ ሁሉ፣ ጠላቸውን ከፊታቸው ላይ በየቤታቸው እያስሞሉ፤ ሳቱን እያስቶሰቶሱ፣ ከጠላውም ሀይል

እያነሱ፤ በነገሙ ፋይል እኔ እንዲህ ብየ ስለሀ፣ ምን ይጠጥሀል? ቢል እንዲ፤ ሌላው በመልስ፤ እንዲህ ብየ እሞግትሀለሁ እየተባበሉ፤ የሙግት ነገር ተንሚልጦና ተዘግቶ፣ እንደኛው መረታቱ ታውቶ፤ የደስታ ብርሌ በጥቂው ተደርድሮና እንኳን ደስ አለህ ተብሉ፤ የማታውን መግት የሚሽረው በድብቅ ሲሰፈር ያደረ ገብ ነበር። አንተንና እኔን በዚያ ጊዜ ብንመስል ለማለት ነው። ታዲያ ከዚያ በመሰስ ያለው መግት ሲይሆን የገብ መስጠት ውድድር ነውና ጉልበትህ የሚመነጨው ከንብረትህ ማየል ጋር ይሆናል፤ የውቡ ጊዜ፤ ቲም ያልበዘበቱ ዘመን! ዘሬማ እንግዲያ ባለቤቱ የማይናገርበትና ጠበቃ የሚበላ ወሸታም የሚቀበለበት፤.. ጥንት ሲሆን ነገረፈጅ አቅም ላነሰው፤ ወተት ከመጉተት በቀር ሌላ ቃል ለማያውቅ ዘላንና አጊት ገሬ ብቻ ነበረ። ቤት ልጅ ከደባበይ ወጥታ በራሷ የምትገተችበት ጊዜ ያኔ ብቻ ነው፤ ዛሬ ግን ተወው፤ መግት ማለት ነገር ማጥሪያ ሳይሆን ወሸት ማስረጃ ሆነ። ይልቅ በልማ፣ በጥንቱ አይነት የመግት ስልትና ብልሀት ነው የተያያዝነው፤ ለገብና ለወሸት ጊዜ ገና አልደረስንም።» ሲሉ አለበል ሲዘብጥ እንደፈለገ ሁሉም ተረድቶታል፤ ግን ዝበጣው ምን ያህል ተበጅን እንደሚረታ የተረዳንለት አልነበርምና ይጠጣውን ልንሰግ እፍእፉን ጠበቅነው።

«አሌ፤ በል እንጂ ግፋ! የኔን ጨዋታ ማወሳደፍ ብቻ ችሉት አይሰራም። ተራመድ፤ መራመድ አታውቅም መሰል!»

«አየዋ፣ መጨረሻህ የእስራኤልና የጦቢያ እግዚሀር አንድ አይደለም ለማለት አይደል?»

«የጉድ ነው፤ "ተንጋሉ ቢተፉ ተመልሶ ታፉ" ይሳል ማጤንን ሳያስብና የቅርብ እንቅፋትን ሳይረዳ ሰው እርምጃ ሲወስድ ያየ፤ ልክ ካሌ የገጠመ። ተመልሰህ ከዚያው፤ አናግረኝ ሳልል በጀመርከው፤ እየሄድኩ ሳለሁ የመጥሁፍህን ዝላፊያ ጀመርክ። አረት ያወገዘውን ጣኦት ለኔ የዳረግከው፤ ቲሜ ገና ትክስ ነውና አልረሳሁም፤ ያንተ ዝወራ ለኔ ጠፍቶኝ ነው? ውታቢየ በጣም የተገራ ነው፤ ቀበቶውን የሚታጠቅብኝን ጠላት በረን ሳይለቅ በውታቢየ እይዘዋለሁ። በልማ፤ ተያይዘናል። ከጨነቀህና እግር መጢያ እጣሁ ካልክ ደግሞ፤ እግዚ-አብሄር እንደተባለው ሁሉ፤ የበራኤል አምላክ ማለት የእስራኤል ነው፤ ለዚያ እግዚሀር የተመረጥን ልጆችም እኛ! ወይ መግት!.. በል በዚህ በኩል እጅ ሰደድና እረታሁህ በለኝ!»

«የተጣፈው የአሪት ቃል የእግዚሀር አይደለም ነው የምትለው?»

«የምናወራው ስለእግዚሀር ምንነትና አይነት ነበረ፤

ስለሆነም፤ አንተ ግን ዘለህ፣ ባልገባኝና ተሰግምተን ስላልሰራነው የፅሁፍ ነገር እሽ ብለህ ተስማማ ነው ጨዋታህ! ወይ መያዝና አለመታወቅ! "አጟጟቴን አባምረው" አለ ያንተ ቢጤ፤ ዝም ብለህ ተጠቃሁ ብትል እንዴት ያለ ፍቅር በመሀላችን ያወርድ ነበር መሰለህ! በእሪታ የተጣራው ብዙ ነው፤ የመሬን አበር ትእዛዝ የወሰድክ እንደሆነ፤ እኔ ከልኩት ምንም አይርቅ፤ አታጥፋ፣ ከጠፋህ ትምታለህ ነው የሚለው። ያጠፋውን ሰይጣን ሁኖ ይመጥቃል፤ ያባጠፋውን ደግሞ ይወደጃቸዋል።

«ባያጠፋ የሚሞት የለም ማለትህ ነው እየዋ»

«ሞትማ የሁሉም ነው። ባያጠፋ የሚሞት እንዴታ! ያውም በቀጥር የሚልቀው ይሆናል፤ አንዳንድ በደረቅ አበባ አርጥብ ጎደድ እንደተባለው ሲቶጣና ሲያግበሰብስ የሚነድፈው ነው። ደግሞም የበሉ ነገር ነው፤ ተማሪን ምዝገባ ያስተማረው እግዚሀር ከመጀመሪያ ያስላውን እንደተማሪ ከመዝገቡ ያዋለው እንደዚያ ይሆን ይሆናል፤ ይባላልና ማከከሻ እንዳለው ግን ያውቃል! ሰው ሲጠንቀቅና ፈተናውን ሲያልፍ ብሎም ጥፋት በግዜር ሲሆን በ ሂሳው አለም የመከስ ነገር አለ ቢሉ አልሰማህም? ይጠድቅ እንደሁ? እንዴመጣህፉ ጎነት የየረሳለም ተከታይ አይደለችም?.. እያሳጋህ ግን ተያቄየን አልመለሰከም። አሉ!»

«አንተ ሰው፤ የድፍረት ድብትርናህ በዛ! ስለኔ አጥብታችሁ አትመራመሩ ይባላል...»

«ተማሪ፣ ስማ! ተጠቅተህል! አትመራመር ያለው ወደ ሂላ የቀረ ነገርን ሁሉ። እኔ የምናገረው ከፊትፊቴ ስላለ ነገር ነው፤ የሚታየኝን። የነዚህን ነጮች እግዚሀር ያየህ እንደሆነ የወደ ሂላ ነገር እንደነሁሉ የጦቢያ ጭፍና እኝኝ ብሎ የያዘ፣ መዳረሻና መወበጫ እጁታ ያጨ. ዱሽ ብትለውም ይሆናል፤ መውጫና መግቢያ የለለውም። ከመጀመሪያው አምባላቸውን ሲከዱና የጥቁር አቡራእል እንዴት ብሉ ሊዋር ይችላል ብለው ሲማማሉ የተመሰከረ፤ ከዚያም የደረሰንበት ጉዳይ ነውና ይሆን እንደመረጃ ያዝ!

«እግዜሮቻቸው ያስተማራቸው መከድን ከሆነ፤ እኔ እንደህ ያለ እግዚሀርም አይገባኘም፤ እግዜር ልብም ነው፤ ከዚህ ራስ እንጂ ልብ የለችም። የእግዜር ልብ እንደጦቢያ ባለው አገር የተሰደደው ጥንት ነው። ከሰዱት ገና አልተመለሰም። እኛም የመጣነው የራስ ነገር እንሰተን ነውና መፍራትን ወደያ ብል። እዚህ ያለው እግዚሀር በጣም ደም ለማኝ፣ አንዳንዳንዱ ሰው ያበሳጨውን የጦቢያ ጅን ይመስል ደም አፍስልኝ የሚል. ከሰው የበለጠ ደም ሰሰ የተጋበ እግዚሀር ነው። ከእያንዳንዳችን ብልት

የፈሰሰውን ደም የማናደላቸው ሰውር ቶሊያቸው መታረቂያ አደረጉት፤ .. አንዳንድ የጥቁር ደሮና ፍየል ደም የእመል መቷደሻ ማድረግ እንደለመደው አውጋር!

«ገና ያልተገባበንና እዚህ አገር ስላለው የሁለንተና ግብር አልተረዳህም። "ወየን ግን ያውቃል?- የቀላወጠ።" ይባላልና የደረሰብኝን ነው የማወራህ፤ እዚህ አገር የደም ግብር እንዱ መሆኑን አንተም ከብልትህ ቁስል የተረዳኸው ነው፤ እግዜር በብዙ ይመሰላልና ተጠንቀቅ፤ ወስላታ ተማሪ!»

የተረሳ ጓዝ

ስለ ጉዟቸው የሚሆን ገንዘብ ለመሰብሰብ ሲሉ እስራኤል በተዘራው ቤተእስራኤል የገንዘብ ድልዳል ከጀመረ ሰንብተዋል። አቢይ ሰብሳቢም እራሳቸው ናቸው። የመዘረፍ አውቶቡሱና ታክሲው ወጭ የሚቀለቀትን እንዲያመነምንባቸውም ቀድመው መልለዋል። ሰጭ እንደመቸው ከየጉዳዩ የሚመለሰውን፣ የከፍያ አበሉን የሚጠብቀውንና ከባንክ ገንዘብ አስኪሰበ ፋታ የሚፈልገውን ሁሉ ለመጠበቅ በየፎቅ ስር ይቀመጣሉ። የየመንደረን አርከበር በማንት ከወዲያ ወዲህ ወጡ-ገብ ማለት፤ ሲደክማቸውም አላፊ-አግዳሚውን በማሰየት ሊገዛ ከሚችል ቅዩዩ መከት ላይ መቀመጥ ሰሞንኛ ተግባራቸው አደረጉት። ቀመው ሲያወሯቸው ፋታ የሚያጡትን፤ ደህና ዋላችሁ? እንዴት አመሻችሁ ?... አይዟችሁ፤ በጊዜ ብዛትና በምሳክ እርዳታ የማይሆንና የማይለወጥ ነገር የለም። ብቻ፤ ቀልጠፍ፣ ቀልጠፍ፣ ፈንዲ-ጉላ ማለትንና መታተርን የመሰለ ነገር የለም።... ሲሉ ጊዜ ለለገሳቸው የገፋ ወረም ያክላሉ። ብቻ ከንዱ መንደር ቢያንስ ሰምንት ይዘግጣሉ። እንደህ ሰስነብቱ ነው ለመንደርተኛው የጉዟቸውን አለማ ደከመኝ ሳይሉ ትስቶብ የሚስጡበት።

«የኔ ኩራት የናንተም ነው። የኔ የተበጀ ወደጦቢያ መሄድ፤ በምኞቴ እንጠር ቢታይም የሌላውን ሁሉ እድማስ የሚመታ ገዘ ነው። ግብፃኖና አለማየን አስተድሚ ተናግረዋለሁና ድፍን እስራኤል (ፈላሻ) ያውቃል። ከኔ ጠባብ ምኞት ሌላ ጦቢያ የቀረውን ወገን ያጠናል፤ ወደዚህ ሊመጣ የተናፈውን በያቅጣጫው ተሳላኪ በማብጀት... መግቢቴን ሲሰማ ሁሉም ከያለበት ከደጃ መገኘት አይቀርምና የትልምን ነገር መጠቆም፣ እንደኛው ያመጣ አይነት ሱዳን ውስጥ አፈር መግቡ እንዳይበዛ፣ ሰሰሊበው፣ ተግኛውና ንዲዱ (ወበ)... ምን የሚቀር ነገር አለ! ታውቁታላችሁ፣ በጠቅላላ ለእንቅፋቱ ማብራሪያና መግለጫ መስጠት ያለብኝ ነው።

«በጦቢያ መቀመጥ ለተመቸው... ሁሉም የግድ ወደእየሩሳሌም ይምጣ የለበትም፤ እዚህ ስለየሁት መያና ትድረት ማብራሪያ መስጠት ይጥርብኝ ይሆናል። እየሩሳሌም ከሌሚውና ከብርቱካኑ አልፎ ቀጋና አጋም የጊዜ አትክልት ያደረገ አገር ነው። አትክልት ለናቀው የጦቢያ ልጅ ሁሉ ስለትክልት እከፋከፍ ማስየቱ ስንት ወበት ያመጣል። ስንገረው ባይገበውም ባደርግ ይቀናና ውድድር ሳስገባው ለተክል ዘር ቀን ይወጣል፤ ይኸ መቸም

በጣም ቀላሉ ነገር ነው፤ መቸም-መቸም፣ ከየሁት ሁሉ የማሸርፈው ብዙ ተግቢር ይኖራል።

«ወገን፤ ... ታዲያ፣... የተባከ የተባከውንና የተያዘውን፤ አንድ ጠጠር (ባንቲም) እንኳ ቢሆን መርጃ ነው፤ አንድ ብለው ሁለት ነው።... ችግር አያስመታውና አያስገርፈው ፊት የለም። የሰው ፊት የቷያ ሳት ነው፤ ይህ የሆነው እግዜር በኔ ላይ እንደሆን ከጠዋት ግንባሬ ላይ በማይታይ ቀለም የጣፈው ቢኖር ይሆናል። ጥሬም ሆነ በ"ቸክ" በቡስጣ እያደረጋችሁ፤ በጣም-በጣም በቅርብ ቀን፣ ባለሁበት... የምታውቁት ነው፣ ብታስገቡልኝ ሰጭን እያመሰገንኩ ከሰብሑት አደርሳለሁ። የቤት ቁጥር የዘነጋ ካለ፤ ይኸው አለሁ እስጣለሁ። ይህችንስ፤ ሰው ሁሉ ቀድሞ አስለብጦኝ መዳረሻየን በነፍስወከፍ ወረቀት አለኝ። እንኩ።» በማለት፤ የወጣቸውንና የተጣለላቸውን ይዘው የቀረውን ለመገፋፋት፤ ገና-ለገናው የሰውን አእምሮ በደሉኝታ ለመገየድ ደምድመው ሲለያዩ፤ «ተባረኩ፣ ብረክ ሁኑ፤ ላብርሀምና ለሳራ የሰጠውን ሲሰይ ለናንተ ይበለው፤ መቸም ሀልሚ ወደውነታ የሚለወጠው በናንተ ላይ መሆኑን አውቀዋለሁና። መውጫ ቀኔን አልቆረጥኩም፤ ልቤ ከነገ ዛሬን ይላል። መቸም... ከተባከ በዚህ ሁለትና ሰስት ቀን በስልኩም ሆነ በመላክተኛ እጄመጣችሂለሁ። ሳይነሳ እስከምንተያይ... በምሳክ ርዳታ የተባከ እንደሆነ፤ እናንተንም በሰላምና በደስታ አቅፎና ደግፎ አቶይቷችሁ ያገናኘን፤ ቸር ይግጠመን!» ብለው መንገድ ሲገቡ ዋና ስንብት ማድረጋቸው ለጥቂቶች አጠራጣሪ ቢሆንም ከባቸው በቅርብ ሳወቁ ግልፅና የቁርጥ ነው። ርመድ-ርመድ፣ ዘወር-ተከዝ፤ ትኩር፤ እንደገና ርመድ ሲያሰኛቸውና ሲያከረተርታቸው ማየት ብዙ ያሳስባል፤ የጡት ጥገኝነቱን አልጥልለት ያለች እናት የደጃፏን የላይ መከርከሚያ ማገር በእጆቿ ይዛና የተንገበገቡ ጡቶቿ የሞሉበትን ደረት ላይኑ አባጥታ ሂድ፣ ልጆች ይጠብቁሀል፤ በንቢይ ከብቱ ወለሀ ና! ብላ ልቅሸኘው ትገፋው የምትምክረውን ሀሣን፤... አሊያም ደንቢ ለሆነ ሰው ደግሞ፤ አንድ ጡበደል ክረምት ለማሳለፍ ከጉንደር ጉጃም አባይን ልትሻገር እናቷን ከጠራው የደንቢያ ግደ ላይ ራቀች፣ ሄደች ወይስ አለች? ፊቷን መለሰች? ከሰመች? በማለት በረፋዱ ጉዳና ላይ ቃዳታዶውን የሚጫግ መሪ ከበክብ ቢሷን የምትከተል ወገቢን የጣመናት ጋግ መስለውት ነው የሚያርፉት ቢሷቸው እስቸው በመልስ ወሸታም ሁሉ ብለው የሚዘበቱ አይሆኑም፤ አቅላቸው እንዲያ በመንታ የተከፈለ ነውና።

ይህ ባንድ ገጥ ሆኖ፤ የተበተነውን ወጣት በተመሳሳይ ኪስ

አስፈታሽነት እያቆ ሹመውታል። ለወኪሉ ከሚከፍሉት የመጊጊዝ ወጭ (አልፈልር) አንድ ለጋሽ ደብልተ እንደሚሰጥ ከገመቱ መሰከተኛ ቢሄድ አይገዳቸውም። «ግደለም፤ የተረፈው የስንቅ ማከያ ይሆናል፤ ሂደህ አንሳ ው!» ነው የሚሉት። የሚቻላቸውን ያህል ለመዝረፍ ለንዳንድ ስብሰቢ ወኪል የሚሰጡት ያፍ ማታለያና የማቸንፈያ ድረቱ ቶፕጴጠንነታቸውን ከሚሰቶቻቸው ዘሉ ለብዙ ሰው ያስጠበቸዋል። «ክንተ ወደኔ የሚመጣ (ገንዘብ) አይቀርም፤... ምንምንኪ ብዙ የምታገዝ ቢሆንም... ወጣት አይደለህ? የወረቱ መሸከፈያ ጊዜ ተርፎሀል፤ ግና ጊዜህና ለመጊጊዝ የምታወለው ሺ ጊዜ ከምትከፍለኝ ገንዘብ ይልቃል.. ከልተሰከልህ ምንም አይደል፤ መቸም ግን አደራህን፤ የምታገኘውን ንብል ሁሉ ተከማልኝ፤ ሀይ በለው፤ ወጣቱ የጊዛየን ነገር ተሉ ጠልቶ ይረዳዋልና ከሌላው የበለጠ የሚራዳኝ ይሆናል ወጣት ተራማጅ ነው» ይሉታል።

ከሰድስት ወር በሳይ (በገሀድ) በዚህ ልፈፋና ዘመቻ ሲከርሙ፣ ያገቻቸው፣ ብዙ ወም የተዛበተባቸው ሰዎች ቁጥር ጥቂት አልነበረም። አወጣጣቸውን በሚመለከት መሰናከል የበዛበት ጋራ፣ ሸለቆ፣ የማያስልፍ ጥቅጥቅ ጫካ አድርገው የተመለከቱት እሳቸው ባይሆኑ ታዛቢዎቻቸው ነበርን።

በኔ በኩል የተሰበሰበላቸው ባንቲም እንዳለ ለማጠራት እያሰለሉ በቁሰፎኑ አረጋግጠው ስለነበር ገበገበው አልመጣም፤ የተገናኘነው የመሰባሰቢያ ወፍታ ልናደርግ በተቃጠርንበት በታ ተገኘን። የሆይፋው ሀዳር (እኛ ፒያሳ ብለን እንደምንለው አይነት ነገር) ለሁላታችንም አማካይ የሆነ በታ ነበርና ወደማረፊያ እንደገባን ለመጀመሪያ ቡና አዘዝን። ወሀ ፍ መጠለስ ስለጀመረ ከፋብሪካው የሚወጣው የጢስ ዝገት ሬት ለፈታችን የተሰጠውን የአቶላንቲክ ውቅያኖስ የተኑን ያህል ጭጋጉ አልሸፈነውም። ጨገጉ ጠፍቷል ማለት አይደለም፤ እንዲያውም በያንዳንዷ የሰከንድ መታጥን የሚጨምር እንጂ፤ የጭጋጉ አስመስለት ግን በጨለማው ተደበሰበሰ ነው። አይኖቻውን እዚያ ላይ እያስረከረኩ፤ የተቻኩሉ መሰሉ።

«ከንደ! ልብህ አንድ ነገር ሲያስብ ዝም ብለህ ተመኝ፤ ተመኝ፤ እምላክም ንዝሪውን የመጥሳትም ይሁን የልብህን ምኞት ሞልቶ ደስታ በስራ እካላትህ ለክትበት ይሆን አሳውቅም የተመኘኸውን በጭቅጨታህ በስቲያ ይሰጣል። ሹምና እግዜር አንድ ነው። ሁለቱም በጭቅጭቅ ነው። "የሹም- ሹም አለው"፤ እንዱን አጥቅተህ አንዱን ነው። የሽለታ መሳኩ የበላይ ሸለታ መንግስቱ አይደሉ?... ግና ሸለታ መሳኩ እቸንፈውኝ ሸለታ መንግስቱን "እግዜር ያስየም፤ እምላክ ያጉልብትም ያልከበት ነገር የለም፤... ጉልበት

ያንሳቸው ይመስል! ታዲያ መቢልን ነው የምስግ። ወደፊት ከጠለብኝ ግን አይቀርም። ዘወድ ባይጭንም በዘወድ ዙሪያ ነውና ያሉት ከዚያው ቁጥር ነው። በግዜር በኩልም እንዲያ አይነት ጉዳና ቅክተሳለሁ። የሱን ሰም ብቻ አትጠራም፤ እጋገፎን እንዲአትካሪ ትልክበታለህ። እናቴ ሰንበቱ እባክሽ እማልጅኝ፤ የደንጉርሆው ቶሌ፤ ያበቴ ወቃቢ፤ የዚያች ተማሳይ እናቴ ፀሎት፤ እኔ ለከፍኪፋ ነኝ፤ የነሱን ደግነትና ላንተ መገዛት በኔ እንደሆነ ቁጠረው፤ ከነሱ አብራክ ነውና የወጣሁት... የማትለው ነገር የለም። ዙሪያ ማናገሪያ ሁሉ ተበጅቶለታል። እያንዳንዱ መቶ የመማለያና የመማጠኛ መላ አለው። የተበፈፈ በለፋ፤ ዘረዘሮ መዳረሻው አንድ... እራሱ ባለቤቱ ነው።

«ታዲያ ሰው ሁሉ ሁ-ጊ-ተ-ኛ ነው። ይህ ብለህተኛ ሽማግሌ፤ የማያፍር! ጦቢያ ልጄድ ነው ብሉ ገንዘብ አስወጥቶን የቴለብዢና የስልኪ ማስገቢያ፤ የደርና የእርጎ ማቀዝቀዥ (ማቶሪያ) ገዘበት» ብሉ እማኝ። ይኸ ማለት ሞት ነው። ደግሞም "ፈፋ ባበይ ሰተ" እንዳሉት ተረት ነው። ተን አይጠልሁ፤ እኔ ግን በተን ተዋረድኩ... ቢሆንም የማታ ማታ እግዜር እፈር አሳለኝም። ቀናኝ! በዚህ ሀጊተኛን አጠቃሁት» አሉ በመንደርደሪያ ወሬያቸው። ቀልባቸው ገና መርጋት አልጀመረም፤ ገና እላይ-እላይ እንደነዘረ ናቸው።«ዘመድ አዝማዴ ደህና ረዳያቸ?»

«ወይ ዘ-መ-ድ- አ-ዝ-ማ-ድ! ዘመድን ብስማውም እኔ ነኝ እንጂ ለኔ ለተበጀ የሚል የለም። የዘመድ ወዳጅ አይወጣልኝም። ኩ-ን-ዴ፣ ባድ ይውደድህ! ላንተ የሚደብቅ ምን ይደብቃል? ከመንገድ እነባስ ላይ እርጋ ማለቴ ጠቅሞኛል። እግዜር መንገዴን የወሀ ቢያደርገውና እንቅፋቴን ሁሉ እስከሁን እንደከላው በሰንበሰት ተይደ ቢይዘው፤ ከመሄሬሪያውና ከበንቁ እልፎ በጦቢያአንኪ ጥቂት የሚራዳኝ ገንዘብ እግኝቻለሁ። በጦቢያ እሀል እርከሽ፤ የብር መገኛው ግን እንጦረጦስ ነው፤ እንዴት ማለት በጦቢያ የተረ ገንዘብ እጥረት ፈትም የነበረ ቢሆንም፤ ዛሬም ብሷልን ነው የምንሰማው፤ ታዲያ የያዝኩት ወረት ብዙ ጉዳይ የሚከላ ይሆን ይሆናል።... ግና፤ ሆዴ በጣም ፈርቷል፤ በጦቢያም ሆኘ የተደመጥኩት፣ ባይኔም ያየሁት ችግር ነበር። ከዚህም መኪሬው ገና ለገና መንሳቴን ቢሰማ እገዋ የተናገረበት ጉዳይ ያደስአበው ቀሳሴና ከስ እወሳቴን ስራ ነው። እጅን ዘመድ እስኪደዘው ድረስ በጣም ፈራሁ። ባለም የቀሳሴው መናገሻና የኪስ መቅሳሪው አዲስአበ ነው። ወሸት አይምሰልህ... ቢሆንም ሀሳብ አይግባህ፣ ገምባሌ ጫማውን በደህና ተን ገዝቻለሁ፤ ሳቢራውም ደህና ይረዳል፤ ጦቢያ አቧራ በጣም

ደበዘል! ጥቅል-ጥቅሉን ግጥም አደርጌ፣ በጉግው ከቁርጭምጭምቴ ራስን እንደጠነዝ ሞፈር እስሬ የግር ሹራቡ ውስጥ የከተ ነው፤ በበላዩ ባለብሰው ጥበብ ልክ ትመጣለች። እንኑበባለሁ ካለ ጊዜቱን በባለጀንር ከዘራ ነው የማነሁልለው። የት አቡቱ እንኪን መትልፎ ይቅርና ተቀምጦ ለመሰመን እንዲደበቃ አደርገዋለሁ።»

አጠናጠናቸው ገረመኝ። አራት ነጥብ ያስቀመጠብትን፤ ግን እስተያየት ማሰሽ ሲጠቅሱ ለዋሉት ሀተታ ምንም ምላሽ ባለመስጠቴ፤ ቡናቸውን እንስተው የማንበራቸውን ቶዳ ከባህር ላይ የወደቀ ከበቅ እንደሚሰራው የተለበተ ማእበል ሽቅብ ገምደው እፊት አሉት፤ ወደያው የማንበር መስመር ቶዳቸውን ቁልቁል አዘንተው ልመጥ ሆነ፤ አይናቸው ወደመሬት ቃጣውና፤ «ወብ መሳ ነው ብለህ?» ብለው እንደገና እፊትታ ገቡ። እየተመለከቱኝ አጠጣጡትና ለመልስ ጠበቁኝ። በሌላ ጨዋታ የማስቀይረው የተያቄ መልስ አልነበረምና፤ «ከዚህ ሲነሱ ጀምረው ነው ገንዘቡን ከግርያ ጋር የሚያስረትን... ይህን መጠየቄ ከሆነ ሀሳብ ተነስቶ ነው፤ ከ"አውሮፕላኑ መወገፍ" ሲደርሱ ገንዘብ ማስቶጠር ይዋርበዎታል፤ ቀብረው ሲያልፉ ከተያዙ ልመና የከረመበት ገንዘብ የመንግስት ሲሳይ ይሆናል። ገንዘቡን በጭንቅ ማስመለስ ቢችሉም በመዘግየት ደብክንበዎታል፤ የተበሳበቱትን ሰው ሁሉ ተመልሰው ማየት ምችት አይሰጥዎም።... ከኢትዮጵያ ሲነሱ፤ በገዳሪፍም ሲዋሬ፣ የገንዘብ እያያዙና እደበበቅ ነገር ባይገጥሬ ቁርጥው ነው እሁን እንደችግር የተጨነቁበት?» እልኩ ትንሽ ፈገግታና ፍርሀት የተቀላቀለበት ፊት እያስመታ ሂቸው፤...

«የጦቢያዊ በገዳሪፍ መሳ በጦቢያ የማይሆን ነው። የታወቀና የረከሰ መሳ ስለሚሆን ነው። የገዳሪፍን መሳ ተወው፤ ከዚያ የቀረ ነው። ሌላኛው ንግግርህ ግን ውብ ይመስላል፤ ከወዲያ ስደርስ፤ ከፍተኛው በሂላ ከውሀው መከፈያ በታ ገብቼ እሰናዳዋለሁ፤ ምን ያህል እንዳልፈጀብኝ ነው? እጠፍ አደርጌ ቶይቼ ጉግን መጀመሪያ ከእግሬ እንደጠለቀ ትቼ፤ እዚያው ላይ ግጥም አደርጌ እርመድ-እርመድ ነው። ሲሆን ከየር "መወገፉ" ዘመድ ደርሰ ይቅደና ይህ ሁሉ ጭንቀት ባለበት እዚህ እንደሰራነው ይቀራል።... ነገሬስ ጭንቀቱ የሚሰቀኝ አይሆንም፤ ስነፈር ተሰፍሮ፤ ስወርደም አብሮ ነው የሚወርደው... እህ! የገንዘብ ነገር!»

«በደርግ ጊዜ ቀላሉው የቀነሰ አይመስልዎም?» አልኩ፤ ከሽንት ቤቱም ቀላሉ ይገኛል ብል...

«እቤቱ! ያንተ ጨወት፤ ይኸ የማዘናጋት፤ የመርዳት ባይሆን

በእወቅ እጅን እንደሰጠ የሚገፋፋ ምክር ነው። እህእፓ ያን ያህል ሰንት ሌባና ቀማኛ በተናጠል ገደል ለገደል እፈፈጣ የጠለምትንና የትግራይን ልማደኛ ባትቻችለው ቁርጥለች። የደርጉም ትግል ከዚያ ያየለ ቢሆንም.... ሙቶ በቀን ቢቀጣ እደስአብ ይሆን የምታየው የጨው ባህር (ሚድትራንያን ከፊታቸው ተሰጥቶ በጃቸው የሚነኩትን ያህል እያዩትና በጣታቸው ወደውሀው እያመለከቱ) ነው። በቀን የሚቀጠው ሰንት ይሆናል? ያደስአባን ያልበጀ ሰው በሞት መፍጀት ማለት በምኒልኩ ከብያ ጣናን ጨልፈህ ማድረቅ ማለት ነው፤ መናገሽ ከተማ አንዱ ሲሄድ ሌላው ሲተካ ነው። የምለበምበትን ንገረኝ ብየዋለሁ- ማዘናጋት! ከመጀመሪያውኑ የሚፈትሽኝ ሹም እንጂ ግን ሊሆን ይችላል? የጠገበት ሌባና ቀጣፊ ሹም ሁዋ ነው የተገኘ፤ "እይመጣንም ስበሽ ይመጣልን ያኙ" እለ የማልያን ጊዜ ሰው! እንተ እንዳልከው ሌባና ቀጣፊ ጠፍቶ ከቶ የኝም ጉርጊሬ የለብኝ- እለም! በዚያውም የደርግን ጉልበት ያስፋው፤ ዙፋኑን ያጥናው እላለሁ። ሌባ ሳይጠፋ ከቶ የኝ መጠርጠሬ መደኛየ ይሆናል። ስትጠረጥር ትጠነቀቃለህ፤ ስትጠነቀቅም ትድን ይሆናል፤ ከዳንክ ሌባ ጠፍቷል ማለት ነው። ተንፋለህ ከሰጠኸው፤ መዘናጋትህ በመጣው ደርግም ሆነ ሌባ የሚወነጀለው ያኔ ነው፤ ማስተዋልና መገንዘብ ብሉም ነገር ማንተርተር አደብ ስትገዛ የሚከተል ደኅነት ነው። ገልጥ ተናገርኩ?»

«በጣም ባት የበሉ ነፃ ተቢ!» አልኳቸው። ሞቅታ ገዝተው ተንሰራፉና እኔንም አንሰራፉኝ፤ ፈገግታ ብቻ ተለዋወጥን። በልማዳቸውና ተመክሯቸው ጥያቄ ለምኔ? ያሉ ከመሆናቸው ሌላ ሸቶጥቋጣ ሀፍረት እርግጣቸው ነው። የወርዳት ነገር ሲሰሙ በኔ ግድም አይደርስ ነው የሚሉት። በህሊናቸው የሆነ ነገር ሲዘር፤ የተገተረ ችግር ከፊታቸው ቢበገር ወገድ ይሉታል፤ የሚመታቸው አይነት ከሆነ ማእዘን መተው (ዘብጠው) ያልፉታል እንጂ ከችግር ጋር ፊት ለፊት ቁመው እንካ-ሰላንትያ እይገጥሙም። በዚህ በኩል የሚያደርጉት ትግል ሁሉ በተመልካች የነውር እንከን ቢዋረው ተበጅ ጉዳያቸው አይደለም፤ "ህበሸ ሲያግ እንድ ሰሞን ነው" ልብህ ያሰበውን ነገር ልታደርግ ስትፈልግ ሌላ ሰው ዙሪህ አትይ፤ ዝም ብለህ እራስህ አድርገው የሚል መሰረታዊ እምነት አላቸው። ግራም ነፈሰ ቀኝ በእንደዚህ ያለ ነገር መቀለጭለጭ የለባቸውም። የወሳኝያቸው ባለቤት ናቸው። ያጥፋቸውም?ያልማቸው እዋስኑኝ ማለት እያውቁም። ግና፤ ወሳኝያቸውን ሲያዋድኑ፤ ባስተዋፅኦ ይረዳል ያሉትን ሰው እእምሮ በመሰለል ያልታወቀባቸው ሌባና ቃራሚ ናቸው። ወደተግባር ስለውጠት ነው ያሰቡት ሰው ሁሉ፤

«እየኸው ይህን ወንበዴ! በዚያ ሰሞን… ያችን ዘዋራ ጠወትና ተያቄ ያነሳት ለተንኮል ኑሯልል፤ ነገር ቢያጠራቅም ክርሞ፣ ምን እንደሚያደርግ ባይታወቅበት፣ ወፍ ባይሰግ… አሁን ከእንዲህ ያለ ነገር ደርሶ አረፈ፤ በጣም የወጣለት ልበም ነው» ይሏቸዋል። ለዚህ ሁሉ ችሎታቸው ፍልስፍና ተመስ ማብራሪያ ይሰጠብታል። ምንጩ ብዙ የሚያጠያይቅ ቢሆንም አጠር ባለማምት ለመከዳን፤ ከሬል የተታረመ፣ ከሬል ከልምድ የመጣ ቢሉት ተበጀንም ቅር አይላቸውም። ታዲያ ይህን መሳቸውን ተንተርሸ በሰንሰሁት ወሬ እንዲህ ደረደረት፤

«እየህ… መሳኔ ጠለበት ነው። የማለሰብና የመንግስት መሳኔ አንድም፣ ሁለትም ባሁሩ ይሆናል። በመንግስትና በትዳር በኩል ስታየው ‹ተማክሮ የፈሉት አይሸትም› የሚለው ማለበሚያ ይገኘመው ይሆናል። በግብር ስራቱ የሚገባበት እጅ ብዙ ነው። አሁን፤ አንተ ዋና እለታ ብትሆንና ስለውን ታዘኝህ ብታደርገው እንዲህ ሳደርግ ነው ግለትን ብትፈራ፤ እንዲህ ብናደርግ ውብ አይሆንም? ትለዋለህ፤… ልብህ አንድ ነገር ለሰራ ፈልጉ ጨዋታ ስትከፍት፤ ‹ሆድ ቢያውቅ ደሮ ማታ› ነውና፤ አቅምህን ደክተህና ተደራጅተህ ነው። አፍህንም፤ መከበድህንም (እድሜ፣ ስልጣን) ከሹክር ተብየው ላይ ሚዋነህበት ያስብከው ይፈልግል። ጠወትህ ባይግባበውም ዝም ብሉ እሺ የሚለው እሹክር ይበዛል። ነፍሱን የሚያጠበት የጦርነት ሚዳእንኳ ቢሆን፤ በግልጥም ይወተው በሁለመ አስተኝቶ ይንገረው፤ ወዲፈቅእንጂ ወደ ሂላ አያፈገፍግም። እሺ ከሰጥኸው በኋላ፣ እንደተራጭ አቅማዳ የምትሞላበትና የምታዳፍርበትም ማታለያ ሞልቷል… ስትበላ አጉርሰው።

«በባልና ሚስት ረገድ ብቻ ስታየው፤ ቀደም ከተጫወትኩት አንጻር የሚርቅ አይሆንም፤ በወንድነት ብቻ የተገራህ ስለሆነ፤ ክሽናና የምጣድ ጉልቻ ማስፋት እንዳማይሆንልህ ታውቀዋለህ፤ እንጂ ብዙ ጊዜ ከዳጅህ ያልጠለውን የሚከበድና ብዙ ጠልቅና ስልፍ የሚያስጨይቅ ጥቅርእንገዳ ለዝና ለጨዋታ ዳግስህ ልትጉትት ስትፈልግ፤ ትዳርህን ሰው በሌለበት ጠርተህ ታዋዛታለህ፤

«እቴ እንዴት!… ስመመኔ፣ ምን ትያለሽ? የሰው ሰውነት አብሮ መዛናት፤ ማስተናገድና መሸፐት እውቀት ነው። መነፋፈትና መፋተር እንጂ ያለም ጤን፤ የሞት ጊዜ ያንዱ በድንብሳ ለሌላው ተለብ አይሆንም… እና እነልጆ እከባቴን እስክእታቴው በፋሲካው ሰሞን ብንጠራ?…» ብለህና ወዝፈህ የተውከው ጊዜ መተመቻዋ ይሰፋል። ከበርበሬውና ከቅመሙ የሚበነው ቅንታዋና በዚያም የሚመጣው ለቅሶ አይታያትም። ባይታወቃት እዳ ወስጥ

ታስገባታለህ። ከዚያ እሷ በመልስ፤ ‹ይኸ ያንተ አሳብ ብቻ መሆኑ ነው እንዴ? ሁዋን እንስተኸው ነው! ያውም የኔ ልብስ ከክጅለው ከርሟል፤ በወንድ ቢመጣ ያምራል ብየ ነው እስካሁን ዝም ያልኩት… ከሆነማ፤ ጨው፣ በርበሬና ቅመሙ ፍልጋ መንገድ ያስወጣልና፤ በጊዜ፣ የበአል መግቢያው ደመና ሳይዘር (የዚያን ሰሞን ገቢያ ሳይወደድ) ከውነህ ከሰጠኸኝ በውስጥ ማስናዳትማ እንግዲያ ያንተ አይሆን፤ የኔ አይደል! ቅንሽ የምትወምረው ነገር ቢዋር፤ ከበሊውን ያንተ መከበድና መዳመት ይገዛዋልና ለጥናቡን ወገጣ ስታሽክፈኝ የእሱኪ እንዲህ ማበረታቻው የኔ ይሆናል። በጆ እንጂ፤ እሺልህ፣ ፈታዶ ነዋ› ብለህ ስታርፍ፤ በሷ እከላት የዘራኸውን ከሽፋጭ ፍቅር የተወለደ ሀቀኛ ፍቅር ባንተ ላይ ትደፋፋብሀለች። ለውጥንህ መንገድ እምቢ-ብሉ ከፍት፣ ለዚያ ብለህ ያነሳኸው ጨዋታ ፍቅር በግራ በቀኝ ሲያዝንብበት የድግሱን ጨዋታ ቅተህ ተሸክመሀት ወደአልጋ ረጥ የሚል ትይበት ይገፋፋሀል።

«መሳኔን ባንድ ሰው (ነፍስገጠከፍ) ጉዳይ ስታየው ለየት ያለ ገጥ ያመጣል። የግልህን ጉዳይ ለሌላ ሀበሽ ያዝልኝ ብለህ መንገር፤ ለሚል የን ሀበሽ አስይዝልኝ ማለት ነው። የሰው ሞኝ፣ ‹ሚስጥር የሁለት ነው› ብሉ ይረገረጋል፤ እንዴኔ፤ ከሁለት ይልቅ በውቅ በሰት ይሸባል፤ ከሰስት ሚስጥረኛ አንዱ ቢያንፍስ ቢታወቅበት የሚያበቅለው ሁለት ጠባት ነው። ከሁለት የምታበቅለው ታዘቢ ግን አንድ ነው። ግና፤ ምስጢር ያንድና የግል፣ ጠለበት ነው፤ ከዚያ ያለፈ ግን ያደባባይ ነው። ሰውን ውደደው፤ እመነውም፤ ግን ምስጢር ያዝልኝ አትበለው ያሉት በቂ ንግግር ነው። ያለመ ሰው ሁሉ እልቶ እኔና አንተ ብቻ ከልቀረን በቀር፤… ያም የምትነግረው ወይም የምነግረው ስለማይቀር… ብቻ አንተ ለኔ ምስጢር ያዝልኝ ብለህ ስትነግረኝ፤ እኔ ደግሞ በሌላ ገጥ ሚስጥር ያዝልኝ የምለው ሰው ይኖረኛል፤ ያም እንዲያ፣ የወዲያኛውም እንደወዲህኛው፤ እንዲህ እያለ በጦቢያ የተዘራው የሰው ፍጥረት እስኪያልቅ ይዘልቃል። ለጉረቤት የተናገርከው ምስጢር፣ ከጃን-እሞራ ጉንደር-ጠዳ ገብቶ ባሙቱ ሰው ልትጠይቅ ስትዘልቅና ሳታየው የጃኸው፤ ብሉም ሰለቡ ያልበግኸው ሰው፤ ተበጆ ደህና ባጆተህል… ታች እምና ግድም… እንዲህ እለ የሚል ጭምጭምታ ሰምተገብህ ይልሀል… ጨዋታ አሰመርኩ ያለው ሰምንተልሆም ይላል። ታዲያ እንዴት ሆነ አደራህን? ቢልህ በጉዱ ወጣሁ ብለህ በድንገት ልብህ ይሰረከረካል። ያለመሰናዳትና የምትለውን ያለማጠናቀር ጉዳይ ስለሚሆን ትደበሰብሳለህ። ሁለት ጊዜ እንዳትበላሽ ትፈራለህ።

ምስጢር ብለህ የነገርከው ሰው ለሌላው ምስጢር ብሎ ሲናገር ሊጎዳህ ብሎ ላይሆን ይችላል። እንደፍቅር መሸመቻ ስለሚጠቀምበትም ነው።

«እያንዳዱ የሚወደደበትንና ዝና የሚሰራበትን ለመፍጠር ትግሉ ጭንቅ ነው። እንደሰው የማይናገረውን አህያኪ ከጭንቅ ብዛት ፈስቶብህ ግር ፍሰ፤ ወርቅ ጣል (ፋንድያውን) ብለህ ፍትር ልታስገባው ትሞክራለህ፤ መሞከርም ብቻ አይደለም፤ ከድምፅህ አለሳለስና ቅኝት ተረድቶ የበጉ ወወት መሆኑን ያውቃል። እህ ብሎ የሚሰማህ ሰውማ እንግዲያ አግዜር ይባርክህ፤ ይህን ወወት የነገርከኝ ብንዋደድና ብንፋቀር ነው ብሎ ተሸክሞልህ ይሮጣል። እንተን በመሰገንህ አንጥር፣ እሱን ወብ እንደሰማው ከሌላው ደስታ ሊቀበል ይሄዳል። ከፋ ከወጣ ምስጢር ነው አልልም። ምስጢር ማለት ልብህን የያዘው ማህደር ነው። ለኔም ምስጢር ብሎ የሚነገረኝ በሽታየ ነው፤ ሸክም አይሆንልኝም። "አይሆንንም ይዘሽ ይሆናልን እንሺ" ብሷል በጥሊያን ጊዜ ባልዋ ከመልስ ላይ ዘግይቶበት ብልግና የጀመረችውን ሴት የታዘበ ሰው። በይሆንም ላይ አይሆንንም ደምረህ እይ፤ በራሰህ ያሰብከውን ነገር ገጥ እስኪሚይዝ ከኪስ አታውጣው። እንዳልኩህ ነው፤ እንተን ሳይታወቅህ ከሳልከው ምቀኛና ጠላት ወድቆ እቀናብታለሁ ያልከው መጥፊያህም ይሆናል። ያሰብከውን ለማንም ሳትነግረው እንቅፋት ቢገጥመው፤ ትጥለውና "ወፍም ዝም፣ እፍም ዝም" ብለህ እንተም ዝም ትላለህ። ዘመንና እድሜ ሲሸረው፤ በዚህ ገጥ የማይሸር ነገር የለምና ለተረቱና ምሳሌ፣ ብሎም ለቢልት ታደርገዋለህ። ለጉብሉ ሁሉ በንድ ዘመን፤ አካሳቴ የሚባል እንደህ ያለ ሰው ነበረ እያልክ፤ እራስህን በሌላ እየመሰልክ እዚያው በዚያ፣ የመኘታ ስእት ማድረሻና የሰት ማዳፊኛ ጊዜ ማታረቢያ ይሆንሀል። አልተኛልህ ያለውን በግብጭ ሆተን፤ ልቡን ከደረቱ በሳት አስለብልበኸውና አባምተኸው፤ ከዚያ በሚፈጠረው መተቶና በንተ ተረት እተቅተኸው በለበት ሲፈነገል፤ ተቸገረህ እንስተህ ከመውደቂያው ትጥለውና እንተም እንደልብህ ከመደቂያህ ትደርሳለህ። ያኔ ሁሉም ተኛ ትላለህ።… አሁን የጥኝ ጥያቄ ታመጣ ይሆናል…»

«እንዴት ብየ? ተቢ»

«ለሰው ሳትነገር እንዴት ቢሆን ነው የማለት አይነት?»

«መልክም፤ እንዲያ ከታየም፤ እንዴት?»

«መልኩም ይበልህ! ይኸ ያኪሄድ ጉዳና ነው፤ በዚህ ረገድ ብቻህን የምታረገው ነገር የለም። ጉዳናና ትልም ስታስብ የሰላውን አወራ ጥርጊያ ብቻ አታስብ። በሰላው ጉዳና ላይ ምንጊዜም የማትሄደበት ይሆናልና፤ ገርጋሪ የሌለበት ጉዳና

የለም። ጉዳናን ሁሉም ተንተበታሽ ፍጥረት ይሸረፈዋል። መቸ እንደምትሄደበት መወሰን ያንተ ፈንታ ነው። ሌላው ይቅር፤ ሌባን … ከብት ነጂን ወሰድ፤ የጉዳናውን በሀሪ፣ መታጠፊያውን፣ ገባሪና መሰበሪያ የእግር መንገድ፣ ዳገታም እከሉን ሁሉ አውጥቶ አውርዶ ዝዞ ይገባል። ይህን ስጠቅምህ ተበጆን ሌባ ነው እትበል።… የጠፋ ንብረት ስፈልግ የተረዳሁት እውቀት ይሆናልና። በዚህ አንጥር፤ ስለማዊው ሰውም በመሪ ጉዳና ሲገባ፤ ሌላ የሚገባ ነገረኛ ሁሉ ያበባል። እንተም የሰውን እእምሮ የምታስበበት ጉዳና ይፃራል በማለት ነው» ብለው፤ በስንቅ መስነቂያው ሰበሰበ የሞልኩላቸውን ለማከካሰም ይህን የፍፍቶቅ መቅረሚ፤ ኪሳቸውን ሊያደመልኝ ተድሞነሞኑ። ከኔ ከመድረሳቸው በፊት ደብታቸውን ያህል ይዘው ነበረና የኔውን አውጥቶ ለመቷጠርም አልቷመጡም። እንዲያው በመተማመን ተደሳድሰው ተቀመጡ። ይልቅን ወሞታቸው ቀጠለ።

«ቡና መቷደሸና የወታቢ ማታለያ ነው፤ የሚያነሰው ስጋ የለም፤ እንዲያው እእምሮ የማነታቂያ ነገር ብቻ እንጂ። በል፤ ከፍራፍሬው፤ ለማጣሜ ደግሞ ከሆምጣጤው የወይራፍሬ እዘዝ! እሆል፤ ከንጀት የሚወድቅና የሚረባ ነገርስ መቸም የለም። ቢራው ግን በይሆን ሽንቅ ያጠራል።… ምንስ፤ ምን ተበልቶ ምኑ እንዳልተጣራ ነው! የኒያ ማደ ወወት ከልሆነ በታ እየገባ በጠበጠኝ፤ ይኸ ልምድ ማለት ከፉ ነው። አርሲ-ኩርሲ ከበዛበት መጥቸ የምናገረው ሁሉ አንዱ ከንዱ አልጋጠምልኝ አለ። በል! መቸም፣ የታየህን እዘዝ። ለመጭ አታስብ! ዛሬ በኔ በኩል ነው። አንተ ያሰብህ «የመጨረሻውን ያበጅልህ» ማለት ብቻ ነው። የእጂየ ሁለመና ተንጠርጥሮ ሞልቷል»

ለኔ ያሉት ለሳቸውም እንዲሆን ይረዳኛልና ለምርጫ እስመሰለው የጠረትን የሀል ዘር ላዝ ሰራተኛው ከፊታችን ቆመ። ከረገርም ፊቱና ቁመቱ እናት ግድም የፈጠጠ አይኑን እንዴ ከኔ ላይ፤ ሌላ ጊዜ ከሳቸው ላይ እንቀዋለለው። ከኔ ወደሳቸው የመመላለሻና መሸጋገሪያ የጠረሰዘውን ወሰል እንደርከን ተጠተመበቅ። ከሳዘኝና ቂባቂስ ፊቱ ተወእዋ ጋር ሁኔታው ተከበደኝና፤ «እያ ተበጀ፤ እንቁላል… መጠጣ፣ ቢራ ወይስ ሌላ ነገር ነው የሚሹት?» አልኩ ፊታዳቸውን ለማወቅ፤

«ምን? ከንቁላል ጋር?… ብስናት ብቻ ልትሆን እምርሀል መሰለኝ! የንቁላል ጥብሱን የሚበላ ጠንከራ ነገር እምጣ በለው። ይህ ሰቀላ፤ እኔንማ መቸም አይሰማኝም።… እሱ ራኤል (ይሁዳዊ) ነው ብለህ?» ብለው የእወንታ መልስ ስጠቻቸው እንደመገርሸት እሉና እኔን ትተው፤

«እህ ሀሀ ሀሀ! እታ ኡዴ?» አሉ፤ በቢረቀ ድምፅ በተምታታ ፊት እየተመለከቱት። ለቋንቋው ገና ባዳ ናቸው። የኖረበት ጊዜ ባያገባቸውም ሊሄድላቸው ያለ ነገር አልነበረም። እስራኤል ውስጥ በመኖር መደናገር ከለተቀበቸው አንዱ ሁኔታ በደረሱበት ለመናገር አለመቻላቸው ነበር። የርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከማንም አገር በድግ ገፍተው የሚመጡ ሰዎችን የሚያጠቃ ክስተት ነው። የታል አጠጣባቸውና ቅንቶ የአረብኛ ተናጋሪወችን በመሆኑ ያናገረት ሰው የ አረብኛ ተናጋሪ መስሎትና በተጣታ ሊረዳቸው ከመፈለግ፤

«ሰላም አሊኩም!» አለ ለዳወረበትና ሀይል ለከሉበት ያ ንግግራቸው። «ምንድን ነው ያለ?» አሉ። ጆሯቸው በር ልኒድ ያለ፤ አይናቸውም የጆሯቸውን መነጠል የሚያውጅ ይመስል ቢ-ብሉ ተከፈተ። «እንዴት ያለ ወሬ አመጣ እባክህ?»

«ምን መጣ ተቤ፤ ጤና ይስጥልኝ ነው ያለሆት»

«ሰላም አሊኩም፤ የሱዳን ነገር ነው፤ ምን አባቱ ብሎ ነው እዚህ መሀል ያስገባው "ሻሎም" አማይል?… ይህ ነገር ተባስተህ እንዳይሆን፤ አረብ ባይሆን እንደህ አይልም ነበር "ሻሎም" ተቀምጦ፤ "ሰላም አሊኩም" ለምን መጣ!»

«በ የከባቢው ያነጋገር ልዩነት አለ፤ ይህ በየርዳዋስ ግድም የሚኖረው፤ እሊያም በሲናይ ተራራ ገፅም የመጣ ይሁዳዊ ሊሆን ይችላል። ይሆን ያሀል ግን ምን አስደወረያት? ይሁዳዊ ቢሆን ባይሆን ምን ቸገረያ፣ ሁሉም እስሳሬያ አይደለም?»

«ያንተ ነገር፤ ልቤማ… ልብ አልሉ ብሉ ኑሮ ነው። እባሳፊን ስታስመቸው ስራት ያስምራል። ደስ ብሉት ምን ልታዘዝ ያለ ጊዜ እጅህ ይሞላል፤ ያችን የገዳሪፍ አበሽ ከማሬት አላየሁትም ? የተንቹ፤ እሷ ፋስካ ሁና የኔንም ቀን የደስታ አደረገችው፤ እንዲያ ያለ አጋጣሚ ከመመኘት ነው፤ መንገድ የምወጣበት ቀን ስለሆነ የዚያ ቀን ቅዝታ መጥቶ ተሹሞብኝ ነው። ገባህ? አሁንእክ በዚህ ወዋታየ ቅስት ይ…» አሉ የተጠራጠረ ፊታቸውን እንዳሰ ዩኝ።

መጀመሪያ ልንገራቸው የፈራሁትን ያሀል አሁን ገፋፍኝና የታል አነባበባቸውን ተንተርሶ የፈጠረው ወዋታ እንደሆነ ጠቆምኩ። «ይህ ደዴ! ምን መስየው ኑሮ ነው?… ንገረማ የሚሰማው እያገሰውም፤ ሰሰደበኝ ነው። እስራኤልነቴን ጠቅሸ እየተወራዉሁ ተናግሬ፤ ባረብኛ መወንቴ የምን ነው?» እንዳሉ፤ በየገጣችን የያዝነውን የንቁላል ዝርያ ምግብ ከዳቦው ጋር ተሸምተንና አጣብተን ከነከስን በኋላ ያረቂ መለኪያቸውን እየገጯው ወደእምብርት ጉዳያችን ገባን።

«የሆነ ሆነና፤ የዚህ ጊዜያ መኪርኪሚያና የጠርዝ መቿሜ ምንድን ነው? መቸም ጆንና ነፃት፤ በሰፃ አይሆን፤ አይፈጠር ታሪክ፣ አያበጁት ዝናም የለም፤ የተመሰከረና የታየለወት ነገር ነው።» አልኩ። ንግግሬ ከእምሬቸው የነጠቀውንና ያስገዛቸውን ሀይል ለመገመት ቢያቅተኝም መለኪያውን ተከሉት። አይናቸው ያረቂው ቀለበታዊ ከፈፍ ከመለኪያው ላይ የሰራውን መስመር መስተካከል የመቻኘት፣ ያንም ለማረጋገጥ መደላደሉን በስልቶና ባደብ እያወረከረ አማተረበት። ገራእጃቸውን ከገጫቸው ስር ተስጉ የገር ከቶዳ አሜናሮ ይጉትት ጀመር፤ ደበታቸውን ያሀል ከተደራጁ በኋላ ፊታቸው ፈካ፣ መልሰ ብርድ አለ፤

«ከንዴ!… ሰማህ ከንዴ?… ሰው ያበላ፣ እግዜር ይፈታማል… ሀይልና ጉልበት የእስራኤል አምሳክ ነው። መቸስ እንግዲህ ተናገር ብለኸኝ አይደል?… ጊዜየ ብዙ አይነት ነው። ባይነታ ስታየው የጊዜ መቅረት ነው፤… ጊዝም አይሆነው የለምና አንተው መንዘረው። የጊዜየ ጣጣ፤ ጣጣ እንዳለቸው፤ ኃብላ ተንጠልጥል፤ አንዱ ቢሰበር ካንዱ ባለው መስ ላይ የተመሰረተ ነው፤ አንዱ ሀሳቤ ባይሳክ ከብዙ አንድ በምንም አይነት አላጣም። እናም ጊዜየ ብዙ አይነት አድማስ የመታ ነው። አንተና እኔ… መቸስ በብዙ ነገር ተሳስረን የለ?… እምንህለሁ»

«እንዴታ፤ መተማመንን ይጠራጠሩ እንዴ?… በተደም ንግግርያ፤ ምስጢር ልብ የያዘው ነው ብለዋልና የሚነግሩኝን ልብ ይበሉት…»

«ወረቀትና ሞኝ ያሰያዙትን አይለቅም… ለዝና ያልሉትን ወዋታ ለመተፋፈሪያ ታጠኘው፤ የመጠራጠር አይደለም፤ መጥቀስ ግን የደንብ ነው። ፍቅርን ጠለጠ ለማደስና የዝና ማከያ ቅመም ነው። ብጠረጥርህ፣ ሌላ አይነት መንገድ ይኖራል እንጂ እንደህ አይሆንም። በወዋታ መሀል ነገር ይጋባል፤ እእምሮ አይሰበው የሀሳብ ወደጂ የለም፤ ሜት እስከተረጠጣኑ ይዞ የተቀመጠ ፉቅራ ማለት ነው። ነው አይደለም?» ቢሉ፤ የንግራቸው ይዘት ባይረዳኝ፤ ወደሉሳው ወዋታ እንዲደርሱ፤ ዝም ብየ የመስማማት አንገቴን ነታንቅሁላቸው።

«የጊዜየ ነገር፣ እንደም የትድረት አለመገባበት፤ ቀጥሉ ቅዝታ፣ ስስትና ናፍቆት ነው። አንተ አሁን ወጣት ነህ፤ ከፊትህ ያለውን የማቸንፍና ወደፊት መገፋት ነው የሚታይህ። ያንን ስታደርግ፣ ልምድ ይመጣል። ወደኔ እድሜ ስትደረስ አሁን ያለህበት፣ አሁን የምትሰራው ትድረትህና ባህልህ ይሆንና በሚመጣው የወደያኛ ህይወ የምታነቃውና የምትጥለው፣ በወዋታ የምታስበው፤ ብቻ ምን ያለፈህ በጭር፤ በመልክም ሴት እጅ

በተያዘ መቀንጠቢያና ዶጋን የምትነድፈው የታሪክ ጥቃ ይሆናል። እኔ ታዲያ፤ ከመሸ ወደዚህ መጥቶ የማየው ነገር ሁሉ በወዲያኛ ዘመን ያደረኩትና የለመድኩት እየሆነ ታመሰኝ። ወደዚህ ስመጣ ራሴን የተሸከምኩት መስሎኝ ነበር፤ ዘግይቶ ባጤነው ግን ሁለንተናየን አልያዝኩትም ኑሯል። የዚህ ሀገር ትድረት አልጣመኝም። ግብሸት ለብሶ ታየኝ። ምን ያለፋሀል፤ እጅ-እጅ ያለውን፣ ተነካክቶ ያደረውን እህል.. በጦቢያ መብላት አምሮት ያነሳል። ምን በሽታ ቢይዘው ነው፤ እጅ-እጅ የሚል ምኞት ያስገባው! ብትል ስህተት የለብህም፤ ያለማየት ነው። ባወድማው ገድም፣ በማህበረ፣ በሰርጉ.. የተሰበሰበው ሰው እጅ ወዳድቶበት፣ ከበረከቱ የተነሳ ተርፎና ትዝታዬ አንሰቶ አፍር ጧት እንደገና ጣት ስትጥልበት ይጥማል። የቃሊቲዳን ሁኖና ለንዲያም ትድረት ተገርቶ የመስለጠንም ይሆናል። እንደማተዘቀዝ አለመኖር እህል ሽቶ የሚወድቅ ቢሆን ኖሮ፤ ደፍን ጦቢያ ድግስ አይጥልም ነበረ። እየሩሳሌም ላይ መልከም የተባለ ነገር ለኔ ጆል ባልትና ያምበሳበሰውና በዚያ ላይም ተረስቶ የሸተተና የጠነባ ነገር ሆኖ የታየኝ።

«በጦቢያ፤ የጉልማሳ ሀይወት አክብሮትና ግእረግ አለበት። እንደኪሰረ ነጋዴ ደንበኛው ሁሉ ፊት አይዘርጋበትም። እድሜ ክብር ነው። እዚህ ግን የግልምቢጥ ነው። አበው! አሁን፤ እንዳንተ ያለ ወጣት፣ በሌላ በኩል እንደኔ ፊቱ የሸመገለ፤.. ልቡግ እንግዲያ ትኩስ፣ ወጣት መሆኑን የሚወቀው ባለቤቱ ነኝ፤ ልጠይቅህ! የትኛው ይከብራል?.. በጦቢያ እይን እትየው፤ እዚህ የሚደረገው ነገር የሸንገባና የሾሚ-ስሚ ግስመስያና የማደረያ ነው። እስከዋናው ሹም ድረስ ቀርቤ አይቸዋለሁ። በጦቢያ ቢሆን፤ ሽማግሌ የብዙ ጉዳይ እወራ ነው። የትድረት እውታር ነው፤ ታሪክ መዝገቡ.. በወረቀት ሳይሆን በልብ፤.. እጅግ በጣም ትልቅ ስራ! በዚያ በፊት የሆነውን፤ የተሰራ ገድሉ የተሰራ በደልና የዝና ነገር፣ ከልጅ ወደልጅ የሚያሸጋግር እዛውንት ነው። በግብብ፤ ተፈትኖ-ተፈትኖ የጠራ ነገር የሚገኘው እድሜ ከጠጣ ሰው ነው። በጆ ግብብ በኩል ስታየው ገና-ለገና ያልተጠረበውን የድንጋር እንጨት ከጆ ላይ በመመዘን፣ አወራረዱና ቀጥታ አካሄዱን፣ መጠረቢያ ሳይወድቅበት የሚናገር በድሜ የገፋና ከቀደም እየተበላሸበት በመጨረሻ ከልኬታው የደረሰ ሰው ነው። ወጣት የሆነ፤ ከአስር ጉማጅ አንድ አልወጣለት ቢል፤ ሽማግሌው ከአስር የጨበ ወይም የገራር ጉማጅ ሀያ ስንጥቆ፤ ሀያ ድግር ያወጣል፤ ያ ግለት መልመድ ነው። በሀከምና መያ፤ ጭንቀትና ግበት የሚጠይቀው የህገረሰብ መድሀኒት ሁሉ የሚገኘው

ባዘውንቱና በባልቴቷ ገድም ነው። ወጣቱስ ለምን ይሆን አያውቅም? ብትል መሰረታዊ ጨዋታ አለው። ስር ቅፍርና ቀጥቅጦ ብቻ ሀኪም አይሆኑም። መድሀኒትን፤ እየለከሁ እየሞከርኩ፣.. ቀስ በቀስ፣ በጊዜ ብዛት ይሆናል። ወጣቱን ሁሉ ለሀከምና መያ አትመርጠውም። ይበጃል ያልከውን በሀሪ መጀመሪያ ቤቱን ከሞላው ኩታራ ጊዜ ከልተሀና ባትሰትን ታጠናለህ፤ ከጠናህ በኋላ ስር በቀጠቀጥክ ቁጥር፣ በለከህና ለታመመው በቶነንክ ጊዜ እንዲያይ ብቻ ካጠገብህ እያስመለከትክ ታቆመዋለህ። ከዚያ፣ እየሞከርከው፤ ቀስ እያለ፣ እድሜ እያነሳ፤ መሳቱኑ እየበረደ፤ ከቁፈራው ለቅጥቀጣው፣ ከዚያ ለመቶነኑ፤ ከዚያ ለማደልም ታደርሰዋለህ። ለሁሉም ልናገር፤ ሁሉም ሀኪም ይሁን ከልክ ጨዋታ ይበላሻል፤ መድሀኒትነቱ ይራከሳል፤ ቀጥሎም ሀኪሙ ሲበዛ ሚቾም ይበዛል፣ መድሀኒት ያልከው ወደምግብነት ይለወጣል። መርከስ ይሉሀል እንዲያ ነው።

«ታዲያ እንደገና እንዳልወለድ የማይሆን ሆነ፤ እየሩሳሌም ከቢና ወረቀት ለሚያተክር ወጣት መከበርን አለበሰው። የኔ ደስታና የኑሮ ጊዜ የቀረው.. ከድግስ ባሻገር!

«ሁለተኛ ረገድ፤ የመንገዱ ነገር ከጦቢያ እገር ስንቅል ካልከሰከሰኩት ሁሉ አንዷ ልጃ ናት። ለዳር አገር ሰው ድረያት፤ ወደእየሩሳሌም እንዳትመጣ አወሳዳፋት። እንሂድ ብየ እጇን ብሰብ አልሆነም፤ የጧ ጉተታ አቸነፈኝ። ነገር ያልገባው፣ የዚህ አገር ወሬ ያላናቃውና ልቡን ያልነካው ሁኖ። ታዲያ፣ ምግሽ ዘሬ እየሩሳሌም፣ ምግሹ ዘሬማ! ከጦቢያም በጣም ደካው የራቀና ወዲያ የሆነ!» ሲሉ ጣልቃ መግባት ታየኝ።

«እርቡ፤ ተራቡ፤ እለምንም መሲቅ ያለውን የእረት ቃል አደረሱ እንጂ ምን ተጉዱ ተቤ! ባልሆነ ነገር ለምን ያማርራሉ?»

«ያንተ ነገር፤ አሁንእኮ ጨዋታ ወጣልኝ ብለህል። ረታሀህ! እነሆ?» ብለው፤ አይናቸውን ሲያፈጡብኝ፤ «ምነው ተቤ? የጤና.. ወይስ እጠፋሁ?»

«ጤና ያጣህስ አንተው ነህ፤ ጥፋትህ በግራ በቀኝ ግጥም ያለ ነዋ! ምንዘረ ስል.. ልዘረዝር የተነሳሁት ጨዋታ፤.. መሰበሚን ሁሉ ወዴት ጥሉት ነው ይሆን ግልጥ ነገር ከዚህ የጠደው?.. መርበትንግ ገና በጣም የምረብ ነኝ፤ አውቀዋለሁ። በህይወቴ ይሆናል ከተባለው ንግርቴ ገና ከግማሹ አልደረስኩም። እንዲቷና ነጋሪዎች (ደብተራ ወይም ጠንቋይ) ደጋግመው ወደባድ አገር ተሸግረህ ትመለሳለህ ያሏት ናት። ይህችም ይኸው መፈፀሟ ነው። ሌላ ሌላውን ግን ከወደግምባር የምጠብቀው ነው። እኔ እባትህ ገና ጡት ያልጣለቸውን ቤት ሁሉ የማደራርብ ነኝ፤ "ያበይን ልጅ

ውሀ ጠማው አለ ከጦት የደረሰ ሰው፤ እዚህ የሀበሻ ሴት ተወደደ ቢሉት እውነት መሰለው? ወደባህሩ ልሄድበት መሰሉኝ?… መተዳደሪያዋን እያዘጋሀ ከሰጠሀትና ህግ ኪልክት ሴት ውብ ናት፤ ሰራዋ ግርበት ነውና ታረበሀለች። ያንተ ተግባር መቶፈርና መዝራት ብቻ ነው… ረሀብ እንዲያጠቃት። ግና፤ ልጁን፤ ብቻዋን ብትዋትት፤ ስሞት ትረግመኛለች። ሁለቱ ጠፋሁ ማለት ነው፤ ከልጆም ሆነ ከነፍሲ ባልሆን መትረት። እሷን በቅርብ ሁኘ መስጋት የግዴ ነው።»

«መስጋት ቢሉ ምን ማለትሽ ነው?»

«ግልፕ ነገር ትጠይቃለህ፤ አይገባህም?… አንድም በግድጊ ሆኖ ቢከፋትም ሆነ የደስታዋ ጊዜ ክብርና ማእረግ መሆን አለብኝ። ከሀይፋ ቢርሸባ በስልክ «ሀሎ» የሚባል ነገር መሰለው? ጊዜው ውብ ከሆነና ብሉም መምጣት ደስታዋ ከሆነ… ከጠዳት፤ በዝግታ ትመጣ ይሆናል፤ እዚህ ለልጆቿ በጣም ውብ አገር ነው… እሷ ግን እኔን መሰል ስትታምና በስ ክባክ ናት። መቸም… ግና ይሆን ተወው፤ ከዚህ ካለው ዘመዷ ብትደረብም ትደረባለች፤ መቸም የሷ ፈታድና መብት ነው። መድፈን ያለብኝ የኔን በኩል፤ ያበት ተብየውን ድክመት ነው።

«ሌላው ጉዳዩ ግን… በጣም ዋና፤ ከጠዋት… መንገድ ስገባ ጀምሮ የረኸረኸኝ ነገር የመያየ አገዳም መውደት ነው። እስራኤል፤ ከየንትና ከግለዴ ግበበኛ ህዝብ ነው። አሁን የምታየው የሰለጠነ አለም ሁሉ ቢያብዘዩ ቢያምርበት በእስራኤል ልጅ መያ ላይ ነው። ደኸ ማለት፤ እግዜር በሰለሞን የጀመረው ምርቃን ሆኖ፤… እጇቢውና አሽከሬ የእስራኤል ልጅ ነው የነበረና ዙሪያውን ሲያገበግብ የግዜር ምራቅ ዤርብራቢ (የእንቶናታ)… ለሰለሞን ያለው ዳርበ ረጭቶት ሁሉም ጠይብ ሆነ። የምታያት ይህች ትንኩሽት አገር (እስራኤል) በግበብ የሳቀችበት መሰረቱ ግልፕ ነው፤ ተመልክት! በጦር ትምህርት፣ በህክም መያ፣ በረብሳ ሰራውና በግክንፉ፣ የተዳበተ የሌላ አገርና መንግስት ምስጢር በመቅዳትና ብሉም በመጠዳት… መቸም በፈጠራውና በመራቀቁ ሰጊ በጣም ተነስቷል። ታዲያ ግን ልቢ መፍራት፤ አንድ ቀን መእት እንዳይወርድበትና ይህ ፍጥረት ሁሉ እንዳያልቅ መደንገጥ፤ ድንጋጤዩም መንታ ያመጣ ነው። አንደኛ ነገር፤ ሰም በጣም ሲነሳ ምቀኛ ይበዛል፤ ምቀኛም ሲበዛ እንቅፋት ይበዛል። ሁለተኛው እንጠር "እኛን-እኛን ያለ፤ ዳብቀኝ-ዳብቀኝ ይላል" ነውና ከወንዱ እልፎ በሴቱ በኩል ከፍከፍ ብሉ መታየቱን አበዙት፤ ታዲያ ልጆቹን እምጥቸ ዘርግፈ፣ ከሳቱ መሀል ጥየ… ሆዱን ባርብር ማለት ፈታው። በመጥናናት ረገድ ግን ያምሳክ

ፈታድ ነው በማለት ተመልሼ እራሴን-በራሴ እበራታዋለሁ። ታዲያ፣ አሁን፣ የእራኤል ልጅ ነገር… መቸም፤ ባለም የተዘረጋ አይደለ? አሁን አሜሪካ ሂድ፤ ባወርባ ባለው በዚያ… በህንድ በታች ነኝ ነው ብላለች ያቺ አሽከር፤ ሰጊን ጥራልኝ… የሀይፋዋ ዋና የሳጆን ክፍል። አንተ… አንቱ… ትክክ-መልክም… ማን ናት? አይወኔ ረባ ጊት»

«ባንድራ ማለትያ ነው?»

«እጠር ያለች፣ ልዝብና ፈገግተኛ ልጅ!»

«እያ ባንድራን ነው የሚሉት»

«ስትዳግመው ቅዝ አለኝ፤ ግና ከመጥራት ዘገየሁኝ፤ የሷ ልጅ አገር ማን ያሰኛል?»

«እ ወሰትራሊያ ይሆን?»

«ልክ ብለሀል። እንዲያ ነው እሷም የምትለው። ውብ አሽከር ናት፤ በሷ አገር ሁሉ ስትሄድ ያገሬ ምስሰ የእራኤል ልጅ ነው ይሉኛል፤ ጆርመን ቢፈጆውም፤ የቀረው ረብዩና ተበትኖ ሳለም ሰልጣኔ ዋና እምብርት ሆኗል። ሌላውን ተወው፤ የራሽያ እስራኤል ነገር የሚያራኩተው ስንቱን ነው? ተባ (እግቻቸውን) በጣም ነው ስለዚህ የሚያሜውተኝ። ጆሮው ከተሰብዢና ከራዲዮ አይሰያይም። … ትንሽም ያሰጋኝ በሌሊቱ ገደም የሚያመጡትን የብልግና (በቴሌቢዥን የፍትህወት ስፓ ተውኔት) ጨዋታ ሰራየ ብሉ መያዙ አልጠመኝም። የብልግናን ቴሌብዢ በተለየ ተው ብል አልበግም። የፍልሰምናን ጨዋታ ግን በሙሉ ይዟታል። በዚያ ልክ የህ አገር ትድረት መልጭ ብሉ እየገባው ነው። የራሽያ እስራኤል ነገር በጣም ችግር ሁኗል፤ ግን በመሀል ተደየኑ፤ ፈላጊያቸው በዛ።»

«እንዴት?… ምን ሰመ?»

«እግዜር በበጉ እንዴት ይበልሀ? ባንድ ገጥ አሜሪካ ራቨውን ግበበኛ እስራኤል ሁሉ ለማግኘትና ከወዲያ የሚሰራውን ሁሉ ለመቅረፅና ለመከተብ… መቸስ እልፍ-ያለ የመናናትና በጉ ያለመስራት ዝብረት ግገምሽ ተደዘ ያለው በመሰብብና ባሜሪካ አይደል ? ከዚህም የኛወቹ እነቢጊንና እነእግበባው ሻሮን የሚፈልጉት እንዲመጣ ነው። እትልፋ፤ እስራኤልን የማይፈልግ ፍጥረት የለም፤ ባፍሪካ ሂድ፤ እዚህ በየቀኑ የሚደረገውን ስሳግቢ ስልፍ ታያለህ፤ ይህ በጥቁር ላይ ያመጣው ብርቱ የነጭ መንግስት ምጣትና የማይቻል የሆነው የእስራኤል ልጅ እጅ ስላለበት ነው። የእስራኤል ልጅ፤ የህምቢና የነህሴ ጨውና በርበሬ ሸቀጥ እንደማለት ነው፤ መገኛው፣ በምጣትና ዙሪያ ተንከራቶ ነው። ሲገኝ ጥያው ከመሬት ጠብ አይልም።»

«እያ ተብጁ፤ እዚህ ላይ፤ ትንተናዉት እንዴት ያለ ቢሆን ነዉ? ብጥብጡ የበዛዉ ይሁዲዉያንን ለማግኘት የመሻግት ባይሆን በራሳቸዉ ፈቃድ ሊኖሬ ወደፈለጉበት ለመሄድ፤ እንዳገኙም ኑሮ እልተመቾንም በማለት ከያሉበት መዉጣት እየፈለጉ ስለሚሆን፤ ከዚህ ሁኔታ የሚመነጨዉ፤ መንግስታቸዉ አትወጡም በማለቱ ይሆናል። እያዩትም?… የረሲያን ይሁዲዎችን ሁኔታ ከኢትዮጵያ ይሁዲዎች ሁኔታ ጋር ምን ይለየዋል?»

«ክንዴ ጨዋታህ የላይላይ ገዛይ ነዉ፤ ዘለህ በትመለስ መቿሚያ የለዉም፤ የጦቢያ እስራኤል አመጣጥ ረገድ ሌላ፤ የራሽያ እስራኤል አወጣጥ ነገር ሌላ! ሰዉ ባይመቸዉ ነዉ ትላለህ ? ይሆን እንገዲያ እንበለ-ምክንያት የሚሆን ነገር ኑሯል እንዴ? እንደራሽያ እስራኤል የጦቢያን እስራኤል ተመችቶት ቢሆን ኑሮስ እዚህ ባልመጣ ነበር፤ ከትክክል የጤፍ እንጀራ፣ በለት ከታረደ ሥጋ ስጋ… ያም ሲሆን የፈለከዉን አይነት ፍጥረት መርጠህ! ጠጠርማ፣ ዳጉስማ፣ ቀይ፣ ነጭ፣ ዳልቻ፤ ተብት፣ እንስት፤ ጠብት፣ ኸህር፣ ብለህ… ቅቤዉ፣ እናቴ ሆዴ ጠላዉ! ኧረ ስንት የኑሮ አይነት፤ እንደሌላዉ ቢመቸዉና የጠራሁትን ሁሉ ቢያገኝ ወዴትና ወዴት በደረሰ ነበር። ከጦቢያ መሬት ላይ እግር የሚያነሳና ወደሌላ አፈር የሚጫም አንድ ሰዉም ባላገኘህ ነበር።

«መሬትና ጥበብ በሁለቱም ገጽ አለ። ልዩነት የምታየዉ ገሀድ ባህሪ ነዉ። የራሽያዉ እስራኤል ከዘመን አመጣሽ ጥበብ በጣም የረቀቀና ዘልቆ የሄደ፤ የጦቢያዉ ደግሞ ባባት አደሬ የጅ ስራ… ግረሽያ፣ ወገል፣ አገረሰብ ማጥድ… እልቢን የነጭ ስራ ነዉ፤ ባለዝናሬ ከራ፣ ወስፌዉ፤… ምን ይቀራል! በጭር የጦቢያዉ ነፍስ መንቀሳቀሽ ነገር ሁሉ የተፈጠረዉ በጦቢያ እስራኤል ነዉ። ግና፤ እጆቻና ጥበበኛ ያልተከበረበት አገር፣ ባለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት ጦቢያ ብቻ ነዉና፤ አንዱ ለስደት የዳረገን ምክንያትነዉ። ልዩነት እንደሁ ሁኖ፤ ወደየረባሌም ያመጣጥ ረገድ ሲነሳ እንደራሽያ እስራኤል ባለጠጋ የለም፤ እይኔ የሚያየዉ ነዉ። የባለጠጋነቱ ምልክታቸዉ፤ ሀብት ተትረፍርፎ መጨነቃቸዉ፤ ከሚያንጠለጥሉት ሰረጢት መዉጣቱ፣ ከከብቸዉ የመንጠርፈፉና እልበታ ማለቱ፤ የግዚረን የጥርስ መንጋጋ እስከስንቀጠጡዉ አርግፈዉ ሲወጡ በወርቅ ጥርስ እየነደዱ ነዉ። … የጋኔል ባት ይመስላል። እየፈገገ ሲመጣ አታየዉም?… እኔን የሚገርመኝ ያርጋፊዉ ጉጡተኛ እዉክክን ነዉ። ሰዉ ወንጀል የሚግረዉ ባልባሌዉ ነገር ነዉ፣ ጊጥም የወንጀል ምንጭ ይሆናል! … ወይስ ሌላ የጠለቀና የማያስምም ጥበብ ይኖር ይሆን? በከኒን አላልቶ እየመዘዘዉ እንዳይሆን?… አይሆንም፤ ምነዉ! አጥንት

ሲያባላ ሌላዉ ነገር እያመልጥም… ነዉ ብለህ?» አሉ።

ቢገረዳደፍባቸዉም ሀተታ አወታተራቸዉና ትዝብታቸዉ በጣም ገረመኝ፤ ዉስጠ ሀሊናየ ተረትቶ ባቅ ተናነቀኝ፤ በዚህ ትንተናቸዉ ተዳክሜ ቢሰለቹኝም፤ የገድ መልስ መስጠት ነበረብኝና ባቅ መጨመሬ ደብሱን ስለሚያንገራቸዉ ተቸገረ ባቴን አንቅሁት። ሀተታቸዉ ብዙ የሚታይ እዉነት ቢኖርበትም፤ በዶግዶም ላይ የምንለያይ በመሆኑ የመታጠፊያ (መዉጫ) መልስ አጤንኩ፤ ግና በጣም አጠጠኝ።

«የረሲያዉያን ጥርስ የሚረግፈዉ በራሱ ነዉ፤ እንደኛ አገር ጥርስ አይመስልወ፤ እየረባሌም የሚደርሱትም ረሲያዉያን እንደኛ መንገድ የተመቱ አይደሉም። እዚህ ከገቡ በኋላ የሚደረግላቸዉ እርዳታ ግን እንደኛ እኩል ይመስለኛል፤ በጠቢርዉ ደጃፍ የምናያቸዉ ምረታቸዉ አንድ አይነት ነዉ።…»

«ስጥቶማህ ማብራሪያ ስጥ፤ እጉል ወደሌላ ጨዋታ አትታጠፍ። የራሽያ ጥርስ እንደኛ አለመሆኑ እንዴት ነዉ? ልዩነት ተናገር… በሰዉና ጥርስ ማጥዳትና ማሰመር በነሱ አይበዛም ?»

«በምግባቸዉ ስኳር ያበዛሉ፤ የጥርስ ዋና መገገሪያዉ ጥዳት ብቻ አይደለም፤ ከዉስጥም ደም የሚያጥብ የምግብ አይነት ያስፈልጋል። የጥርስ ጠንክ ምግብና መጠጥ አለ። እኛ ተገመጥምጠን ብቻ ነዉ ጥርሳችን ከጭታችን ጋር እኩል የሚሆነዉ፤ ይህን ሀሰት የሚሉ ነዎት?»

«እንዳንድ የዉነት ጊጊል የተዘበረቀበት ጨዋታህን ተወዉና የራሽያዎች ጥርስ ከፍጥረቱ ጠንካራ ተብሉ በወርቅ መንደዱ ያጋጠሚ ከሆነ፤ ከዚህ በደረሱ በወሬ ባጥንት መለወጡ የምን ነዉ? የወረት ፍላጋ አይደለም ነዎ?… በል የዚህን መላ ፍንጭ አስይዘኝ። »

«ዙሪያ የሚከባቸዉ ሰዉ አጥንት የለበሰ መሆኑን ከማየትና ልዩ መስሉ ላለመታየት እንደሁ ተቢ!»

«እጡብ - ድንቅ፤ ጨዋታህ ሆድ ይበረብራል፤… አፈር ልቅመስለት! ግና ንጡህ ቀልድ አበዛህ!»

«ጠባትያ አፈር ይቅመስ! ምነዉ ይህን ያህል!» አልኩ፤ ከዘለፋቸዉ የማስተንስ መላ፤ ግና ጠራዉን ባይናቸዉ ገጭተዉ ተመለሱ፤ መለኪያዉን እንስተዉ መልሰዉ ጉለቱት፤

«እይ ወዲያልኝ፤ የተማሬ ልብስ ጀል ነዉ፤ ገም ብሉ ግልብ ጨዋታ፤ እኔን የመጨለልም ይሆናል፤… በል መችም፤ ባይታወቅህም ይሆናልና ሀሳብ አይግባህ፣ ጠልቂ ያላየሁትን ጉዳይ ጨዋታ ብየ

አለመጠወም፣ ተግ! በንጡ የመታደል ነገር ሲነሳማ በቃኝ የሚሉ አሉዋል እንዴ? እዲ የማያገባውንና ቀይቶ ባሬጣና በወስድ የማይለፈለውን እያየና እየሞገተ መወሰድ፤ ዘመንና እዋጅ የሚሸረውን ደግሞ እየገመተና በምስት ጣቱ እየፈረመ መወሰድ ያቋቀመዋል እንጂ አይጉዳውም። ሀበሻ ያልተረዳው ሙሉ ይኸን ነው፤ ነገሬስ ቢለምንም አይበጡትም።» ብሎ ሌላ ቅንትና ሳይገቡና ጊዜ ሳይቆርጠን፤ «እና የዝዩ ነገር እንዴት ነው? ይድፋልኝ።»

«ይድፋልኝ ደላል? ጥንቅ የተደፋ ነገር! እየተነተንኩ ወደመድረፉ ደርሸ መስሉኝ፤ ቀላል-ቀላሉን እንደሁ ነግሬሀለሁ። የቀረኝና ብሎም የዝዩ አንድ ጥና አላማ የመጥሁፉ ጉዳይ ነው፤ ዳዊቴ!»

እንደበታቸው ገነገ፤ የቀኝ በኩል የኩታ ሸርባቸውን ነክ-ነክ፤ ትከሻቸው ደግሞ ራሱን ችሉ መታ-መለስ፤ እንዲያው ፈንዲ-ጌላ አሰኛቸውና መስኪያውን እንስተው ጨበጡት፤ «ክንዴ! ይኸን መሉተዋት ያልበዋል መስል! ባልጠጣው ደረቀ። ወሬ ይዘን ውቃቢያችን በጉን አካል እየገዛና እየወረደ ይጠጣው! ይሀን ስቀላ አሰላፈ ከረቂው ጨምር በለው! መጠጥ ከዝናና ከጨዋታ ጋር ነው።.. ራቴ ሆዴ!.. እንዲያ በዚያ ግደ ሲሆን... አይነት ነበረው!»

«ሊሄዱበት፤ ምን አስችክለዎ?»

«የመጠጥ አሜሪፈረው ሰው ነው። ሰሰው ሰውዬዩ ከዚህ ቀረ አይደል!.. ሌላውን ተወው፤.. ጊደኛን በሄድክበት ሁሉ እንዳበጀኸው ነው። ግና፤ የዝና ነገር ከሰው ሰው ይለያል። ሁሉም ይቅር!.. አሁን እንዳንተ ያለ ፋሲከ ሰው ከየት ይገኛል!»

«እ ን ዲ ቹ! አሁን ገና በቀሚ ገደሉኝ፤ ተቤ፤ እንጀቴ ወስጥ ተጣጥፈው ገቡብት!»

«ይሀ ጆል! ወሽቴን መሰለው? እኔ የኔ ነው ያልኩትን ሰው ስለጥረንቱ በፊት መናገር አልወድም፤ እንዲያ ባደርግ የሚበላሽብኝና የሚነፍበኝ ትይመስለኛል። በመለያያ ቀን ግን "ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነው"ና፤ በጉበጉውን እየተመኘሁ፣ ለምናልባቱም ያልብሁን ነገርኸው ትሄዳለሀ። እኔማ እንገዲያ ከነጭናሜና ጠባይ ከነሳው ወሽ ጋር ቢሆን እድራለሁ ሁሉም ይወደኛል። እድገቴ ከክርስቲያኑና ከስላሙ ጋር ነው። በኑሮ ውድድርም ቢሆን የምተያየው "ጉዳን" ነው። የኛ ሰውማ እንገዲያ ምን ያውቃል?... ብረት መቀጥቀጥ፤ ልቅ (ፈትል) መወርወር፤ ሸንኩራ መሰሰን፤ ሙጉን መወልወልና እሳምሮ ለሌላው መስጠት ብቻ! ከዚህ የሚያልፈው በጣም እጭር ነው»

«ተቤ፤ እስቶም እንዳሌለው! ቀደም ጥበብ ብለውት ነበር፤

አሁን ግን ማጠጡያ የምን ነው?»

«የለም፤ የለም፤... የማጠጣል አይደለም። ሌላ መያ ከልተጨመረበት... ይኸ ግለት በስተዳደር፤ በመጣፍ ኪነት የሚገባ ሰው ከሌላ ጥጋ የለውም። ለሰው መስራትና ማገልገል ብቻ እያስመሰገነም። በታሪክ የሚጣፈው ስራ ሳይሆን ያስራ ነው። ንጉስ ስለጥን መቅደስ ቢያስጠርብ እንድ ደንጊያ አላነሳም። እጨ ፋሲልም "ጉ"ን በመፈለግ ደፍን በጉምድርን እስዙሬ ግምብ ሲያስንጡ እሳቸው እንድ ደንጊያ እንስተዋል የሚል ታሪክ አይገኝም። በመጨረሻ ጥና መናገሻ ጉንደር ሲጠና፤ እንዲያ የገነባውን የነጭ መንጋ ከፈሉት ዋቅ ነው ይባላል። ስማቸው ስም ግን እንደስለጥን የሚጥቅ አይመስልም። ልብ ብለሀ እጨነው፤ ሀንጣውም የሚፈርስ አይመስልም፤ ጠንኝ ከሰላበት ዘመን የደረሰና በጣም የታደለ ሀንጣ! እናም የጥበብ ማስከበሪያውና መከበቻው እደበባይን ጨምረሀ ስትይዝ ነው።

«ቅድም እንዳልኩሀ፤ እውዱ-ነገስቴ ብዙ ማእረግ፣ ብዙ ዝና ያተረፈልኝ ጊዜ ነው። የቀን መጥፋት፤ "ገርገር ለሌብ ያመቻል" እንደባል፤ የለውጥ ነገር ሲነሳ ፈታሽ በዛብኝ። ከጡቡ-መንጂ የማይተናነስና ከጀ የማይለይ የመንፈስ ጠባቂ እቃ ነበር። ብረት ያለው ለጦርነት፤ የከተት ዘመቻ እብሮ ታሰሰ። ለዚያ የተባለው እሰሳ ሌላውንም ጭምር ያስተያያቸው ጆመረ፤ አገር ይሀንን የመሰለውን ጊዝ ሲቀብር እኔም ፈራሁ። እብሮቅ ከተነሳ አገር የፈጀ ነገር ቢኖር በለስልጣን ብቻ ሳይሆን የጉረቤት ነገሬስሪ ነው። የቀደሞ ወዳጅህ ባብሮት ጠላትህ። እናትም የማትታመንበት ዘመን ብትለው ከውነት የራቀ አይሆንም፤ ታውቀዋለህ ... በከባቢው ብርበራ ሲበዛ ተጠበቡ ብየ፤ ከጀ ተለይቶ የማያውቀውን እቃ ከመንደር እርቄ ከልብሌ ዘመድ ማስቀመጥ፤ በድንገት የየረሳሉም ጊዜ መነሳት፤ የብርበራ ቀን ሳያልፍ ወደእየረሳሉም ጆው በማለቴ ስንት እውቀቴንና የምርምር ልፋቴን ወና አስበላሁት።

«ሰማሀ ክንዴ! የያገሬ እስራኤል ጥበቡን ወደዚህ አገር ይዞ በመግባቱ፤ እራሱን ጠቅሞ ይሀችን ቅንኩሽት አገር እንዳኛ በማድረግም ተራዳ። የጥበብ ቅንሽና ትልቅ የለውም፤ መርፌን ማቅጠን- እንድ ነገር፤ ጆሮ መጨመር ሌላ ጣጣ ነው።

«የንብን ተግባር ወስድ፤ ለጨወቴ ውብ ምሳሌ ነው። ንግስቲቱ የሁሉም ማእከል ናት። ከሌላው በጣም እምራ የተፈጠረች፤ ወብት ሲዳፋብትና ሲያጠጃጃት የጥለ ሰትሆን፤ ሀይሷና ሽታዋ የጥን ሰብስቢ ጉልበቷ ጠረኗ ነው። በጠረኗ ሁሉንም ገደዳ ትይዝጥለች። ወሀ ተሸካሚው ድንጉል ንብ

በሄደበት በረሀ ሸክሙና ጓዙ መሮት ጉራ በልቶት አይቀርም፤ በውሀ ሸክም ጀርባው ተመልጦ የሚመለሰው የጠረጴ ሰስ ነው። ክዚህ በመጣ ታዛቢው የሰው ልጅ ዋና ብሙን ትቶ ባሪያው ንብ ይለዋል። ባሪያም ሰበደል ኀዑሉ ማታ የጌታውን ወደቤት መሸከፍ አረጋግጦና አግር ሰጦ ከልተኛ ህይወቱ ጨለማ ውስጥ እንደገባ ይቶዋረዋል። እንዲያ እንዲሆን ስለተገራ ይሆን ይሆናል። እንዲልከህ... እንደኔ ከሆነ ሰፈፍ ሰሪው ንብም ተገኝ ነው፤ ያደስእባውን ኩሊ አይተህ ያን ማየት ማለት ነው። ከንግስቲቱ በቀር እልፈት ያለው የለም። ንብ ለንግስቱ እሽ ብሎ ታማኝና ተገዥ ነው፤... እንግሊዞቹስ ከዚህ የተለበሙት መሳ ሳይሆን ይቀራል! ... ይሆን መችም ለተረብ አመጣሁት እንጂ የኛም ቅድረት የንብን ይማስሳል። ያበባ ቅመም ሰብሳቢው፤ ቤት አመቻቺው፤ ሰፈፍ ሰሪው፤ ይህ ሁሉ በየግጡ የራሱ ግብብ አለው። አንዱ ያለሌሳው ግብብ አይሰራም። አንዱን ግበበኛ የሚያሰኘው የሌላው በተለየ ነገር ግበበኛ መሆን ነው። መርፌ እንብለ-ክር መርፌ አይደለም። ታዲያ ከጦቢያ ወደስራኤል የመጣ የግብብ ነገር አለየሁም። ከልቤ የገባ፤ ለመልስ የገፋፋኝና ያስነሳኝም ዋና ነገር ይኼ ነው። በጦቢያ፤ ዋና አራሽ ብሆን፤ ብንዲ፤ በብረት ብታጀብ፤ አዲራሽ አልባብ-አልባብ ቢሸት የመፅሀፍ አውቀቴ አጃቢት ነው። የገለጥኩለትና ያነብብኩለት እንደሌላ ጆል ዳብተራ አማርሮኝ አያውቅም።

«ዳብተራ ብዙ አይነት ነው። ወደተንኮል የሚተያይ፤ በሰው ላይ የሚውል፤ እንዱን ጠቅም ሌላውን የሚጎዳ... ብዙ አይነት አለበት። ጆንን እንዲዘዝክውና እንደመራኸው ነው። ሰው ወደክፋት ያልመራው ጆን ጋኔል አይሆንም። አሁን ክፋት፤ የጆን ይመስልህ ይሆናል፤ በውነት ሲሆን ጆን ምንጊዜም ጆን ነው፤ ክፋትና ደግነት ግን የሰውና የሚጎትተው ዳብተራ ብቻ ነው። ጆን የሚሰራውም በግድ፤ በድግምት አድርግ ተብሎና ተቸግሮ ተይዞ ነው። እንዲያ ሲሆን ጆኑ ይለምናል፤ ኧረ ባክህ ተወኝ፤ አለፈኝ! ሳይል ግዲጅ አይፈልግም፤ ለምዋ አልሰክለት ሲል ነው የታዘዘውን ወለት የሚወለው»

«ሰው ያልመራው ጋኔል የለም ነው የሚሉት?»

«እነሆ! እምጠልኝ! አግኝተኸውና ሁዋን ነው!»

«ይኼ በውሀ ግድም የሚሰልበው፤ የሰው ደም አቷድሱኝ የሚለው ...› ሳልጨርስ ዘለው ገቡ። ‹ይሆን እንደምትል አላጠሁትም። በጣም አጥብበህና እጥቆመጠህ ያየኸው ምሳሌ ነው። ሰው በጣም ተጋፊ ፍጥረት ነው። ጊዜ ካልከደው ልድረስ የማይልበት በታ የለም። ይኼ ባህሪያችን ነው። እንዲያ ሲሆን

የግፊ ቅጣት ይዋራል። አትምጡብኝ፤ ክልላችሁን አክብሩ የማለትና የስእት አለማክበርን የመጠቆም ነው። ከባቢውን አሉ በሚፈልግበት ጊዜ ሲሄድበት ለዚያ ማስተገሻ፤ ክልል ስታልፍና አልቶምም ሰቅል፤ ማከከሸ ግብር የሚጠይቀው ለዚህ ነው። ግብርን የሚያስለምደው ሰው ነው። ደም አፍስሱልኝ ሲል፤ አንድ ነገር እርጉልኝ ተብሉ ነው። ጆን ወደጋኔልነትና ወደሰይጣንነት የሚለወጠው ሰው ሲገፋው ነው። ከጆን በሬት ጋኔል አሊያም ሰይጣን የሚሆነው ሰው ነው። ጆን ሰይጣን የሚሆነው የሰው የወለት መንፈስ ሲሰረከረክበት ነው። ያንን ሳለመሆንእንኳ ብዙ መሳ አለው፤ መጀመሪያ የጠየቀውን ግብር ሰው ሲያቀርብለት ሰውን ለማስተማር ሲል የልጅህን ደም አፍስስልኝ ይላል። ስራልኝ ያልከው በደል ሌላውን እንደሚያመው የማስረዳት መሳ። የጉረቤትህንም ሆነ የሩቅ አገር ህዝን አፍንህ ብታቀርብለት የማይቀበል የጆን ዘር አለ፤... ሀይለሰላሴም በጆን ተመርተው ነበር ይዋረ የነበር፤ ያጠፉቸው ከጋኔል ጋር መጣላታቸውና የጠየቀውን የደንብ ግብር አላቀርብ ሲሉ ነው አሉ፤ የልጃቸውን ልጅ እንዲያርዱ ተጠይቀው ባለመስማማታቸው። ጆን የሚፈታተነው የሚፈታተነውን ሰው ነው። ሰው ግብዝ ነውና ለተጠማበት ነገር ሲነሳ የሸፈነ ነገር ሸፍዋት ነውና አንዳንድ ልጅን ለጆን ያደግ ሰውም እናውቃለን። ከጊዲ ተነስቶ የዶሮም ሆነ የዲልቻ በሬ ደም ግብር ያለ የጆን ዘር ግን አለለማንም፤ ሰውግ እንግዲያ የመጨረሻ ደም ነው»

«መልክም፤ ያውጉ!»

«ጨዋታዮን እያበላሽልክ!... ብቻ የማጥራትም ነው። እኔ ይሆን አይነት ድብቅርና አልወደውም። ለስራኤል ልጅ የተበጀ ደንብ አይደለም፤ ከግዜር ጋር ያጣላል። በጆል መንገድም ከጆን ጋር ጨዋታ እንድ ቀን እኪለ-ሰንኩል ያደርጋል። የማስገደጃውና የመጠቢያው እፅ ሰልቶ አይገኝም፤ እንዲያ ባታጋለ ስትተላለከው በጣም ቅእቢተኛ ፍጥረት ነው። እየደገምክ፤ እእምሮህን ለማሳት ይታገለሀል። አንድ ቃል ባት ካለሀ በደበለባ ይመታሀና አይንህ ጠንጋራ ይሆናል፤ ወይም እጅ-ከግርህ ቅልብጥ ብሉ ያርፋል፤... መቸም አንድ ጉድለት ይሰራብሀል። እንዳንዴም፤ ቀጥታ የተፈጠረውን ደረትህን፤ ከሆድህ ራስጌ እንደተገተረ፤ እግርህ ሬት ወደሚነትልበት ይተውና፤ እንገትህን እጣም እንዲያ ወዲያ ገድም ወደገራ፤ አሊያም ወደቀኝም ገርቶ እገሮት ይቀራል... እርጥብ ጨፈታ እጋግግ የምትቶሰቅሉ... እ-ሀ-ሀ- እንዴንድ! አሸር ቆይ የሆምሌ ቤት መስሉት ያርፋል።

«የሰው ልጅ ከጅን ያልተማረው አንድ እውነት አለ! ጅን መንጃለኛውን በሞት አይቀጣም፤ እጥፊን በሞት ስትቀጣው ከንተ ላይ የማይለምጥ ቁስል ትቶ ይሄዳል። በአንድ ዘመን በሞት የቀጣኸው ጉዳይ በሌላ ዘመን የምትጠወርበት ይሆናል። ጅን ግን ማስፈፀ ከልነሳኸው በቀር... ልክ አይተ ድመቱን እንደምትነክሰው አይነት አጋጣሚ ካልሆነ አይገድልም፤ የሰው መሳቂያና የዘመድ ማፈሪያ ነው የሚያደርገው፤ ተመቾውማ እንግዲያ ጠንጋራነቱን ይለምዱዋልና ምንም አይሰማውም። ታዲያ እሱን ያየ ተቀጣ የማለት እንዲያ ጉድ ሰርቶ ይተወዋል። ስንኩልና ጠንጋራውን ደብተራ ያየ ምን ቢያጠፋ ይሆን ብሎ ይጠይቃል፤ ሰው ከሳየ አይማርም፤ የጅንን ዘደቢ ከሰው የሚለየው እንዲያ ነው። የየረብሌም መንግስት በዚህ በኩል ትልቅ እርምጃ አይሞክታለሁ፤ ያየ ተቀጣን የሚያሰየው በማጉር ነው፤ ከዚህ ከመጣሁም ቢሆን አንድ ሰው ገቢያ ላይ ሲሰቀል ገና አላየሁም ይመስለኛል። በብዛት እንጠር ቢሆን የጅን ቤቱ ጦቢያ ነው፤ በጉ መሳውን ግን እስከሁን የተጠቀመበት አላየሁም።»

«እያ ተበጃ!»

«እህ ወገን»

«ጅን ይገድላል፤ አይገድልም ነው የሚሉቱ...»

«ጅንን በጠም ሰትብድበውና ሲፈታ እዚያው ላይም ያፈርጥሀል! ጠንከራ ደብተራ ከሆንክ፤ እንዴን እሱ ቢያዝዋልህ፤ ሌላ ምስህ አሊያም ተንገስህ እንደምትመለሰበት ያውቃል። የሽሚያ በቀር የምትመታውም በዚህ እንጠር ሰመጠብህ ነው።»

«ሰውም እንዲያ ሲያደርግ የሽሚያ አይሆንም እንዴ?»

«ሰው ፍርድ ቤት አብጅቶ ነው የሚገድል፤ ጅን ግን ፊታ ሲቆርጠውና ቀን ሲጥለው በድንገት የሚወስደው ርምጃ ነው፤ ሰውም በልምቅብይ ተጋዲይነት ሲገድል ማምጋሚው የተለየ ነው፤ የፍርድ ቤትና የጅን ያየ ተቀጣ ቅድረት የስማይ-መሪቱን ያህል ርቀት ነው።»

«መልከም የሰዎን የድብትርና አይነት ያብራሪ!»

«የኔ፤ ቀደም ከልኩህ የድብትርና አይነት የተለየ ገጥ የያዘ ነው። ከጥንቱ፤ ከማለዳ እንደተሰጠው ለሰው ልጅ የየቅል ባህሪ፤ እመልና ጠባይ፤ ክፍልና የወደፊት እድሉ የሚመሰልውን እየመሰልክ መምራትና መንገር ነው። ክክቡን በትህክል በማቷጠር፤ የማይበጀውን ወሁ- አይበጅህም፤ ጥክቡ ጠብ ከፈር ጋርም ከሆነ እንዲያ፤ የሚከፍለውን ደግሞ- ይኸ ያስኬድሀል ማለት ብቻ ነው። አሁን በዚህ በኩል አይገባህ ይሆናል፤ ካልገባህ ደግሞ እውነት አይመስልህም። የጅን ጉተታውን ያህል ብዙ ጥልቀትና

ብርቱ ስራ አለበት።»

«እንዴት? ተቢው።»

«እንዴት ማለት ወብ ነገር። ከሰሉ ስትስት ከመዝጊያ አትደርስም፤ እህዝ የሁሉም የዳኝነት መሰረት ነው። ወሸታም የምትባለው እህዝ ስትስት ነው። እኔ ግን፤ ከመጥፉ የጠረጠርኩትን በጆ-መደፉ እይዝዋለሁ። ከልተጣጣመ ከናትህ ወይም ከባትህ ስም ማጣብ ስተህል እለውና ቁልጭ ያለ ማጣብ ሲያመጣ ቶጠራና ክክብም አይጋጭም። ይህንንም አድርገህና ደጋግመህ ቶጥረህ ጨጥታ አልጋጠም ከሰ ከናትህ ወይም ከባትህ የተለዋወጠ ስም ይቀር ይሆናል ብየው ቤቱን ይመሰላል። አጥርቶ እንዲመጣ ታስናብተዋለህ። በናቱ ወይም በባቱ በኩል ነፍስ የገደለ ወይም በሌላ ጣጣ ስም የተየረ ሊቀር ስለሚችል ነው። ያልገጠመ ነገር እንዲያው አልናገርም፤ አይረብም፤ አጉል ስሜን በምን ላጥፋው ብሉ በራስ ላይ ስለት እንደመሳል ያለውን ነው። ለጨወቱ ነው እንጂ እንዲህ ያለ የገጠመኝ ከጥቅስ የሚገባ አይደለም። ... ጊዜ፤ እንዴት ይሮጣል ከንዴ? ወትያዋሱ ጨለማ ሰበሰ፤ ባይታወቀን መሸ! በል እንገዲህ፤ ባምላክ ርዳታ ከዲዊቱም... በዋና የጥንት ዶጋጌቹ፤ በብራና የተከተበ። የዶጋጌቹ መንፈስ ከዋለበት ንብረቴ እደርስለሁ።...

«አየህ! እግሬ እስኪነቃ ብንቀዋለል የተገባ ነው። እዚህ ሁሉም ነገር ያልተገባበኝ የዲዊቱ ረድኤት ባይከተለኝ ነው። ከፍቶኝ ሰማህ የመታን ወቃቤ አቤት! ምን ሁነህ ነው? እንዲይለኝና እንዲልባገው ተራራትን። የመታንና ገና በቅም ያለነው ግንኙነት መታን ትተውት በሄዱት ንብረት በኩል ነው። የመታንን ጥሪ ያህል ከባድ ሀይል የለም። እንደበድን ሰጋ ግድም ወድቄ! እነሱንም ትቻቸው! መጥፋንም እንዲዚያው ጣልኩት። ወርደና ተዋርዶ ከቤቴ እያቶቸ ድረስ የሚዘልቅ መፅሀፍ ነው። ስለሆነም፤ ከተጣፈውና በሰው አይን ከሚታየው ቀለም ሌላ፤ የመታኑ ታስወቃቤ አብሮ ይኖራል። ገቢያና ሽንጉ ባስብና ዲዊቴን እልብ ስመጣ በሰላም ተመልሸ ቤቴን ገብቸ አላውቅም፤ ገጭታ አይጠፋም።

«ከዚሁ ጋር አይነታው የእስራኤል ልጅ የዘር ግንድ መዝገብ ከዲዊቴ ጋር ቀርቷል ከማህደሬ። ከዚህ የዘር ግንድ ቀጠሪ ሲባል አይን እየፈጠጠ ቀርቷል። ቅርንጫፉን እወራርዶ የመቀጠር ከልሆነ ዋናወቹ የጦቢያ እስራኤል ግንዶች ሰባት ናቸው፤... ባይሞቱ፤ ያይኑምባ፤... እያለ ከሰባት ይደርሳል። ከሰባት ግን አያልፍም። የዘምድና ማለቂያው ዙሪህ ለማቢ የምትተያየው በሰባተኛው የትውልድ ተዋረድ ላይ ነውና፤ ስትገባ ዙሪያ

ተስበት በራሁ ማለት ነው። ዙሪሀ ከሰባቱ አትወጣም። ታዲያ፤ ፈረንጆች ይህን ምስጢር አልደረሰበትም፤ በመዝገብ አትርበ ያበራ ሰው አልተገኘም። የመጣመም ነው። መጀመሪያ ስረ-መሰረት ሳይዙ ስራ አይጀመርም ነበር። ግና "አወቶ የተኛን ቢተሰቅሱት አይሰማም" እንደሚባል ተመልሰው ጠመውናል።

«ሌላ! ወደ ሂሳ የተውኪት የልብ ምስጢርም አለቻኝ። በጣም ችግር ነው፤ ግና ከመምከር ከሚተር ልቡን ብዙ ነገር ይታየዋል!»

«ምን ታየ?»

«ከጨዋታ ደጋግሞ ተነስቷል። ይህ በየክርስቲያኑ ገዳምና ታቦት ቤት የገባና የተደበቀ የጥንት መጽሐፎችን፣ ታሪካችን ነውና መውጣት አለበት። እስራኤል ወደመጣያ ሲገባ ዋናው ዳዊትና አረት በብራይስጥ ነበረ ይባላል። በእስራኤልና በክርስቲያኖች መሀከል በተደረገው ብዙ ጦርነት፣ መጽሐፉ ሁሉ እየተማረከ፣ ከእስራኤል እጅ ከጠፋ ዘመን አልፎታል። ይህን የነጭ መንግስት ብንማለስ ወም አልሆነ፤ ቢሆንልኝ በልመናም የሚሆን ነው። ለምን ማለት፤ የምክርና የወርስ ነገር ሁኖ ነው እንጂ ለክርስቲያኖች የሚጠቅም ንብረት አይደለም። እንደያነቡት፤ የያዘው የእስራኤሉ ነክ እምነት ነው። ገም ብሎ ያይንና አምሮት መውጫ፤ የተረፈው ያይጥ ቀለብ ነው የሆነው። በይዞታቸው የዋረ ነገር፤ ሲጠይቋቸው ብልጠት ይመስላቸዋልና... ሰው መቸስ የትናት መጠንበሽ ጋን አይደል፤ ታዲያ ሰራሹ ውጣ ውረድ በዚያው ልክ አያሌ ነው።... መቸም የኔ ጣጣ ይሆን ይሆናል።... እግዜር ይቅናህ በለኝ ክንዴ!»

«ይቅናህ!»

«እንቅፋትን ያጥፋው በል!»

«ያጥፋው!»

«እዚህ ያለው ፈላሽ፤... መቸም አይረባም... ግና፣ በግዜር እጅ፣ በያምና በፀሎት ኑረልና የዘረወን ብልሽት ረስቶ፣ የፊቱን መገፋትና መንገላታት... መቸም ሲንገላታ ነው የዋረውና የእስራኤል አምላክ ብልፅግናና ምቾት ይሰጠው። ለኛ የሚራዳውን ያማሪክ እስራኤል ያኑር፤ አለምን ይግዛ፤ ምናባቱ፤ እንደፈቀደው ወብ ናቸው፤ መሆንስ.. ከጠዋት «እንቅፍቅፍ» ያለባቸው ባለፀጋና ቱጃሮች እነሱ ናቸው። ታዲያ፤ ህዝብ ለንጉስ፣ ደሀ ለሀብታም እንደጠልይ የነበረ ልምድ ነው። ብዙ ነፍስም አድነዋል፤ የኔ በረኸት መስጠትም ከዚያ የከረቀ ልምድ ነው፤ ያቤት አደር!

«እይዘህ እንተያያለን፤ ልቡን አላምነውም፤ ከዚህ ስትሆን የዚያ ግዶ ልማድ፤ ከወዲያ ስትሆን ደግሞ የዚህ ወሰል ብሉ

ይታይሀል፤... ምን ይታወቃል? ትዝታ የገደል ማሚቶ ነው፤ የገደል ማሚቶው ዝም ብሉ አይሰማም፤ ያላየኸው ደግሞ አይናፍቅም፤ ታዲያ ያዘለህ ስትለው ዝም ብሉ መሄድ፤ መራት፤ እንተ መከተል፤ መድረሽ የለውም። አሁንም ከወዲያ ማዶው ገደል የሚሰራው ማሚቶ አላስተኛኝ አለ። እኔን አትሆን ክንዴ! ሰው ደግሞ "የፍላጐትና የምኞት ባሪያ ነው" ይባላል፤ ይመስላል፤ ጀርባው ያለ ድልዲል ባሸዋ ጭንቅ የተመለጠ የሱዳን አገር ገጠብ ሰናር አህያ ማለት ነው። በል!... "ከረብላው መወገፍ"... ነገ ባራት ሰአ የምትመጣ አይደለህ?»

«እንዴታ! ጥያቄ አለበት እንዴ? እያ ተብጀ። መጠየቅያም አለማፈርያ ነው»

«መጠየቅ፣ ማረጋገጥ የደንብ ነው። ደግሞ፣ በጥፋት ረገድ ከታየ ይቅርታ! በዚህ አገር የጊዜ ነገር በመታጥን እየተበከ ነውና፤ የተማረ ነገር.. ጊዜ መስፈር በጣም ታበዛላችሁና፤ እንተንም ለምደብህ ይሆናል በማለት ነው፤... አይደለም እንዴ?»

«ጊዜ እንደያ የምስፍር ከሆነ እንድ መታጥን ለሰዎ መቅረጥ ነወር ይዋረዋል እንዴ?»

«ጨዋታ መጣልህ፤ በመድረፍ ያንተው መግት አየለ!... እግዜር ይባርክህ፤ ምንዋ! ከመጣህማ ደስታየ ልዩ ነው። ይሞቀኛል።... ልተኛ ስጋደም ብዙ ነገር ይብራራልኛል፤ የምታጣናኝ ነገር አይጠፋምና ... መገኘት መቸስ ከየረ መንሽ በጣም ቀደም ብሉ አይደል? ታዲያ፣ ቡና ቢጤ ይዘን ትንሽ እናወጋለን። በል፤ ከዋናው የቤቴ አድራሻ ያውቶቡስ "መወገፍ" የሚያደርሰኝ "መኪት" እጀን ይዘህ እጋባኝ! ቸር ያደርገን!»

ሰው በሰው ጉንደሬ።

በነጋው፤ በተባልኩበት በታ፤ ከሚሰፈረበት ሰአት ትንሽ ቀደም ብየ ተገኘሁ። ዘመድ-አዝማዳቸውም እንደኔ ሊሸኛቸው ተሰብስቧል። ወደብር ያልተሰጠ ንብረት አልነበረምና ጓዛቸው በጣም ቀላል ነው። ግራ ቀኝ ሚስቶቻቸው አሁን የልጅ እናቶቻቸው ማለት ይሰማማው ይሆናል፣ የማጊደንና የቅብ ግንኙነት ካልሆነ እንዷን በሀገ ለቀዋል፤ ብሉም እንዷንም አላስከተሉም። ያገረው ሰው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸውን በበጉ የተመለከተው አልነበረምና ከጥርጣሬ ቅኪዜ ልጆቻቸው ከታች በሀሳብ ማእበል ተውጠዋል። የመጨረሻ ልንጨባበጥ ቀረብ ብየ፤ «ሰው መገን?» አልኩ። ቢሰጡኝም እንዳልሰማ ተውኝ፤ ወደውም

አልነበር ያላሰቡት ሸኝ ከርቀት ሲነጉድ በመመልከታቸው ነበር። ደግሜ «እያ ተበጀ!ብል «ልብሴ» እሉ በመልሳቸው፣ የወይ" መተኪያ እንዱ ያላቸው ነበርና።

«እንግዲህ፣ እየተስተዋለ! ከኢትዮጵያው አየር "መወገፍ" ሲደርሱ እንኳን ደሀና መጣህ የሚለው የሰው አይነት ደብዛ ይሆናል። በተጠየቅ ነፍስያት እንዲታለፍ ይወቀበታል። ንግግሬያን ይወቀበት...» አሉኝ። እሳቸው ቀምነገር እንደሚያደሉት ቢገባኝም፣ ሌላ የመሰያያ የምግለው ቃል ስላልነበረኝ፤ ተቸገሬ ያሰብኩት ቢሆንም ከረፍተነገሬ መድረ ያ አላደረሱኝም፣

«ከንዴ የሰው ፍርሀት የሚመጣው ከባህሪውና ከየው ችግር ነው። ነገሬ የእንኳን ደሀና መጣህ! ከሆነ፣ ችግር እዚያው ላይ ያልታል። ግና የዉዋታህን መዳረሻ ይዤዋለሁ፣ ነገሬ ግልፕ ነው፣ የጠየቀ ቢጠይቅ መልሲ የታወቀ ነው፣ ምን አዲ የሚያስገባኝ ነገር አለ ብለህ ነው? አገሬ መቢያ ተቀበለኝ ብየ ነው የምሄደው፣ የዚህን አገር ዉዋታ ቢያነሱ የኔ የባላገሬ እውቀት ከነሱ የተረፈና ያለፈ ነው። ያየኸውን ውብና ጀል ነገር እውጥ የሚበል አግሬኛ ከተነሳ መልሲ ምንጊዜም እውነት ነው፣ ለጠጅና ለቤት ውብና ሰድ አገር፣ ለሸማግሌ መጠለስ ነው፣ አይረብም! ይቻት! ይችው ናት ንግግሬ።... አንተ ለወሬ ታሪግው ታስበለህ፣... የጉንዳሬን አስተዳዳሬ ከቢሮ ገብቶ ሳይቀር ሳልሞግት የምቀር ይመስልሀል? እምቢ ቢሉ ደግሞ ሸዋ ከበላዩ መድረሲ የማይቀር ነው፣ ጉንደር እምቢ ቢል ሸዋ እሽ ይል ይሆናል። ከዚህ ምናልም ቢጊንን ለማግኘት የቷንቷ አስተርጓሚው ፍላጎ ሀያል ነው፣ ከዚያማ፡ ምን አለበት! ስልክ እንስሽና መቶቸ ከጋፋሪው የመግቢያ ቀጠሮ መቀበል ነው። መፅሀፉን ከተቀበረበት እውጥቼ፡ በግልፕ፣ ከዋና ስራየ ሰገባ፣ በመንደር የሚያልቅ መግት አይደለም። ከላይ መርገጫ (ማህተም) የሚያስፈልገው ስራ ነው።... ብዙ እንነግርህ ነበር፣ ግና ይሆን ሊሸግኝ የቆመ ህዝብ እየሰማኩ ወደቤትህ ዙር ልበለው፣ አንተም ዙር፣ ከዚህ የረብሻ መናኸሪያ ብርድ እንዳይገልህ። ነገር አለቀ፣ ቸር ይግጠመን!... ጋሻግ፣ ኧረግ-ኧረግ! ረሸቸ፣ ቤና ይዘሀል?» ሲሉ፣ የጠየቁትን ብርእ በጥቻቸው ከኔ ጋር አብሮ ያዋረንን አጊታችና አቶራኝ ቅይበት ተወራርድን።

የከበቢቸውን ሰው በደንብ ተሰናብተው፣ የቀረቢቸው ግን መሰለም፣ ሲገቡ እንጂ ሲወጡ አይሆንም እንዲሉ ራቲቸው። እሳቸውንም አልገደዳቸውም። በደንዳናና በክራ እክሄድ የመሰያያ ደረጃውን ከወገባቸው ወታ፡ ከመቀመጫቸው ጉብደድ፣ ከወደጉኛቸው ከንዳቸው ከርፈፍ፡ ከግራቸው ረጠዋ ብሰው፣ ታቹ

ችግራውን ሲያያዙት፣ ከኔ ሰደስት ርምጃ ያህል ርቀት የቆመ የመሀከለኛ እድሜ ሰው ሲራመዋ አይቶ ጀሮየን-ከይኔ አብሬ ወደሰውየው እዘመቅኩት።

«አንተ እየዋ ተበጀ! ና እዋ ወዲህ (ወልቃይቴ ነው) ዝቅ በልግ» ብሉ በሀይል ከወሰን እልፎ ሊማም ሲል እርከበር ጠበቂው ወታደር ዘሎና ፈጥርቶ ያዘው። የያዘውን ወታደር ልቶተኝ ለማለት የሳቸው ርምጃ ፋታ ያሰጠው መሰለ። ጥሬውን ሰምተው እንደገና እየተመለሱ ባለ ዘለግ ባለ ደምፀ፣

«ጋሼ በሞቴ አደራህን፣ ማሲንቆን፣ ዋሸንትን፣ ከራርንም ሆነ ይሆን የመሰለ ነገር... ባንተ በኩል ባይሆንም፣ የሚመጣውን ሰው እሀ ብለህ እናያው፣ አስለብሰው። የጊሸና የጤና-አዳም መበቀያውንም ገና አልደረስንበትም (እስራ-ኢል ወሰዋ) ይሆን እንዳትረሳ!» ሲል፣ ይሆን ቸከሳ የተመሳበትና የአመለጠኝ ንግግር የቀደና ከእድሜ የገፉ ወዘዘር፣ «እሬር ልቅመስ!... ጀሮየ አይሰማው ጉድ የለም፣ እንዴት፣ እንዴት ከለው የወንድ ዘመንና ጊዜ መሀል ዘነቀኝ? ዛሬ የጠፋለት ዉዋታ ሰማሁ፣ የእጅ ሰራውን እንደሰስት መቀጠሬ ምን ተብሉ ነው? ይልቅ ጊሸውና ጤና-አዳው ውብ ነገር፣ ሴላ-ሴላም የጊር አትክልት... ፍሬው የሚሜነውን ነገር አይርሱ ወንድሜ! ይቅናዎ!» ያሉት፣ ወደእያ ተበጀ የተጣለ የመጨረሻ ቃል ሆነ።

ጉዟቸው በጠም ዋጋ ከማግኘት ጋር፣ የፍጥረታቸው ባሀሬ ተዳብሉ በልዩ እረግመዳቸው በደረጃው ላይ እንደገና ብቻቸውን ተንፈራጠጠበት። እንዳንገጠቡ ሲሄዱ ያየች የሆታቸው ልጅ ከጠገቧ ለቶመችና "ለግሳወታት " ጉብል፣ «ተመልከችልኝግ በሞቴ! ወትሮም ከይሲና ታሪከኛ ነበር፣ ዛሬም እንዳትሳንትናው! ይሆን የረብሻ መንገድ የወንዝ ጅረት አደረገው፣ ጃ ሬ ዱ ያ! የስሜኑ አድባር፣ የትግሬው ቅኝት፣ የሸዋው ግርፍ፣... የጉበዟ አጉት... "ሰው በላው" ጉንደሬ!...»

ቃላት።

> ሱዳንኛ ቃል።
* እብራይስጥ ቃል።

"እስራ ኤል"፣ "ፈላሻ"፣ "ካይላ"፣ "ቤተእስራ ኤል"፣ "የኢትዮጵያ ይሁዲዎች - እነዚህ ቃላት በሙሉ ፖለቲካ-ነክ ቃላት መሆናቸውን እርስ ነ-ደካቸውን በመከተል መረዳት ይቻላል። ስለሆነም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ትንሽ ያምታታሉ። ያጠራር ምርጫ እንደየባህሪያቱ ይለያል። ትንሽ ማብሪሪያ ለመስጠት፤

ፈላሽ - ፀሐፊዎች (በብዛት ምእራባውያን) የዚህን ቃል ምንጭ በሁለት በኩል ሊመነዝሩት ይሞክራሉ። አንደኛው ወገን የኢትዮጵያ ይሁዲዎች ከውጭ የመጡ ዜጋዎች በመሆናቸው ከጥንቱ ሰደተኝነታቸውን የሚያሳይ ስም ነው» ሲሉ የዚህን አይነት ድርደራ ከዘጠኝ መቶ እስከ ሁለት ሽህ አመት ያከልሉታል። የይሁዲውያውን ስደት ሁለት ጊዜ (ባንደኛውና በሁለተኛው መቅደስ ፍርሽ) ነውና ያመቱ ልዩነት ከዚህ የመጣ ይመስላል። ሁለተኛው ዘርፍ ደግሞ «በሱስንዮስ ዘመነ መንግስት የተፈጠረ ስም ነው። ለስልጣን ተዋጉ፤ ሲጠቁ ቅጣቱ ከእርስት መንቀል ነበረና ይሁዲዊ የሆነ ሁሉ፤ «ፍልስ --- ፈላሽ» ተብለ የሚል ሲሆን በሁለቱ አቀረረቦች መሀከል ያለውን ግጭት እስከሁን ያስታረቀ ፀሀፊ ግን ገና አልተወለደም።

ቤተእስራ ኤል - መስጊዱ እሲያም የፈላሽ መንደር። በቅርብ ግን ቡድኑ (ሰው) ተተክቶ እንደጠራበት መፈክረን ያነበው አንድ ቤተእስራ ኤል-ነክ ቡድን (ካናዳ ውስጥ) ሲሆን፤ እስራ ኤል ውስጥም ይህን ስም ለማስወደቅ የሚሰራ ቅርንጫፍ ቡድን አለው። የማህበሩም የህግ ስምም ያው «ቤተእስራ ኤል» ነው።

የኢትዮጵያ ይሁዲወች - ይህ የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ውሽንፍር (በፈላሽና እስራ ኤላውያን መሀል) የፈጠረው አጠራር ነው። እስራ ኤል ውስጥ በተፈጠረው ሙግት «ቤተእስራ ኤል»ም፣ ሆነ «ፈላሽ» ወደልዩ መሆን የሚያመራ ቅኝት መሆኑን የታዘቡ ሰዎች ያቀነቀኑት (ለመፍትሄ) አጠራር ነው። በጥር እንጋገር፤ እንደእያ ተብጆ ከእድሜ የበሰ «እስራ ኤል»ና «ጌይ» ብሉ ያለመን ሰው ሲከፍለው «እየረሳሲም» በመባል ብቻ ያውቂት የነበረችው «እስራ ኤል» ሁና ሲያገኙ፤ ከጊሳው ስም ጋር ተጋጭቶባቸዋል። ይህን ግጭት ሲያስታርቁ «የነጭ እስራ ኤል»ና «የጠቢያ እስራ ኤል»

ሲሉ ይታያሉ። ይህን በጭር ለመመልከት፤ «እስራ ኤሉች» የሚለውን ቃል እድሜ፤ እዘ ውንቶች ጥንት የነበረ አድርገው ይናገራሉ።

ካይላ - በጽፍን ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ማህበረሰባት ውስጥ በኪነት ሰወች (ቀጥቃጮች፣ ዘምዛሚወች፣ አንጣሪወችንና ሸክላ ሰሪወች) ላይ ሲለጠፍ የኖረ ስም መሆኑን ሁሉም በክባቢው የሚረዳው ይሆናልና ማገናዘብን ሳንበቢ ሁሉ እተወዋለሁ። «እጀኛ» ማለት የታረመ ንግግር ሆኖ ሲታይ «ካይላ»ና «ጠይብ» (ከሆነት ቀመስ ሰወች «ጠቢብ» ያሰኙታል) ትርጉማቸው አንድ ነው፤ በጠብ ቃለዜማ ሲወረወር ያው ስድብ ነው።

አገረመንገዶችን ግን «ካይላ» የሚለው ቃል (ቀንሰሀሳብ) «ቡዳ» ከሚሉት ቡድን ጋር ያለው ዝምድና ምንድን ነው? የሚል ቢነሳ፤ «ካይላ» ይበልጥ ብሄራዊ ባህሪ ይይዛል፤ «ካይላ» ማለት ፈላሻ ብቻ አይደለም፤ ሌላ ሀቅ የመናገር ከተነሳ ሁሉም «ቡዳ» ተብየ «ካይላ»ም አይባልም፤ ከሁሉም በላይ «ቡዳ» ተብየወች ጭራሹን «ፈላሽ» ሲሆኑ አላየንም። «እንዴት?» ማለት «የቡዳ መድሀኒት» (እትሊትም ይሉታል) እያንዳንዱ ቤተእስራ ኤል ያሰራልና። ቤንጉሪዮን አየር ማረፊያ ላይ ካገኘት ከወረዱት የፈላሽ ጥሪት ግሀል አንዱ ነው። ከተሰደዱት አንዱ ዋና ተከልም ጤናእዳም ነው፤ (ያትሊት አንዱ ቅመም ነውና።) ስለሆነም የጠበቶቹ ቅንተና ብዙ የሌሉችንም ታሪክ የሚያጠሩ፣ ሲጠናም የሚለወር ነውና «ካይላ» የሚባል ሁሉ ፈላሽ ብቻ አይደለም፤ እንደጉንደርና እንደትግሬ ሌሎችስ ፈላሽ ያልሆኑ «ካይሉች» የሏቸውም? መልሱን ለታሪክ ሰወች ጥናት ትቸዋለሁ።

ሀይ - ራስ ደጀን ተራራ ግርጌ ያንድ አምባ ስም።
ሀግ-ማለት - መሰማት፣ ማቋጠር።
ሀረይ - ቀልብ
ለመጭ - ብስል (ለፍራፍሬ)
ለም-ወድር - መጭልጭለ
>ላጅን - ሱዳን ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ስደተኛ።
መለጉተ - ከፍ መውተፍ (የበቅሉ ልጓም)
መለከፍ - መታመስ፣ መቋረስ
መረሀረሀ - መብተክተክ
መሰናጠቅ - መከፋፈል
መሸለቅ - ከሙቀት የሚመጣ መንፍረቅ።
መቀለት - መታገዝ፣ መቸር (መቀበል)
መቀረሜ ልጅ - መጨረሽ፣ መጨለሜ

መባጨት - ማጣጣል፣ ማመናጨቅ።
መንደ - ባለእንቁር በቅር/ ዘንግ
መክፈልት - ቁርስ፤ መክሰስ።
መክሸም - መዳራት፣ "መገበር
>መወገፍ - የህዝብ ማመሳሰሽ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች መነሻና መድረሻ ነው።
መዳፈያ - የቁልቁለት እናት፣ መድረሻ፣ መዝጊያ
መጋኛ - የዋረ በሽታ
መጠለስ - ዐር
መጨንገዝ - ያለስልት፣ በጉለብት መክፈል።
መፍጀት - ማቃጠል (ሳት)፤ መክላት፣ ማለቅ፣
*ሙኒት - ታክሲ
*ሚሽጣራ - ፖሊስ
ማሰለበም - ማስገንዘብ
ማስናስን - ማብቃቃት።
ማበራየት - መቅሰቅስ፣ ማገላበጥ፣ ማደባለቅ።
ማወናጨፍ - ማዝለግለግ፣ በሀይል ማወዛወዝ
ማኸንገፕ - ከቅክሽ እስከ ታፋ ያለው የጉልበት ሀይል
ማድሪሀ - የቡድን መሪ፤ የክፍል ሀላፊ።
ማጀል - በመርገጥ ማስማማት
ሚጫፈር - ሰብበብ መያዝ፣ ማቅናጠጥ፣ ቧጦ መያዝ።
ምንጨ-ህዝብ - አውራ፣ ባሳባት፣ MAIN STREAM
ሞባይት - የስንበት (ቅዳሜ) የቤተእስራኤል መና (ዳቦ) ሲሆን «ሀብስት» ከሚለው ቃል ባህሪው ይመሳሰላል።
ሞጠረ - ጠነከረ፣ ገበዘ።
ሰመመን - ንእስ እንቅልፍ።
ሰጀና - ለቆቅና ዝገራ መያዣ (እንገት) ከብዙ እንቂት (ቀጭንና ነጠላ የጭራ ገመድ) የተሰራ ወፍመድ።
ሸወኪያ ንግድ - ከንቅርበንድ
ቀንጃ - ተጣማጅ፣
ቀፕታጣ - ስስታም
ቀልቢፕ - ከድርጉ ከፍ ያለ መስፈሪያ (ሰፌት)
ቋንቁራ - ጊዝ፣ የቤት እቃ።
ቅስ-ወሀ - የመልክ እጣጣል፣ ዶምገብቅና ለሽቅን ጠቀስ ነገር ሁሉ። ለምሳሌ ቅስ-ወሀው የዳንውን ሰው ይመስላል።
ቅራተኛ - ከብት እልታጊ
ቅርጠት - የሙራ ምታት እደንን ሲያባብጥ።
ቅጡቅፕ - ሁኔታ፣ የፍፐረት እሰራር።

ባድማ - እዳሪ የተተወ ጨስ (መንደር)
ባደበሉበሽ - ባደበሉባ፣ የመዳፍ ጀርባ
>ብረንዛ - ንእስ እውቶቡስ
ብድር - ቂም፣...
ተርቲመኛ - ቡና እጣጭ
ተንፋራ - ያልተቋጨ፣ ያልተስተካከለ
ቅደስት - እወሊያ፣ ዛር፣ እመል
ኀቶራ - እሬት
እሊ - ሀሰት፣ መክዳት
እልጫ ወንድ - ለፈስፋሳ፣ መያ የለሽ
እግረኛ - እያያዝ፣ ሁኔታ፣ ቅድረት፣ ብልሀት፣ መላ...
እቅል - ቀልብ
እብደናኙ - ብቅንቅን ወይም ዝብርቅርቅ ማለት።
እወዛ (ሀወዛ) - የሚቅና ግር ፐጅት፤ ዝፍዝፍ።
እይኑ-ወጊ - በወበት ላይ ለፍፎ ከሀመም ማድረስ
እድማስ - በእንግሊዝኛው «ዳይመንሽን» የሚሉት ስሜቱ እንዳለ ሆኖ፤ እይን የመሬት አቀማመጥን ለማየት የሚከለልበት መስመር (ስንሰለት)፤ አቅጣጫ ለመለየትም እንጠቀምበታለን።
እጥቢያ ኮከብ (እጥቢት) - ቤኑስ
እግማስ - ነፋስ። እግማስ ሲያዝር፣ የጠዋት እግማስ፣ የቀትር እግማስ፣...)
እለፍ-ገይድ፣ - «ፖስፖርት» የሚለውን ቃል ለመተካት በንጥቀት የተወረወረ ሲሆን፤ አንድ «ፖስፖርት» ማለት የረሱ አርሰ-አደር ሽማግሌ «እንዴመጠሰቸው» የዘረፉት ቃል ሆኖ ቃሉ የተፈጠረው አቴና (ግሪክ) አውሮፐሳን ጠቢያ ላይ ነው ይባላል። በንክሮ ስመለከተው እዛውንቱ የነጣቃቸው ሳይሆን አደብ ገዝተው የፈጠሯት ስለመሰለኝ እኔም አልገደፍኩትም፤ እይመስልም?
እምል - ከጊዜ መብዛትና ከመታፈግ መለወጥ፤ መበላሸት (ጥሬ እህል ለሆን ሁሉና ለ ዱቄት።)
እዳሪ መውጣት - ሳይነምድር መቀመጥ
እጄ-ሰብ - መድሀኒት ሰሪ (ብዙ ጊዜ እሉታዊ በተለይ ደብተሮችን፣ መተታሞችን ይመለከታል)
ከመጡብ - ያን ያህልም፣ ምንም ሲሆን ምንም ያልቀረው፤
*ኩሽር - ያልረከሰ፤ የተባረከ፣ ክንክኪ የራቀ
የበረ እቃ - ምራና፣ መርገጫ፣ ወገል፣ ማንቂያ፣ ቀንበር፣ ሞፈር፣ ድግር፣ ቅቅርቅ፣ ወሻል፣ እርፍ፣ ጅራፍ
ጉይ - ቤተእስራኤል ያልሆነ ማለት ሲሆን በመሰረቱ

ይሁዳዊ ያልሆነ ሁሉ ማለት ነው።

«ወሀ-መከፈል» - መሸናት። በቤት በኩል እንዲያው «መቀመጥ» ብቻ ይሉታል።

ወገቴ - ወሬ፣ ወሞታ።

ወቶ-ቶካ - አወቶማቲክ

ወታቢ - «ቴሌግዚ» የሚለውን የሚማበል፣ ቢበሩ ደግሞ «ሳይኪክ» የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ይሆናል። ከተሜው፣ ምሁሩ ይህን ቃል ሊጠቀምበት ይቀፈዋል፣ በገርቤት ግን ያልምር እቅምን ብሉም እመልን የሚናገር ቃልም ሲሆን ይታያል።

1- ከጀርባ እንዲማከላከል ሀይል፣

ለምሳሌ፣ ከሰው የማያታርብ ወታቢ አለበት። (አመል)

ወታቢየ ይነገረኛል፣ ምልክቱ በውነቴን ይቀፈኛል።

2- እንዳንዴ ዘር (ትይሰት፣ ቀራኛ) ወደማለው ብቻ የሚቀኙት አሉ፣ ነገር ግን ዘር በሌላቸው ሰወችም በያሌ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያልና የሚያሸግ አይሆንም።

ወፈንጠር - አላማው እንዲሸከለ ሁዋ የሚያተኩረው እገር መያዝን ነው፣

ወራንታ - የመለኪያ ሰፈት፣ (ግማሽ ማድጋ ይይዛል።)

ጋሽ - የግራ በኩል እቅጣጫ

ገድ - ወፍ

ግብረ-ወሀ - አበሽ ሴቶች ጠዋትና ማታ የሚያደርጉት የመታጠብ ደንብ። ... የማያፍሬት የእምስ ወሀም ይሉታል።

ግደም - ወርድ፣ መቅ፣ ቅርብ፣ ከባቢ፣

ክቅር-መልቀም - የጉፈሬ ዳር ማብጀት፣ መላወት።

ግስንግስ - ቅልቋንቁራ፣ ድሪቶ

ዘር-አዘርቅ - ትውልድ

ድርጉ - እሬያ (ለእንስራ፣ ለማድጋ)

ደመር - እሰከረን ያላጀበ ለቅሰ፣

ደቢያተኛ - ጉልበት ከፋይ፣ ወበረኛ

ደብር - ፣ ቀበሌ፣ ታቦት፣ ያንድ ታቦት ክበብ በሙሉ

ዳበ - የጉልበት ብድር ከፋሳ፣ ቅዋሬ ከበዛ ወበራም ይሆናል።

ዳርብ - ድምድም፣ ፎቅና-ምድር ቤት

ዳልቻ - ቀለም (ያልየለቅ ቡላ)

ዲ-ማለት - ዝግ ማለት፣ ዲ ስትልብኝ ተውኳት።

ድርበብ - ከከንፈር የቀረ (የቆና ድርበብ፣ የፍንጃል ድርበብ ቡና...)

ድንጉል - ወሀ ተሸካሚው ንብ፣ ስራው ይኸ ብቻ ነው።

አይቀበሙም።

ድዳናም - ብርዳም።

>ጉፈር - አደስ ገብ ላጅን፣ ያገረን ትድረቅ ያልለመደ።

ፕጃ ግራክቢያ - ከብት መውጫና መግቢያ፣ ግታና ቧት።

ጫ ማለት - ሰጥ፣ ፀጥ።

ጭበሳ - በፍ መሰብሰብ፣ እውነታ የሌለበት ምስጋናም ሆነ ድጋፍ

ፈተት ማለት - ዘና ማለት (ለበውነት፣ ለአየር፣ ለወሀይ)